# ጉዘዉ

## እና ሌሎችም ልብ ወለዶች

552/2000

# ጉዞው

እና

ሌሎችም ልቦለዶች

## ከተለያዩ ደራሲያን

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፸፱

KURAZ PUBLISHING AGENCY

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ
Tel. 11 27 19

ፖ. ሣ. ቊ.
P. O. Box 30933

የመጀመሪያ እትም ፲፱፻፹፭
ሁለተኛ እትም ፲፱፻፹፱

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ሽፋን ሥዕል — ሉቃስ አማረ

አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት
Artistic Printing Press

# ማ ው ጫ

ገጽ

እያስመዘገብኩ ነው

— ከአውግቸው ተረፈ ---------- 1

ደብዳቤው

— ከሰለሞን ለማ ---------- 20

ጉዞው

— ከሲሳይ ንጉሡ ---------- 37

ማሞ ቢጩ

— ከአውግቸው ተረፈ ---------- 273

ቁራው

— ከሰለሞን ለማ ---------- 293

# ማሳሰቢያ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ስሞች (ገፀ ባሕርያት) በሞት የተለዩም ሆነ በሕይወት ያሉ ሰዎችን ስም ቢጠቅስ ባጋጣሚ የሆነ እንጂ ሆነ ተብሎ የተደረገ አይደለም ።

አሳታሚው

# እያስመዘገብኩ ነው

ከአውግቸው ተረፈ

ዛሬም እንደወትሮዬ የደንቧን ቀምሼ ለመመለስ ከሰፈራችን ጠጅ ቤቶች አንደኛው ዘንድ ጉራ አልኩ ። ስገባም ሁለት እጆቼን አንስቼ ለግራና ቀኙ ሰላምታ እየ ሰጠሁ አልፌ አግዳሚ ወንበር ላይ ጥግ ይዤ ተቀመጥኩ

ጠጅ ቀጂ አልቀዳልኝ ብሎ ስለነበር እጂ እስቲቃ ጠል አጨበጭባለሁ ። በዚህ ጊዜ አንድ እፍ ቢሏቸው ተሽቀንጥረው እዚያ ማዶ ይወድቁ እሚመስሉ ሰውዬ መጡና ከፊት ለፊቴ ቆመው አጠገቤ ወደ አለው ባዶ ቦታ እያመለከቱ "ልቀመጥ ?" አሉ ። "እሺ" እንደ ማለት አንገቴን ነቀንቅኩና ዝም አልኩ ። አግዳሚውን ጠረጴዛ በጥንቃቄ ተራምደው ቁጭ ካሉ በኋላ ባርኔጣቸ ውን አወልቀው ቀኝ እጃቸውን ለሰላምታ ዘረጉልኝ ። ጨበጥኳቸው ።

ካናቴራና ሸሚዝ ስለአለበሱ አሮጌ ኮታቸው የደረ ታቸውን ከሳት አጋልጦ አጥንታቸው እስቲቆጠር ድረስ ያሳጣቸዋል ። ጉንጫቸው ጉንና ጉን የተጠረመሰ የጉ ልት ጣሳ ይመስላል ። ሱሪያቸው ከጉልበታቸው እስከ ቁርጭምጭሚታቸው ድረስ ተቀዶአል ። ጫማቸው ከተ

ረከዛቸው ላይ ከመንሻፈፋቸው በላይ ሁሉቱንም አውራ ጣቶቻቸውን አሾልኳቸዋል ። አሮጌ የሰሌን ባርኔጣቸውን አውልቀው በእጃቸው ስለያዙት ሽፍ ብሎ የበቀለው ፀጉራቸው ከተላጨ ብዙ ጊዜ እንዳልሆነውና ሽበት የወረራቸው መሆኑን ያሳያል ።

ለብዙ ጊዜ ሌላውን ጫጫታ እያዳመጥኩ ተቀመጥኩ ። ሰውዬው የተቀዳላቸውን ጠጅ አልነኩትም ። እየተ እድርጌያቸው ዘወር ስል ጐሸም አደረጉኝና “ ጋሽየ ይኸ ጥሩ ሥራ ነው? ” አሉኝ ። እኔ ግን የጥያቄያቸው ሥረ-መሠረት ስላልገባኝ ዝም አልኳቸው ። “ በእውነት በውነት - - - ይኸ ጥሩ ሥራ ነው ? ” አሉኝ ፣ ደገሙና ። የባሰ ግራ ተጋባሁና ትኩር ብዬ አየኋቸው ። ዓይናቸውን አፍጠው ፣ መንጋጭላቸውን ኩርትም አርገው አንገታቸውን እያንዘረዘሩ “ ይገባል ? ” አሉኝ ።

“ ምኑ ? ” አልኳቸው

“ እኔ ቀለም ስቀባ ውየ የሠራሁበትን ቆርጦ ማስቀረት ተገቢ ነው ? ”

ምንም ሳልመልስላቸው ብርሌየን አንስቼ አንደቀደኩት ። ቀጠሉና “ ይህማ ጣትን መቁረጥ ማለት ነው ። ለመሆኑ ከትንሿ ጣት ላይ ምኗ ይቆረጣል ? ”

“ ማነው የቆረጠብዎ ? ”

"ሌላ ማን ሊሆን ነው ? ጌቶች ናቸዋ ! ጌቶች ! መሥራት አትፈልግም ትፈልጋለህ?እንግዲያውስ ና ደህና ገንዘብ እከፍልሃለሁ ። እየጠጣህ ባትስክር ኖሮ በሥራ ማን አጠገብህ ይደርሳል ?" አሉኝ ። "ምንቆርጦኝ ነው ጌታየ እሠራለሁ እንጂ ። ከተገኝ ማንኛውንም ሥራ እሠራለሁ" አልኳቸውና ቤታቸውን ስጠርግ አቧራ ውን ሳራግፍ ፣ የሸረሪት ድሩም ፣ ጥቅርሻወም ፣ ምኑም ምኑም በዓይኔ ፣ በጆሮየ ፣ በአፌ ሲገባ ፣ ስሠራ ፣ ስሠራ ውየ የድካሜን ዋጋ ከለከሉኝ ፤ የቀለሜንም ዋጋ አብረው አስቀሩብኝ ፤ አስቀሩብኝ --- ወይኔ መኩሪያ እዎ -- ታዲያ ችላ ብዬ ያለፍኩት አይምሰልህ -- እያስመዘገብኩ ነው" ።

ዓይናቸውን ግራና ቀኝ ከብለል ከብለል እያደረጉ አዘኔታና ፍትህ በሚለምን አመለካከት አዩኝ ። ዕውነ ትም ደም ስርቧቸው ፍም የመሳሰሉት ዓይኖቻቸው ፣ በአንድ በኩል በደል የተፈጸመባቸውና አግባብ አለመ ሆኑን ሲገልጹ ፣ በሌላ በኩል እጃቸውን እያወዛወዙ ከን ፈራቸውን ሲነክሱ "ቆይ ግድ የለም ይጠብቅ" የሚሉ ይመስላሉ ።

ብርሌየን እያነሳሁ ጠጄን በማንደቅደቅ ማዳመጤን ቀጠልሁ ።

"ባልና ሚስት ሲጣሉ ፥ ሲጨቃጨቁ ፥ መሣሪያ መዞ መጥቶ በሰደፍ መማታት ተገቢ ነው ? ይኸውልህ ለምን ከባለቤትህ ጋር ትጣላለህ ብሎ በሰደፍ የመታኝን ላሳይ ህ ?" ብለው እጇን ጕተቱና ጀርባቸው ላይ አንድ ያበጠ ነገር አስዳሰሱኝ ።

"ምንስ አብዮት ጠባቂ ቢሆን እንደኔ ድንጋይ ሲሸ ከም ፥ ጭቃ ሲያቦካ ፥ ቀለም ሲቀባ አደል እሚውለው ። እያወኩት --- ልክ አይደለም ። ልክ አይደለም" እያሉ እጃቸውን በማወናጨፍ ብሶታቸውን ሁሉ ለመናገር ከመ ቸኮላቸው የተነሳ የምራቃቸው ፍንጥርጣሪ እፊቴ ላይ ማረፉን ያጤኑት አይመስልም ። ቅሬታና ብስጭታቸውን ራሳቸውን ግራ ቀኝ በማማታት እየገለጹ ተከዝ እንደ ማለት ቀርቀር ብለው ቆዩ ።

"እንዴት ነው አንዱን ሳይጨርሱ ሌላውን የሚ ጀምሩት ?" እያልኩ ሳምሰለስል ጕሸም ሲያደርጉኝና "ጋሽዬ አንተን ጨምሬ አስለቀስኩህ ልበል ?" ሲሉ ነው እንደገና ቀና ማለታቸውን ያጤንኩትና ፍንጥርጣሪ ዎቹን በመሐረቤ ያባበስኩት ።

"--- ተመልከተው ይኸን ደሞ ከጓዳ የሚወጣውን --- የሁለት ብርሌ የከፈልኩለት እኔ ነኝ ። በቀደም ጠመንጃ ህን አፈሙዙን ቀና አድርገህ ያዘው ፤ ካርታ ሙሉ ጥይት

እንደጐረሰ ምላጩን ነካ ካደረከው ሰው ትገላለህ አል ኩት፤ ይኸ መጥፎ አባባል ነው? ይኸን በመናገሬ በጥፊ አጮለኝ ----"

ግንባሬን ኮስተር አድርጌ ዓይኖቼን ፊት ለፊት ካለው ግድግዳ ላይ ባለው የሥነ ሥቅለት ሥዕል ላይ ተክየ "ታዲያ እኔን ምን አድርግ ይሉኛል?" እንደማለት ግዴ ለሽ ለመምሰል ሞርኩ። አጠገቤ የነበረው ሰውዬ "ይኸ መጥፎ ሽማግሌ ከያዘ አይለቅ? ምን አድርግ ነው የምት ለው?" አላቸው "ድኃ ስለማይንቅ ከኛ ጋር ሲበላ ሲጠጣ ጊዜ የሱ ቢጤ መሐይምን መሰለውኮ እባካችሁ?" አፈርኩ ።

ስምተው እንዳልሰሙ ሆኑና ቀጠሉ ።

"---አሁን ስብሰባ አለብኝ ብሎ ሄደ። ምን እሚ መከር ይመስልሃል? በኔ ላይ እኮ ነው ምክራቸው። የፈለ ገኝን ያህል ብጠጣ፣ የትስ ባድር ምን አገባቸው? የም ሬንኮ ነው ጋሽየ 'የት ዋልክ? ስንት ጠጅ ጠጣህ? ምን አወራህ?' ይኸን ምን አባባላቸው ? እኔ የም ጠጣወ ዛሬ ብቻ አይደለሞ፤ ሚስቴንም የምመታት ዛሬ ብቻ አይደለም። ዱሮ ጀምሬ ጠጅ እጠጣ ነበር፤ ሚስቴ ንም እመታት ነበር። እሱዋም ልብሴን ትቀድብኝ ነበር። ተመልከተው ። ሸሚዝና ካናቴራ የለኝም ። ባለቤቴ ቀዳ

ብኝ ነው” ብለው አሮጌ ኮታቸውን ገለጡና ያንን የከሳ ደረታቸውን አጥንት አስቆጠሩኝ ። “ታዲያ የትናንቱ ጠብ አዲስ መሆኑ ነው፤ በሰደፍ እንድመታና እንድታሰር ያደረገኝ? ተገቢ ነው? ባጠፋስ በሕጉ መሠረት አልጠየ ቅም? ለምን ስም ወጣልኝ? ለቤቴስ ቁጥር ለምን ተሰ ጠው? መታወቂያስ ለምን ተሰጠኝ? ወንጀል ብሠራ በሕጉ መሠረት እንድጠየቅበት አይደለም? ማስትህን መታህ ተብዬ በሰደፍ - - ጋሽዬ ይኸ ጥሩ ሥራ ነው ----

“ታዲያ ማስትህን እንድትደበድብ ተፈቅዶልሃል?” አላቸው አጠገቤ የተቀመጠው ሰውዬ ። ቀና ብለው እንኳ ሳያዩት ቀጠሉ ።

“አትዘከርብኝ ጋሽዬ፤ ተበሳጭቼ ነው ። ግን የሰከ ርኩ እንዳይመስልህ” ቀጠሉ “ትናንት እኛ ቀበሌ ሳሙና መጣ፤ ጦርነት የተነሳውም በሱ ነው ። ትግል፤ ትንንቅ፤ ግብ ግብ ተነሳ ። ልጅ አዋቂው ዋይ፤ ዋይ አለ ። ይኸው ልህ ኮቴን ይዘው ሲጐትቱኝ ቀደዱት” ኮታቸውን አሳዩኝ ። “ያንን ሁሉ ጩኸት ምን አመጣው? ሊቀመንበሩ መጣና እንዲዘጋ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሂደ ። እኛም ወጣንና እደጅ ቆመን ዝናብ ይቀጠቅጠን ጀመር ። ታዲያ ይኸ ተገቢ ነው? ይህንንም እያስመዘገብኩ ነው ።”

ጠጅ ቀጂ አልቀዳልኝ ብሎ በብርሌ ጠረጴዛውን እቀ ጠቅጣለሁ ። የሰው ጩኸት ጆሮ ቢቆርጡ አያስማም ።

"---ዱሮ የነበርኩበትን ቤት ባለቤት ታውቀው የለ?" አሉኝ የብዙ ጊዜ እውቂያ ያለን ይመስል ። ቢሆ ንም ቶሎ ጨርሰው ብገላገል ብዬ "አዎ" አልኳቸው ። " ይኸውልህ እሱ ነው ፣ ያኔ አሥራ አምስት ብር የሚሸጠ ውን ጫማ ዛሬ አርባ ብር ፣ ሃምሳ ብር ፣ የሰባት ብር ሸሚዝ ሠላሳ ብር ፣ የዓርባ ብር ኮት ፣ መቶ ሃምሳ ብር የሚ ሸጥ ፤ ላንተ ምን እነግርሃለሁ ። ስንት ሱቅ እንዳለው እያ ወክ? ---ይባስ ብሎ የቀበሌው ሕብረት ሱቅ የሚያስመ ጣውን ዕቃ ሁሉ ባሽከር ፣ በገረድ ፣ በሚስት ፣ በዘመድ አዝማድ አስገዝቶ ይወስደዋል ። የሳሙናውንም ጦርነት ያስነሳው እሱ ነው ። ለመሆኑ ያ ሁሉ እረብሻና ጩኸት ከየት መጣ? ሕብረት ሱቅስ ለምን ተዘጋ? እንደሚባለ ውማ ከሊቀ መንበሩ ጋር ተሻርኮ አዘግቶ ሲያበቃ በጉን ያስወስደዋል ። ከዚያ ሳሙና አለቀ ይባልና ፣ ስኳር አለቀ ይባልና--- እንደገና እስቲመጣ ጠብቁ ይባላል ። ለነገ ሩማ የአንድ ሳሙና መግዣ አጥቼ ተበድሬ አልነበር የሄ ድኩ ። ብገዛውስ ምኑን ላጥብበት ነው? ኧረ ለምን--- ይሄንንም እያስመዘገብኩ ነው"

"ዓይናቸውን እያጉረጠረጡ ፣ እጃቸውን እያወና ጨፉ ፣ በንዴት ፣ በችኮላ ሲናገሩ አሁንም ምራቃቸው እየተፈናጠረ ፊቴን ሲያለብሰው እኔ ስጠርግ አልተገነዘ ቡትም ። የደም ሥራቸው በቁጣ ተገታትሮ የሲቃና የእልህ እሮሮአቸውን ቀጥለዋል ።

" ጋሽዬ ፣ መኩሪያ ብለው ስም ያወጡልኝ ለምንድ ነው ? ከሌሎች ሰዎች ተለይቼ እንድታወቅበት አይደለ ። ለቤቱስ ቁጥር ለምን ተሰጠው ? አጥፍቼ ብከሰስ የትም ሄጄ እንዳላመልጥ አይደል ? ገና ለገና ቤት ኪራይ ከፍያ ለሁ ብዬ ባልከፈሉት ሰዎች ላይ መኩራትና መሳቅ ይገባ ኛል ? ቤት በሌላቸው ላይ መኩራት ይገባኛል ?---

" ይችን ደባላችንን ፣ አሁን እንዲህ መከራችንን ልታሳየን ፣ መጀመሪያ ብታያት እንዴት ታሳዝን ነበር መሰለህ ። ረስተኸው ካልሆን የመጣች ዕለት ከባድ ዝናብ ይዘንብ ነበር ። ታዲያ ልጅዋን አዝላ መጣችና ከዝ ናቡ ለመጠለል እጥግ ቆመች ። የኛን ቤት ታውቀው የለ ? በረንዳ የለው ፣ ምን የለው ፣ እንዲያውም ቆርቆሮው አር ጅቶ ፣ ወንፊት ሆኖ የቤቱን ግድግዳ ስለማያስጥለው ከላይ ዝናቡ ፣ ከታች ጐርፉ ተጋግዘው ሊጥሉት እንደ ሐምሌ ደመና ከብዶ ያስፈራራል ።

"ሴትዮ ምን ትፈልጊያለሽ ? መቸም በዚያ ዝናብ ጤነኛ ሰው እደጅ አይቆምም ። በዚያ ላይ ብርድ እንዳ ድረስ ገብቶ ያንቀጠቅጣታል ። ከውሃ የወጣች እይጥ መስላ ሳያት በጣም አሳዘነችኝ ። የኋላውን ምኑን አውቄ ፤ እንዲያው ሆዴ ስለማይችል ብቻ ነው ።

" ሴትዮ ልጅሽን ጨምረሽ በዝናብ አትግደይ ። ግቢና አባሪው ። ምንም ቢሆን ውስጡ ከውጩ ሳይሻል

አይቀርም" ስላት እያፈረች ገብታ ተቀመጠች ። ባለቤቴ ደግሞ 'ይህን ያህል ዝናብ ከሚያበሰብስሽ ለምን እንዱ ቤት አትጠለይም ነሯል?' ብላ ለቡና ማፍያ ያቀጣጠለች ውን ከሰል እንድትሞቅ አቀረበችላት ።

"ኋላ ብናያት አትሄድም ። ብናያት አትሄድም ። ሴትዮዋ ምን ሆናለች ከባል ተጣልታ ይሆን ? እልኩና እምዬ ዝናቡ አባርቷል ። ሂጅና ለባለቤትሽ ምናምን አብ ስይለት' አልኳት ።

አንገቷን ቀና አደረገችና "እሂሂ ባል እንዳለው ሰው ሁሉ" አለች ።

"ባል የለሽም እንዴ?" "የለኝም" ። "ቤትሳ? ባል ባይ ኖርሽ ወደ ቤትሽ አትሄጅም ?" አልኳት ።

'የለኝም' አለችና ዓይኗን ባዶው ግድግዳ ላይ ሰክታ ልጅዋን ማጥባት ቀጠለች ። እንግዲህ ሲመሽ የት ትሄዳለች ? ባይሆን እድራ ነገ ትሄዳለች ብለን እሳያርናት ። በበነጋታው ብንጠይቃት "ምን መሄጃ አለኝ ። ይሄን ሰሞን ብርድ ሲሆን ጊዜ ልጄን እመሙብኝና ምን እልባት ብርዱ ይሆናል ትንሽ እስቲሻለው የሚያስጠጋኝ ሰው ባገኝ ብዬ ስፈልግ እግሬ እናንተ ቤት አደረሰኝ" ብላ ልጇዋን ታቅፋ ለመሄድ ስትነሳ ሆዴ ተንቦጫቦጨ ።

ባለቤቴ ደግሞ አብራን እንድትሰነብት ስለማትፈ ልግ በከፋ ዓይኗ አየቻት ። ፊት ነሳቻት ። ወንድ ነኝ ብዬ የባለቤቴን ቁጣ ንቄ 'እንግዲያውስ ትንሽ ቀን ተቀመጭ' ብየ ወጥቼ ሄድኩ ።

የባለቤቴን ቁጣ ለማብረድ ስል ።

" ክረምቱን አብራን ክረመች ። ይሄው በጋውንም አጋመስነው ። አሁን ከቤት ውጭልን ። አልወጣም ። ህት ኪራይ አግኙን 'ገንዘብ የለኝም' የምናደርገውን ተቸግረናል ። ደግሞ በዚያ ላይ ቤት ውስጥ ምንም ዕቃ ማስቀመጥ አልቻልንም ፤ እንጀራው ፤ ሽሮው ፤ ሽንኩርቱ ከራት ከተረፈ ቀን ይሰረቃል ። ቢቸግረን እልብሳችን ሣጥን ውስጥ እንቆልፍበታለን ። ከእንጀራ አቅም እንኳ

" ደሞ በሷ ተብሶ ፤ በሆነ ባልሆነው እየከሰሰች ቀበሌ ትወስደናለች ። አንድ ቀንማ ለእብዮት ጠባቂው ጠላና አረቄ ስትገዛለት በዓይኔ በብረቱ አይቻታለሁ ። ያውም የጎጃም ዐረቄ ፤ ዳግም ----

ይሄንንም እያስመዘገብኩ ነው ።

እሰይ ጨረሱ ። እንግዲህ ተገላገልኩ አልኩና "በቃ ይርሱት መበሳጨት አያስፈልግም" አልኳቸው ። በሆዴ ደግሞ "አሁን ምን ቸገረዎ የመጣሁበትን ጠጥቼ ብሄድ ፤ ሁሉም በየቤቱ የራሱ ሃሳብና ብሶት አለው" አልኩ ።

"እንደኔ ወዛደር ስለመሰልከኝ ምክርህን እንድታካፍለኝ ብየ ነው ጋሽየ" አሉኝ ። ነገሩን ለማሳጠር ስል "አይደለሁም" አልኳቸው ። የተቀዳላቸውን ጠጅ አንስተው አፋቸው ላይ ካደረሱት በኋላ ሳይጠጡት መልሰው አስቀመጡት ። እኔ ግን ብርሌየን አነሳሁና እንደቀደኩት ።

"ጋሽዬ የጠጭ አጭበርባሪ ዛሬ ሁለት ብርሌ ነው የጠጣሁ ቢልህ ልቀቀው ። እንደለመደ ነገ ሲመጣ ሁለት ጠጥቶ እንደሆነ ያራት ስታስከፍለው ልክ ይመጣል ። ግን የቀጅ አጭበርባሪ አይጣልብህ ፤ ገና ለገና ሶስት እጥፍ አድርጐ ይጠይቅሃል ። ያለብህን ዝም ብለህ መክፈል ብቻ ነው ። ሁሉም የሚረዳው ለቀጁ ነው ። ያ ሁሉ አጨብጫቢና አቃጣሪ አንተ አጭበረበርክ እንጂ ቀጅ አጭበረበረ አይልም ። በተለይ እንደኔ ራቁትህን የምትሄድ ከሆነ - - ሰው እንዴት ከትንሹዋ ጣት ይቆርጣል - - አሁን ሁለት ሰዓት ነው ። አይደለም ? ።"

"የለም ገና ሩብ ጉዳይ ነው ።"

"ግዴለም ሁለት ሰዓት ነው እንበል ። ግን ያቆጣጠሩን ደንብ ፣ ሕጉን ስላወከው ነው ሰዓት ያስርከው ። አይደለም ? እስቲ በል ፍረደኝ ፤ ምላጭና ቃታ ለይቶ የማያውቅ ሰው ፣ ካርታ ጥይት አቅሞ ፣ አፈሙዙን ወዳንተ አዙሮ ሳያስጠብቅ አጠገብህ ቢቆም ምን ይሰማሃል ?

ጋሽዬ በኔ ደርሶብኛል ። እኔ ሌላ ምንም አላልኩት ። እባ ክህን ሰውዬ ጠመንጃህን ቀና አድርገህ ያዘው ። ወዲያ ውም ሕጉን አውቀህ ማክበር አለብህ ።''

"አንተ ምን ያስፈራሀል ? ፀረ - ሕዝብ ነህ እንዴ? ካልሆንክ አይነካህም'' አለኝ ።

" ይሄ ተገቢ ነው ? ከሚስቴ ጋር ብጣላስ መመታ ትና መታሰር አለብኝ ? ለምን ስም ወጣልኝ ? ለቢቱስ ቁጥር ለምን ተሰጠው ? መታወቂያስ ለምን ተሰጠኝ? ከሌ ሎች ተለይቼ እንድታወቅበት ፤ ወንጀል እንዳልሠራ አይ ደለም ? ታዲያ ባጠፋስ በሕጉ መሠረት አልጠየቅም ? እሰረው ፤ ስደበው ይላል ሕጉ ? ጋሽዬ በጣም አዝኜ አለቀ ስኩ ። ባልማር ፤ ገንዘብ ባይኖረኝ አይደል እማውቀው ጓደኛዬ አብረን እየሠራን ፤ እኔን በሰደፍ መምታትና ማሰር ይገባው ኑሯል ? ያውም ያለምንም ጥፋት ። እንባ እንዳይመስልህ ፤ ደም አልቅሼ ነው ለፈጣሪ የነገርኩት ። እንዲህ አድርጌ አሉና ጠጁን እጃቸው ላይ አፍስሰው ወደ ላይ ፈነጠቁት ። ተመልሶ ረጨን ።

" ጠመንጃ እሚመዘዘው እንደኔ ዓይነቱ ድሃ ጓደ ኛው ላይ ነው ? አወን ይሄንንም እያስመዘገብኩ ነው ''

"እኔን እንግዲህ ምን አድርግ ይሉኛል?'' ብዩ ከፍዩ ለመሄድ ኪሴን ስዳብስ "ጋሽዬ ቀበሌዎችን ጨምሬ ነው የምከስ ። በነሱም ላይ ብዙ ብዙ ነጥብ ይዣለሁ ። መቸስ የሚ

ሁሩትን ሥራ ታውቀው የለ? እንሱስ መቸ አጡት ። ሐሙስ ለት እኔን እያዩ ተንሾካሾኩብኝ ። ሳቁብኝ ። ክፋት ማሰቤን አውቀው ። በነሱም ላይ ብዙ ብዙ ነጥብ አለኝ ። የመጣውን ጤፍ የት አደረሱት? ስኳርና ብርድ ልብሱን ለማን አከፋፈሉት? ማክሰኞ ለታ ጤፍ መጣ ፣ ጧትም ማታም ጥሩንባ ተነፋ ። ወጥተን ተሰለፍን ። በደንብ አል ተሰለፋችሁም ፣ ረብሻ አስነስታችኋል ብለው ኀብረት ሱቁን ዘጉት ። ግን ጤፉ የት ደረሰ? ሱቁስ ለምን ተዘጋ? ሰውስ ዋይ ዋይ ብሎ ለምን አለቀሰ? በዚህ ሁሉ ነገር በጣም አዝኛለሁ ። በቀበሌዎች ላይ ብዙ ቅሬታ ፣ ብዙ ብዙ ቅሬታ ----

ትንንሽ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ገብስ ቆሎ ፣ ስንዴ ቆሎ ፣ አተር እንግርግብ ፣ ባቄላ እንግርግብ ፣ሽንብራ ቆሎ --- በቁና ፣ በጎድጓዳ ሳህን ፣ ባገልግል ይዘው ቆሏ ቸውን እያንቀራጩ እያዞሩ ይሸጣሉ ። ሱቅ በደረቴው ሹራብ ነጋዴው ፣ ካልሲ አዙዋሪው ፣ ለማኙ ሁሉ አንዱ ሲወጣ ሌላው እየገባ ጠጅ ቤቱን አጣበውታል ። የሳህ ኑና የሹካው ኳኳታ ፣ የብርሌው ቋቋታ ፣ የጠጁ ፏፏታ ፣ የጠጭው ሁካታ ለጆሮውና ለዓይን የማያሳከር ሁኔታ ፈጥሯል ።

ብርሌየን ጨረስኩና ላስቀዳ ወይስ ይብቃኝ እያ ልኩ ሳመነታ "ጋሽዬ ልጅን መቅጣት በልጅነቱ ነው"

አሉ አቶ መኩሪያ “ ልቅ ከሰደድከው ዋጋ የለውም ። ሚስትና ልጆችህን ማስተዳደር ካቃተህ ራስህን አዋረድክ ማለት ነው ። ይሄ ለጨው ፣ ይሄ ለበርበሬ ብለህ የቤት ወጭ ስጣት ። ግን ደግሞ እንዳትንቅህ ያስፈልጋል ። ገን ዘብ ከሌለህ ፣ ቤትህን ማስተዳደር ካቃተህ እንዴት ብለህ ሚስትህን ለመቅጣት ትነሳለህ ? ምንህ ናት ? የኔ ነገር ያሁኑ ይህን ይመስላል ። ከገንዘቡ ገንዘብ የለኝም ። ከክብሩ ክብር የለኝም ። ምን የቀረ ነገር አለኝ ? ምንም ። አቤት በፊት ገንዘብ በነበረኝ ጊዜ ባለቤቴና ልጆቼ ገና ከሩቅ ድምጼን ሲሰሙ የት እንግባ ይሉ ነበር ። ዛሬ ግን አይ - - - ገንዘብ - - - ” ብለው ዓይን ሕሊናቸውን ወደ ዱሮው መልሰው ልጆቻቸውን እንዴት አድርገው ለማሳ ደግ ያቅዱ እንደነበር ፣ ባለቤታቸውን እንዴት አክብረው ያስተዳድሩ እንደነበር - - ያ ሁሉ አልሆን ብሏቸው ጠብና ጭቅጭቅ ውስጥ ገብተው ፣ ያንን ሁሉ ከበሬታ አጥተው ፣ ዛሬ አሉበት የውርደት ደረጃ እንዴት እንደደረሱ ባጭሩ ቃኝተው የተመለሱ መሰለኝ ፤ ዓይናቸውን ባዶ ነገር ላይ ሰክተው ፀጥ ብለው ሲያስቡ ።

ከሃሳባቸው ተመልሰው ራሳቸውን ነቅንቁና “ ባለቤ ቴን ታውቃት የለ?” አሉኝ ።“እስዎንም ያለ ዛሬ አይቸዎት አላውቅ እንኳን ባለቤትዎን” ልላቸው ስል “ምነው እዚህ መንታው መንገድ ላይ ወደ ግራ ስትጣጠፍ አንድ ቡና ህት የለም ? ” አሉኝ ። “ አለ ” አልኳቸው ። “ ታዲያ የቡና ቤቱ እንጀራ ጋጋሪ መሆኗን አታውቅም ? እንዴት

አታውቅትም ? እዚህ እኛ ሠፈር እየኖርክ ። እርግጥ ዱሮ ወፍጮ ቤቱ አጠገብ ስንኖር እኔ በምሰጣት ገንዘብ ነበር የምንተዳደር --- ”

ይሞ እንደገና ሊቀጥሉ ነው ብየ ፊቴን ዞር ሳደርግ ባቻው ጉሽም አደረጉኝና ዓይናቸውን አዲስ ከሚገቡ ሰዎች ላይ ተክለው አስተዋሏቸው ። ሰዎቹ ሰላምታ እየ ሰጡ ወደ ጓዳ ገቡ ። በድጋሜ ጉንተል አደረጉኝና “ኪ ሳቸውን አየህልኝ ? ምን ያሳበጠው ይመስለሀል ?” አሉና መልስ ሳይጠብቁ “ነገር ነው ፤ በኪሳቸው ሙሉ የያዙት ተን ኮል ነው ። ቅድም ስብሰባ ፡ አሁን ጠጅ ቤት ፤ ኋላ መስከ ርና እኔን መደብደብ ፤ ማሰር ፤ በሠይፍ መምታት ። ሕጉ እንደዚህ ይላል ጋሼዬ ? ምን ሲመክሩ አምሽተው ነው በኔ ላይ ደረታቸውን የሚነፉ ? እነሱ ሰክረው እኔን ሰካ ራም ይሉኛል ። እውን ጋሼዬ ፤ ጋዜጣውና ሬዲዮው ፤ ደብ ድቡ ፤ እሰሩ ይላል ? እኔ ጋዜጣ ማንበብ አልችልም ። ሬዲዮም የለኝም --” ሲሉ አቋረጥኩና እኒህን ያለዛሬ አይቻቸው የማላውቀውን ሰው ተሰናብቼ ልወጣ ስል ልብሴን ጭምድድ አድርገው ይዘው “ይህችን ብቻ ስማኝ በሞቴ ! ጋሼዬ በግዚሀር ይገርሀሉ !” አሉኝ ። መሄድም ከለከሉኝ ።

“ገንዘብ ከሌለዎት ልክፈልልዎ ። አለበለዚያ መሸ ቶብኛል ልሂድ ብላቸው” “ጋሼዬ ገንዘብስ ባይኖረኝ

ስንት ዓመት ከተቀመጥኩበት ቤት ውጣ እባላለሁ ? የት ሊጥሉኝ ነው ? ሕጉስ ይፈቅድላቸዋል ? ሥራ በነበረኝ ጊዜ የቤት ኪራይስ ልክ በልደታ ማግሥት ነበር የምከፍል ። ዛሬ ግን ከየት አመጣለሁ ? መክፈል አቃተኝ ። እግዚር.ስ ከተንኮለኞች ጋር አይደል ? ለኔ ምን ያዝንልኛል ፣ የቀበሌያችንን ሊቀመንበር ታውቀው የለ ? ዱሮ ከኛ ባል ተሻለ ቤት ይኖር ነበር ። ዛሬማ የሚኖርበትን ቤት በእ ግርህ ለመርገጥ ያሳዝንሃል ፤ በዚያ ላይ ፎቴ ወንበሩ ፣ ፋሚሊ አልጋው ፣ የቤት ዕቃው --- አንድም የቀረ የለም ።

"ይታደስልኝ እያልኩ ሳመለክት ስንት ጊዜዬ መሰ ለህ ? የሚገርመው ደሞ እኔን አስወጥቶ ላንድ ሾፌር ሊያከራያት ነው አሉ ። አንድ ቀን በሌለሁበት አሽንት ሄደ ። እግሩ ላይ ወድቄ አቤት አልኩ ። ሥራ ሳገኝ እከ ፍላለሁ አልኩት ። አይሆንም አለኝ ። ባይሆን እኔን እሰ ሩና ባለቤቴና ልጆቼ ቤቱ ተከፍቶላቸው ይግቡ አልኩ ። "መታሰሩን ትታሰራለህ ግን ከነባለቤትህ ነው አለኛ !" ይሄ ጥሩ ሥራ ነው ? ይሄንንም እያስመዘገብኩ ነው ።

ከነፈራቸውን እየነከሱ ፣ ጋሽዬ ለመሆኑ ቀበሌዎች የት እንደሚያመሹ ታውቃለህ ? አዎን ታውቀዋለህ ። ያንን ግሮሰሪ እንኳን አንተ ሕፃን ልጅ ያውቀዋል ። እዚያ ያጠመደ አያጣቸውም ። ከፈለግህ ባራት ጠጅ እንወራረ ድ ፤ አሁንም ብንሄድ እናገኛቸዋለን ። ያች የኔ ደሳሳ

ጎጆም የተሸጠች እዚያ ቤት ውስጥ ነው ። የዋዛ ሰው አል ምሰልህ ጋሽዬ ፣ ብዙ ብዙ ነገር አውቃለሁ ። ደግሞም ለበ ላይ አቤት እላለሁ ። ላንድ ትልቅ መኪና ለሚነዳ ሾፌር ቤቱን አሜሪቱብኝ ብዬ ። ምናልባት እሱ ባንድ ጊዜ ጭነት ከሰውም ከዕቃውም ብሎ ያሙት ቀለቡን ያገኝ ይሆ ናል ። የሱን የትርፍ ጭነት ገቢ የኔ የስምንት ዓመት ድካም ዋጋ አያስተካከለውም ። እኔ ምን ጐለኝ ? ከእግሬና ከእጄ በስተቀር ቤሳ ቢስቲን የሌለኝ ፣ ድሀ ነኝ ፣ እን ደሱ ጉቦ መክፈል አልችልም ፣ ብዬ አመለክታለሁ ። ቆይ ታያለህ ሳላሸንፈው ብቀር ። በገንዘብ መደለል አይ ሠራም እላቸዋለሁ ። ምን ያስፈራኛል ። አልፈራቸውም ። እነሱ ቅቤና ጮማ ደፍኗቸው ልባቸወ ቢደነድንና ሰውን ከቁም ነገር ባይቆጥሩም አሳያቸዋለሁ ።

ለሊቀመንበሩ ለራሱ ፍትፍት ባገልግል ተሸክመው ቤቱ ድረስ ሲወስዱለት እና ሌላም ሌላም አይቻለሁ ። ይሄ ተገቢ ሥራ ነው ? ይሄንንም እያስመዘገብኩ ነው ” ዛሬማ አካሄዱና አነጋገሩ ሳይቀር ተቀይሯል ።”

እኔ የምወጣበትን ዘዴ ሳሰላስል እንዲያውም ያወቁ ብኝ ይመስል የአቶ መኩሪያ ውትወታ እየተጠናከረ በመ ሄድ ላይ ነው ----

“ ጋሽዬ ያች መናጢ ደግሞ አዝኜ ባስጠጋት ላገኘ ችው ሰው ሁሉ ‘ ባጣና አልጋ ይተኛል ። (ሣር

ፍራቹ እርጅቶ ቢቱን ገለባ በገለባ አድርጕታል ። ልጆቹ የናታቸውን እርጌ ቀሚስ ነው ለብሰው የሚተኙ ' እያለች ትናገራለች ። ይሄ ተገቢ ነው ? እሷ ጠማን ተያፍታ ስታድር ፣ ልጅዋ ረሀብ እየሞሸለቀው የነጠፈ ጡት እየጐ ተተ ለቅሶው እንቅልፍ ከልክሎን ሲያድር ለሰው ተናገ ርኩባት ? ይሄማ የክርስቲያን ወግ አይደለም ። የቤትን ገመና ለውጭ ሰው ማውራት ከየት የመጣ ነው ? ታዲያ ምንስ በልቼ ባድር ምን አገባት ? ከትናንት ወዲያ ጦም አደሩ ፣ ትናንት ቆሎ ገዝተው በሉ ። ዛሬ ደሞ ከነቆሎው ም አረረባቸው ። እንደዚህ ማለት ይገባታል ? እንዲያው ም ለሊቀመንበሩ ለራሱ ጭምር ነግረዋለች አሉ ። ትንገ ረው ፣ ምን ታስደርገኛለች ? ምንስ ያስፈራኛል ? አልፈ ራም ። እሱስ ቢሆን ዛሬ ሱፍ መልበሱን አየች እንጂ ለሱ ሪውንኳ መጣፊያ ያልነበረው መሆኑን እኔ አጥቼው ነው ? ዛሬ ውስኪና ቢራ መጠጣቱን አየች እንጂ ትናንት ከእኔ ጋር ጠጅ ይጠጣ አልነበረም ? ዛሬ ከትልልቅ ሰዎች ጋር ውሎ እኔን ናቀኝ እንጂ ጓደኛው አልነበርኩም ? ደሞስ ሁል ጊዜ ማክሰኞና ሐሙስ ስብሰባ ላይ ናቸው እየተባ ልኩ አንድ መታወቂያ ለማሳደስ ስንት ወር መመላለስ አለብኝ ? ዛሬ አልተፈረመም ፣ ነገም አልተፈረመም ፣ ቱንገ ወዲያም ሙንተም አልተደረገበትም --- ይሄንንም እያስ መዘገብኩ ነው ።

እንዴት እንደተስፈናጠርኩ አላወቀውም ፤ እበሩ ላይ እንደ ደረስሁ እየሩ ይበልጥ ሲጫኑኝና ጩለማው

ሲያፈጥብኝ ነው የገባኝ ፣ ማን ቢለቀኝ -- “ እሺ እሺ እንግዲያው ታዲያ ምን ያደርግልኛል -- መታወቂያው ፣ የቤቱ ቁጥር ፣ ስሜ ምን ያደርግልኛል ? ---

“ ሰውዬው እለ ነገር አጥብቀው አልያዙኝም ? ከኔና ከኔው ራስ ላይ አልወረዱም ----- ፍረደኝ --- ፍረ ደኝ --- ከትንሿ ጣት ምኗ ይቆረጣል ።”

# ደብዳቤው

ከሰለሞን ለማ

“ ለተወዳጇዋ እህቴ ለወይዘሪት ብስራት ። አይችሽ ፣ ድንገተኛው ፍቅርሽ የዘወትር ሰቀቀን ሆኖብኛል ። በፍቅርሽ ወጥመድ ውስጥ ገብቼ በጉምኸርት ካራ መተፍተፍ ከጀመርኩ ውዬ አድሬአለሁ ። ዳሌሽ ፣ ጣቶችሽ ፣ ፀጉርሽ አንገትሽ ብዬ ውበትሽን ለማድነቅ አልሞክርም ። ቃላት አጥረውኝ በጅምር ከምተወው አለመሞከሩን መርጫለሁ ። ፈጣሪ ብዙ ሰዎችን መሥራት የሚችልበትን ጊዜ በአንቺ ላይ አጥፍቶአል ። ተጨንቆ ተጠቦ የሠራሽ በመሆንሽ ኩራት ይሰማሽ ። አንቺን በማፍቀሬ እኔም ኩራት ይሰማኛል ። በዓይኖችሽ ግርፍታ ከተገረፍኩ ወዲህ ፣ ዋኝቼ ከማልወጣው የፍቅር ባሕር ውስጥ ገብቻለሁ ። ከአንቺና አንቺን ከወደደው ከእኔ ሰውነት በቀር ሌላ ማየት አስጠልቶኛል ። የምበላው አይሰማማኝም ፣ የሰዎች ፣ ወሬ አይጥመኝም ። ምን አለፋሽ ዘመድ የሌለው እብድ ሆኜልሻለሁ ። ይህ ሁሉ አንቺን በማፍቀሬ አንቺን በመውደዴ ነው ። ብስራት ፍቅረኛዬ እንድትሆኚ መርጬሻለሁ ። እንደማትጨክኚብኝ አውቃለሁ ። በእኔ መጨከን ያን ተጨንቆ ተጠቦ የሠራሽን አምላክ ማስቀየም ነው ። ዓይኖችሽ ብዙ በማንበብ እንዲቀሉ አልፈልግም ። መልስሽም አጭር ቢሆን ደስ ይለኛል ። ቁርጥ ያለ ። እሺ ወይም እምቢ ። ይኸን

ያልኩሽ ያንቺን መልስ ማንበብ ይሰለቸኛል ብዬ አይ ደለም ። ብዙ በመጻፍ እኒያ አለንጋ ጣቶችሽ በብዕር እንዲዶለድሙ አልፈልግምና ነው ። በተስፋ መልስሽን እጠብቃለሁ ። ሰላምና ጤና ከአንቺ ጋር ይሁን ።”

የፍቅርሽ ምርኮኛ

ህዳር 21 ቀን 1950 ዓ.ም.

ደጋግሜ አነበብኩት ። ጥሩ አልነበረም ። አያረ ካም ፤ አይስብም ። እንደገና የሚያሳዝን እኔ ከገባሁበት የፍቅር ባሕር ውስጥ እሷንም ስቦ የማስገባት ኃይል ያለው ደብዳቤ መጻፍ አለብኝ ። እንደገና መጻፍ አለ በት ። ስሜትን ኰርኩሮ ፤ አሳዝኖ ፤ አሳልቆ ፤ የፍቅር ወጥ መድ ውስጥ የማስገባት ኃይል ያለው ።

ነፍሳቸውን ይማረውና አባ ተገኝ መርቴሎ ፤ የቀን ሥራ ሲሠሩ ውለው ሞቅ ብሏቸው ማታ ሲመለሱ “ሴቶችን መካብ እራሴ ላይ ውጭብኝ ማለት ነው” ይሉ ነበር ። የአባ ተገኝ ንግግር ትዝ አለኝ ። እውነትም ሴቶ ችን መካብ አያስፈልግም ። ኩራብኝ ፣ ዘንጭብኝ ማለት ነው ። በእራሴ ላይ አልፈርድም ። ይኸም የልብ ኩራት ሳይሰጣት አይቀርም ። ይኸንኑ እንዳለ ወስጀ እስረክ ባታለሁ ። ልቤን ግን ዳግመኛ አልሰጣትም ።

የህዳር ማርያም ናት ይኸን ሁሉ ጉድ የሠራችኝ ። እራሷ እንዳመጣች እራሷ ትወጣታለች ። ያን ዕለት

የምሠራበት መሥሪያ ቤት ዘበኛ አቶ ቀናኒ የህዳር ማር ያምን ደግሰው ለምሳ ይጠሩኛል ። ፀሐይ በራስ ትክ ክል ስትሆን የጀመርኩ ሥራየን ትቼ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ከአራት ማንቆርቆሪያ ጋር ብቻዬን ስጋ ተር ውዬ በመጨረሻ ስግተረተር ፣ ሰጀንን ፣ ወደ ሥራ ቦታዬ አመራሁ ። የመሥሪያ ቤታችንን የሠራተኞች ማስታወቂያ ሠሌዳ ስታነብ ነበር ያችን ንብል አይቼ በፍቅሯ የተነደፍኩ ። ዕድሜ ለአራቱ ማንቆርቆሪያ ጠላ ። ስሟንና ምን እንደምትፈልግ ለማወቅ ጊዜም አልፈጀ ብኝ ። ታዲያ ምን ይሆናል። አራት ማንቆርቆሪያ ጠላ ይገፍ ግማሽ ልቤን አስረክቤ እቤቴ ገባሁ ። ከህዳር ማርያም ወዲህ ጤና አጥቻለሁ ። እንቅልፍ የሚነሳ ፣ አበድ ሰከር የሚያደርግ ። ሁለት ሰዓት ተኩል መሆኑን የሚያበስርልኝ የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ደወል ድም ጹን ሲያሰማ ወደ መሥሪያ ቤቴ አመራለሁ ። አቶ ገዛኸኝ ቢሮ ገብተው ከመቀመጣቸው በፊት ነው ደወል የሚያ ሰሙት ። የሚሰለች ድምፅ ። ወ/ሮ አስካለ የሂሳብ ቤቱ ሹም እንግዳ ይበዛባቸዋል ። በየደቂቃው ሁለት ሻይ ማለ ትን ያዘወትራሉ ። ዛሬም እንደ ትላንቱ በህዳር ማር ያም ፍቅር እየተሰቃየሁ የምሠራውን ሳላውቅ ውዬ አደ ርኩ ።

የብስራት ፍቅር እንቅልፍ ነስቶኛል ። ትናንት ያለወ ትሮዬ ሰክሬ መምጣቴ አልነበረም እናቴን ያስገረማት ።

ያሳመሴ እራት ያለመብላቴ ፣ ቁርስም ያለመጠየቁ ነበር ያሳሰባት ። እና ለዚህ ሁሉ ሲባል አንድ ማስረያ ያስፈ ልገው ነበር ፣ የብስራት ፍቅር ። ብስራትን ፈልጌ በቀ ጥታ በፍቅሯ መውደቄን መንገር ወይም ደብዳቤ ጽፎ መስጠት ። በደብዳቤውም ቆረጥኩበት ። ትልቁ ጣጣ ግን ማድረስ ነበር ።

ብስራት አሁን የት ትገኛለች ? ተመልሳም እኛ መሥሪያ ቤት መምጣቷን እግዜር ይወቀው ። ለብዙ ጊዜ ሥራዬን ትቼ የምትገኝበትን አካባቢ ማጥናት ነበረ ብኝ ። የፍቅር ደብዳቤ እንደቀላል ዕቃ አይሰጥምና አመቺ ጊዜና ቦታም ያስፈልገኛል ። በክብርና በፍቅር ፣ በተቀ ሰቀሰ ስሜትና በፈገግታ ግለት መሆን አለበት የሚሰ ጠው ። ታዲያ ለዚያ ቁም ነገር ስል ከአቶ ገዛኸኝ የሚሰ ለቱ የደወል ድምፅ መላቀቄን አልጠላሁም ። የወይዘሮ አስካለንም እንግዶች ማየት አስጠልቶኝ ነበር ። ከወዳጄ ከአቶ ቀናኒ ጋር አለሙተያየቴ ነበር ትንሽ ቅር ያለኝ ።

ዛሬ ከተማው ን ዝምታ ውጦታል ። ሰዎች የዝም የዝምታ የተባሉ ይመስል ቀጥ ፀጥ ብለው በፍርሃት መሬ ቱን ይረግጣሉ ። መኪናዎች ይመላለሳሉ ። በስተቀኝ በኩል ወደፒያሳ ተርታውን ይርመሰመሳሉ ። በስተግራም እጥፍ እጥፍ ሆነው በየመኪናው ያወራሉ ። የሚያወሩት ግን አይሰማም ። አቶ ገዛኸኝ ግራቸውን ይዘው ከፒያሳ በኩል

በዝግታ ይመጣሉ ። ሥራ ባለመግባቴ እንኳን እሳቸው መኪናቸውም የተቆጣች ትመስላለች ። ከፊት ለፊት ካለው ፎርማታ እንዷት ልጅ ያዘሉ ሴት ከአንድ ሽማግሌ ጋር ያወራሉ ። በግራና በቀኛቸው ወጣት ወጣት ወንድና ሴት ተኮራርፈው ቆመዋል ። ፈንጠር ብላ አካባቢዋን የናቀች የምትመስል ወይም እዚህ ቀረበ የማትባል ልጅ ቆማ ከፊት ለፊቷ ያለውን ሕንፃ በጥሞና ታስታውሳለች ። ባለደብዳቤዋ ብስራት ናት ። ቶሎ ውኃ ጠማኝ ከንፈሮቼ መንቀጥቀጥ ጀመሩ ። ቀስ ብዬ ከደረት ኪሴ ደብዳቤውን አወጣሁ ። ላብ ፤ ላብ አለኝ ። ደብዳቤውን በግራ እጄ ጥብቅ አድርጌ ይዣለሁ ። ፍርሃት ፤ ፍርሀት አለኝ ። ባልዲ ውሀ በራሴ የተደፋ ይመስል ፤ ከመሀል አናቴ ፀጉሬን አቋርጦ የሚወርደው ላብ ፊቴን ሸፈነው ። መኀበዝ አለብኝ ብዬ ቆረጥሁ ። አራሴን ታዘብኩት ። በግራ እጄ ፊቴን አጥርቼ ጠረግሁ ። ጠንከር ፤ ጀገን ጀገን አልኩ ። በብስራትና በእኔ መካከል ከአስር ሜትር የማያንስ ርቀት አለ ። ቀና ብዬ ወደ ብስራት አተኮርኩ ፤ ፊት ለፊት ካለው ሕንፃ ዓይኗን እንደተከለች ናት ። በሙሀከላችን የነበረውን እርቀት በጀግንነት ቀነስኩ ። ከጐኗ ቆሜ እንደእሷ ዓይኔን ከሕንፃው ላይ ተከልኩ ። ረስታኝ ይሆን? ምን ብዬ ላናግራት ። አውቶቡሷ አለፈች ልበላት ወይስ መሥሪያ ቤታችን ከፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ አውጥቷል ልበላት? የለም ዝም ብዬ ደብዳቤውን ልስጣት ። የምን ደብዳቤ? ብትለኝስ ከሕዝብ ፊት ላፍር? ሰውነቴን

የጭንቀት ማእበል ዋጠው ። ብስራት የእኔ ጭንቀት አል ተሰማትም ። እሷን ፍለጋ መምጣቴንም አታውቅ ። "ወይ የአንድ ወገን ፍቅር" ብዬ አዘንኩ ። አሁን ዶብዳ ቤውን መስጠት አሰብኝ ። ጕበዝ ጀገን አልኩ ፣ ከንፈሬን አላወስኩት ። ምን መናገር እንደነበረብኝ ግን አላው ቅም ። ትኩር ብዬ አየኋት ። ዘወር ብላ ገ መጠችኝ ። ፈገግ አልኩ ። ለፈገግታዬ ምንም መልስ አልሰጠች ኝም ። ደስ አለኝ ። የፍቅር ስሜት ተቀሰቀሰብኝ ። "የጎ ዳር ማርያም እንቺው አሳኪው" አልኩ ።

"ታዲያስ እህት?" አልኩ ፣ በጭንቀት ድምጽ ። አልሰማችም ። ቁጥሩን ያላየሁት አውቶቡስ ድንገት መጥቶ በሮቹን በርግዶ ይገተራል ። ሰዎች እየተጋፉ ገቡ ። ብስራትም ትጋፋለች ። ዶብዳቤውን አልሰጠሁም ። አው ቶቡሱ ውስጥ ገብቼ ልስጥ ? የለም ። ትኬት ቆራጯ ጋር እጣላለሁ ። ከተሣፋሪት ፊት ላፍር ? አላደርገውም ። ግን አውቶቡሱ ጥሩ አጋጣሚ ነበር ። ገፍቶ ይቅርታ ይባላል ። በምክንያት ይወራል ። መተሻሸት ይቻል ነበር ። የእኔን የፍቅር ግለት በትሽሽት ወደ እሷ ለማስተላለፍ ። ምን ያደርጋል ብስራት ሄደች ። እኔ ግን አስራ አምስት ሳንቲም አልነበረኝም ።

በንዴትና በብስጭት ጉዞዬ ወደ ቤቴ ሆነ ። ዛሬ ከመ ቼውም ይልቅ ሃሳብ ገብቶኛል ። አንደ የጎደለኝ ነገር አለ ። ቅንጣትም ያህል ጀግንነት አልፈጠረብኝም ። ወይ ወኔ ማጣት ።

እነ ታደስ እነ ገብረ መስቀል ፣ አይ የከተማልጆች ! ስምንተኛ ክፍል አብረውኝ ይማሩ ነበር ። በትምህርት ቤታችን የታወቁ ልጆች ነበሩ ። ምነው ፣ የነሱን ወኔ በሰጠኝ ፣ እነ አሰለፍ የእነ ታደሰ እነ ታደሰ የእነ አሰለፍ ነበሩ ። በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ጨዋታው ሁሉ ስለእነሱ ነበር ። እኔ ደግሞ የአማርኛን ክፍለ ጊዜ በጣም እጠላው ነበር ። በተለይ ንባብ ከሆነ እምባ ይመጣብኛል ። የእኔ ተራ ደርሶ ተነስቼ ሳነብ ፣ እነ አሰለፍ በሱሪዬ ቀዳዳ ቂጤን እያዩ ይሳሳቁብኝ ስለነበር ፣ በዚህ የተነሳ አማርኛን ከነ አስተማሪው ነው የምጠላ ። አይ የዱሮ ጓደኞቹ ! አሁንማ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ። ይሄኔ እንደ አቶ ዓለሙ የከተማውን ቆንጆዎች እንደጨርቅ ሳይለዋውጡ ይቀራሉ?

ተስፋ መቁረጥ የለብኝም ። የፈጀውን ጊዜ ይፍጅ እንጂ የብስራት ደብዳቤ ለብስራት መድረስ አለበት ። የፈለገው ደመወዝ ይቆራረጥ እንጂ ዓላማዬ ሳይሳካ ወደ ሥራዬ አልልም ። ለናቴስ ቢሆን ከገንዘቡ መጉደል የኔ መቅበዝበዝ ጭንቀቷን አያባብሰውም ?

እለቱ ሰንበት ነው ። እናቴ በጧት ተነስታ ቤተክ ርስቲያን ሄዳለች ። እናቴ ሳትኖር ቁርሴን የማዘጋጀው እኔው ነበርኩ ። ዛሬ ግን ሳይበላ ይቅር እንጂ ማድቤትም አልገባ ። ተኝቼ ስለ ብስራት አስባለሁ ። ዛሬ ሰንበት ስለ ሆነ ብስራት ከቤት አትወጣም ። ነገ በትናንቱ ሰዓት

መጠበቅ አለብኝ ። የነገው የሞት ቀጠሮ ነው ። በቀጥታ እጅዋን ይገፍ እነጋግራለሁ ። ደብዳቤዋን የእንቺ ነው ብዬ እሰጣለሁ ። የምታደርገኝን እየዋለሁ ። በብስራት ፍቅር የመጣውን ሁሉ እቀበለዋለሁ ፣ እያልኩ የብስራትን ደብ ዳቤ በእጄ ይገፍ በሃሳብ ሳወጣና ሳወርድ በሩን በርግዳ እናቴ ትገባለች ።

" አልተነሳህም እንዴ ?

" አልተነሳሁም ምነው ቶሎ ተመለሽ ? "

" የለም ዛሬ እንግዳ ቤታችን ስለሚመጣ ቃለ እግ ዚአብሔር ሲሰማ ነው አቋርጬ የመጣሁት "

"የምን እንግዳ ነው የሚመጣው ? "

"እዬ ምን ቸገረህ ጥቁር እንግዳ ነው "

እናቴ ከእኔ ጋር ብዙ ጥያቄና መልስ ለማድረግ የፈ ለገች አልመሰለኝም ። ሮጣ ማድቤት ገባች ። ቆየት ብሎ ቡና ስትወቅጥ ተሰማኝ ። የማላውቀው እንግዳም ወዲ ያው መጥቶ ከቡናው መስተናገድ ጀመረ ። "እንዴት ነው የሚያያርገው ?" ይላል እንግዳው ከቡና ቁርሱ እየቆረ ጠመ ። "ይኸውልዎ አይናገር ፣ ምግብ አይወስድ ፍዝዝ ብሎብኝ ተቸግሬለሁ ። ለወትሮው ሳቂ ተጫዋች ነበር ። የነካብኝን አላውቅም ። ሌሊትም እንቅልፍ የለውም ፣ አንዱ ልጄ አንጉል ሆኖብኛል "። "ብዙ ቀን አደረገ ?" ይላል እንግዳው ኮስተር ብሎ "መቸ ነው እቴ -- እዎ ። ያለፈ ችው ህዳር ማርያም ዕለት መጠጥ ጦሳይ ወስዶ እምኝቶ

መጣ ። እራቴንም አላለም ፤ ጢትም ዝም ብሎ ወጣ ። ተዚያ ወዲህ ነው የተለከፈው" ። ጥቁሩ እንግዳ ከያዘዉ ኮሩዳ ውስጥ መጽሐፍ ማገላበጥ ጀመረ ። እንግዳው ለም፣ እንደመጣ አወቅሁ ። "ወይ እናቴ" አልኩኝ በሐዘን ። እኔ የሆንኩ ሌላ እሷ የምታስብ ሌላ ።

እናቴን ላለማስቀየም ምንም ድምፅ አልሰጠሁም ። ትኝቸ ነገሩን ሁሉ በጽሞና እመለከታለሁ ።

"አዎ እሜቴ" አለ ጥቁሩ እንግዳ

እናቴ ጆሮዎቿን ከመቸውም ይልቅ ከፍታ አፍጥጣ ታያለች ። የድንጋጤ የመሸበርና የጉጉት ስሜት ምል ክት ከፊቷ ይነበባል ።

"አዎ ። ጓደኞቹ ናቸው ያጠፉት በጠላ አቅምሰው ታል" አለ እንግዳው

"ታዲያ ም ን ይሻለዋል ጌታዬ ?"

"ቀላል ነው የእሬንሳውን ሶስት ብር ያምጡና መድ ኃኒቱን ቆርጬ እቀብርለታለሁ ። ወዲያው ቀጥ ነው የሚያደርገው"

"እንዳፍዎ ያርግልኝ ፤ እንዳፍዎ ያርግልኝ" እያ ለች ሶስት ብሩን ለማምጣት ሽር ጉድ ማለት ጀመረች ።

"አይሆንም - - አይሆንም" አልኩ በቁጣ ድምጽ ድንገት ። ትዕግሥቴ አልቆ ተሟጦ የእናቴ ምስት

ብር በከንቱ ሲጠፋ በመዘጋጀቱ ፡፡እናቴም ጥቁሩ እንግ ዳም ለሁለት ያዙኝ ከተኛሁበት ላይ ፡፡

"እሱው ነው እንዲህ የሚያደርገው" አለ ጥቁሩ እንግዳ

"ለወትሮው ሌሊት ሌሊት ነበር እንዲህ የሚያደር ገው ዛሬስ በቀኑ አቃገተው" አለች እናቴ ፡፡

"ሙጽሐፉን አልወደደውም ፡፡ የሰማዩ አይወድም እኮ ፡፡ እኔማ ብዙ ያናግረዋል ብዬ ነበር ስደግም ፡፡ አዲስ በመሆኑ ነው አለመደውምና ነው ብዙ ያላ ስጮኸው ፡፡"

"ኧረ አይልመድብኝ፡፡ ልጄን ሳይለምደው ይቅር" አለች እናቴ በቁጭት ድምጽ ፡፡ እራሱዋን እያወዛወዘች በእጆቿ ደረቷን እቅፋ፡፡

ምንም መናገር አልፈለግሁም ፡፡ በተናገርኩ ቁጥር ፣ የሚያናግረው እሱው ነው ስለሚሉኝ፡፡ ጥቁሩ እንግዳ ሰስ ቱን ብር ይዞ ወጣ፡፡ ወይ የብሥራት ጣጣ ! ድርስ ለያ ዘኝ የፍቅር አባዜ ማርከሻው መቸ ጥቁሩ እንግዳ ኑሯል ? ደብዳቤዬን ከኪሴ ዳበስኳት ፡፡ ችግሩ ወኔው ነው ስል ተራሴ ጋር ተሟገትኩ፡፡

እሁድም አልፎ ሰኞ ተተካ ፡፡ ሚዳውም ያውልህ ፣ ፈረሱም ይኸውና ይል ይመስል ፡፡ ሰባት ሰዓት ሆኗል ፡፡ ሰዎች የተለመደ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ውለው ወደ የቤታቸው ይጣደፋሉ ፡፡ መኪናዎች እየተደራረቡ ያል

ፋሉ። በስተቀኝም በስተግራም ብስራት የምትቆምበት ፌርማታ በሰዎች ተሞልቷል። መጽሐፍና ደብተር የያዙ ወጣቶች ይበዛሉ ። አንድ ባንድ የሰዎችን ፊት አጠና ሁኝ። ብስራት አልነበረችም ። የብስራት መምጫ ሰዓት አልደረሰም ነበር ። ከፌርማታው ፊንጠር ብዬ ብስራ ትን መጠበቅ ጀመርኩ ። የብዙ ጊዜ ፍቅር ያደረባቸው ወጣቶች እጅ ለእጅ እየተያያዙ ያልፋሉ ። እየተሳሳቁ። "የታደላችሁ" አልኩ በሆዴ ቅናት እየኮረኮረኝ። የብስ ራትን ደብዳቤ አንቄ ግራ ቀኝ መባዘን ጀመርኩ ፤የፍርድ ቤት መጥሪያ እንደሚሰጥ ሰው ። የሰው ብዛት ቀለል ብሏል ። አልፎ አልፎ መኪናዎች እየፎከሩ ያልፋሉ ። ብስራት ከአንድ ደልደል ብላ የምታምር አፍንጫ ጉራዳ ጋር ጠደፍ ጠደፍ እያለች ስትመጣ ከሩቅ አየሁ። ብቻ ዋን ባለመሆኗ ደስ አላለኝም ። ሽንጤን ገትሬ ኮራ ብዬ ጠበቅኋት ። አውቶቡስም የምትጠብቅ አይመስልም ፤ ፌርማታውን አለፈች ። ትንሽ ቆሜ ከተመለከትኳት በኋላ መከተል ጀመርኩ ። ብስራት ፊት ፊት እኔ ከኋላ ። ላነጋግራት ? ምን ብዬ? ብስራት ልበላት ? ሳትረሳኝም አትቀር ። የት ታውቀኛለህ ብትለኝስ ። ከራሴ ጋር ሙግት ያዝኩ ።

ብስራት ከመቸውም ይልቅ ዛሬ አምራና ደምቃ ታየችኝ ። ከኋላዋ ሆኘ አፈጣጠሯን እያደንቅሁ ምራቄን ውጬ ጨረስኩ ። ብስራት ብቻዋን አለመሆኗ ጎድቶ ኛል ። ሀዘንና ትካዜ ወረሩኝ ። አቀርቅሬ በሀዘን መከ

ተሴን ቀጠልኩ ያርባ ቀን ዕድሌን እያማረርኩ ። የለም - - - ዛሬ ወንድ ይውጣኝ እጁዋን አፈፍ አድርጌ ደብዳቤውን ሰጥቼ መልሱን ነገ ልበላት አልኩ ። ፍጥነቴን ጨመር አደረኩ ። ከፊቴ የማገኘውን ነገር ሁሉ በእግሬ እየመታሁ አቀርቅሬ ስገሰግስ ከፊት ለፊት ካለው የመብራት ብረት ጋር ተጋጨሁ ። ከፉኛ ነበር የመታኝ ። ከግንባሬ ደም ፍልቅ ፤ ፍልቅ ፣ ትንን ፤ ትንንንን ማለት ጀመረ ። ብስ ራትን መከተል አቁሜ ግንባሬን አፍኘ ተመለስኩ ። ለካስ ችግሬ ወኔው አልነበረም ። ያርባቀን ዕድሌ እንጂ ።

በማግሥቱ ሶስት ሰዓት ላይ መሥሪያ ቤት ደረ ስኩ ። ግንባሬ በመለጠፉ ጠያቂ በዛብኝ ። ያም ምን ሆንክ ? ያም ምን ሆንክ ? አቶ ቀናኒ ጋር ቁጭ ብዬ ሳወራ አቶ ዓለሙ ይመጣል ። አቶ ዓለሙ ሰላምተኛና ተጫዋች ሰው ነው ። አቶ ቀናኒና እኔን አይቶ ትንሽ ሳያዋራን አያልፍም ። በቅርቡ ከዩኒቨርሲቲ ጨርሶ ነው እዚህ ሥራ የያዘው ። ዓመት ቢሆነው ነው እዚህ ሥራ ከገባ ። “ምን ሆንክ ?” መዳቡ ይለኛል ። ዓለሙን ልሸ ሽገው አልፈለግሁም ። ያንን ሁሉ ኮረዳ የሚያመላልስ ሰው ዘዴ አያጣም ብዬ ሚሥጥሬን እስከዳር አጫወት ኩት ። በነገሩ በጣም ያዘነልኝ መሰለኝ ።

የህዳር ማርያም ታምር ማብቂያም የለው ። አምስት ሰዓት ይሆናል ብሥራት ወረቀቶች ይዛ በድንገት መሥ ሪያ ቤታችን ከተፍ ትላለች የምገባበትን አጣሁ ።

በጭንቀትና በደስታ ተወጥሬ ፈዝዤ ቀረሁ ።

"ለሥራ የሚመዘገበው የት ክፍል ነው ጋሼ?" አለችኝ ወደ እኔ ጠጋ ብላ ። ረስታኛለች ። ደብዳቤውን ከኪሴ እየፈለግሁ "ሥራ ጠያቂ ነሽ?" አልኳት ።

"አዎ"

"መረጃዎችን ይዘሻል?" ደግሜ ጠየቅሁኝ የማ ያገባኝን ። አዎ ነበር መልሷ ። ወደ አቶ ዓለሙ ቢሮ መራ ኋት ። አቶ ዓለሙ ነው አዲስ ሠራተኞችን የሚቀጥር ። ከየት መጡ ሳይባሉ አቶ ዓለሙ የሚለዋውጣቸው ቆን ጆዎች በዓይነ ኅሊናዬ ድቅን አሉብኝ ። ከመቅጽበት ቢሮው በር ላይ ጆሮየን ለጥፌ ማዳመጥ ጀመርኩ ። ምን ምን እንደሚባባሉ ። ስም? ዕድሜ--የትምህርት ደረጃ? ይላል አቶ ዓለሙ ። ብስራትም ትመልሳለች ። ትንሽ ቆይ ቶም አቶ ዓለሙ "ተዚህ በፊት እዚህ አመልክተሻል?--" ይላል ። ልቤ ከመጠን በላይ ይመታ ጀመር ።

ለአቶ ዓለሙ የሆንኩትን ሁሉ እጫውትዋለሁ ። ይህች ነች እንዲህ ያደረገችኝ ልበለው? የለም ። እሷ ስትወጣ ይሻላል ። መቸም የበለጠ አጋጣሚ አላገኝም ። ድንገት ይደውላል ። ከአቶ ዓለሙ ቢሮ ነው ። መግባት አልፈለግሁም ። ደግሞ ተደወለ ። ብርግድ አድርጌ ገባሁ ። "ታዲያስ ጃል ምን ልርዳህ" አልኩ ነቃ ብዬ እንደ ጓደ ኛዬ ። "ሁለት ሻይ በልልኝ" አለኝ ። ላመጣ አልፈለ

ግሁም ። በሩን ዘግቼ ወጣሁ ። ስለእኔ የሚያወሩ መስ
ላኝ ። ብዙም አላዳመጥኩ ሻዬን ለማስመጣት ሮጥኩ ።
ስለእኔ ያወራውን ብሰማ ደስ ባለኝ ነበር ። ሻዬን አዝዤ ፣
በሩ ላይ ተለጥፌ ማዳመጤን ቀጠልኩ ። የሚያወሩት
አይሰማም ። ጋሽ ታደሰ ሁለት ሻሂ ይዞ ከተፍ አለ ።
ጋሽ ታደሰን አስከትዬ ዘው ብዬ ገባሁ ። ዓለሙና ብስ
ራት ይሳሳቃሉ የብዙ ጊዜ ትውውቅ እንዳለው ። እንደ
ሀውልት ተገትሬ በጥሞና ሁለቱንም ተመለከትኩ ። ቶሎ
ደሜ ፈላ ማንባረቦቃ ያደረገኝ ፍቅር ማስሪያ ስለአጣ ።
ከቆምኩበት ሳልንቃንቅ ሻዩን ጨረሱ ። የማደርገውን
ባጣ በቀጥታ ቢሮውን ለቀቅሁ ። ከጥቂት ደቂቃዎች
በኋላ በሩ ይከፈታል ። ብስራት ለአቶ ዓለሙ ያሰበችውን
ፈገግታ በጨረፍታ አሳየችኝ ። ለመናገር የፈለገችውን
ሳትናገር የወጣች ትመስላለች ። ለጨረፍታው ፈገግታ
የፈገግታ ሙልስ ሰጠሁ ።

"እግዜር ይስጥልኝ አመሰግናለሁ" አለችኝ ፤ ጠጋ
ብላ ። ብስራት ከመቸውም ይልቅ ሽንጧ ቀጥኖ ፣ ፀጉሯ
ረዝሞ ፣ የምትዋጥ የምትገመጥ መስላ ታየችኝ ። ለ"እግ
ዜር ይስጥልኝ" ምንም መልስ አልሰጠኋትም ። ፈዝዤ
ቀረሁ ። ብስራት ጥላኝ ሄዳለች ። ሻይ ስላስመጣሁ ይሆን
ወይስ ቢሮውን ስለመራኋት "እግዜር ይስጥልኝ" ያለ
ችኝ ። አልገባኝም ። ምን እንደሆንኩ ደግሞ አታው
ቅም አቶ ዓለሙ ካልነገረ በቀር ። አቶ ዓለሙንም

ቢሆን "ታዲያስ ጃል ?" ብየዋለሁ እሷ ፊት ። በፍጹም ማንነቴን አትጠረጥርም ። ግን ሻይ ላስመጣ ስወጣ ስለግ ማውራት መጀመሩን እርግጠኛ ነኝ ። ቢሆንም ልታውቅ አትችልም ። እንዲያውም አቶ ዓለሙ ስለኔ ሆኖ ሳያኔ ባባልኝ ይቀራል ?

ብስራት መሥሪያ ቤታችን በመጣች በስድስተኛው ቀን ከተለመደው አውቶቡስ መጠበቂያ አገኘሁዋት ። ዛሬ እንደቀድሞው አልፈራኋትም ። በቀጥታ ሄጄ ጨበጥኳት ። ሰላም አለችኝ ። ፈገግታዬን ሰጠኋት ። እጥፍ አድ ርጋ መለሰች ። አቶ ዓለሙ ብስራትን በጁ እንዳስገባ ልኝ ተረዳሁ ። ብዙ ጊዜ ማጥፋት አልፈለግሁም ። ደብ ዳቤዋን አውጥቼ መልሱን ለነገ ብዬ አስረከብኳት ። ምንም አልተግደረደረችም ፥ ተቀበለችኝ ። እንደገና ፈገግ ታዬን መገብኳት ፥ እሱዋም እንዲሁ ። በዚህ ተሰነባብ ተን ወደቤቴ ተመለስኩ ። የህዳር ማርያም ፍቅር እሳት ማሰሪያ በማግኘቱ ተደሰትኩ ። እናቴ ከጭንቀቷ ልትገ ላገል ነው ። በሕይወቴ እንደዛሬዋ ዕለት የተደሰትኩ ባት ቀን አላገኝም ። ቤት ገብቶ እናቴን ሳጫውታት ፥ ሳስደስታት አደርኩ ።

በቀጠሮዬ ቀን የብስራትን መልስ ለመቀበል ወደ ቀጠሮው ቦታ አመራሁ ። ብስራት በትክክለኛው ሰዓት አልተገኘችም ። አትመጣም ብዬ አልተጠራጠርኩም ። የምትመልስልኝ አጭር መልስ ነበር ያሳሰበኝ ። እምቢ ሂትለኝም ። ምናልባት ላስብበት እንደሆን እንጂ ። ብስ

ራት መጥታ እሽ ወይም እምቢ የሚለውን መልስ ለማን በብ ቸኩዬአለሁ ።

ሰው በሰው ላይ የተደራረበበት ከጭነቱ የተነሳ አልፎ አልፎ ቂጡ ከመሬት ጋር እየተላተመ የሚሄድ አውቶቡስ ድንገት ጡጥቶ ከፊቴ ይቆማል ። "ወራጅ ወራጅ" የሚል ድምጽ ከውስጡ ይሰማል ። በሩ ተከፍቶ ሰዎች ትከሻቸውን አስቀድመው የሌሎችን ትከሻ በትከሻቸው እየሰረሰሩ ፣ እየገፉ ፣ እየተጋፉ ለመውረድ ይሻማሉ ። "ወ ራጅ ወራጅ" የሚል ወፍራም ድምጽ እየተሰማ ። አፌን ከፍቸ ስመለከት ብስራት እጇን ያዝ ታደርገዋለች ። ከየት በኩል እንደመጣች አላውቅም ። ኩራት ተሰማኝ ። ይዛ የመጣችው መልስ "እሽ" የሚል መሆኑ ከፊቷ ፈገግታ ይታወቃል ። እጥፍ ደስታ ተሰማኝ ። ከእሷ ጋር ብዙ መቆየት አልፈለግሁም ። መልሱን ለማወቅ ስለጓጓሁ ።

"መልሱን ብስራት" አልኳት

ቦርሳዋን ከፍታ የታሸገ ፖስታ ሰጠችኝ ። አድራሻ አል ተጻፈበትም ። ደህና እደሪ ብዬ ተሰናበትኳት ። የአቶ ዓለሙን ውለታ እንዴት እንደምመልስ እያሰላሰልኩ በፍ ጥነት ወደ ቤቴ መገስገስ ጀመርኩ ። ዛሬ ከፍተኛ ድል ነው የተጎናጸፍኩት ። "የልፋቴ የድካሜ ዋጋ ነው ይህ ደብዳቤ" አልኩ ፖስታውን እያሻሸሁ ። እንደችኮላዬ በመንገድ ላነበው ግን አልፈለግሁም ። የልፋቴን ዋጋ አረፍ ብዬ ነው ላየው የፈለግሁ ።

ዛሬም እኔና እናቴ ደስተኞች ሆነናል ። አባቴ ከዛፍ ላይ ወድቆ ከሞተ ወዲህ እናቴ ትናትናና ዛሬ ብቻ ነው የተደሰተችው ። ለእናቴ ሰላምታ ሰጥቸ ቀጥታ ወደ እልጋዬ ሄድኩ ። የድካምና የልፋቴን ዋጋ ፣ የብስራትን መልስ ተንጋልዬ ማንበብ ጀመርኩ ።

"በአንድ ቀን አውቄህ በአንድ ቀን ላፈቀርኩህ ወንድሜ ለአቶ መሣቡ ዳዲ ። ሰላምና ጤና ከአንተ ጋር ይሁን ። የጻፍክልኝን ደብዳቤ ሳነበው እውነትም አልመሰለኝም ። አይቸህ በፍቅር ከወደቅሁ በኋላ የማደርገው ጠፍቶኝ በጭንቀት ላይ እንዳለሁ ነው ደብዳቤህ የደረሰኝ ። የደስታ ሲቃ ይዞኝ የጻፍኩት ስለሆነ ምን አልባት ደብዳቤዬ ላያረካህ ይችላል ። "እሺ" ወይም "እምቢ" ቢሆን ደስ ይለኛል ላልከው ፣ መልሴ እሺ ነው ። ሁልጊዜ ከፊትህ ቁጭ ብዬ ስመለከትህ ብውል ደስ ይለኛል ። መልክህንና ፀባይህን ነው በፍቅርህ የወደቅሁት ። ለተደረገልኝ የሻይ ግብዣም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ። በቅርብ ውለታህን እመልሳለሁ ። የአንተና የእኔ ፍቅር በሁለታችን መሀል ብቻ ቢሆን ደስ ይለኛል ። የጻፍክልኝንም ደብዳቤ አንተው እምጥተህ ልትሰጠኝ ሲገባህ በተላላኪያችሁ በመላክህ ተቀይሜህለሁ ። ቢሆንም ሁሉንም ተገናኝተን እስክንጨዋወት ደህና ሁንልኝ ።"

ቻው

# ጉዞው

ከሲሳይ ንጉሡ

## 1

በነርሶች ሚሠልጠኛ ት/ቤት ሳለሁ የተዋወቅኋት ፣ ጓደኛዬ ትሩፋት ፣ ውሎዋም አዳሯም ከእኔው ጋር ስለነበረ መግባባታችንም ከመቀራረባችን ጋር አብሮ አደገ ። መተሳሰባችንንና መፈቃቀራችንን ለተመለከተ ፣ ከአንድ እናት ማሕፀን የወጣን እህትማማቾች እንመስል ነበር ። አስፋው ስለተባለው እጮኛዋ ሁኔታም በዝርዝር የገለጸለችልኝና ያስተዋወቀችኝ በዚሁ ት/ ቤት እያለን ነበር ።

አስፋው የሀብታም ነጋዴ ልጅ ስለነበር በትምህርቱ ብዙም ሳይዘልቅበት አቋርጦ የአባቱን የንግድ ቦታ ከያዘ ቆይቷል ። ራሱን በመንከባከብና አለባበሱን በመለዋወጥ ወጣት ለመምሰል ቢሞክርም በዕድሜው ጠና ያለ መሆኑን እንደመኮማተር ያለው ግንባሩ ይመሰክርበታል ።

ትሩፋት እንደገለፀችልኝ የተገናኙት ገና በልጅነቷ ነው ፤ ሌሎች ወጣቶች እንደሚያደርጉት ሁሉ ት/ቤት ስትሄድ ተከታትሏታል ፤ በመኪናም አልፎ አልፎ ሸኝቷታል ። ከኔ ጋር በነርስነት ት/ ቤት በምንማርበትም ወቅት ቢሆን በሳምንት ሶስት ጊዜ ያህል ይጎበኛት ነበር ። እሷም ቢሆን የሱ ነገር አይሆንላትም ፤ በመኝታ ሰዓት ስለእሱ ሳታጫውተኝ የተኛችበት ጊዜ በቁጥር ነው ። የተዟዟሩበትን ቦታ ቢሰተቦቻቸው በእነሱ ፍቅር

ጣልቃ ገብተው ያደረሱባቸውን በደል ፣ በዚህም የተ ነሳ ተቃቅረው እምብዛም እንደማትቀርባቸው ፣ ጋብቻ ቸውን ለመፈጸም የትምህርቷን መጨረስ እንደሚጠ ባበቁ - - - አስፋው ጎጆዋም ፣ ቤተሰቧም ፣ ምናም ምናምእን ደሚሆን ያላት ተስፋ የጸና መሆኑን - - ምንም ሳትደብቀኝ ዝክዝክ አድርጋ ታጫውተኝ ነበር ። ማንኛውም ጨዋታ ቢነሳ በመሀል የአስፋው ነገር ጣልቃ መግባቱ አይቀ ርም ። በድንገተኛ አጋጣሚ ስትደነግጥ እንኳ "አስፍዬ ድረስ" ማለት ይቀናታል

በመጀመሪያ አካባቢ ፣ በዕድሜ በጣም የሚራራቁ ሰዎች ይህን ያህል መፋቀራቸው ያስደንቀኝ ነበር ። የኋላ ኋላ እየተላመድኳቸው ስመጣና ከአስፋውም ጋር በደንብ ስንቀራረብ ግን ጭራሽ ያስቀኑኝ ነበር ። በእ ሁዱ የእረፍት ቀናችን መኪናዋን ይዞ ይመጣና የማ ያስጐበኘን ቦታ የለም ። አንዳንድ ማስታወሻዎችም ይዞ ላት ሲመጣ ለእኔም ማምጣቱ አይቀርም ። አንዳንዴ ከቅ ናት የተነሳ ትሩፋትን ለማጥላላት እሞክር እንደነበር አስ ታውሳለሁ ፤ እሱዋን መሆን የተመኘሁበትም ጊዜ ነበር ።

በዚህ ዓይነት ፍቅራቸው እያደገ ሲሄድ እኛም ትም ህርታችንን የምንጨርስበት ጊዜ ተቃረበ ። በየሆስፒ

ታሉ የምናደርገውን ተግባራዊ ልምምድ እጅግ አድካሚ መሆን ጀመረ ። ለምንወዳቸውና ለምናፈቅራቸው ሰዎች የሚኖረን ትርፍ ጊዜ እያነሰ ሄደ ። አስፋው እንደ ወትሮው መምጣቱም ባይቀር እንደለመደው ይዞን ለሽር ሽር መውጣት ባለመቻሉ እየተበሳጨ የተመለሰባቸው ጊዜያት አልታጡም ። ትሩፋትም ቢሆን የተለመደ ፍላጐቷ ስለተጓደለ ብስጩነትና ነጭናጫነት እያደረባት ሄዷል ፤ በሽተኞችን በትህትና አታነጋግርም ፣ መርፌ በምትወጋበት ጊዜ የበሽተኞቹን ሥር ለማግኘት ያቅታታል ። የታዘዘችውን መድኃኒት በጊዜው ለበሽተኞች አታቀርብም ፤ ከዚህም የተነሳ ሥራዋ መበደል ጀምሯል ። በሰውነቷም ላይ ቢሆን የሚታየው ለውጥ ቀላል አልነበረም ከውስጧ የምትቃጠል ዓይነት ፊቷ ወዙን እያጣ የሚያባብሉ ዓይኖቿ ውሃ የደረቀ ዓይነት ክችል ያለ አስተያየት እየተሿሿረበትና ዙሪያውንም ቀጫጭን ስሮች እየተዘረጋጉበት ነው ። የአፏም አካባቢ ቢሆን ሁሉ ጥርሶቹዋን ኩርትም አድርጋ ያለች ነው የሚመስለው ፤ በከንፈሮቿ ላይ ይታይ የነበረው ደማምነት ተደብቋል ።

## 2

በዚህ መካከል ነው አንድ ቀን ዘመድ ነኝ ባይ ሰው ሊፈልጋት የመጣው ። ትሩፋት ቀዶ ጥገና ክፍል ስለነበረች የእኔንና የእሱዋን ጓደኝነት የሚያውቁ

ሌሎች ነርሶች የሆስፒታሉን ዘበኛ እኔ ዘንድ ይዘውት መጡ ። እኔም ጉዳዩን እንዳስረዳኝ ተከትየው ወጣሁ ። ሰውዬውን እበሩ አጠገብ ቆመው አገኘናቸው ። ሰውየው በኔ መምጣት አልተደሰቱም ፤ ገና ሲያዩኝ "ትሩፋት የታለች?" ብለው ጠየቁኝ ፣ እኔም የተቻለኝን ያህል ለማስረዳት ሞከርሁ ፣ ከዚያ የባጥ የቆጡን መቀባጠር ጀመሩ ። " አይገባም ፣ አይገባም ፤ እንዴት ሰው የሚሞት አባት ዓይኑን ማየት አይሻም ? እርግጠኛ ነኝ እኔ እሥራ ላይ እንዳልሆነች ፣ በሱዋ ቤት መደበቅ ያለችው ነው - - የእርኩስ ልጅ እርኩስ ነው - - በእርግጥም የእናቷ ልጅ ነች–" የማያወርዱት ርግማንና ስድብ አልነበረም ፤ በበሩ አካባቢ የነበሩ ሰዎችና እኔም ዝም ብለን አዳመጥናቸው ። ትንሽ የበረደላቸው ሲመስለኝ ነው መልዕክት እንዳላቸው እንዲነግሩኝ አለዚያ እሷ እስከትመጣ እንዲጠብቁ ነግሬያቸው ልመለስ ስል " እግዚአብሔር ዓይኗን አያሳየኝ ፣ እሷን ለማየት እኔ አልፈልግም - - " በማለት የመጡበትን መናገር (ጀመሩት" ብቻ እስከዛሬ ተዶጋግሞ ቢነገራትም የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብላለች - ሆኖም ከእኔው ይቅር ግድየለም - - እና የምፈልገው ወላጅ አባትሽ ከዛሬ ነገ መሞቱ ስለሆነ ሊያነጋግርሽ ስለሚፈልግ በነፍሱ ድረሽ ብለሽ እንድትነግሪልኝ ነው - - አሁንም ሰምታ ከቀረች—እግዚአብሔር ፍርዱን አይንሳት ፣ ሌላ ምን እላለሁ- - - "ብለው እየተቆናጠሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

ሰውየውን እየተመለከትሁ እቆምኩበት እንደተገተርኩ ቀረሁ ፤ ለጊዜው በአእምሮዬ የሚመላለሰው ነገር ባይታወቀኝም ፣ አጠቃላይ ሁኔታው ረብሾኛል ። በመሠረቱ ትሩፋት ስለቤተሰቧ ብዙ አታወራም ፤ አባቷ ግን ገና በልጅነቷ መሞታቸውን ገልጻልኛለች ።

እሷዋ እንዳለችው ከሆነ ሰውየው የሀሰት መልዕክተኛ ናቸው ማለት ነው ። እሱዋ ግን ዋሽታኝ ከሆነ ፣ ለምንስ ትዋሸኛለች ፣ ለምን ሄዳ አትጠይቃቸውም ? ነርስ እንደ መሆኗ ለምንስ አትረዳቸውም ? ምናልባት በመካከላቸው ቂም እንኳ ቢኖር ፣ ለእናቷ አግዛ ተቀይማቸው ሊሆን ይችላል --- እንዴት በሞት አፋፍ ላይ እያሉ ትጨክናለች ? ጭራሽ ሊገባኝ አልቻለም ። በእርግጥም ሰውን አውቀዋለሁ ማለት ዘበት መሆኑ ተሰማኝ ።

ትሩፋት ከቀዶ ጥገናው ክፍል ሰባት ሰዓት ገደማ ወጣች ። ሥራው አድካሚ እንደ ነበረ በፊቷ ላይ ያስታውቃል ። እረግጠውጂ ጭምር ድክምክም ማለቷን ያሳያል ። በውነቱ ሳያት አዘንኩላት ፣ እንደዚህ ደክሟት ልትሰማው የማትፈልገውን ነገር ብነግራት የባሰ ትጸቀ ቃለች በማለት ጊዜ ልሰጣት አሰብሁ "ምነው ከባድ አፕሬሽን ነበር ? ደምሽ ሁሉ ከፊትሽ ላይ ጠፍቷል" "በጣም" ብላ ለመናገር የፈለገችውን ካፏ ላይ መለሰችው ። "ምነው አስፈላጊው ምርመራና ዝግጅት አልተ

ደረገም ነበር ? ማለቴ ድንገተኛ ናቸው--?" ብዬ ላና ግራት ሞከርኩ እንደገና ፣ እሱዋ ግን ይብሱን እንኀሸገሻ ትና ጥላኝ ወደ ልብስ መለወጫችን ክፍል ገባች ።

በዚህ ጊዜ በቀዶ ጥገናው ክፍል አብራት የነበረች ዋና ነርስ ወደነበርንበት መጣች "ትሩፋትን አየሻት ?" ብላ ጠየቀችኝ ። "ምነው ደህና አይደለችም?" "እባክ ሽን እባቷ ሞተዋል መሰለኝ ፣ በጠና ስለታመሙ በነፍሳ ቸው ትድረስ የሚል ማስታወሻ አሁን ሰጥቶኝ ሄዶ ያስ ተዳደር ክፍሉ ተላላኪ ። እንዴት ነው የምናረዳት ታዲያ ፣ እቢሮ ጠርተን እንንገራት ፣ መቼም አሁኑኑ መሄድ ያለባት መሰለኝ..."

"አፕራሲዎኑ የተሳካ ነበር እንዴ ? ስትወጣ አይ ቻት ድንጋጤ ይታይባት ነበር ---

"ይኸው ታይቷት ይሆናል ፣ የምታደርገውንም የምታውቅ አትመልስም ነበር ፣ እኔው ነኝ የሱዋን ሥራ የሠራሁት --- አፕራሲዎኑም ተሳክቷል ፤ ይገርምሻል ፣ እንዴት ያሉ መልከመልካም ሰው ናቸው ፤ የአንድ እግራቸው ሶስት ጣት ግን የለም -- ዶክተሩን ብጠይቀው በአደጋ ወይንም በሥጋ ደዌ ሊሆን ይችላል አለኝ -- አሁን ምን ይሻላል ስለ ትሩፋት ?

ትሩፋትን ዋና ነርሷ ቢሮ ጠርተን ነገርናት ፣ ምንም ዓይነት ድንጋጤ አላሳየችም ፤ እንዲያውም የመሞታቸ

ውን ወሬ ስትጠባበቅ እንደነበረ ዓይነት ነው የተሰማኝ ፤ ለእኔም አባቷ ቀደም ብለው መሞታቸውን መንገሯን የዘነጋችው ትመስላለች ። ወደ መኝታ ክፍሏ አብረን ሄድን ፤ ሁላችንም በየበኩላችን ልብሳችንን መለዋወጥ ጀመርን ። በዚህን ጊዜ ነው ትሩፋት መናገር የጀመረ ችው "ይቅርታችሁንና እኔ ማንም ሰው እንዲከተለኝ አልፈልግም ፤ አዜብም ጭምር ... አዜብዬ እንደማትቀየሚኝ ተስፋ አደርጋለሁ" በማለት ድንገት ከመካከ ላችን ውልቅ አለች ፤ ለባብሰን ስላላበቃን እየተጣጣ ሀንም ብንከተል አልሆነም ፤ ከግቢው እንደወጣች በየት በኩል እንደሄደች እንኳ ለማወቅ አልቻልንም ።

እንደገና ወደግቢው ተመለስኩና ለአስፋው ስልክ ደወልኩለት ። እንዳጋጣሚ እሱቱ ኖሮ አገኘሁት ። የትሩፋት አባት መሞታቸውን ነገርኩት ። ለትንሽ ጊዜ ግራ የገባው ዓይነት ዝም አለ ፤ ምናልባት ለኔ እንደነገ ረችኝ ያባቷን በልጅነቷ መሞት ነግራው ይሆን ብዬ ጠረ ጠርኩ ። ከዚያም ቤቱን ያውቀው እንደሁ ይዞን እንዲ ሄድ ጠየቅሁት "-- አዎ እናቷ ነው መሰለኝ በልጅ ነቴ ሞቱ ያለችው" ይላል በስልኩ ውስጥ ፤ ለማንኛውም ቤቱን እንደማያውቀውና ከእግረኛ መኪናኛ ስለሚሻል አብሮን ለመፈልግ እንደሚመጣ ገልጾልኝ ተሰነባበትን ።

ከስምንት ሰዓት ጀምሮ መቃብር ቦታዎችን ማዳረስ ጀመርን ። ወደ አሥር ሰዓት ገደማ ነው ቦታውን የደረ

ስንበት ፤ ስለዚያውም በአስፋው ምክንያት ትሩፋትን የሚ
ያውቃት ሰው ሬሳ ተከትላ ስትሄድ አይቷት ስለነገረን ።
ቦታውን ስናገኝ የገረመን ነገር ቢኖር ደግሞ የሟቹ
ሰው ስምና የትሩፋት አባቴ ነው ብላ የምትጠራበት አለ
መገጣጠሙ ። ስለሆነም እኔ በበኩሌ እኝህኛው የእንጀራ
አባቷ ፣ ወይንም የአባቷ ወንድም ሊሆን ይችላሉ የሚል
ግምት አደረብኝ ፤ የስሙ አለመገናኘት የአባቷን በል
ጅነቷ መሞት በይበልጥ ስላጠናከረልኝ ።

ትሩፋት እኛን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ዙሪያ ቆመን
አየችን ፤ ሰውነቷ ባንዴ ተለዋወጠ ፤ መምጣታችንን
ጨርሶ እንዳልወደደችው ገባኝ ። እኔን በይበልጥ ትገላ
ምጠኝ ጀመር ። ሁኔታዋ አልገባኝም ብሎ ልጠጋት
ብሞክርም ሸሸችኝ ። አስፋው ሁኔታውን ይመለከት ነ
በርና እሱም በበኩሉ ሊያናግራት ወደ እሱዋ ቢያመራ
እሙሾ ለቀስተኞቹ ውስጥ ገባች ። ጊዜ ይፍታው ብለን
እነበርንበት ተመልሰን ቆምን ። ሙሾ አውራጅዋ ስለ
ሟቹ ጀግንነት በሰፊው ገጠመች ፣ ስለፊታውራሪ ቆራጥ
ነት በአምስቱ የጠላት ዘመን ጠላትን እንዴት እንዳር
በደበዱት ፣ ብዙ ኒሻን እንደ ተሸለሙ (ወደ አንድ ኒሻ
ናቸውንና የክብር ልብሳቸውን ወደ ያዘ ሰውዬ እያመ
ለከተች) ሠርቶ መብላት የማይችል በሽተኛና እጅ እግ
ሩን ያጣን ሁሉ ይደግፉ እንደነበረ ፣ አወረደችው

ማጥሙን ። እኔም ተደንቄ ማዳመጤን ቀጠልኩ፣ በልቤ ሰውን አውቀዋለሁ ማለት ለካ ዘበት ነው እያ ልኩ፤ የትልቅ ሰው ዘር መሆኗን ሳትገልጽልኝ ጓደኛዬ ሆና መኖሯ እየገረመኝ ---

በአስር ሰዓት ተኩል ገደማ ቀብሩ አለቀ፤ ወደ ቤት መልስ ሆነ፤ እኛም አብረን ተከተልን ። እቤትም ያው እንደ ማንኛውም ሌላ ቀብር ሥነ ሥርዓት ነበር የተካሄደው፤ እግ ቢው በር ላይ እጃችንን ታጠብን፣ እግቢው ውስጥ እተተከ ለው ትልቅ ድንኳን ውስጥ ገባን፣ በአግዳሚዎች ላይ ተኮለ ኮልን ፣ ንፍሮና ቆሎ ቀረበ፣ ቡና ለሚፈልግ ቡና፣ ለስላሳ ለሚፈልግ ለስላሳ ታደለ ። አልፎአልፎ በቀብሩ ላይ ያል ነበረ ለቀስተኛ እየተጯጯኸ ገባ፤ ቀስ በቀስም ሰው እየተ ሰናበተ መውጣት ጀመረ ። ይህ ሁሉ ሲሆን የገረመኝ አንድ ነገር ቢኖር ፣ ለሰውየው ተንሰፍስፈው ያለቅሱ የነበሩት ወንድም ፣ እህት ፣ ወይም ልጆች ነን ባዮች ሳይሆኑ ባለባበሳቸውና በሁኔታቸው ችግረኞች መሆና ቸው የሚታይባቸው ሰዎች መሆናቸው ነበር፤ ዓይነ ስውሩ ፣ በእንቶቅቁ የሚሄደው ፣ የሥጋ ደዌ በሽተኛው እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ።

አሥራአንድ ሰዓት ሲሆን እኔም ወደ ሥራዬ መመ ለስ ፈለግሁ ። አስፋውና እኔ ተሰያይተን ስለነበረ የተ ቀመጥነው እሱ ሰፊ ጨዋታ ይዟል፤ እሆስፒታል ድረስ መጥተው እየተራገሙ ከተመለሱ ሰውዬ ጋር ። ቢሆንም

የግድ የሱን እርዳታ ስለፈለግሁ እነበረበት ቦታ ሄጄ የሚሄድ እንደሆነ ቢያደርሰኝ ጠየቅሁት ። ሰውዬው ያው ቁኝ አልመሰለኝም ፣ ቢያውቁኝም እንዳላወቁኝ ነው የሆኑት "ታዲያ ፣ እንዴት ሰው አባቱን ፣ ያውም ፊታውራሪን ያህል ከባድ ሰው ፣ በውነቱ ልንገርህ ወንድሜ ስለሆነ አይምሰልህ ---" ይላሉ እልፍ እልፍ እመዳፋቸው ላይ ጎብጠው ባሉበት በደረቁ የቀኝ እጅ ጣቶቻቸው ጢማቸ ውን ጎተት ጎተት እያደረጉ ። አስፋው አገጩን በጁ ደግፎ ፣ በርግጥም የሚሰማውና የሚያየው ነገር ባንዴ እርጅት ጅት ያደረገው ዓይነት ፊቱ ኮሶ የጠጣ ሰው መልክ ዓይ ነት መስሎ ፣ ዓይኑን በግርግዳ ሥር ተክሎ ያዳምጣል ። እኔን ወደ እነሱ ስመጣ አየት አደረገኝና ለጠየቅሁት ጥያቄ "እኔ ትንሽ እቆያለሁ" ከማለቱ በስተቀር ተመ ልሼ ልሂድ ወይም እዚያው ቆሜ ልጠብቅ ያጤነኝ አይ መስልም ነበር ። የሰውየው ጨዋታም ይሁን ሌላ ነገር ስሜቱን የያዘው ሊያደርሰኝ አለመፈለጉን ስረዳ ተመ ልሼ ወጣሁ ።

ማታ አራት ሰዓት ገደማ ትሩፋት ተመለሰች ። ምንም ሳትናገር እመኝታዋ ውስጥ ገብታ ተኛች ። ማዕ ናናት የሚያሻት መስሏቸው አንዳንድ ነርሶች ወደ አል ጋዋ ቢመጡም ይባሱኑ ተሸፋፈነች ። የያዛት አባዜ እስኪ ለቃት እኛም ተውናት በማግስቱ ካልጋዋ ሳትወጣ ዋለች ። ለሳልስቱም ለቅሶ አልሄደችም ፣ እኛም ስለማንኛውም እድራጐቷ ልንጠይቃት አልፈለግንም ።

በዚህ ዓይነት ሶስት ቀናት ያህል እንዳለፉ ወደ
ሥራዋ ገባች ፤ ሥራዋ ደግሞ የግድ ከሰዎች ጋር መተባበ
ርንና መነጋገርን ስለሚጠይቅ የግድ ከሰዎች ጋር ሀሳብ
መለዋወጥ ጀመረች ። ከእኔም ጋር ፣ ባይበዛም ፣ መነጋገር
ጀመርን ። ሳምንት አለፈ ፣ አሥራ አምስት ቀን አለፈ ፣
ቀስበቀስ እንደዱሯችን መሆን ጀመርን ። እንደ ዱሯችን
ሳንደባበቅ ምስጢሮቻችንን መካፈሉን ቀጠልን ። ስለሞ
ቱት ሰውየና ስለ ለቅሶው ቢሆን አንስተን አናውቅም ፤ መነ
ሳት እንደማያስፈልግም ሳንነጋገር የተግባባን መሰለኝ ።

አስፋውም ቢሆን በርግጥ ለውጥ ቢታይበትም እየ
መጣ መጠየቁንና ስጦታም ማምጣቱን ቀጥሏል ። ስለሆ
ነም ብዙ አይናገርም ። ብዙም አይስቅም ፤ ሳቁ ደረቅ ዓይ
ነትና ሹል ስለሚሆን ሲሰሙት አያስደስትም ። በዚህ ላይ
አንዳንድ ልምዶቻችንን ቀንሷል ፣ በተለይ ከሽርሽር
ሲመልሰን ይስመን ነበር ፤ እሷን አፏ ላይ ፣ እኔን ጉንጭና
ጉንጩን ። አሁን ይኸን ትቷል ፣ እኔም ፣ አላውቅም ፣ ብዙ
ነገር የቀረብኝ ነው የመሰለኝ -- ቻው ብሎ እጁን ሲያ
ሾል ሲል ፊቱን አዙሬ ነው የምሄደው ፣ ልክ በጥፊ ያጮ
ለኝ ያህል ። ትሩፋት ምን እንደሚሰማት እግዜር ይወቅ ።

## 3

የትሩፋትና የአስፋው መራራቅ በግልፅ እየታየ መጥ
ቷል ። አዳዲስ አቃቂር ማውጣት ጀምሮአል ፤ በተለይ ትም

ሀርታችንን ልናጠናቅቅ ጥቂት ወሮች ሲቀሩን ስለአስፋው የሚወራው ወሬና የምናያቸውም አንዳንድ ነገሮች ከበፊቱ እጅግ የባሱ እየሆኑበት ሄዱ ። በመኪናው ሽርሽር ወስዶን ሲመለስ ትምህርት ቤታችን አጠገብ ያወርደንና ያው በደረቁ "በሉ ቻው!" ካለ በኋላ ዘወር ብሎ ወደ ትሩፋት እየተመለከተ ይስቃል ። መኪናውንም አስነስቶ ከሚሄድበት ጊዜ መሳቁን አያቋርጥም ። አሳሳቁ ደግሞ የመገረምና ነገር አዘል መሆኑ ያስታውቃል ። ከለት እለትም በተገናኘን ቁጥርና በተጫወትንበት ቦታ ሁሉ ይህንን የመገረም ሳቅ አበዛ ።

ይህ አዲሱ ፀባዩ ለብዙ ጊዜ አብራው ለቆየችው የሚያስበውን አውቅለታለሁ ለምትለው ውድ ፍቅረኛው ለትሩፋት እንኳ እንግዳ ነገር ሆናባታል ። አዘውትራም " አስፋው የሚስቅብኝ ምን አይቶብኝ ነው?" እያለች ትጠይቀኛለች ። እሁድ እሁድ ቀን እንደ ወትሮው ሁሉ ሽር ሽር አድርሶን ሲመለስ ከመኪና ካወረደን በኋላ ሳቅ እያለ ሞተሩን ሲያስነሳ ፣ ትሩፋት የሳቁን ነገር ለመረዳት ወደ መኪናዋ መስታወት መለስ አለችና በመስኮት በኩል አንገቷን ገባ አድርጋ " አስፍዬ በቅርቡ የገጠመህ ምን አዲስ ነገር አለ? ወይስ የሚያስገርምህ ምን ነገር አለ? አይታወቅህ እንደሆን እንጂ ዝም ብለህ ትስቃለህኮ" ብላ ተንኮል ሳታስብ የሩህሩህነቷንና የፍቅሯን ጠየቀችው ።

አሁንም በመገረም የመኪናውን መሪ ተደገፈና እየ ሳቀ "ስለእንቺው እጮኛዬ እያሰብኩ ነዋ!" አላት "እባክህ

አትቀልድብኝ ይልቅ የሚያስቅህን ነገር ንገረኝ ! በእኔ
ላይ ምን የተለየ ነገር እየህና ነው ? ”እንደገና ጠየ
ቀችው ፣ እሱም “ እኔ የምልሽ ---” አለና ጀምሮ ሲና
ገር የፈለገውን መልሶ ዋጠው ። ይህ ሁናቴው ከትሩ
ፋትም አልፎ እኔን ጭምር ከነከነኝ ። የልባቸውን ሁሉ
እያወጡ ሲጫወቱ የነበሩ ፍቅረኞች ሲደባበቁ ፣ ሲጠራጠ
ሩና ሁኔታቸው ሁሉ ለወጥ ሲል አጃቢ መሆን አያድርስ
ነው ። ወደየትኛው ሆኖ የትኛውን መጣል ይቻላል ?

ትሩፋት መኪናዋን አለቅም ብላ መልሱን ትጠባ
በቅ ስለነበረች ወደ እኔ ዞወር አለና “ጓደኛሽን አትገላ
ግይኝም ? ” ሲል ጠየቀኝ ። ከሳቅ ሌላ መልስ አልነበረ
ኝም ። እንደገና ወዲያው ወደ እሱዋው መለስ አለና “እባ
ክሽ ልሂድበት መስኮቱን ልቀቂልኝ ” አላት ። ይኸኛው
አነጋገሩ እንደ ጥንቱ ቀልድና ፍቅር አዘል ስለነበር ትሩ
ፋት ነገሩን ሁሉ በማቅለል “እንጃልኝ ጤነኛ አልመስ
ልከኝም ፣ በሽታህ የሕክምና ትምህርቴን እስከጨርስ ፋታ
የሚሰጥ ከሆነ እኔው አክምሃለሁ ” ብላ ቀለደችና ተደ
ግፎው የነበረውን የመኪናውን መስታወት ለቀቅ አድርጋ
ልትሰናበተው እጆዋን ስትዘረጋ ፣ ለስለስ ባለ ድምጽና
ፈዝ በተቀላቀለበት አነጋገር “እስኪ ቻው እመኛዬ ፣
ለትዳር የምትጠብቂው እኔን አይደል ?! ” አላት ።

“እኔን ያልገባኝ ፣ አዲስ አድርገህ አሥር ጊዜ እመ
ኛዬ የምትለው ነገር ነው ፤ ለፍቅሩ አዲስ አይደለን --”
ብላ መሰላቸት የተቀላቀለበት አነጋገሯን ሳትጨርስ ፣

“እምነሽ የምትጠብቂው እኔኑ ነዋ?” አለና እንደገና ደገመው፤በቀልድ መልክ። ምን መልስ ትስጠው? በቆመችበት የጨው ሀውልት ሆና ቀረች፤እኔንም ዘወር ብላ ለማየት አፈረችኝ፣እሱም ያንኑ ሳቁን እየሳቀ መኪናውን አስነስቶ በረረ። ከዚያን እለት ጀምሮ ትፋሩት በሀሳብ ተዋጠች። በለቅሶው ሰሞን እንደተለወጠችው ዓይነት ለዛ ያለው ጨዋታዋ ጥሏት ሸሸ። ሆኖም በሚቀጥሉት ቀናትም ሆነ ሳምንታት በሙሉ አፏ “እስፋው ጠላኝ” ያለችበት ጊዜ አልነበረም።

“እስፋውን አባለጉት መሰለኝ” ነበር አንዳንዴ የምትለው፤ለዚያውም እየተጠራጠች “ምናልባት ራሱን ነካ አድርጉት ይሆን?ይሄ የንግድ ሥራ መከራ ነው” በማለት ሳትጨምር አታበቃም። እኔም “ይሆናል ማን ያውቃል” ከማለት ሌላ የምጨምረው አልነበረኝም።

ቢጨንቃት ነው እንጂ ያበዱ መች እንዲህ ራሱን ይጠብቃል፤ብቻ ምንም ይሁን ምን ምክንያቱ በእርግጥ አስፋው ይጠላኛል የሚል እምነት አልነበራትም። እስፋው ግን መለወጡን ለማጠናከር ይመስላል፣ያለወትሮው በዚያው ሰሞን አንዱን እሁድ ቀን ሳይመጣ ቀረ። ትፋሩትም ይበልጥ መደናገጥ ጀመረች፤በይበልጥም ጥርጣሬና ስጋት ውስጥ ገባች። እኔም ፍቅራቸው ያበቃ

ዓይነት እየመሰለኝ "በቃሽ ስለእሱ አታስቢ ! ምነው ያለእሱ ሰው የለም እንዴ?» ልላት አስብና የምቀኝነት ወይም የቅናት ሊመስልብኝ ስለሚችል ከአፌ ስመልሰው ቆየሁ ።

4

በዚህን ጊዜ የፊታውራሪ አርባ ደርሶ ኖሮ ተጠራን ። በወቅቱ የገረመኝ ነገር ቢኖር ለትሩፋትም እንደማንኛ ውም ሌላ ሰው የጥሪ ወረቀት መላኩ ነው ። እዋናዋ ነርሷ ቢሮ ለንደሚገኝ ተነግሮን ከእርሷ ዘንድ እየሄድን ነበር የወሰድነው ። ጥሪው ለፊታውራሪው አርባ መሆኑን እን ደተረዳሁ ምናልባት የምረዳው ሥራ እንዳለ አብረን እን ድንሄድ ትሩፋትን ጠየቅኋት ። በዚህን ጊዜ ነው ትሩ ፋት ድምጹዋ እንደመሳሳት እያለ "ትቀልጃለሽ መሰለኝ?" በማለት እሱዋም የተጠራችበትን ተመሳሳይ ወረቀት ያሳየችኝ ።

የግብዣው ወረቀት "በምሣ ሰዓት መጥተው ጠበል ጠዲቅ እንዲቀምሱልኝ" ስለሚል በሰባት ሰዓት እቦ ታው ደረስን ። ብዙም ሰው አልቀደመን ። እንደማንኛ ውም እንግዳ መቀመጫችንን ይዘን ዙሪያውን መመለ ካከት ጀመርን ። "ጉድ ፈላልሽ!" ስትለኝና እሷ ወዳተ ኮረችበት አቅጣጫ ስመለከት ነው እኔም ግራ የገባኝ ። አስፋው ከእኛ የሀሰት መልዕክተኛ ከመሰሉኝ የፊታው

ራሪ ወንድም ጋር አፍ ለአፍ ገጥሞ ያወራል ። ስንገባ አይ ቶን ወይም በሰውየው ጨዋታ ተመስጦ ፊቱን እንዳላየ ያዙር መግባታችንን ሳያጤን ይቅር አልገባኝም ፤ ብቻ ሰውዬው ወደ እኛ አቅጣጫ እየተመለከቱ ወሬያቸውን ቀጥለዋል ---እኛን ከመጤፍም የቆጠረን የለም ። አስፋ ውን ልጠራውም ፈለግሁ ፤ ሂጂ ላነጋግረውም ፈለግሁ ፣ መጥተናል ብዬ ሰው ልልንዘተም ፈለግሁ -- ግን ማን ኛውንም አላደረግሁ ። እንዲያውም ለትንሽ ጊዜ ትሩፋት ንም የረሳኋት መሰለኝ ። በጅዋ ጭኔን ነካ ነካ ስታደር ገው ነው ድንገት ያስታወስኳት "ምነው ምን ነካሽ ? ፊትሽ ምን እንደሚመስል ባየሽው ፤ እየሳቀ የሚያለቅስ ፊት ዓይነት --እኔን ስትመክሪ--" ብላ ሳትጨርሰው ሰውዬው በርግጥ አይተውን ኖሮ ወደ እኛ መጡ ፣ አስፋ ውም መጀመሪያ እንዳየን አይነት ተከትሎ መጣ ። ከመ ቀመጫችን ብድግ ብድግ አልን ፣ ተጨባበጥን ፣ ከዚያ የም ንናገረው የጠፋብን መሰለኝ ሰውዬው ናቸው "እቶ አስፋ ውን ትልቅ ዘመድ አስተዋወቅሽን ፣ የትልቅ ሰው ዘር---" በማለት ፀጥታውን ያስተነፈሱት ፤ ከዚያ አዎ ፣ አስፋው ለጠቀ ፣ ካፋቸው ነጥቆ "ምነው ትሩፋትስ ብትሆን ምን ያንሳታል የትልቅ ሰው ዘር---" እያለ በመናገር ፣ አዲስ ያመጣው ልምጭጭ ሳቁ ፊቱን እያለበሰው "አዎ ፣ በውነት ማን ያደርገዋል አንተ ያደረግሽውን ውለታ---" ቀጠሉ ሰውዬውም በበኩላቸው "አምስት ሣጥን ለስሳሳ ፣ አምስት ሣጥን አምቦ ሀው ፣ አሳብህ ብቻ ይበቃል እና

እንዲያው አሁንም ቢሆን ታዲያ መድፈር ባይሆን ዋጋ ውን ብንከፍል --- አዎ አዎ ! አይነሳብኝ ብለሃል ---" በማለት ፣ በዚህን ወቅት ነው ሰውዬው በመናገር ላይ እን ዳሉ ትሩፋት አንድ ነገር አስፋው ኪስ ስትጨምርለት ያየነው ። እሱም ወዲያው ቶሎ ከኪሱ አወጣው የሃምሳ ብር ኖት ነበር ። ዝምታ ሆነ ፣ ዝምታ ፣ ሰውዬው ትሩፋትን አንዴ አየት አደረጓትና ዞር ብለው ተመለሱ ። አስፋውም ሙልጭልጭ ሳቁን እያፈታ ተመለሰ ። ትሩፋት እንባዋ አነቃት ፣ አስጨነቃት ፣ ወደ ውጭ ወጣች ፣ ተከትያት ወጣሁ ፣ አለቀሰች ፣ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ፣ ስትጨርስ በፊቷ ላይ ሰላም የወረደ መሰለ ። ተመልሰን ገባን ።

አስፋው እቦታው ተመልሶ ተቀምጧል ፣ ሰውየውም አጠገቡ ተቀምጠዋል ። አልፎ አልፎ በቀኝ እጃቸው ጢማቸውን ይሳስባሉ ፣ አስፋውም ልክ እንደሳቸው የሌለውን ጢም አገጩን ይሳስባል ፣ በቀኝ እጁ ጣቶቹን እንደሳቸው እመዳፉ ላይ በበሽታ ተቆልፈው የደረቁ አስ መስሎ ፣ ልምጭጭ ሳቁን እፊቱ ላይ እያዟዟረ ፣ አልፎ አልፎ በግራ እጁ አውራ ጣት አፍንጫውን እየጎረጎረ ።

እውጪ ላሊበላዎች "ወየው ዓለም" ማለት ከጀመሩ ቆይተዋል ፣ የሚፈልጉትን ያገኙ ይመስላል ፣ ምሥጋናው ይደረደራል ፣ "የወንድማችንን ነፍስ ይማርልን ፣ ዘሩን የተባረከ ያድርግልን ---"

## 5

አርባው በዚህ ዓይነት አልፎ ትንሽ እንደሰነባበትን ፣ አንድ ቀን ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ አልጋችን ላይ ጋደም ብለን የባጥ የቆጡን ስንቀባጥር ዘበኛው ደብዳቤ ይዘው ከተፍ አሉ ፤ እንዲህ በአስቸኳይና በምሽት ደብ ዳቤ ሲደርሰን ይህ የመጀመሪያ ጊዜያችን ነበር ። ደግሞም ደብዳቤ በመጣ ጊዜ እኛው ከቢሮ ድረስ ሄደን እንወስዳ ለን እንጂ በጣም አጣዳፊ ካልሆነ በቀር በዘበኛ ተልኮልን አያውቅም ። ስለዚህ ሁለታችንም ተደናገጥን ። ከለቅሶ ቦታ ፣ ከሐኪም ቤት ፣ ወዘተ--- በስቸኳይ ድረሱ የምን ባልበት መርዶ የተላከልን መሰለን ። ትሩፋት በውስጥ ልብሷ ብቻ ከመኝታዋ እየወጣች "አዜብዬ አስፋው ታሞ ሳይሆን ቀረ? ኧረ ምን መታመም ብቻ . . . በጤናውኮ አልቀረም "እያለች ደብዳቤውን ለመቀበል ስትቃጣ ዘበ ኛው ወደ እኔ መጡና" ጤነኛዋ እንኪ ብለው ደብ ዳቤ ውን ለእኔ ሰጥተውኝ ወዲያውኑ ወጥተው ሄዱ ።

ከየት እንዳመጡት ለመጠየቅ እንኳ ጊዜ አልሰጡ ንም ። ደብዳቤው ያለበት ፖስታ ምንም ዓይነት አድራሻ አልተፃፈበትም "ለወይዘሪት ትሩፋት የሚሰጥ" የሚል ጽሁፍ ብቻ ሰፍሮበታል ። እሷ ይህን ስትመለከት "ጉዱ የእኔው ነው " እያለች መጮኋን ቀጥላለች ። እኔም ብሆን

ለእሷ የተሳከ መሆኑ ቢገባኝም እሽጉን በምከፍትበት ጊዜ እጇ መንቀጥቀጡ አልቀረም ፡፡ደብዳቤውን አወጣሁና ገለጥ አድርጌ ስጀምር ‘‘ በጥሩም ሆነ በመጥፎ ነገሮች መለወጥ የእድገት ምልክት ነው ፡፡ በልጅነቴ አፈቅራ ቸው የነበሩትን መጫወቻዎች አሁን ጉዳይ ማለት ደግሞ እድገቴን መቃወም ይሆናል ፡፡’’ የሚል ቃል በት ምህርተ ጥቅስ ተከቦ ተመለከትሁ ፡፡ እሷም ከኔው ጋር ትመለከት ነበርና በፍጥነት የላኪውን ስም ለመመል ከት ወደ ጽሑፉ መጨረሻ ወረደች ፡፡ ’’ ያንቺው የነበ ረው አስፍዬ በላቸው ’’ ይላል ፡፡ ለእኔ ሁሉም ነገር ግልጽ ሆነልኝ ፡፡ ከላይ የሰፈረው ጥቅስ ምን ለማለት ታስቦ እን ደሆነ ወዲያውኑ ገባኝ ፡፡

ቀና ብዬ ትሩፋትን ተመለከትኳት ፡፡ ነገሩ ሳይገባት ቀርቶ ይሁን ወይም አውቃ ችላው ፤ ዝም ብላ ማንበቧን ቀጠለች ፡፡ ያ ጠይሙ ፊቷ ከሰል መስሏል ፡፡ ግንባሯም ቆራጥነትና ኩስታራነት የተመላበት መስሎ ተኮመታት ሯል ፡፡ በጠቅላላው የፊቷ ቅርጽ አዲስና የማላውቀው ሆኗል ፡፡ . . . ጥናቱን ይስጥሽ እንጂ ሌላ ምን ልረዳሽ እች ላለሁ’’ የሚለው ጽሑፍ ጋ ስትደርስ የብስጭት ፈገግታ እየሳቀች ቃሉን ደጋገመችው ፡፡ “ምን ታድርግ እየገደል ከኝ ጥናቱን ይስጥሽ በለኝ እንጂ’’ እያለች ጭንቅላትዋን ከፉኛ እየነቀነቀች ፡፡

ነገሩ ምንኛ እርር ድብን እንዳደረጋት እኔም ተረ ዳሁት ፡፡ አብሬያት ከመናደድ ሌላ ምን ላደርግላት እች

ሳለሁ? አስፋው ከትሩፋት ጋር ያሳለፍናቸው የፍቅር ጊዜያት ከልቡ እንደማይወጡና እሷንም ምንጊዜም እን ደማይረሳት ገልጿል ።

ከዚህም አያይዞ "ስለሆነም አባትሽ ካረፉበት ቀን ጀምሮ አንቺን በእህትነት እንጂ በጋብቻ የመፈለግ ዝን ባሌዬ እየደከመ ስለሄደ---" በማለት ቀጥሏል ። እኔን የገረመኝ ታዲያ "አባትሽ ካረፉበት ቀን ጀምሮ የሚለው ሐረግ ከሥሩ መሰረዙ ነው ። ለምን ከዚያን ቀን ጀምሮ ፍቅሩ መቀዝቀዝ ጀመረ? ምን አገኘባት? ምን ሰማባት? እርግጥ ሌላ የሚወዳት ልጅ ማግኘቱንም ገልጿል ፤ ፍቅ ሩም ወደ አዲሱ እንዲያዘነብል ያደረገው "የእድገት ሂደት" መሆኑን ጠቁሟል ። እኔ ግን እነዚህ አባባሎች መሸፋፈኛዎች መሰሉኝ ። ሌላው ቀርቶ የፊታውራሪን ወንድምም ጠረጠርሁ ፣ ምን አሟውተውት ይሆን? ደግ ሞስ ፊታውራሪው አባቷ ለመሆናቸው እንዴት እርግጠኛ ሆነ? በሳቸው አትጠራ ---"

ትሩፋት ደብዳቤውን አንብባ ስትጨርስ ሽክሙን አውርዶ እንዳሳረፈ ሰው ከመጠን በላይ ተነፈሰች ።

እንደዱሮው ቢሆን ችግሯንም ፣ ሐዘኗንም ፣ ደስታ ዋንም አዋይታኝ አብረን እንቋቋመው ነበር ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ጠባይዋ ተለዋውጧል ። አንዳንዴ ጨርሶ የማላውቃት እየሆነች ሄዳለች ። እና አሁንም ምንም ልታናግረኝ አልፈለገችም ። እንዲያውም ብሶትዋን ሁሉ

በሆድዋ እፍን አድርጋ ከእኔ ለመደበቅ ሞከረች ። ደም የለበሰው ዓይኗ ፣ እንባዋ እንዳይወርድ ከፋኛ ትንቅንቅ ሲያካሂድ ይታያል ። ወይ አልቅሳ ቢወጣላት ይሻል ነበር ። እንዲሁ ድርቅ ማግር ብላ ሁሉንም በሆድዋ ስታብሰለስል ፣ በልቧ ውስጥ የሚነደው እሳት ሲለበል ባት በስሜት ታየኝ ። ወባ በሽታ እንደያዘው ሰው እያን ቀጠቀጣት ከመኝታዋ ውስጥ ገባችና ጥቅልል ብላ ተኛች ። በዚህ ጊዜ ታፍኖ የቆየው እንባ ሰውር ቦታ ያገኘ ይመስል ሲጐርፍ ተሰማኝ ።

ስቅታዋ ክፍሉን አልፎ ውጭ ድረስ አስተጋባ ። ሐዘኑ መች ለእሷ ብቻ ሆነ ? ከብስጭቴና ከድንጋጤዬ የተነሳ ከተቀመጥኩበት መነቃነቅ አቅቶኝ ደብዳቤውም እጄ ላይ እንዳለ ነው ። ማስቀመጫው ጠረጴዛ ባይ ርቅም እጄን ማነቃነቁ ከብዶ ታየኝ ። እኔ እንደ ትሩ ፋት በሆዴ ማመቅ አልቻልኩም "አይ ሰው !" እያልኩ እንባዬን እንቆረቁረው ጀመር ። ማልቀሴና ማዘኔ ጓደኛ ዬን ለመርዳት ወይም ለማስመሰል አይደለም ። በእስ ፋው ላይ ከልብ የመነጨና እውነተኛ ፍቅር ነበረኝ ። እጮኛነቱ ለትሩፋት ቢሆንም ቅሉ ፣ ለእኔ ለጓደኛዋ ያደረገልኝ ውለታም ስፍር ቁጥር የለውም ። ፍቅሩም የዚያኑ ያህል ነበር ። ታዲያ እንዲህ ያለ ሰው እንዳል ነበረ ሲሆን ለቅሶ ምን ነው ? በእውነቱ እስከመጨ ረሻው ሰውን መውደድ የሚያስመኝ አልነበረም ።

የትሩፋት እንባ መቆምያ አላገኘም ። ጭራሽ እየጮ ኸች ታነባው ጀመር ። ለዚሁ ቀን ብላ አጠራቅማው እንደሆን እንጂ በእውነትስ የሰው ልጅ ይህን እያነባም ። ቆራጥ ስትመስለኝ ጠንካራ ስትመስለኝ --እኔ ደሞ ያችን ስታንቆራጥጣት የነበረች ፣ አምሳ ብር እኪሱ ስትጨም ርለት ምንኛ አስመክታኝ ነበር ፣ ለካ ከፉነቷን ማሳየቷ ብቻ አልነበረም ፤ የበለጠ ፍቅርም ለማትረፍ ኖሯል ? ከዚ ያን ጊዜ ጀምሮ ፍቅሩ ተጠናክሮ እንዲመጣ ኖሯል የም ትጠብቀው ፣ ለገንዘብህ አይደለም የምወድህ ለማለት -- ሞኝት ተላሊት ።

"አይዞሽ ትሩፋቴ ፣ ተዋዶ መለየት በእናንተ አልተ ጀመረም" ብዬ የማጽናናት ቃል እንዳላሰማት የምታመ ናጭቀኝ መሰለኝ ። አዲስና ኃይለኛ ፍጡር እንጂ የጥንቷ ውዷ ጓደኛዬ ትሩፋት አልመሰል አለችኝ ። ለማነጋገርም ፍርሃት ፣ ፍርሃት አለኝ ። እንዲህ ዓይነቱን በሽታ ማስታ መም በጣም አስቸጋሪ ነው ። ከኔን አይወስድበት ፣ ዶክ ተር አይጠራለት እንዲያው ብቻ አብሮ "እህህ" ማለት ሆነ ።

የጭንቂን "ተይ እንጂ ትሩፋት ፣ የምን እንዲህ መሆን ነው ? ደግሞ ለዘንድሮ ፍቅር ---" አልኩና በአንሶላው ጫፍ እንባ ያራሰውን ልጠርግላት እጇን ስዘረጋ ፣ በሚሞ ቁት እጆቿ ያዝ አደረገችኝና "ስታውቂው አዜብዬ ስታው ቂው" ብላ በዚህ በአጭር ቃል ስፊውን ትርዒት ከፊቴ

ደቀነችብኝ ። የተንሸራሸርንባቸው ቦታዎች ፣ የመጡልን የስጦታ ዕቃዎች ፣ የተነሳናቸው ፎቶግራፎች ፣ ከተዋወቅንበት ቀን ጀምሮ ከአስፋው ጋር ያደረግናቸው ጭውውቶች በሙሉ ድቅን አሉብኝ ። ሁለታችንም እዩዩውን አቀለጥነው ። ላጽናና የሄድኩትም ቤትዮ ሌላ አጽናኝ ፈለግሁ ። እንግዲህ ማን መቻሏን ይወቅበት ? ገላጋዩ ያው ድካም መጥቶ ሲያስተኛን ብቻ መሆኑ ነው ።

ከዚያች ምሽት ጀምሮ የትሩፋት ነገር ባይወራ ይሻላል ። እንደ ልብ ድካሙ ፣ እንደ ራስ ምታቱ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብስጭቱ በጠበጣት ፣ ይህ ሐኪም የማይገኝለት በሽታ ክፉኛ አሰቃያት ። የድሮዋ ትሩፋት ልትሆን አልቻለችም ። ሰውነቷ እየመነመነ በእጥንቷ የምትሄድ መሰለች ። የደስ ደስ የነበራቸው ጉንጮቿ መጎድጎድና ማጎጥ አመጡ ። ለዛ የነበረው ጨዋታዋ ጠፍቶ በአጭር ቁርጥ የሚለውና የሚዘጋው ንግግሯ ተተካበት ። “ከሥራ በስተቀር ስለምንም አትናገሩ” አለች ። ሰዎችን የሚያስደስታቸውና የሚያዝናናቸው ነገር ለእሷ ምንም መስሎ አልታይ አላት ። ፍቅረኞች እንኳ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወይም ተቃቅፈው ስትመለከት ፊቷ ከሰል መስሎ ከመቅጽበት ከአጠገባቸው ርቃ ትሄዳለች ። ትዳር ስለሚባለው ነገር የነበራት ምኞትና ሀሳብም ጨርሶ ጠፋ ። በአጭሩ ፤ በምኗም በምኗም የድሮዋ ትሩፋት መሆኗ ቀርቶ አዲስና ልዩ ፀባይ ያላት ትሩፋት ሆነች ።

የአስታማሚነት ትምህርታችንን ጨርሰን ተመረቅን ። በየሆስፒታሉም ተደለደልን ፤ በአዲስ አበባ ውስጥ ባሉት ሆስፒታሎች ። ከትሩፋት በስተቀር ሁላችንም ሥራችንን ጀመርን ።

ትሩፋት የወትሮ ጠባይዋ ተለውጦ ጨርሳ ብቸኛ ሆና ነበር ፤ ወደ መጨረሻ ገደማ ። መነጋገር የለ ፤ ሃሳብ መለዋወጥ የለ ፤ መመካከር የለ - - - እንዲሁ ብቻ ነበር አብ ረን የምንውለው ። ዲፕሎማችንን የተቀበልን ምሽት አድርገነው እነበረው የደስደስ በዓል ላይ እንኳ አልተገ ኘችም ።

ወደየምድብ ሥራችን ከተሰማራን ከአንድ ወር ያህል በኋላ ብቸኝነት እየተሰማኝ ስለሄደ ልዕልት ዘነበወ ርቅ ሆስፒታል ደወልሁ ፤ ትሩፋት የተመደበችው እዚያ ስለነበር ። በዚያን ቀንም ሆነ በተከታታዮቹ ቀናት ስለ እሷ የሚነግረኝ አላገኘሁም ። ከሳምንት በኋላ ይመስለ ኛል አስተዳዳሪውን በስልክ አግኝቻቸው በሥራ ላይ ያለ መገኘቷን የገለጹልኝ ። ለጊዜው ዘመዶቿም ቢሆን ይህ ንነቷን እንጂ የት እንደምትሠራ አያውቁም ነበር ። ከብዙ ፍለጋ በኋላ ነው መርካቶ ውስጥ አንድ እግል ክሊኒክ ውስጥ የምትሠራ መሆኗን የደረስሁበት ።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ክሊኒኩ ሄድሁ ። ለጊዜው ስላልገባች ትንሽ ቁጭ እንዳልሁ የክሊኒኩ ባለን ብረት ጀርመናዊ ዶክተር ገቡ ። ከዚያም ምንም ያህል ሳይቆይ የትሩፋት እኅት ነኝ ባዩ ፣ እመዳፋቸው ላይ በተቆለፉ ደረቅ ጣቶቻቸው ጢማቸውን እየደባበሱ ገቡ ። እኔን ያጤኑኝ አልመሰለኝም ፤ ዙሪያውን መልከት ብለው ተቀመጡ ።

በሽተኞችን ሲያስተናግድ የነበረው የሐኪሙ እረዳት እንደገለጸልኝ ትሩፋት የዚያን እለት ያህል ዘግይታ አታውቅም ። አራት ሰዓት ገደማ ነው የመጣችው ፤ እንደ መጣችም ግራና ቀኝ ሳትመለከት የሥራ ልብሱዋ ወዳለበት ክፍል ገባችና ለዋውጣ ብቅ አለች ።

እኔን መጀመሪያ አየችኝ ። ለጊዜው እሷም እንደ ኔው የናፈቀችኝ መሰለኝ ። ሮጣ መጥታ ሳመችኝ ። ትንሽም ልታነጋግረኝ ፈልጋ ይመስለኛል እጐኔ ቁጭ አለች ። በዚህን ጊዜ ነው ሰውዬውን ያየቻቸውና ሰውነቷ ባንዴ የተለዋወጠው ፤

" ደግሞ ዛሬ ምን አመጣዎት ፣ ነግሬዎታለሁኮ ፣ ለመቃብር ሐውልት ገንዘብ አላዋጣም -- አላዋጣም --- ስንትዬ እንድነግርዎት ይፈልጋሉ --" በማለት ወደ ሰውዬው የተፈናጠረችው ። ለጊዜው ገፍትራ ልታስወጣቸውም መስሎኝ ነበር ። ሆኖም አጠገባቸው ስትደርስ ራሱዋን ገታች ።

ሰውዬው ቁጣዋን የለመዱት ዓይነት ንክችም አላሉ ፣ ዝግ ባለ አንደበት ፣ “ ለሐውልቱ መዋጮ ለማድረግ አለመፈለግሽን ደጋግመሽ ነግረሽናል ፤ እኔም አልረሳሁትም ፣ እና ዛሬ የመጣሁት መልዕክት ለማድረስ ነው —”

“ከእናንተ የሚመጣ መልዕክት መስማት አልሻም —”

“ - - - እንደሚታወቂው የልዕልት ዘነበወርቅ ሆስፒታል አስተዳዳሪ እየደወሉ - - ”

“ ብህግ አምላክ ይውጡልኝ - - - ”

“እንዴ ምን ያከረተርትሻል - - አልወጣም - -አንቺ ብትፈልጊ እኔን ላለየማየት ልትወጪ ትችያለሽ - - - - - እርግጠኛ ነኝ ዘነበወርቅ ሆስፒታልንም የጠላሽው እኔን ላለማየት ነው - - - ሰማሽይ ፣ እኔስ ቢሆን ፈልጌ ያመጣሁት መሰለሽ - - - ”

“ በሕግ አምላክ ብየዎታለሁ - -

“ በዛሬ ልጆች ሲሰኛኑት - - ባንቺም ላይ - - ባንቺም ላይ ሊመጣ ይችላል - ያቺ እናትሽ እኔን በመጠየፏዋ አባትሽን ጥላው ሄደች ፣ ደግሞ ያንቺ - - ግዴለሽም ላስተዳዳሪው እነግርልሻለሁ ያለሽበትን ቦታ - - ይቺ - - - ቆይ - - - ይህን የምትጠይውን ደዌ ስታባብይ ያልተገኘሽ እንደሁ

ሰውዬው ፣ ከዚህ ቀደም ያባቷን (እርግጠኛም ባል ሆን) መታመም ለመንገር ሆስፒታል መጥተው ተቆናጥ

ረው እየተሳደቡ የሄዱትን ዓይነት ፣ ዛሬም በዚያው ዓይ ነት ወጡ ። የትሩፋት ፊት ድሮ መጉመጥመጥ ጀምሯል ፤ እንባ ሲተናነቃት --- ሮጣ ወደ ልብስ መለወጫዋ ገባች ። ያስፋውን ደብዳቤ በተቀበለች ምሽት ያነባችውን ዓይነት የሚያበርድ እንባ እንዲሆንላት ተመኘሁ ---- ልቧ እንዲ በርድላት ። አሥራ አምስት ደቂቃዎች ያህል ቆይታ ተመለሰች ፣ እልሁ የወጣላት አይመስልም ፤ የዓይኗ ንዳድ አልከሰመም ።

"ይኸውልሽ የገዛ ዘመዶቼ እየተከታተሉ አላስኖር አሉኝ ---" እያለች ከንጆቿን ጠለፍ አርጋ በመደገፍ ወደ ውጪ መውጣት ጀመርን "--እስኪገድ እይልኝ ፣ አነጋገራቸው ሁሉ የምን ይመስላል ፣ እኔን ሰው እንዲ ሸሸኝ -- የምጠየፍ አስመስለው ---

"ምንም አይደለም ፣ እስከዚህ አትዘኚ የሚያቅሽ እንደሁ ያውቅሻል --- የፊላጋቸውን ቢቀባጥሩ --- "ተይ ተይ እንዲህ አትበይ ፣ በአሁኑ ጊዜ ማን ማንን ያውቀዋል -- ሁሉም የፊት የፊቱን ነው --- እንቺስ ብትሆኚ ስለኔ ምን ታውቂያለሽ --"እሱ እውነትሽን ነው ---"

"እንቺም ሊመስልሽ ይችላል ፤ መስሎሽም ይሆ ናል --- "እንዴት ፣ ምን ማለትሽ ነው ?

“ ተይው ተይው --- ምን ያደርጋል -- ለምኑ ፤ ደህና ሁኚልኝ አሁን ---” እጉንጬም ላይ ሳም አደረገ ችኝና ተመልሳ ሮጣ ገባች ።

እስፋውም መስሎት ይሆን እንዴያ የተለወጠው — በማለት እሰላስል ገባሁ --- የሰማሁትን ሁሉ እያምሰለ ሰልሁ ። ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ ስመለስ አላገኘኋትም ። ባጠያይቅም ፤ ከአዲስ አበባ የመውጣቷን ጭምጭምታ ከመስማቴ በስተቀር በርግጥ ወዴት እንደሄደች ለመረዳት አልቻልኩም ።

# 7

በትሩፋት ላይ የደረሰው በደል እኔንም ፣ ብዙ ጊዜ አንገብግቦኛል ፣ ሕይወቴንም በብዙ አንፃር ለውጦታል ። ሰዎች የሚያደንቋቸውንና የሚቀኑባቸውን ፍቅረኞች እኔ ከቁጥር ማግባት ትቻለሁ ፣ ትክክለኛና ዘላቂ ፍቅር ሊመሠረት አይችልም የሚል እምነት አድሮብኛል ፤ ለዚህም ጦስ መነሻ ወንዶች ናቸው ብያለሁ ። ከአስፋው ድርጊት በኋላ ወንዶችን እንደ ወላዋይ ፣ አጥፊ ፣ ከዳተኛ አድርጌ በመመልከት እኔም በበኩሌ ያስቀየምኳቸውና ያስኮረፍኳቸው ጥቂት አይደሉም ።

ከትሩፋት ጋር ከተራራቅንበት ጊዜ ጀምሮ ጥብቅ ጓደኛዬ አድርጌ የያዝኩት መጽሐፍን ነው ። ሌላ ምንም ዓይነት ጓደኛ አላፈራሁም "መውደድ አጥብቆ መውደድ መጽሐፍንና ሥራን ነው" ሰውን አጥብቆ ማፍቀር ግን ትርፉ ብስጭት ፣ ሐዘን ፣ ጭንቀት ብቻ ነው" የሚል ጥቅስ ጽፌ ከመኝታዬ ራስጌ ሰቅያለሁ ። አንዳንዶም የማነባቸው የፍቅር መጻሕፍት ፍቅራቸውን የሚያፋልስባቸው ሞት ብቻ የሆነና በምድር ላይ እስካሉ ድረስ ተሳስረው የሚኖሩ ፍቅረኞች ጥቂት እንዳልሆኑ ያስረዱኛል ። በዚህ ጊዜ ልቤ መለስ ይልና እውነተኛ ፍቅር ልመሰርትበት የሚያስችለኝን መንገድና የምመርጠውን ሰው መመዘኛ አሰላስላለሁ ። ጥቂት ሳልቆይ

ደግሞ "ከንቱ ድካም ነው!" አሁን እውነተኛ ሰው ከየት ልታገኝ ነው? እውነትስ ከልቡ የተፋቀረና የተማመነ ሰው ከእነትተሩፋት ወዲያ ይገኛል? ውጤቱ ግን እንዳያ ሆነ ። የሰውን ልብ ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው" የሚለው ሃሳብ ከፊቴ ይመጣና ድቅን ይልብኛል ። በዚህ ጊዜ ልቤ እያወቀው ለእራሴ ያህል "እረ ልክ ነው ወደ ከመጨነቅ እድሜ ልክ እርፌ ሙቀመጥ ይሻላል" እላ ለሁ ። እኔና ትሩፋት አልጋ ላይ ቁጭ ብለን ባለቀስንበት ጊዜ --"ጤነኛስ ሆኜ ወንድ አላፈቅርም" ያልኩት ቃል ትውስ ይለኝና ቃሌን ማጠፉ ነውር መስሎ ስለሚታየኝ ግትር ብዬ እንዲሁ እዘልቀበታለሁ በማለት ራሴን እታል ላለሁ ። ይህ ሁኔታዬ ለቤተሰቦቼም እንግዳ ነገር ሳይሆ ንባቸው አልቀረም ። ጐረቤቶቻችንም "ሥራ ስትይዝ መኩራቷ ነዋ" የሚል ሐሜት ሰንዝረውብኛል ። ለእኔ ግን ምንም አልደነቀኝም ። ሁሉም አልተዋጠልኝም ።

የሥራ ቦታዬም "ሐምሌ 19" በተባለው ሆስፒታል ውስጥ ሲሆን ከዚያም የማሳየው ፀባይ በአካባቢዬ ከማሳ የው ፀባይ የተለየ አልነበረም ሥራዬን ሠርቼ ስጨርስ ከቢ ሮዬ ገብቼ መጽሐፍ ከማንበብ ሌላ ከማንም ጋር ቀልድም ሆነ ጨዋታ አልነበረኝም ። በሥራ ምክንያት የምንገናኛ ቸው አንዳንድ ወንዶች ለመቃለድ ዳር ዳር ቢሉም ፊት አላሳያቸውም ። ኮስተርተር እልና "ወንድሞቼ የሥራ ጊዜ መሆኑን ረሳችሁት እንዴ?" ብዬ ቅልል አደርጋቸዋ

ለሁ ። በሆዴም "ክሃዲዎች" እላቸዋለሁ ይህ ቃል "እፍቅሬአለሁ" የሚል ወንድ ባየሁ ቁጥር አፌ ላይ ይመጣብኛል ። እኔንም ቢሆን እፍቅሬሻለሁ ሲለኝ የሚ ቃጣውን ሁሉ በሙሉ አፌ "ክሃዲ" እለዋለሁ ። ምን ጊዜም ነገር የፍቅር ነገር ሲነሳ ትዝ የሚለኝ ፤ በጅምር የቀረውና ሥቃይ ላይ የጣላት የትሩፋት ፍቅርና የአስፋው ከዳተኛነት ነው ። እንዲያ የረዥም ጊዜ የነበረውና ጥብቅ የሆነው ፍቅር ሲወዳድቅ በተገነዘበው ልቢ አዲስ ፍቅር መስርቼስ ለምን ልቃጠል ? " ታዲያ በብቸኝነት እስከ መቼ ? " የሚለው ጥያቄም ከሕሊናዬ ተሰንዝሮልኛል ። በጊዜው የነበረኝ መልስ "እስከዘለዓለሙ ነዋ! ምን እንዳ ልሆን ? " የሚል ነበር ። ይህ ሁሉ ግብዝነት መሆኑ ይታ ወቀኛል ።

ፍጡር ሆኜ ከፍጥረታት የተለየሁ ለመሆን መሞ ከር የማይቻል መሆኑ ግልጽ ነው ። ለማንኛውም ነገር በፍጥረታት ላይ ያለው የማይለወጥ ውስጣዊ ስሜት በእ ኔም ላይ መኖሩ የማይካድ ነው ። ይህን ሁሉ አሸንፌ ፣ ከሰው የተለየሁ ሆኜ በብቸኝነት እዘልቃለሁ ማለት ዘበት ነው ። ባደርገውም በግትርነት ፣ በአልረታም ባይ ነት ፣ በአስመሳይነት እንጂ በእውነትስ ከሙሉ ስሜት በመነጨ ጥንካሬ ሊሆን አይችልም ።

ዝምተኝነትና አለመቅለብለብ ብቻ ለመልካም ትዳር መመዘኛ የሚሆን ይመስል ፣ ብዙ ወንዶች በወላጆቼ በኩ

ልና በሌላም ተዘዋዋሪ መንገድ የትዳር ጓደኛቸው እን ድሆን ጥያቄ አቅርበውልኛል ። ዘመዶቼም "ባል አታገ ቢም እንዴ ? ከእንግዲህ ምን እስክትሆኚ ትጠ ብቂያለሽ ፣ ኧረ ወግሽንና ፍሬሽን እንኳ እንየው" ማለታቸው አል ቀረም ። እኔ ግን ሁሉንም አላዳመጥኳቸው ፣ አልፎ አልፎ ቅር እንዳይሰኙ "ዘንድሮ ባልመቼ ይገኛል ብላችሁ ነው" የሚል መልስ እሰጣቸዋለሁ ።

ከሁሉም ይልቅ ቀርቦና ደፍሮ ፣ እንዳገባው በግልጽ የጠየቀኝ በአካባቢያችን የሚገኘው መሃንዲስ አቶ ተካልኝ ነበር ። የአጠያየቁም አቀራረብና ሁኔታ ፣ ብዙ እንዳሳሰበ ውና እንዴት ብዬ ልጠይቃት ? በሚል ሃሳብ አውጥቶና አውርዶ መምጣቱን በደንብ ለመረዳት ያስችላል ።

አቶ ተካልኝ በመጀመሪያ ቀን ቀርቦ ያነጋገረኝ በአ ካባቢያችን ያለውን ኮረኮንች መንገድ አስፋልት ለማስ ነጠፍ በሚያደርገው መሯሯጥ የሞራልም ሆነ የማቴሪያል እርዳታ እንዳደርግለት በመጠየቅ ነበር። የአቀራረብ ሥልቱ በጣም ግሩም ነው ። ብዙውን ጊዜ ከመሥሪያ ቤቴ አም ሽቼ ወደ ቤት ስመለስ እስከ ቤቴ አካባቢ መኪና መግ ባት ስለማይችልና ሰርቪሱ (አመላላሹ መኪና) ከቤቴ ራቅ ወዳለ ሥፍራ አውርዶኝ ስለሚመለስ በጭለማ ያንን ኮረኮንች መደናበሩ አማርሮኝ ነበር ። ይህ ብዙ ጊዜ የሚ ያጋጥመኝ በመሆኑ ነው እንጂ ከዚያም የባሱ ችግሮች በመ ኪና አለመግባት ምክንያት ደርሰውብኛል ። ስለዚህ ያለ

ምንም ማመንታት ለመርዳት ያለኝን ሙሉ ፈቃደኝነት ገለጽኩለት ። በዚህ ሁኔታ ከተቀራረብን በኋላ አልፎ አልፎ ወደ እኔ እየመጣ ስለመንገዱም ሆነ ስለሌሎች የአካባቢ ያችን ችግሮች ያዋየኝ ጀመር ። የመንገድ ሥራው ዕቅድ ግን እምብዛም በተግባር አልተተረጐመም ። አንዳንዴም ምን እክል እንዳጋጠመው ስጠይቀው የሚሰጠኝ መልስ ፣ "አካባቢው አልተባበረኝም ፣ የመንገድ ሥራ ድርጅቱን ኃላፊ አላገኘኋቸውም ፣ ከእኛ ቀድመው ያመለከቱ ቦታ ዎች አሉ --" የሚል ነበር ።

ለካ ይህ ሁሉ መቀራረብ በእርግጥ ለአካባቢው ልማት ታስቦ አልነበረም ። ከቀረበኝ ሁለት ወር እንኳ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ "ላግባሽ የሚለውን ጥያቄ አቀረበ ልኝ ። አቀራረቡም እንዲህ ነበር ።

ስለ መንገድ ሥራው በፍጥነት ያለመጀመር ካወራ ልኝ በኋላ ፣ አቀማመጡ ከእኔ ፊንጠር ብሎ ጥንት በጠ ፍር ከተሠራው በርጩማ ላይ ስለነበር ፣ "የጥንት ዕቃ እንዴት ጠንካራ ነው" እያለ በእጁ ዳበስ ዳበስ አደረ ገውና ወደ እኔ እየተመለከተ" ሲስተር አዜብ ይህንን በርጩማ ከክፍለ ሀገር ማስመጣትሽን ከአሁን በፊት ያጫወትሽኝ መሰለኝ " አለ ። ጥፍሬን እቆርጥበት የነበ ረውን ምላጭ ወደ ጠረጴዛው ወርወር አደረግሁትና " አዎ ! ምነው ደግመህ ጠየቅሽኝ?" አልኩት ። አነጋገሬ ትንኮል ያላዘለ ንጹህ ነበር ።

አቶ ተካልኝ ፈገግ ብሎ ወደ እኔ እየተመለከተ ጥቂት ዝም ካለ በኋላ "የቤት ዕቃዎች ማሟላት ትወጃለሽ፣ ጥሩ ባለ ትዳር ይወጣሻል" አለኝ ።

"ምናልባት ---" አልኩት በተናገርኩት ቃል ላይ ሆን በድምፄ መቆጣቴ እየታወቀ ። ተካልኝ ደንገጥ ሲል ታየኝ ፤ "እንዴት ? ባል አታገቢም ማለት ነው እንዴ?" ቀጠለ ጥያቄውን ። እኔም ፤ " ዛሬ ስለልማት የምናደርገው ውይይት ያበቃ ይመስላል ፣ ምናልባት በሌላ ጊዜ ---" ብዬ ሳልጨርስ ፤ ለምን ይከፋሻል ሲስተር ፣ ሰው መቼም በብቸኝነት አይኖርም --" ብሎ ሲናገር ፣

" እ---ፉ" ብዬ ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና ወደ ኮመዲኖ ሄጄ መጽሐፍ ማገላበጥ ቀጠልኩ ። እሱም ለጥ ቂት ጊዜ ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ በድንገት " እጮኛ እን ድትሆኚኝ ነውኮ የምጠይቅሽ " አለኝ ። ማገላበጥ የጀመ ርኩትን መጽሐፍ ተውኩና ወደ እሱ ዘወር ብዬ በመደ ነቅ እየተመለከትኩት "እ--እ- ?" አልኩት ። ምንም መልስ አልሰጠኝም ። መጀመሪያውንም " ያበጠው ይፈ ንዳ " በሚል ዓይነት በትልቅ ጭንቅ ከአፉ ማውጣቱን በእንዴ ፍም የመሰለው ፊቱ ይመሰክርበታል ። "ያ ሁሉ የመንገድ ውትወታ እስከዚሁ ኖሯል --? የወንዶች ነገር--" አልኩና መጽሐፉን ወርውሬ ተነሳሁ ። እሱም ቀስ እያለ በመነሳት " አትቆጪ እንጅ ሲስተር !

ምን አዲስ ነገር አለ? ጋብቻን መጠየቅ ኃጢአት ነው እንዴ?" እያለ ወጥቶ ሲሄድ ሲል "ይቅርታ አድርግ ልኝ ወንድሜ! አንተ እጮኛህን ለመምረጥ ያለህን መብት ያህል እኔም የመምረጥ መብት አለኝ፣ አንተ ስለመረጥ ከኝ ብቻ--" ብዬ ሳልጨርስ፣ "ጥሩ ነው ሲስተር! እጮ ኛሽን የመምረጥ መብትሽ የተጠበቀ ነው፣ ሆኖም እኔ ንም ከምትመርጪቸው አንዱ አድርገሽ ከልብሽ ውስጥ ብታ ስቀምጪኝ እንደምደሰት መግለጽ ያስነውራል? ስለ ፀባዩ አትጠራጠሪ፣ እስካሁንም ሳላገባ የቆየሁት እቻዬን በመፈ ለግ ነው" አለኝ። የአነጋገሩ ለዘብ ያለ መሆንና የቃላት አመራረጡ እውነተኛነቱን ለመግለጽ ይሁን ለመሸንገል ከፍ ያለ ችሎታ እንዳለው ያመለክታል። ለእኔ ግን ጭራ ሹን በሽታዬን ቀሰቀሰብኝ "ስለ ፀባዩ አትጠራጠሪ" ሲለኝ፣ ታማኝነት የነበረውና በከሃዲው አስፋው የፈረሰው የእነ ትሩፋት ፍቅር ፊቴ ላይ ድቅን አለ ብኝ። ቁጣ በተሞላውና በጩኸት አነጋገር "እባከህ አታ ታለኝ የእኔ ወንድም" አልኩና ወደ በረንዳው ለመው ጣት እየተራመድኩ፣ "ከሃዲዎች" አልኩ። ይህን ቃል ሆን ብዬ የተናገርኩት አልነበረም። በድንገት ከአፌ ሲወጣ መልሶ ራሴን አስደነገጠኝ። ቃሉ እሱንም ስለአስደነገ ጠው "ከሃዲዎች!?" የሚለውን ቃል ከደጋገመው በኋላ "ሲስተር እንዲህ አልሽ?" ከሃዲ ነው ያለሽ ማነው? እስኪ አቅርቢው! 'ከዳኝ' የምትለዋ እስኪ ትቅረብ--" እያለ ገና ብዙ ለመናገር ሲቃጣ በመሀል አቋረጥኩትና

"ይቅርታ አድርግልኝ! ከሃዲዎች እንጂ ከሃዲ የሚል ቃል አልሰነዘርኩም" አልኩት ።

"እሃ ወንዶችን ሁሉ ማለትሽ ነው? ታዲያ ሁሉም ወንዶች አንድ ዓይነት መሰሉሽ እንዴ? በዚህ በኩልስ አትጠራጠሪኝ ፣ ግድ የለሽም እመኚኝ!" ካለ በኋላ ጥቂት ሲያስብ ቆየና "--ግን ከአሁን በፊት "ወድጄሻ ለሁ" ብሎ የካደሽ አለ እንዴ?" የሚል ጥያቄ አቀረበ ልኝ ፣ እዚያው አበሩ አካባቢ እንደቆምን ። እኔም እንደ ገና በማገርገር "እቶ ተካልኝ! ጤነኛም አይደለህ እንዴ? እንዲህ ዓይነቱን ምርመራ ምን አመጣው? በቃ ይበቃ ናል" አልኩትና ወደ በረንዳው ወጣሁ ። እሱም ተከት ሎኝ ወጣ ።

አጠገቤ ሲደርስ ትንሽ ወደ መሬት አቀርቅሮ ከቆየ በኋላ "እንግዲህ መሄዴ ነው ፣ ሲስተር ፣"አለኝ ። እነጋገሩ ዕቃ ለመግዛት ወደ ሱቅ ገብቶ በዕቃው ዋጋ ሳይስማማ ቀርቶ ቅር እያለው የሚወጣን ተራ ገበያተኛ ሰው ይመስል ነበር ። "ጤናይስጥልኝ" አልኩት ፣ ትኩር ብሎ ከተ መለከተኝና ጭንቅላቱን ከነቀነቀ በኋላ የመገረም ፈገግታ እያሳየ ግቢውን ለቆ ወጣ ።

ተካልኝ በሌሎች ቀናትም እየተመላለሰ ጠይቆኛል ። ከእሱም ሌላ ብዙ ሰዎች ጠይቀውኛል ። በእርግጥ የሁ

ሉም አመጣጥ ለጊዜያዊ ፍቅርና ለድሪያ ሳይሆን ለትዳር መሆኑ ገብቶኛል ። ከብዙዎቹም የተሰነዘረልኝ "መል ካም የትዳር ጓደኛ ይወጣሻል" የሚል ነበር ። ረጋ ያልኩ ከመሆኔና ከኩሩነቴ በስተቀር ስለውስጣዊውም ሆነ ውጭ ያዊ ፀባዬ በደንብ ጠልቆ የተከታተለኝና የተረዳ ወይም ለመረዳት የሞከረ አንድም ሰው አልነበረም ።

ይህን ያህል የምኩራራው ከሰው የተለየ ውበት ኖሮኝ አይደለም ። እንዲያውም የውበት ነገር ጨርሶ እንዲነሳብኝ አልፈልግም ። ስለዓይን ፥ ጥርስ ፥ አፍንጫ ፥ ቅንድብ ወዘተ---ውበት ሥራዬ ብለው ለሚከታተሉ ትም አዝንላቸዋለሁ ። በተፈጥሮዬ እንደማንኛውም ሰው ሙሉ አካላት ይዤ የተፈጠርኩት ጤነኛ ሰው ነኝ ። የም ኮራብትም ፥ የምመካበትም በዚሁ ጤነኛ ተፈጥሮዬ ብቻ ነው ። ቁንጅናን ቦታ አልሰጠውም ። እንዲያውም ብዙ ዎቹን ለትዳር የሚጠይቁኝን ወንዶች አሳፍሬ የማባርራ ቸው አስቀድመው ውበቴን ስለሚገልጹልኝ ነው ። ውበ ቱን እንደያዘ እስከ ዘለዓለም የቆየ ማን አለ ?

እምቢተኛነቴም ፥ የኩራት ፥ የንቀት ፥ የበላይነት ወይም የሌላ አልነበረም ። እንደ አስፋው ያሉ ጥቂት አታላዮች በሰው ላይ የሚያስከትሉትን ምሬት ስለተገ ነዘብሁና በጓደኛዬ ላይ የደረሰው በደል ከልቤ አልወ ጣም ስላለኝ ነበር ። ከዚህም ሌላ ምርጫዬን የራሴ ማድ ረግ እፈልጋለሁ ። ሁል ጊዜ ተመራጭ መሆንን አልሻም ። መራጭ መሆን እንደምችልም አውቃለሁ ።

ብዙ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ሲያልፍ ከህሊናዬም "እን ዲህ ባለው የብቸኛ ኑሮሽ እስከመቼ ትዘልቂበታለሽ ?" የሚል ተደጋጋሚ ጥያቄ ሳይነሳብኝ አልቀረም ። ብቻ እምቢተኛነቴ በግትርነት የተደረገም ይሁን በግድርድ ርነት ለረዥም ጊዜ ቆየሁኝ ።

8

" ሐምሌ 19 " የተባለው ሆስፒታል ትልቅና ሰፊ በመሆኑ ፣ ለጐብኚዎችም ሆነ ለሠራተኞች እንዳያስቸግርና በቀላሉ የሚፈልገውን ቁጥር ለማግኘት እንዲቻል በክፍል ክልል ተመድቦ ቁጥር ተሰጥቶታል ፤ እያንዳንዱ ክልል ተቆጣጣሪና ሥራውን በደንብ ተከታታይ አንድ አንድ ዶክተር አለው ። እኔም የነበርኩበትን "ምድብ ሶስት" የሚቆጣጠሩትና በየጊዜው የሚጐበኙት ዶክተር ገድሉ ነበሩ ።

ዶክተር ገድሉ በግምት የ37 ዓመት ዕድሜ ያላ ቸው ይመስላሉ ። ነገር ግን እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሚስ ትም ሆነ ልጅ እንደሌላቸው የወሬወሬ ሰምቻለሁ ። ሥራ ቸውና ሁኔታቸው ሁሉ ስለሚያስደንቀኝ ፣ በማያገባኝ እየገባሁ ስለሕይወት ታሪካቸውም ለመረዳት ሞክሬ አለሁ ። ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት በእንግሊዝ አገር

ውስጥ ሲሆን ጥሩ ውጤት በማምጣታቸው እዚያው እን ዲቀሩ የእንግሊዝ መንግሥት ጠይቋቸው ያስተማረቻቸ ውን እናት ሀገራቸውን ለመርዳት ባላቸው ስሜት የመቅ ረቱን ጥያቄ ሳይቀበሉ ወደ ሀገራቸው መምጣታቸውንና ሥራ ከጀመሩም ገና አራት ዓመታቸው መሆኑን በዚያው አጋጣሚ ለመረዳት ችያለሁ ።

ከእኔ ጋር የምንገናኘው በሥራ ምክንያት ነው ። ዘወ ትር ጠዋት አብሬያቸው በሽተኞችን እየጎበኘሁ የሚያዙ ላቸውን መድሐኒቶች በጽሑፍ ይገፎ ለየታዘዘላቸው በየ ሰዓቱ በማደል የጤንነታቸውን ሁኔታ እከታተላለሁ ። ከ ከሚያስቸግሩኝ ተግባራት አንደኛው ዶክተሩ በጽሑፍ የሚያዝዙትን የመድሐኒት ዓይነት ማንበቡ ነው ። የአማ ርኛም ሆነ እንግሊዝኛ ጽሑፋቸው አቀማመጥ ትርጉም የሌለው የእንግሊዝኛ ሙጭርጭር ይመስላል ፣ በተለምዶ አነጋገር "ዶሮ የጫረው ይመስላል" የምንለውን ዓይነት ። ለአነጋገራቸውም ቢሆን እንግሊዝኛው ይቀናቸዋል ። በመርሳትም ይሁን ቀድሞውን ባለማወቅ ብዙ የአማርኛ ቃላት ያስቸግራቸዋል ። ሌላው ችግሬ ደግሞ ለዶክተር ከበሽተኞች የሚቀርቡላቸውን ከበድ ያሉ የአማርኛ ቃላት ወደ እንግሊዝኛው መተርጎሙ ሲሆን ጭራሹን አማርኛ ከማይገባቸው ዶክተር ጋር የምሠራ ብሆን ኖሮ ከምሰጠው ግልጋሎት ይልቅ የሚደርሰው ጥፋት በበለጠም ነበር ። እንዳንዴ ሳስበው ለምን በሰው ቋንቋ መከራዬን እንደ

ማይ አይገባኝም ። የበሽተኛውን ችግር አብረን ከሰማን በኋላ ውስጢን አልፈው በሚያዩ ዓይነት ትኩር ብለው ሲያውኝ አስተርጓሚ ያሉኝ ያህል ምን እንደሚያግተረ ትረኝ --- ለምን ዝም እንደማልላቸው ---

ከእነስተኛ ርዳታ ሰጪዎች ሌላ ለዚያ ምድብ የነበ ርኩት ነርስ እንድ እኔ ብቻ ነኝ ። ስለዚህ ዶክተር በመጡ ቁጥር ማንኛውንም ነገር የሚያማክሩኝ ለኔኑ ነው ። የበላ ይነት ተሰምቷቸው በቁጣ ያዘዙበትን ቀን ፈጽሞ አላስ ታውስም ። ፈገግታም ቢሆን እምብዛም አይታይባቸውም። የዓይናቸውን መነጽር በእጃቸው ከፍ ዝቅ እያደረጉ ኩራት በተመላበት አነጋገር፣ “ሲስተር አዜብ ፣ እንዲህ ብናደርግስ ?” የሚል ኅብረትን የሚሻ ጥያቄ ማቅረብ ልማ ዳቸው ነው ። በሽተኞችንም በአቀራረብ ብቻ የመፈወስ ጥበብ አላቸው ። “ሕመሜ ፀናብኝ” እያለ የሚጮኸው በሽተኛ ሌሎች ሐኪሞች መርፌና ክኒን ከሚያዙለት ይልቅ ዶክተር ገድሉ መጥተው መድህን በሆነው ድምጻቸው “የቱ ጋ ነው የሚያምህ ፣ አይዞህ ፣ ይህማ ቀላል አይደለም እንዴ” እያሉ በእጃቸው የቁስሉን ቦታ ነካ ነካ ቢያደርጉለት ይመርጣል ። ምን ሥራ ቢበዛባቸው በቀን ሁለት ጊዜ ሕሙማንን ሳይጎበኙ አይውሉም ። በጉብኝቱ ሰዓት እኔንም ባያገኙ አስፈላጊ የሆነውን ነገር በዚያው ዶሮ የጫረው በሚመስለው ጽሑፋቸው ሞንጫ ጭረው ከቢሮ ጥለውልኝ ይሄዳሉ ። አጻጻፋቸውም እንደ

አነጋገራቸው ሁሉ ‘‘ሲስተር በቁጥር2ውስጥ ያለው በሽተኛ ‘‘ማሉኮዝ’’ ቢሰጠው ጥቂት ይረዳዋል ብዬ እገምታለሁ’’ የሚል ዓይነት ነው።በአጠቃላይ በሥራቸውም ሆነ በአነጋገራቸው በሚያውቁት መጠን ለመርዳት ወደ ኋላ የማይሉ ራሳቸውንም ፍጹም አድርገው የማያቀርቡ ከማንኛውም ሰው ትብብርን የሚጠይቁ ናቸው። እኔም የማከብራቸውና የምወዳቸው በዚሁ ፀባያቸው ነው።

ዘወትር በሽተኞችን ጎብኝተን ስንጨርስ እኔ ወዲያው ወደ ቢሮዬ እመለስና ለዚሁ ተግባር በገዛኋት የኤሌትሪክ ምድጃ ሻይ እያፈላሁ መጠጣት ልማዴ ነው። አንድ ቀን ሥራ በጣም ስለበዛብኝ የሻይ ሰዓቴ አለፈና በተደጋጋሚ እያዛጋሁ ስራዬን ቀጠልሁ። ባልታወቀ መንገድ ተላላፊ በሽታ በሆስፒታሉ ውስጥ ስለገባ በክፍሌ ውስጥ ያለውን የእያንዳንዱን በሽተኛ የትኩሳት መጠን እየለካሁ በአስቸኳይ ርዳታ የመስጠት አጣዳፊና ጊዜ የማይሰጥ ሥራ ላይ ነበርኩኝ። በዚህ ሥራ ተጠምጄ ነው እንግዲህ ዶክተር ገድሉ ከተፍ ያሉት። አመጣጣቸው በጥድፊያ ስለነበር ለአንድ አስቸኳይ ነገር ቶሎ ድረሱ የተባሉ ይመስላል። አጠገቤ ሲደርሱ የጥድፊያ ትንፋሻቸውን እንደመቆጣጠር እያሉ

‘‘ሲስተር፣ ይህ የእረፍት ጊዜሽ አልነበረምንዴ?’’ አሉኝ።

‘‘ይህን ሁሉ ሕመምተኛ አስቀምጦ ምን እረፍት አለ ብለው ነው?’’ አልኳቸው።

ራሳቸውን እየነቀነቁ በመገረም አይነት " መል ካም —መልካም ተመልክተሻል—" አሉና የያዝኩትን ሥራ ይረዱኝ ጀመር ። እሳቸው እንዲህ አይነቱን በሥራ መተባበርን ሥራን አለመናቅን አላማዬ ብለው ቢይዙ ትም እኔ እንደትልቅ ውለታ ቆጠርኩት ። ትኩሳት መለ ካት ከእኔ ከነርሷም ወርዶ የተራ ሰራተኞች ተግባር ነው ። እሳቸው ግን ለዚህ ሁሉ ቦታ አልሰጡትም ። እየተዟዟሩ የኢያንዳንዱን በሽተኛ ትኩሳት አብረውኝ ከለኩ በኋላ "የጨረስን መሰለኝ ፣ ሲስተር ፣ ምድር ቤት ትንሽ ሥራ ስላለብኝ ልወርድ ነኝ እንግዲህ" አሉኝ ፣ አነጋገራ ቸው በችግር ምክንያት የታዘዘውን ሥራ ያልጨረሰ ሠራ ተኛ የሚጠይቀውን ይቅርታ እየመሰለ ።

"—ስለእገዛዎ አመሰግናለሁ —" አልኳቸው ።

ፈገግ ብለው እየተመለከቱኝ "አይ ሲስተር ፣ ምን ምስጋና ያስፈልገኛል ፣ ለእኔስ ስራዬ አይደለም እንዴ" አሉና ከክፍሉ ለመውጣት ራመድ ሲሉ ፣ ድንገት ሻይስ ብትጋብዣቸው የሚል ሀሳብ መጣብኝ ። ወዲያውም የያ ዝኩትን የሙቀት መለኪያ ጣል አደረኩና ተከትያቸው በመውጣት "ዶክተር ፣ ዶክተር ፤ ፈቃድዎ ቢሆን —ሥራ ዬን ስጨርስ ከሩብ ሰዓት በኋላ የማፈላውን ሻይ መጥ ተው ቢጋበዙልኝ "አልኳቸው ። በነገሩ አልተገረሙም ፤ ራሳቸውን በመነቅነቅ ብቻ የእሺታ መልሳቸውን ሰጥተ ውኝ ሄዱ ።

እንደነገርኳቸው ከሩብ ሰዓት በኋላ መጡ። እራታቸው ላይ ፈገግታ ያንዣብባል ፣ ለጊዜው ደንገርገር እንዳለኝ ይታወሰኛል ፣ ከነርሶች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ከወጣሁበት ጊዜ ወዲህ ከወንድ ጋር እንዲህ በመንፈስ ተቀራርቤ ስለማላውቅ ። ትቀመጡ እንኳ ያልኳቸው አልመሰለኝም ።

እንዲሁ ዝም እንንደተባባልን ሻዩን ጠጥተው ጨረሱና ብርጭቆውን ከጠረጴዛው ሲመልሱ፣ "ታንክዩ ሲስተር" አሉኝ፣ በዚያው በሚቀናቸው እንግሊዝኛ ፤ ወዲያውም ለጠቅ በማድረግ "ግሩም ሻይ ነበር"አሉ ።

"ልደገምዎታ" አልኩና የሻይ ጀበናውን ብድግ ሳደርግ እንደማይደግሙ ለመግለጽ የብርጭቆውን አፍ በእጃቸው መዳፍ ከደኑትና "ጠላዋ እምርሳት —" የሚለውን እንጋገር ጀምረው መጨረሻው ስለጠፋባቸው በማሰላሰል ወደመሬት አቀረቀሩ ። አማርኛውን አቀነባብረው መናገር አቅቷቸው ነው እንጂ የፈለጉት "ጠላዋ ያማረላትን ሴት ይመስል —" ብለው ለመቀለድ ነበር ።

"ተወት ፣ ተውት ፣ ገባኝ" አልኳቸውና ለመናገር የፈለጉትን ቃል ከነገርኳቸው በኋላ ፣ "እኔስ ከባለጠላዋ በምን እንሳለሁ —" ብዬ ገና ከአፌ ሳልጨርስ "ምንም ምንም ፣ ሲሆን ትበልጫያለሽ እንጂ ፣ ላንቺም ይታወቅሻል —"አሉኝ

ከዶክተር ገድሉ እንዲህ የመቻኮልና የማድነቅ ንግ ግር ስሰማ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር ። ለማንኛውም ነገር ረጋ ያሉና ፣ ነገርንም ማድነቅ የማይወዱ አይነት ስለነበሩ ምን ማለታቸው ነው ምንስ ሊሉኝ ፈልገው ነው ?" እያል ልኩ በሆዴ ማሰላሰሌ አልቀረም ።

ያን እለት በዚህ አይነት ጥቂት እንደተጫወትን "አሁንስ ሰዓት ደረሰ ፣ በሥራ ቀልድ የለም ፣ በይ እንግ ዲህ ቻዎ" በማለት ተሰናብተውኝ ወጡ ። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ በልቤ ውስጥ የደስታ ይሁን ጭንቀት ፍጹም ያልገባኝ ስሜት ተተራመሰ ። ወደቤቴም ሄጄ ተኝቼ እንቅልፍ እስኪወስደኝ ድረስ እንኳ መላ አላገኘሁለትም--- ----የማፍቀር ዳርዳሩ ይሆን---እንዴት ሊሆን ይችላል ? ሊሆን አይችልም ---ከሆነም ደሞ ማሰሪያ አበጅለታለሁ--- እዎ ንግግሬን ቆጠብ----ግንኙነቴን እጠር ማድረግ ነው--- ---ከሥራዬ ሌላ ምን ያገናኘኛል ---እዎ---ቀልዳዊ አነጋገር ቢሰነዝሩብኝ እንኳ ፣ " ይቅርታዎን የሚያገናኘን ስራችን ብቻ ነው ።"ብዬ ቅስማቸውን መስበር ይኖርብኛል—እዎ- ---- ግን እኮ ዶክተር ገድሉ ግሩም ሰው ናቸው ። ባፈቅራቸውም ፣ ካፈቀሩኝ የሚከዱኝ ዓይነት አይደሉም ። ደግሞም ይህን ያህል ተምረው ብዙ ችግርችን ተቋቁመው አልፈው ከዚህ የደረሱ ሰው እንዴት በቀላል ነገር ሊዋ ረዱ ይችላሉ ? እኔስ በብቸኝነት እስከ መቼ እገፋዋለሁ ? ከእሳቸው የበለጠ ሰው የማገኝ አይመስለኝም ። ዕድሜዬን

ሙሉ ብቻዬን እኖራለሁ በሚለው ግትር አስተሳሰቤ እስከ መቼ እጸናለሁ . . . ብቻ ሰውን ስለተማረ ማመን አይቻልም ፡፡ ገንዘብና ፍቅር ዕውቀታቸውን የሚያስታቸው ጥቂት አይደሉም ፡፡ . . . ኧረ እንዲህ ዓይነት የማይረባ ሃሳብ ውስጥ ገብቼ መጨነቄስ ለምንድነው? የዶክተር ገድሉን ሃሳብ መች በደንብ ተረዳሁትና ነው ? እሳቸው ይህንን ሁሉ አላሰቡትም ይሆናል ፡፡ አቀራረባቸውም እንደ እህታቸው እያዩኝ ሊሆን ይችላል ፡፡ ማን ያውቃል! ሌላ የሚወዱዋት ፍቅረኛቸው ትኖር ይሆናል ፡፡ ኧረ እንዲያው ከንቱ ሃሳብ ነው - - ይህ ሁሉ መኝታዬ ላይ ሆኜ የማወጣው የማወርደው ጥያቄና መልስ ነበር ፡፡ ለጤንነት ይበለው እንጂ እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ማሰላሰል ከተውኩ በጣም ረዥም ጊዜ ሆኖኛል ፡፡ ምናልባት ለሕይወቴ አዲስ ምዕራፍ መክፈቻዬ ሊሆን ይችላል ወይም መጥፊያዬ ሊሆን ይችላል ፡፡

## 9

ከዶክተር ገድሉ ጋር ቀስ በቀስ እየተላመድን መጣን፡፡ ሲስተር እያሉ መጥራታቸውንም እየተው አንዳንዴ "አዜቢና" ይሉኛል በማቆላመጥ ፡፡ እኔም ምንም ቅር አላለኝም ፡፡ ለታዛቢ ምን ይመስላል ለሚለውም ጥያቄ ቦታ አልሰጠሁትም ፡፡ በሻይ ሰዓት ወደእኔ እየመጡ የሚጠጡበትም ጊዜ በርካታ ሆነ ፡፡

እልፎ እልፎ ስለሳቸው ስሜቴ ሲቀሰቀስ፣ ዶክተር
ፍቅረኛ ሲኖራቸው ይችላል በሚል ሳቢያ ውዴታዬን
ላላ ለማድረግ ሞክሬአለሁ ። እሳቸውም ሳይጠረጥሩ የቀሩ
አይመስለኝም ። ሆኖም ሁለታችንም ከመቀራረባችንና ከመ
ግባባታችን ሌላ እንዳችን ስለ እንዳችን ምኞትና ፍላጐት
ፈጽሞ ማወቅ አልቻልንም ። ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆ
ነው “ ፍቅረኛ አላቸው ይሆን?” “ፍቅረኛ አላት
ይሆን?” የሚለው ጥርጣሬአችን ሳይሆን አይቀርም ።
እኔ ግን ምንም እንኳ ይህ አጠራጣሪ ነገር ከልቤ
ውስጥ ቢኖርም ከማፍቀር እንደ ማይቆጥበኝ በመገመት፣
ሌላው ቢቀር እንደ ውድ ወንድሜ አከብሬአቸውና አፍ
ቅሬአቸው መኖር እንደምችል ወስኜ ነበር ።

አንድ ቀን ሥራዬን ጨርሼ ከቢሮዬ ቁጭ ብዬ
መጽሐፍ ሳነብ ዶክተር ገድሉ በአጋጣሚ መጡና ፈገ
ግታ እያሳዩ በተለመደው አነጋገራቸው ፣

“ምን ችግር አለ አዜቢና?” አሉኝ ።

የማነበውን መጽሐፍ የደረስኩበትን ገጽ እንዳይጠ
ፉኝ ከጫፍ ላይ አጠፍ አደረግሁና ከከደንኩት በኋላ
ወደ ታካሚዎቹ የየእለት ጤንነት መቆጣጠሪያ ካርድ
እያመለከትኩ “ይኸው ሁሉም ተሠርቷል ። ለጊዜው ምንም
ችግር የለም ።” የሚል መልስ ሰጠኋቸው ። ወደ ጠቆምኋ
ቸው ካርድ ሄደው እያንዳንዱን አገላብጠው ከተመለ

ከቱ በኋላ የውጤቱን ጥሩነት ለመግለጽ በእንግሊዝኛ "ዌል" አሉ ። ችግር ያለ አይመስልም ለማለት ያህል ። ከዚያም ለመውጣት ወደበሩ መለስ ሲሉ ሳነበው የነበ ረውን መጽሐፍ ርዕስ "ሕይወትህን ምራው" የሚለውን ተመለከቱ ። በዚህ ጊዜ ግንባራቸውን ኮስተር አድርገው (አኮማትረው) ጥቂት ሲያስቡ ቆዩና ፣ "አዎ! አዎ! ይህን መጽሐፍ ከአሁን በፊት አንብቤዋለሁ" እያሉ ወደጠረጴዛው ቀረቡና መጽሐፉን አንስተው አንድ አራት ገጽ ካገላበጡ በኋላ ፣ "ልክ ነው ፣ አንብቤዋለሁ ፣ ግሩም እኮ ነው ! እንዲህ ዓይነት ድርሰት ትወጂያለሽ እንዴ?" አሉኝ ።

"ገና መጀመሬ ስለሆነ ጣዕሙን አላወቅሁትም ፤ ግን ከአሁን በፊት ሌሎች እንዲህ ዓይነት ብዙ መጻሕ ፍት አንብቤአለሁ" ። አልኳቸው ።

"ለምን ይጠቅምሻል እንዲህ ዓይነቱን ማንበብ—?

"ምን ዓይነት ጥያቄ ነው ዶክተር"

"--ማለቴ ፣ እኔ ለምሣሌ መጻሕፍት የማነብበት የራሴ የሆነ ምክንያት አለኝ፤ አንቺስ?"

"እኔ የማነበው የሕይወቴን መንገድ ለመቀየስና ከማነባቸው ታሪኮች ልምዶችን ለመቅሰምነው ።»

"እ?እ? የሕይወቴን መንገድ ለመቀየስ?"

"እዎ ፤ ምነው ንግግሬን ደገሙት?"

ይህ እንጋገሬ ሀሣብ ውስጥ የጨመራቸው መስለኝ ። ሲሄዱ ሲጋበዙ የነበሩት ሰውዬ ጭራሽ ተቀምጠው ለጥቂት ሴኮንዶች ካሰቡ በኋላ "የሕይወትሽን መንገድ የምትቀይሽው ገና አሁን ነው እንዴ?" በማለት ጥርጣሬ የተሞላበት ጥያቄአቸውን አቀረቡልኝ ።

"እዎና ለዚህ ደግሞ የዕድሜ ገደብ አለው?"
"አልተሳሳትሽም ፤ ምንም የጊዜ ገደብ የለውም ። እያንዳንዱ ሰው ባሰበት ደረጃ ስለወደፊቱ አኗኗሩ ማስሙና መስመሩን መቀየሱ የማይቀር ነው ።" ካሉ በኋላ ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ቆዩና ካቀረቀሩበት ቀና ብለው እኔን እየተመለከቱ ፣ "ችግሩ እኮ ብዙ ሰዎች በቀየሱት መንገድ ሙጓዝ አለመቻላቸው ነው ።" አሉኝ ።
"ምን ማለት ፈልገው ነው ዶክተር?"

"ለማለት የፈለኩት ፣ አንዳንድ ሰዎች ጥንካሬ ይጐድላቸውና በጥቃቅን ነገር በመሸነፍ በቀየሱት መንገድ መጓዛቸው ይቀርና በአጭር ይቀራሉ ። ዕቅዳቸውን ከግቡ ማድረስ ያቅታቸዋል ማለቴ ነው ።"

"አሃ! አነጋገርዎ ገባኝ ። የእኔ ግን እንደዚያ አይደለም ፤ በራሴ እተማመናለሁ ።"
"ልክ እንደኔ ነሻ"
"እንዴት እንደርስዎ ?"
«እኔ ዕቅዴ መስመር ስላልያዘልኝ እስካሁን ድረስ

ሳልበገር በዓላማዬ እንደፀናሁ ቆይቻለሁ --በብዙ ውሳኔ ዎቼ ረገድ"

ነገሩ ቢገባኝም ቅሉ ዝም አልኳቸው ። እሳቸው ግን ያልገባኝ መስሏቸው በሌላ አነጋገር ለመድገም ያህል ለምሣሌ--የገንዘብ ኃብታም የመሆን ፍላጐት የለኝም ፣ ይህንንም የሚያስለውጠኝ ምክንያት አልገጠመኝም—ብዙ ጓደኞችንም ማፍራት አልሻም---ሌላው ቀርቶ ምርጫ ዬን ባለማግኘቴ ብቸኛ ነኝ --" እስከዚያ ድረስ ሲያስ ጨንቀኝ የነበረው "ፍቅረኛ አላቸው ይሆን? የሚለው ጥያቄ በነኚህ አጭር ቃላት ተመለሰልኝ ።

ዶክተር ገድሉ ወዲያውኑ ሰዓታቸውን ተመለከ ቱና ራሳቸውን በመነቅነቅ ፣ "ከሥራ ሰዓታችን አም ስት ደቂቃ ያህል አቃጠልን" ብለው ወደ እኔ መለስ አሉና "እንግዲህ ሲስተር ይህንን ጨዋታችንን ወደ ፊት እንጨርሰዋለን" አሉ ።

"ጀምረን ያልጨረስነው ጨዋታ አለ እንዴ?" አልኳቸው ። ወዲያው ግን ራሴን ማቃለሌ ስለተሰማኝ ደንገጥ አልኩ ።

ስለዚህ ጥያቄዬ ዶክተር ምንም መልስ አልሰጡኝም ። የመገረም ሳቅ እየሳቁ ክፍሉን ለቀው ወጡ ። ያስገረማቸው ራሴ ልመልሰው የምችለውን ጥያቄ ማቅረቤ ነበር ። እኔም ተነስቼ ሻይ የጠጣንበትን ብርጭቆ አለቃለቅኩና ሥራዬን ለመቀጠል ወደ ሕመምተኞቹ ክፍል ሄድኩ ።

የመጀመሪያው ሥራዬ የቆዩ ቁስሎችን ማጠብና ፋሻ መለወጥ ስለነበር ለዚሁ የሚጠቅሙትን መሣሪያ ዎች ከነጋሪው ይዤ እየተዘዋወርኩ በምሠራበት ጊዜ በሥራው ላይ ስሬ ልምምድ ስለነበረኝ ምንም ሳልሳ ሳት ቀረሁ እንጂ የሚሠሩት እጆቼ ብቻ ነበሩ። ልቤም ዓይኔም ከዶክተር ጋር ለጥቂት ጊዜ ያደረግነው ውይይት ላይ ቀርተዋል። ፋሻውንና መቀሱን ሳነሳና ሳስቀምጥ እንዲሁም ስቆራርጥ አይኔ ለጌጥ እንደ ተቀመጠና እን ደማይጠቅም አርቲፊሻል ዓይን ሆኖ ነበር። ልቤም በው ይይት ወቅት ዶክተር ላቀረቡልኝ ጥያቄ የመለስኩላቸ ውን መልስ በማሰላሰል ላይ እንደነበር ቀርቷል። በተ ለይም ሰዓታቸውን ተመልክተው "አምስት ደቂቃ ያህል አቃጠልን--" ባሉበት ጊዜ ፊታቸው ላይ ይነበብ የነ በረው ቅሬታና የትካዜ ምልክት ባልጨረስነው ውይይት መበሳጨታቸውንና የሥራ ጊዜ ባይሆን ኖሮ ከእኔው ጋር ቁጭ ብለው ሲጫወቱ ቢውሉ መፍቀዳቸውን ይገልጽ ነበር። ይህ ሁኔታ ፈጽሞ ከዓይኔ ላይ ሊጠፋልኝ አልቻ ለም። እንደ ደመና ጊዜ ወይም በደንብ እንደማያሳይ ደብዛዛ መነጽር ዓይኔን ሸፍኖ ሌሎችን ነገሮች በደንብ እንዳይመለከት ለጥቂት ጊዜ አግዶት ቆይቷል።

በእርግጥ አንድ ተራ ሰው እጠገባችን ቁጭ ብሎ በወ ቅቱ የነበረውን ውይይታችንን ቢያዳምጥ ምንም እያስደን

ቀውም ። በቀላሉ ለፈዝ የሚቀርቡ ተራ ጨዋታዎችን የም ነለዋወጥ ሊመስለው ይችላል ። ለእኔ ግን እያንዳንዷ ቃሏ ጥሩ ትርጉም ነበራት ፤ እንደገመትሁት ለዶክተር ገድ ሉም።ለብዙ ጊዜ ሁለታችንን ሲያሳስቡን የነበሩትንና በሆ ዳችን ታምቀው የቆዩትን ችግሮቻችን የተገላለጽንበት ጊዜ ነበር ። በአጭር አነጋገር ሁለታችንም በፊት ለፊት ሳይሆን በስውር ቃላት ብቸኝነታችንን ይፋ ያወጣንበት ጨዋታውን ሳንጨርስ የሥራ ሰዓት በመድ ረሱና ያለመ ዝጊያ መለያየታችን ግን ሌላ ሃሳብና በሽታ ሊሆን ችሏል ።

## 10

በዚያው ሰሞን የዓመት ፈቃዴን ተቀብዬ ጥቂትእረ ፍት ለማድረግ ወሰንኩና አሥራ አምስት ቀን ወሰ ድኩ ። በቤት አካባቢ ወይም ከዚያ ውጭ ልሠራው ያቀ ድኩት ምንም ነገር አልነበረም ። ስለዚህ ተኝቼ መጽሐፍ በማንበብና ሹራብና ዳንቴል በመሥራት የእረፍቴን ቀን አጋመስኩት ። በእጅ ሥራው በኩል ደካማና ሰነፍ ነኝ ። ጥቂት ዙር እንኳ ሳልገፋ ይሰለቸኝና “ኤድያ! ማ ተጨነቂ አለኝ ? ” ብዬ ወደ ጠረጴዛው ወርወር አደርገዋለሁ ። ከመጽሐፍ ጋር ግን ብዙ ስለተለማመድንና ከስሜት ስለማ

ነበው በጥብቅ የተያያዝኩት ከእሱው ጋር ነበር ። እንዳንድ ቀን ግሩም ታሪክ ያጋጠመኝ እንደሆን ሳልጨርስ አላቋርጥም ። በታሪኩ ብቻ በመጥገብ ምግቤን ሳልበላ አቀርቅሬ ሳነብ የምውልበት ቀን ጥቂት አልነበረም ። ልክ ፊልም ቤት ያለሁ ይመስለኛል ። ከቤቱ መሆኔ ትዝ የሚለኝ " ኧረ ይብቃሽ ፤ እስቲ እህል ቀምሰሽ ተመለሺበት " የሚለው የእናቴን ድምጽ ስሰማ ነበር ።

በዚህ የእረፍት ጊዜዬ የማነባቸው መጻሕፍት እንዳለፈው ጊዜ አልሆንልሽ አሉኝ ። መጻሕፍቱ በፊት ከማነባቸው ዓይነቶች የተለዩ አልነበሩም ። በደንብ አልታዘዝልኝ ያለኝ አእምሮዬ መሆኑ ገባኝ ። አንዳንድ ጊዜ አራት ገጽ ያህል ምንም ሳይገባኝ አነብና እንደገና እመለስበታለሁ ። ግን ልብ ከሌለ ይህ ሁሉ ከንቱ ድካም ነው ።

ልቤ የሚያሰላስለው ለጥቂት ቀናት የተለየሁትን መሥሪያ ቤቴንና ሰዎቹን ነው ። ከመሥሪያ ቤት ፈቃድ ስወስድ የመጀመሪያ ጊዜዬ አልነበረም ። የናፈቅሁበትም ጊዜ የለም ። የአሁኑ ናፍቆት ከዶክተር ገድሉ ጋር ሳንተያይ መቆየታችን መሆኑ ግልጽ ነው ። መሥሪያ ቤቱ የሚናፍቀኝ ምናልባት ከእሳቸው ጋር የተቀራረብንበትና አንድ ላይ የምንሠራበት ቦታ በመሆኑ ይሆናል ።

አንዳንዴም ከልቤ እያስተዋልኩ ብዙ ገጾች በማነብበት ጊዜ ባለታሪኮቹን ከዶክተር ገድሉ ጋር አዛምዳቸውና

የማነበው መጽሐፍ ስለእሳቸው ዓይነት ሰዎች የሚገልጽ ይመስለኛል ። አንዳንዶቹንም ድርጊቶች እኔና ዶክተር ገድሉ ወደፊት የምንፈጽማቸው መስሎ ይታየኛል ። እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ውስጥ በምገባበት ሰዓት እንደተለመደው ሳይገባኝ ብዙ ገጾች አነብና እንደገና ን መለስባችዋለሁ ።

አብሶ በመሀል እየመጣ ትውስ የሚለኝ መደምደሚያ ሳናበጅለት በሥራ ሰዓት መድረስ ምክንያት የተለያየንበት ውይይት ነው ። ያኔውኑ ቢያልቅ ኖሮ ቁርጡን አውቄ ነበር ብዬ አስባለሁ ።

በእንዲህ ዓይነቱ በሽታ ስለከፍ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ። ለሀሳብ ፣ ለጭንቀት ፈጽሞ ቦታ አልሰጣቸውም ነበር ። አንዳንዴ እንኳ ስበሳጭ መድኃኒቴ እንቅልፍ ነበር ። ተኝቼ ስነሳ ወዲያውኑ እረሳዋለሁ ። አሁን ግን የተለየ ነገር ነው ። ብተኛም እንቅልፍ አይወስደኝም ፣ ደግሞ ተኝቼ እንቅልፍ ወስዶኝ ስነሳም ወደ ሃሳቡ መመለሴ አልቀረልኝም ! መድኃኒቱን ማግኘት በፍጹም አልተቻለም ። ለአፌ ያህል "ምን መሆኔ ነው?ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ጠንክሬ ስከላከል የቆየሁት እንዲህ ዓይነቱ ጭንቀት ውስጥ እንዳልገባ አይደለም እንዴ? በጥንካሬዬ መቀጠል አለብኝ ። ለእንዲህ ዓይነቱ ጭንቀትና ሃሳብ ፈጽሞ ቦታ መስጠት የለብኝም" ማለቴ አልቀረም ። ግን ምንም

ብዋሽ ልቤ መጨነቁንና ግብዝነቴን ማስረዳቱን አልተ ወም ፣ የማላውቀው ኃይል ከፊቴ እየመጣ እፍአዊ ሃሳቤን በመቃረን እንዲህ ይለኛል ፡

"- - - ውሸታም ! ምን ራስሽን ታታልያለሽ ? አሁን ስለፍቅር ምንም ነገር አታስቢም ? ከዶክተር ገድሉ ጋር በልብ የተገናኛችሁበት ምንም ነገር የለም ? ይልቅ ግብዝ አትሁኚ ፣ ስሜትሽን ከመጠን በላይ አትቆጣጠሪ - - - -"

በዚህ ሁኔታ የእረፍት ጊዜዬን ጨረስኩ ። መቼም የማያልቅ ነገር የለምና ነው እንጂ አሥራ አምስት ቀን የዓመት ያህል ረዝሞብኝ ነበር ። በመሀል ሄጄ ናፍቆቴን መወጣትም የሚያሳፍር መስሎ ታየኝ ። ከአሁን በፊት ቦታ የማልሰጠው "ሰው ምን ይለኛል?" የሚለው ይሉ ኝታኛነትም ባላሰብኩት መንገድ ከጭንቅላቴ ገብቷል ። ስለዚህ የነበረኝ አማራጭ የረፍት ጊዜዬን ጨርሼ መመ ለስ ብቻ ነበር ።

## 11

እረፍቴን ጨርሼ ተመለስሁ ። ከመሥሪያ ቤቱ እንደ ደረስኩ ከእኔ ቀድሞ የገባ ሠራተኛ ስላልነበረ ቢሮዬን ከፈትኩና የሥራ ሽርጤን ካጠለቅኩ በኋላ

የሥራ ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ለአሥራ አምስት ቀን ያህል ሳላያቸው የከረምኩትን ሕሙምተኞች እየተዘዋወርኩ ሰላምታ ሰጠኋቸው ። የሰላምታ አሰጣጣ ቸውና ፊገግታቸው መምጣቴን በናፍቆት ይጠባበቁ እንደ ነበር ይገልጻል ። እንዲያውም ከመሐላቸው አንዱ በእረ ፍት ቀናት ውስጥ መጥቼ ስላልጐበኘኋቸው ቅሬታ እንደ ተሰማው በግልጽ ነገረኝ ።

ወዲያው የጽዳት ሠራተኞቹና ድሬሰሮቹ እየተከታ ተሉ ገብተው ሥራቸውን ቀጠሉ ። እኔም ወደቢሮዬ ተመ ልሼ የሕክምና ካርዶችን እያገላበጥኩ የሕሙማኑን ውጤት እመለከት ጀመር ። ብዙ ገጾች እያገላበጥኩ ብመለከትም የዶክተር ገድሉን ጽሕፈት ማግኘት አልቻልኩም ። በም ትኩ ሌላ ግሩም የሆነ የእጅ ጽሑፍ ተተክቶበታል ። ይህን በተመለከትኩ ጊዜ ልቤ እንደመደንገጥ አለ ። ዶክ ተር ገድሉ ከዚህ መሥራታቸውን አቋርጠው ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አደረብኝ ። በምትካቸው የመጣውን ሰው ለማወቅ ጓጓሁ ።

ለማንኛውም ወደሠራተኞቹ ብቅ ብዬ ነገሩን ለማ ጣራት ወሰንኩ ። ከቢሮዬም ወጥቼ ወደ ልብስ መቀየሪያ ቸው ክፍል ሄድኩ ። የዶክተር ገድሉ የሥራ ልብስ (ጋዋን) እንደ ተሰቀለ ነው ። ምናልባት በምትካቸው የመጣው ሐኪም የሚጠቀምበት ይሆናል ብዬ ስለገመ

ትኩ ነገሩን ለማረጋገጥ ወደ ጋዋኑ ጠጋ አልኩና ከላይ ኛው ኪስ አጠገብ ያለውን የባለቤትነት ምልክት አየ ሁት ። እንደ ጥንቱ የዶክተር ገድሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ " D.G. " የሚል ጽሑፍ እንደ ተለጠፈበት ነው ። በዚህ ጊዜ መንፈሴ በጥቂቱ ርጋታ አገኘ ፣ ዶክተር ገድሉ ከዚያ ቦታ ጭራሽ አለመቀየራቸውን አረጋገጥኩ ። ሆኖም ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ለመሆን እንዲያስችለኝ በክል ላችን ውስጥ ያሉትን የጽዳት ኃላፊ ቀርቤ ጠየቅኋቸው ። አጠያየቄ ናፍቆቴን እንዳያሳይብኝ ትልቅ ጥንቃቄ የተሞላ በት ነበር ። ግንባሬን ኮስተር በማድረግ አስቀድሚ ሰላምታ ከሰጠኋቸው በኋላ

"ዶክተር ገድሉ ሰሞኑን ሥራ አልገቡም እንዴ? ዛሬ ምነው ቀሩ? የበሽተኞቹ መግቢያ ሰዓት አለፈኮ" ብዬ ጠየቅኋቸው ።

እሳቸውም ከአፌ ቀሙኝና "ሰሞኑን ለአንድ ሳምንት ያህል እስቸኳይ ስብሰባ ላይ ናቸው ። ምናልባት ዛሬና ነገ ሳጨርሱ አይቀሩም ። ከትላንት ወዲያ ብቅ ብለው ስለ እርስዎ መግባትና አለመግባት ጠይቀው ነበር ። እሳቸው የስብሰባውን ጊዜ እስኪጨርሱ ድረስ ግን ሌላ ዶክተር ተመ ድቦአል" አሉኝና እንደገና ወደኔው ጥያቄ በማቅረብ

"--ግን እስካሁን አዲሱ ዶክተር አልገቡም እንዴ?" አሉኝ

" የጠየቅሁዎት ማንንም በማጣቴ አይደለም" አልኩኝ፤

"ማ እንደ ዶክተር ገድሉ" አሉና ጀምረው የነበረውን የመስታወት መወልወል ሥራ ቀጠሉ ።

እኔም ብቻዬንም ቢሆን ሕመምተኞቹን ለመጐብኘት ወሰንኩና ወደ ቢሮዬ ገብቼ የሕክምና መሣሪያዎች የያዘውን ጋሪ እየገፋሁ ስወጣ የዚያው ግቢ ሠራተኛ የሆነ ሰው ከሩቅ ሲመጣ አየሁ ። አመጣጡ እኔን እየተመለከተ ስለ ነበር ቆሜ ጠበቅኩት ። አጠገቢም እንደ ደረሰ አንገቱን ሰበር በማድረግ ሰላምታ ከሰጠኝ በኋላ፤

"የከፍሉ ነርስ እርስዎ ነዎት፤" ሲል ጠየቀኝ

"አዎ፤ ለምን ፈለግከኝ፤"

"ዶክተር አብርሃም ልከውኝ ነበር ።"

"ዶክተር" የሚለውን ቃል እንደሰማሁ "ገድሉ" የሚለው ስም ይከተላል በሚል ግምት በተመስጦ ሳዳምጠው "አብርሃም" የሚል ስም በመጥራቱ ወዲያውኑ ንግግሩ ሁሉ ዘጋኝ ። መልዕክቱንም ለማዳመጥ ሙሉ ስሜት አልሰጠሁትም ። ሆኖም ዶክተር አብርሃም በዚያው ሆስፒታል ውስጥ እንደሚገኙ ስለማውቅ በዶክተር ገድሉ ምትክ ለሰሞኑ የተመደቡት እሳቸው መሆናቸውን ገመትኩ ።

መልዕክተኛው ፣ ሀሳብ ውስጥ መግባቴን በመመል ከት ለጥቂት ጊዜ ያህል ዝም ካለ በኋላ "አዳምጠው ኛል ሲስተር?" አሉኝ ።

አነጋገሩ ለዘብ ያለና ትህትና ያዘለ ቢሆንም የእኔ አመላለስ በቁጣና በመሰልቸት ዓይነት ነበር ።

"ታዲያ እዚህ የቆምኩት ምን ቀርቶኝ ነው?"

"ምን አስቆጣዎት ፤ ስለተከዙ ወደሌላ ሀሳብ የገቡ መስሎኝ ነው የጠየቅኩዎት"

"አሁን ንዝንዙን ትተህ የመጣህበትን ብትነግረኝ--

በሆዱ ፣ ጤነኛ አይደለችም እንዴ ማለቱ የማያጠራ ጥር ነው ። በመገረም ሳቀና "ዶክተር አብርሃም ሥራ ላይ ስለሆንኩ የጠናበት ሕመምተኛ ካለ የቢሮ ቁጥር ፴፯ ድረስ አምጡት ፤ በሽተኞቶቹን ለመጎብኘት ግን ጊዜ አላገኘሁም" ብለዋል አለኝና ወደ መጣበት ለመመለስ ፊቱን ዘወር አደረገ ። ወዲያው እኔም ፣

"ትሰማኛለህ?" አልኩትና ወደእኔ ዘወር ሲል በግድ የለሽነት አነጋገር ፣

"በሆስፒታል ውስጥ የተኙትን ሕመምተኞች ዶክ ተር እየዞረ ሲጐበኛቸው እንጂ ሕሙማን ዶክተር ቢሮ ሲሄዱ እስከ ዛሬ ስላልተመለከትኩ አላደርገውም" አልኩት ።

ምንም ሳይናገር ዝም ብሎ ሄደ ። መልዕክቱን ከነ ገረኝ በኋላ መገላገሉን ሳይፈልግ አልቀረም ። እኔም ዶክ ተሩን የምጐዳ ይመስል ልሠራበት ያወጣሁትን የሕክ ምና ዕቃ ከቦታው መልሼ ከቢሮዬ ገብቼ ያለ ምንም ሥራ ቁጭ አልኩ ።

ምን መሆኔ ይሆን? ፍቅር እንዲህ ያደርጋል? በእለቱ ዶክተር ገድሉን በሥራ ቦታ ያለማግኘቴ ቅር እንዳሰኘኝ የታወቀ ነው ። ከዚያ ሌላ ግን ለቁጣና ለብስጭት አሳ ልፎ የሚሰጥ ምንም ችግር አላጋጠመኝም ። ከመልዕክተ ኛው ጋር ስንነጋገርም ሆነ ከዚያ በኋላ ለማየው ነገር ሁሉ ቁጣ ቁጣ ፣ ይለኛል ። አልፎ አልፎም በራሴ በመገረም ፣ ምን ሆኜአለሁ ? የሚል ጥያቄ ባቀርብም ምንም መልስ አላገኘሁም ።

ዶክተር አብርሃም በፍጥነት እየተራመዱ መጡና ከቢሮዬ ሰተት ብለው ከገቡ በኋላ "ጤና ይስጥልኝ" በማለት ሰላምታ ሰጡኝ ።

እኔም ከተቀመጥኩበት ሳልነሳ ሰላምታ ሰጠኋቸው ። የሕመምተኞቹን ካርድ እያገላበጡ " አስቸኳይ ርዳታ የሚያስፈልገው ህመምተኛ አለ እንዴ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"አልጎበኘኋቸውም" የሚል አጭር መልስ ሰጠኋ ቸው ።

“ ለምን ? እኔ እኮ ያልመጣሁት ሥራ ስለበዛብኝ ነው ።”

“ የእኔም ብቻዬን መጐብኘት ለበሽተ ኞቹ የሚጠ ቅም አልመሰለኝም ።”

ግድ የለሽነት በተሞላው አነጋገሬ በመበሳጨት የበ ሽተኞቹን ካርድ ይዘው ወደየክፍሉ ገቡ ። እኔም ተከት ያቸው ሄድኩና ሕሙማኑን ጐብኝተን ስንመለስ የምሳ ሰዓት ደርሶ ስለነበር ሁላችንም ወደ የቤታችን ሄድን ።

12

አቤትም ሆንኩ መሥሪያ ቤት የመበሳጨትና የመጨነቅ ስሜት አልለቀቀኝም ። እንዲያው ብቻ የማ የው ሰው ሁሉ ያስጠላኛል ። የምወደውን መጽሐፍ እንኳ ማንበብ አላስኘሽ ብሎኛል ። መሥሪያ ቤትም ገብቼ ሥራ ከምሠራ ይልቅ እንዲሁ ቁጭ ብል እመርጣለሁ ። አኳኋኔ ሁሉ ቤት ለማሠራት አስጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በአንዳንድ ነገሮች አለመቀላጠፍ ምክንያት የሚጉላላና የሚበሳጭን ሰው መስያለሁ ። በጣም ያቁነጠንጠኛል ።

ከእረፍቴ በኋላ ለሁለት ቀን ያህል በዚህ ዓይነት ገፋሁት ። በሶስተኛው ቀን ማለዳ ሥራዬ እንደገባሁ ዶክ

ተር ገድሉም ከተፍ አሉ። የሥራ ሽርጤን አውልቄ በመ ስቀል ላይ ስለነበርኩኝ ከበስተኋላዬ ኮቴ ብሰማም ዶክ ተር አብርሃም ስለመሰሉኝ ፊቴን አላዞርኩም ። ወዲያው ግን "አዜቢና" የሚለውን ቃል ስሰማ ዶክተር ገድሉ መሆናቸውን አወቅሁና ፊቴን ወደሳቸው ዘወር ሳድርግ ፊታቸውን ፈገግ አድርገው በማየቴ የእኔኑ ሰላምታ እየተጠባበቁ መሆናቸው ገባኝ ። ፈገግ ብዬ ወደሳቸው እየተጠጋሁ ለመጨበጥ እጄን ስነዘርኩና "እንደምን ስነበቱ ዶክተር?" አልኳቸው ። "ላቀረብኩላቸው ሰላ ምታ አጠፌታውን በመመለስ ጠበቅ አድርገው ከጨ በጡኝ በኋላ "እረፍቱስ እንዴት ነበር?" በማለት ጠየቁኝ።

እኔም ብሶቴን ለመግለጽ አጋጣሚ ስላገኘሁ ከፈገግታ ቆጠብ በማለት ፤

" ስለእረፍቱ አይጠይቁኝ ፤ እርስዎ ሰው ቢሞትም የሚጠይቁ ዓይነት አይደሉም" አልኩና ተቆጣሁ ።

"በስብሰባ ላይ መሰንበቴን አልሰማሽም እንዴ?"

" ታዲያ ቢሆንስ እኔን መጠየቂያ ጊዜ አጡና ነው?"

" ወደ ስብሰባ ከመሄዴ በፊትማ መጥቼ ነበር ፤ ነገር ግን ወደሥራ አለመግባትሽን ስለአረጋገጥሁ ተመ ልሼ ሄድኩኝ ። ከዚያ በኋላ ባሉት ቀናት ግን በጣም ትልቅ ውጥረት ላይ ስለነበርኩ መምጣት አልቻልኩም መምጣትም አልነበረብኝም ። የእኛ አለመገናኘት ከናፍ ቆት የበለጠ ጉዳይ አያመጣም ። ስብሰባውን ማቋረጥ ግን የብዙ ሰዎችን ዓላማ ሊያጓትት ይችላል" አሉኝ ።

የአነጋገራቸው አቀራረብ በይቅርታ መልክ ሳይሆን "አልተሳሳትኩም" በሚል ዓይነት ነበር ፤ እኔም ይህንን አላጣሁትም ። ሆኖም ለጨዋታ ያህል መናገሩን ስለወደ ድኩት ፤ "ስለሰው የሚያስብና የማያስብ ያስታውቅ የለ" አልኩና ቀለድኩ ። ዶክተር ሳቁና ፥—

"እስቲ እሱን በእረፍት ሰዓት እንጫወትበታለን ። አሁን ሕሙማኑን እንጎብኝ" ብለውኝ የሕሙምተኞቹን ካርድ ያዙና ቀድመውኝ ወጡ ። ከእሳቸው ጋር ትንሽ መቃለዱን ብወደውም ሥራን ማስቀደማቸው ትክክለ ኛነት ስለነበረው በነገሩ ተስማምቼ አብሬአቸው ሕመ ምተኞቹን እጐበኝ ጀመር ።

ገና የመጀመሪያውን ክፍል ለመጎበኘት ስገባ አንድ አዛውንት ህመምተኛ ከመኝታቸው ቀና ብለው ተቀመ ጡና ወደ እኛ እየተመለከቱ ፥—

"ተመስገን ነው ዛሬስ ፥ እነ ዶክተር ገድሉ መጡ -- -" አሉ ።

በዚህ ጊዜ ዶክተር ገድሉ እኔን እየት በማድረግ ወደ አዛውንቱ ጠጋ አሉና "አባቴ ለምን እንዲህ ተና ገሩ - -" ብለው ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ገና ሽማግ ሌው ከአፋቸው ቀሟቸውና "ኧረ ይተውኝ ዶክተር፤ ለበሽተኛ አንዱ መድኃኒቱ የሐኪሙ ፊት ፈካ ብሎ ማ

የቱ ነው እኮ ! ፊታቸውን ኮስ አስመስለው ለሚጎበኙ ንግ ችግራችንን እንኳን ለመግለጽ ምላሳችን ይተሳሰራል --" ካሉ በኋላ ራሳቸውን ነቅነቅ አደረጉና "ብቻ ማን እንደ ርስዎ ---"

ዶክተር ገድሉ በሥራቸው መደሰታቸውን ለመግለጽ ያህል ፈገግ እሉና እየተዘዋወሩ ሕመምተኞቹን ሁሉ መጎብኘታቸውን ቀጠሉ ። ሁሉም የሚቀበሏቸው በናፍቆትና በደስታ ነበር ። ገና ፊታቸውን ሲመለከቱ ከመኝታቸው ቀና ይሉና ፤ "ደህና ነን በጎ ነን" በማለት ደስታቸውን ይገልጹሉ ።

ያን እለት ጉብኝታችንን ጨርሰን ስንወጣ ዶክተር ገድሉ ተመላላሽ ሕክምና ክፍል ሥራ ስለነበራቸው በሻይ ሰዓት ወደ እኔ እንደሚመጡ ገልጸውልኝ ሄዱ ። እኔም እስከዚያው ድረስ ሥራዬን ለማጠናቀቅ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ጉድ ፣ ጉድ ስል በድንገት "ዶክተር ገድሉ እኮ ---" የሚል ድምጽ ከአንድ ክፍል ወጥቶ ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ አለ ። ይሄ ክፍል ቀደም ሲል እኔና ዶክተር ገድሉ ስንጎበኛቸው በጉጉትና በደስታ የተቀበሉንን ሕመምተኞች የያዘው ክፍል ነበር ።

ሕሙማኑ ጉብኝተናቸው ከወጣን በኋላ ስለእኛ እየተጫወቱ መሆኑ ገባኝና እንዳፍታ በሩን ከለላ አድርጌ ቆሜ የሚሉትን ሁሉ አዳምጥ ጀመር ።

" ዶክተር ገድሉ እኮ በሥራቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በውጭም የተወደዱ ሰው መሆናቸው ይነገርላቸዋል--- እንዲያውም ካሁን በፊት እዚህ ግቢ ሲረዳ ለቆየ አንድ ችግረኛ ግለሰብ በደግነት የፈጸሙአትን ተግባር እኔ ራሴ በደንብ የማውቀው ጉዳይ ነው ።" በማለት አንድ ሕመምተኛ ተናገር ሳይጨርስ ገና ሌሎቹ ስለሁኔታው በጥልቅ ለማወቅ ስለጓጉ ፤ « ምን አደረጉለት ? እስቲ አውጋን ።" እያሉ አዋከቡት ። እሱም ታሪኩን ቀጠለ ፡—

ተራኪው ሐኪም ቤት ብዙ የቆየው የኪንታሮት ሕመምተኛ ነበር ።

"...ይህ በዶክተር ገድሉ ተረዳ የምላችሁ ሰው ከወሎ ክፍለ ሀገር በንግድ ምክንያት መጥቶ አዲስ አበባ ጥቂት ቀን እንደተቀመጠ በርከት ያለ ገንዘብ የያዘ መሆኑን የጠረጠሩ ቀማኞች እንዳይሞት እንዳይሽር ቀጥቅጠው ገንዘቡን ቀሙት ። በዚሁ ምክንያት ወደ ሐኪም ቤት ገባ ። ይህ የሆነው ከምሽቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ስለነበረ ፈጥኖ ርዳታ ሊያደርግለት የሚችል ሐኪም እንኳ በቅርብ አልነበረም ። መቼም እንደምታውቁት ለችግር ጊዜ ደራሽ ያው ዶክተር ገድሉ ናቸውና በስልክ ተጠርተው በዚያ ሌሊት ሲሮጡ ደረሱለት ። ጉዳቱ ከባድ ስለነበረም ወደ ቀዶ ጥገናው ክፍል አስገብተው ከተረኛ የጤና ረዳቶች ጋር በመተባበር ልትወጣ የደረሰች ነፍሱን መለሱለት ።

"ሰውየው በሶስት ሳምንት ውስጥ ሕመሙ ስለ ተሻለው አልጋውን ለሌላ ሕመምተኛ ማስለቀቅ የግድ ሆነ ። በርግጥ ገና በማገገም ላይ ያለ እንጂ ፈጽሞ ያልዳነ ቢሆንም በዚያን ጊዜ ከነበረው የአልጋ ችግር አንፃር ግለሰብን ማስለቀቁ የማያስመኑታ መንገድ ነበር ።

"እንግዲህ ችግሩ እዚህ ላይ ነው ። ይህ ሰው በከተማ ውስጥ እገሌ የሚለው ዘመድ ወይም የሚያ ውቀው ሰው የለውም ። ወደ ሀገሩ የሚመለስበትን ገን ዘብ ቀማኞች ወስደውበታል ። ታዲያ ከዚህ ሐኪም ቤት ወጥቶ የት ይውደቅ ?

"ይህን ችግሩን እንደቅርብ ጓደኛው ሆነው በማ ዋየት መፍትሔ የፈለጉለት ዶክተር ገድሉ ነበሩ ። ዶክ ተር ገድሉ ችግሩን በሚገባ ካጸመጡ በኋላ ፣ "መል ካም ፣ በዚህ ላይ አትጨነቅ ! በደንብ እስኪሻልህ ድረስ ከእኔ መኖሪያ ቤት አቆይሃለሁ ። ከዳንክ በኋላ ደግሞ ወደ አገርህ የምትሔድበትን ዘዴ በጊዜው እናስብበታ ለን !" ሲሉት ሰውየው የራሱን ጆሮ ማመን አቅቶት እንደነበር ባሌላ ጊዜ አጫውቶኛል ።

"እንዳሉትም ሰውየው በደንብ እስኪድን ድረስ ከመኖሪያ ቤታቸው ወ ስጥ እየረዱ አቆይተውት በመ ጨረሻ መሳፈሪያ ገንዘብ ከኪሳቸው ሰጥተው ወደ ሀገሩ እንዲመለስ አደረጉ ። ከዚያ ወዲህም ሰውዬው እንደ

ቅርብ ዘመዱ እየተመለከታቸው እሳቸውን ለመጉብ ኘት ብቻ ከሕለበት ሀገር ድረስ ይመጣ እንደነበር የዚህ ግቢ ነርሶች ሲያወሩ እሰማለሁ ። እና አሁን ይህን ሁሉ ያነሳሁላችሁ የዶክተር ገድሉ ትህትናና ችግረኛ ረዳት ነት በሥራቸው ላይ የሚያሳዩት ፀባይ ብቻ ሳይሆን በማ ንኛውም ቦታ ያላቸው ከሕዝባዊ አመለካከታቸው የመ ነጨ መሆኑን ለመግለጽ ነው ። ”

ሕመማኑ ታሪኩን በጥሞና ሲያዳምጡ ከቆዩ በኋላ፤ “ልክ ነው እንጂ ጀረ ልክ ነህ ! የሕዝብ ወገን እኮ በዓይን ውሃውም ያስታውቃል ።” ሲባባሉ ልቤን እን ዳች የደስታ ስሜት እየተሰማው ጀምሬ ወደ ነበረው ሥራዬ ሄድኩ ። የሳቸውን በሕዝብ ተወዳጅነት ባደነቅሁ በት ልቤም “እኔስ ማነኝ ?” ብዬ ራሴን ጠየቅሁት ።

ሥራዬን ካጠናቀቅሁ በኋላ በተወሰነው ሰዓት ሻይ ለማፍላት ከክፍሌ ገባሁ ። ሰሞኑን ተለክፌበት የነበረው በሽታ ለቆኝ ሄዷል ። በሥራዬም ወቅት ምንም ዓይ ነት መሰልቸት አላሳየሁም ። ወደ ቁጣ ያዘነበለው ንግ ግሬም ተመልሶ ከቦታው ገብቶ ረጋ ያለ ሆኗል ። የበ ሽታዬ መንስኤ ምን እንደ ነበር ለማወቅ ችያለሁ ።

ዶክተር ገድሉ ልክ በሰዓቱ መጡ ። ከበራፉ እንደ ደረሱም በተለመደው አነጋገራቸው “ ሻይ ደረሰ ? አዜቢና ” አሉኝ ።

እሳቸው እያቆላመጡ ሲጠሩኝ እኔም እያቆላመጥኩ ልመልስላቸው ስለፈለግሁ "አዎ ዶርዕአል ፤ ይግቡልኝ እንጂ - - -" አልኩና ንግግሬን አቋረጥኩት ። ልቀጥል የፈለግሁት የስማቸውን ቁልምጫ ነበር ። ነገር ግን "አንቱ" እያልኩ ማቆላመጡ እንደማፈቅራቸው ጓደ ኛዬ ሳይሆን እንደ ማከብራቸው አሳዳጊዬ የሚያስመስ ልብኝ ስለመሰለኝ ይህንን ሳልጠቅስ ዝም አልኩ ።

ዶክተር ገድሉ እየሳቁ መቀመጫቸውን ሳብ አድር ገው ተቀመጡና ፤ "ንግግርሽን ለምን አቋረጥሽው ? ለማ ለት የፈለግሽውን እንደሆን አውቄዋለሁ" አሉኝ ።

" ደግሞ በልቤ ውስጥ የማስበውን ያዳምጡ ጀመር እንዴ ? ይህስ ተአምር ነው " አልኩ ። እነጋገሬ ለቀልድ የተሰነዘረ ነበር ።

አሁንም እየሳቁ ወደ ኋላቸው በመደገፍ ዘርጠጥ ብለው ተቀመጡና ፣ " የሚዋደድ ሰው ልብ ለልብ መገ ናኘቱ የት ይቀራል ብለሽ ነው ?" አሉኝ ።

" የሚዋደድ አሉኝ - - - ?"
"እህሳ - - -"

ሁለታችንም እነጋገራችን ፈጠን ባለ መንገድ ነበር። ገና ከአፌ አውጥቼ ሳልጨርስ የእሳቸው መልስ ተከ ተለ ። ከዚያ በኋላ ለጥቂት ጊዜ በሁለታችንም ዘንድ ፀጥታ ሰፈነ ።

"ይልቅ አንተ ብትይኝ ለማቆላመጥም ስለሚረዳሽ እንዳቅሙ አትቸገሪም። ደግሞስ እየወደዱ 'አንቱ' ምን ድነው ?"

"አሁንስ ጭራሽ ያላሰብኩትን ---- ደግሞ ለማቆላ መጥ ያሰብኩት መቼ ነው" አልኩና ሻዩን ፉት ለማ ለት ብርጭቆዩን አነሳሁ። እስቤው የነበረውን ሲነግሩኝ ኃጢአቱ እንደተዘረዘረበት ሌባ ደነገጥኩኝ ። ለመሽፋፈ ንም ሞከርኩኝ ። እሳቸውም ይህ ሁኔታዬ ስለገባቸው ነገሩን ተወት አደረጉትና ወደሌላ ጨዋታ በመሻገር ፥ "ታዲያ ስለ ኑሮሽ ምን ታስቢያለሽ ? " አሉኝ ።
"እንዴት ስለ ኑሮዬ ?"

ባለፈው ጊዜ ጀምረን ያቋረጥነውን ጨዋታ በማን ሳት ፤ "ስለምትቀይሺው የሕይወትሽ መንገድ ነዋ" አሉኝ ።

"ለምን መጠየቅ አስፈለገዎ ዶክተር?" አልኳቸው። አጠያየቁ ፍቅሬንና ሃሳቤን ለመሸፈን ያደረግኩት ነበር እንጂ የዚህ ጨዋታ መነሳቱ ደስ ብሎኛል ። ለምን እንደሆነም ገብቶኛል ።

"አይ ሲስተር" አሉና እየሳቁ እንደሚያስብ ሰው ለጥቂት ጊዜ አቀርቅረው መሬት መሬቱን ተመለከቱ ። ከዚያም እንዲህ አሉኝ ።

“አዜቢና ! መውደዷም ሆነ መውደድሽ ነውር አይደለም ። ይህንን እያወቅን ደግሞ በሚታችንን ለመደበቅ መሞከር ራሳችንን ማታለል ነው ። እውነቱን ልንገርሽ ፣ እወድሻለሁ ። እስካሁንም በደብብቆሽ ያሳለፍነው ጊዜ ይቅርታ የሚያስጠይቅ ነው ። በእኔ በኩል እንደሆን ጨርሻለሁ ። ከልቤ ስለምወድሽ የኑሮ ጓደኛዬ ላደርግሽ ፈቃዶ ነው ። አንቺም እንደምትወጂኝ አውቃለሁ ። አትደብቂኝ ። ሆኖም የምወድህ የሥራ ጓደኛዬ ስለሆንክ ብቻ ነው ። ለትዳር ጓደኝነት የመረጥኩት ወይም የምመርጠው ሌላ ሰው ነው የምትይም ከሆነ ቁርጤን ልወቀው ። ይህ ደግሞ የሚያበሳጨኝና የሚያስቆጣኝ አይሆንም ። ይልቁንም እኔም የፍቅሬን መንገድ በሚገባ አውቄ እንድከተል ያደርገኛል እንጂ ! አሁንም ደግሜ የምነግርሽ - - የልጅ ጨዋታ እናድርገው ፣ እውነተኛውን ልብሽን ግለጭልኝ ።”

አነጋገራቸው አዲስ ዓይነት በመሆኑ ቢያስደነግጠኝም የልባቸውን ስለ ገለጹልኝና ዳርዳር የምንልበትን ሁኔታ በሙሉ ስላወጡልኝ ትልቅ ደስታ ተሰማኝ ። እንድደፍርም አደረገኝ ባለፈው ጊዜ ሲያበሳጨኝና ሲያስቆጣኝ የነበረውም ያልታወቀ በሽታ ይህ መሆኑ ተሰማኝ ። ጭንቀት ፣ ብስጭት ፣ ይሉኝታ በሙሉ ለአንዳፍታ ያህል ከጭንቅላቴ ወጡልኝ ።

“ ከእርስዎ የበለጠ የምወደው ሰው የለም ፣ ሊኖርም የሚችል አይመስለኝም -- ልቤ ውስጥ የሚርመሰመሰውን ሁሉ በማውጣትዎ በጣም ደስ ብሎኛል ። እውነተኛነት ምንም እንደገምት አድርጎኛል ። ከእንግዲህ የርስዎ ልብ ግልጽ ሆኖ የእኔ የሚደበቅበት ምክንያት የለም ። ሆኖም ጊዜ ቢሰጡኝ ባሰብበት -- ” አልኳቸው ።

የሁለታችንም አነጋገር ከወትሮው ልዩ ነበር ። ሳቅም ሆነ የቀልድ አነጋገር ፈጽሞ አልታየብንም ። አጣዳፊን ችግር ለመወጣት የሚደረግ ሥነ-ሥርዓት የያዘና ጊዜ የማይባክንበትን ስብሰባ ይመስል ነበር ።

ያንን ያህል ግልጽነትና ጥንካሬን ለዚያች ደቂቃ ያህል ከየት እንዳገኘኋት ሲገርመኝ ይኖራል ።

እንዲህ ኮስተርና ጠንከር ባለ ሁኔታ የየልባችንን ከተወያየን በኋላ ዶክተር ገድሉ ደስታቸውን ለመግለጽ ፈገግታ እያሳዩ ፣ “እሺ እንግዲህ አዜቢና ፣ ዋናውን ነገር ጨርሰነዋል ፣ የተቀረውን ሌላ ጊዜ እንጫወታለን ፤ የሥራ ሰዓትም ደርሷል ” አሉ ፤ ወደሚወዱት ሥራም እየተ ተጣደፉ ሄዱ ።

ለብዙ ጊዜ አላስደፍርም ያልኩትን ልቤን መስጠቴ
ተሰማኝ ። ለጥቂት ሰዓታት ከቢሮዬ ሳልወጣ ቁጭ እን
ዳልኩኝ የሩቅና የቅርቡን አሰላስል ጀመር ። እንዲያ
ጠንካራና ግትር ልቤ ላልቶና ተሸንፌ ለዶክተር ገድሉ
ግልጽ የሆነበት ምክንያት ምን እንደሆነ ራሴን ደጋ
ግሜ ጠየቅኩት ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፍቅራችን እየጠነከረ መጣ ።
እንዳለፈው መደባበቃችንም ቀርቶ ግልፅ ሆንን ። በከ
ፍል 3 የሚገኙ ሠራተኞችም ስለዚህ ሁኔታ በደንብ
ሳይረዱ አልቀሩም ። እኔና ዶክተር ገድሉ አንድ ላይ
በምንሠራበት ጊዜ የሠራተኞቹ ዓይን የሚመለከተን በስ
ርቆትና ጥርጣሬ ሁኔታ ነበር ። አንዳንድ ሐሜታዎች
ይሰነዘሩብን እንደነበረም አያጠራጥርም ።

በሥራችን ረገድ የነበረን ሕብረትም እየጠነከረ ሄዶ
አል ። ዶክተር ገድሉ በአጋጣሚ ምክንያት ሳይመጡ የቀሩ
እንደሆነ እንኳ እኔው ራሴ እንደሁለታችንም ሆኜ ሕሙ
ማኑን አገለግላለሁ ። ርግጥ ሥራው ሁሉ የሚቀላጠፈው
አብረን ሥንሠራ ስለሆነ እሳቸው በሌሉበት ቀን ፥ ቅር
እንደሚለኝ ለማንም ግልጽ ነበረ ።

ከሥዩራ በኋላ እቤቴ በገባሁ ቁጥር ከራስጌዬ የተሰቀ
ለው “ መውደድ ፤ አጥብቶ መውደድ መጽሐፍንና ሥራን
ነው ። ” ሰውን አጥብቆ ማፍቀር ግን ትርፉ ጭንቀት ፣
ብስጭት ፤ ሐዘን ብቻ ነው ። ” የሚለው ጥቅስ ይታ

የኘና ለአንድ አፍታ ያህል ወደኋላዬ ዘወር ብዬ አስ ባለሁ ፡፡ ራሴን ኮስተር አድርጌም "ልክ ነው ፣ ልክ ነው" የሚል ድምጽ ለጣራና ለግድግዳው አሰማለሁ ፡፡ ከዶ ክተር ገድሉ ጋር ያለኝንም ፍቅር መጠነኛ ለማድረግ አስባለሁ ፡፡ ለፍቅር ይህን ያህል በወጣሁ በገባሁ ቁጥር በማሰቤም " ተሳስቻለሁ " በማለት ራሴን እወቅሳለሁ ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው ፡፡ ከቤቴ ስወጣ ወይም ከእንቅልፌ ስነቃ ተመልሼ እዚ ያው ናፍቆትና ሐሳብ ውስጥ መዘፈቄ አይቀርም ፤ ከንቱ ድካም ነው እንጂ በእንዲህ ዓይነቱ መግባባትና መተሳሰ ብን ደራርቦ በያዘ ፍቅር ላይ እንዴት መጨከን ይቻላል ?

አንዳንድ ጊዜ ከዶክተር ጋር ስንጫወት ሳይታሰብ በድንገት ፣ "እኮ ፍቅራችንን በመጠኑ እናድርገው " እላለሁ ፣ ነገር ግን ከልቤ ያልመነጨ በመሆኑ ወዲያው መልሶ ይጨንቀኛል ፡፡ ዶክተርን አስከፋኋቸው ይሆን ? የሚል ጥያቄ መልሼ ለራሴው አቀርባለሁ ፡፡

## 13

እኔና ዶክተር ገድሉ ከሥራችን ውጭ በትርፍ ጊዜ ያችን ተገናኝተን ሰፋ ያለ ጨዋታ የተጫወትነው አንድ

እሁድ ቀን ብቻ ነበር ። ስፍራውም እሳቸው ቤት ነው ። ይህ ቀን በሁለታችንም ልብ ውስጥ ከፍተኛ ትዝታ ጥሎ አልፎአል ።

ዶክተር ገድሉ የሚኖሩት ከእናታቸው ጋር ነው ። በቤቱ ውስጥ ከሁለቱ ሌላ ማንም ሰው አልነበረም ። እኔም ሰፋ ላለ ጨዋታ ወደዚሁ ቤት በሄድኩበት ጊዜ ያገኘኋቸው ሁለቱን ብቻ ነበር ። እናትዮዋ የሚበላውንና የሚጠጣውን ካቀረቡልን በኋላ ክፍሉን ለሁለታችን ለቅቀው ወጡ ። ከዚያ በኋላ የነበረውን ሁኔታ ምን ማውራት ያስፈልጋል? ፀጥ - ረጭ ባለው ክፍል ውስጥ ሁለታችን ብቻ ተቀምጠን ያለፈውንና የወደፊቱን ማውጋት ጀመርን ። ለእኔ መቼም እንዲህ ዓይነቱ "አዲስ ዓለም" ውስጥ ስገባ የጀመሪያ ጊዜዬ ነው ። ለእሳቸውም እንዲሁ እንደነበር ከሁኔታቸው ለመረዳት ችያለሁ ። በእጃቸው ስጐርስም የመጀመሪያ ጊዜ ነበር ። በዚሁ ጉርሻቸው ውስጥ የተላለፈልኝ የፍቅር መልዕክት እንደምግቡ ተቃጥሎ ወደ ኃይልና ወደ ቆሻሻነት የሚለወጥ አልሆነም ። እስከዘለዓለሙ ከልቤ ውስጥ ተቀምጦአል ። የአጐራረሴም ሥዕል ዘወትር በዓይኔ ላይ ሲዘዋወር ይኖራል ። ምግቡን ከጨረስን በኋላ ጭር ባለው ቤት ድምቀት ለመስጠት ቴፑን ከፍተነው በመጀመሪያ ላይ ሁለት ዘፈኖች ብቻ በእንክሮ አዳመጥን ፣ ከዚያ በኋላ ግን የእኛ ጨዋታ ስለአየለ ቴፑን ጭራሽ ረሳነው ።

ዶክተር ገድሉ በፊት የማሳየው ፀባይ ይገርማቸው ስለነበር ያለፈውን በማንሳት እንዲህ ሲሉ ጫዋታውን ከፈቱ ፤

"አዜቢና ፣ እንደዛሬው እንዲህ ሳልቀርብሽ በፊት እኮ ለማነጋገር እንኳ እፈራሽ ነበር ።"

"እንዴት ? ምኔ የሚያስፈራ ነበር? "

"አኳኋንሽ ሁሉ ነዋ ፤ ከቁም ነገር በስተቀር ቀልድ አይቹብሽ አላውቅም ። ደግሞም ወንዶች ሲያነጋግ ሩሽ ቁጣ ታስቀድሚያለሽ ፤ ኧረ ስንቱን ፀባይሽን እዘረዝ ረዋለሁ ።

"ታዲያ በዚህ ምክንያት ነው ይፈሩኝ የነበረው ? "
ራሳቸውን እየነቀነቁ "አይ አዜብ ፣ መቼ በዚህ ብቻ ሆነና ፣ መነሻው ይህ ይሁን እንጂ መድረሻውማ የመው ደድ ፍርሃት ነው ። የአሰራርሽ ሁኔታ ፣ የአረማመድሽ ሁኔታ ዘወትር በዓይኔ ላይ እየሄዱብኝ ስለተቸገርኩ እን ዴት ቀርቤ ስለ ውዴታዬ ልገለጽላት እያልኩ ራሴን በም ጠይቅበት ጊዜ አስቀድሞ የሚታየኝ ቁጣ ያዘለው አነ ጋገርሽ በመሆኑ ከወዲሁ ፍርሃት ያድርብኛል ። ስሥራ ጉዳይ ለማነጋገር ቢሆንማ ምን ያስፈራኛል ብለሽ ነው ፤ እንዲያው ታስለፈልፊኛለሽ እንጂ ይህንን ሁሉ መች አጣሽው -- ብቻ ያም ሆነ ይህ የሥራ ቦታችን አንድ ላይ ባይሆንና ባንቀራረብ ኖሮ በፍጹም ደፍሬ አላናግ

ሽም ነበር ። ይህን ያህል የመቀራረባችንም ነገር የማ ይታለም ነበር ።

"ግን እንደዚህ ያደረገኝ ምን እንደሆነ ያውቃሉ ?"

"እስቲ ንገሪኝ አዜቢና ! ምንድን ነበር ?"

መቼም ከዶክተር ገድሉ የምደብቀው ምንም ነገር የለኝም ። ከትሩፋት ጋር ከተገናኘንበት ጊዜ ጀምሮ ያጋጠመኝን ሁሉ ፣ የመጀመሪያው ፀባዬ ምን እንደነበረ ፣ በኋላ የተለወጠው ለምን እንደሆነ ፣ በዚሁ ፀባየ ብዙ ወንዶች እያስቀየምሁ ማባረሬን -- ሁሉንም ዝክዝክ አድርጌ አጫወትኳቸው ።

ንግግሬን ሁሉ በአንክሮ ከአዳመጡኝ በኋላ ትክዝ ብለው እየተመከቱኝ "ይህን ሁሉ አልፈሽ ነዋ የእኔ የሆ ንሽው ?" አሉኝ ።

ፊቱን ትክ ብለው የሚመለከቱት ልክ እንደ አዲ ስና አስደናቂ እንደሆነ ነገር ነበር ። ፊታቸው ያለወት ሮው ቀልቶ የደስታም ይሁን የድንጋጤ ያልታወቀ ነገር ይነበብበታል ። ዓይናቸው በተመስጦና በናፍቆት እኔን ይመለከታል ። ገጻቸው በሙሉ አይቸው የማላውቀው አዲስ ሁኔታ ነበር ።

የእሳቸው ሲገርመኝ ለካስ የእኔም የተለየ አልመሰ ለኝም ። አይኖቼ ፈዝዘው እሳቸውን ይመለከታሉ ። ፊቴ ያቃጥለኛል ! እጆችቼን አልቦኛል ። ልቤም ድንጋጤና ደስታ የተደባለቀበት አዲስና ልዩ ጣዕም ባለው ስሜት ይሞቀኛል ። በመሐላችን ፀጥታ ሰፍኗል ።

ወዲያው ወንበራቸውን ለቀው እኔ ከተቀመጥኩበት ሰፋ ያለ ፎቴ ላይ መጡና ቁጭ አሉ ። እንዴት እንደሚ ያደርጉኝ እንዴት እንደሚጠግቡኝ ግራ ገብቷቸዋል ። እኔ ም አይን አይናቸውን እያየሁ ፈገግታ ከማሳየት ሌላ መናገር ተስኖኛል ።

"አዜቢና ብዙዎቹን አልፈሽ አሁን የእኔ ሆንሽ" አሉኝ ። አነጋገራቸው በጣም የለሰለሰና የሚዳሰስ ዓይ ነት ከመሆኑም የተነሳ ልክ በጆሮ የሚነገር ምስጢር ይመስል ነበር ።

ትከሻቸውን ደገፍ ብዬ "አዎና ታዲያ" አልኳቸው ። እጄን በአንገታቸው ስር አሳለፋት ። ፊታቸው ጉንጨን ዳሰሰው—ጢማቸው የሞቀ ሰውነቴን አበሰው—ልቤ ና ድ ናድ አለ—ጉንጨን ሳም አደረጉኝና ቀና ብለው ተመለከ ቱኝ —በሚዳስስ አንደበታቸውም "አዜቢና ፣ መቼ ነው ታዲያ ጎጆአችንን የምንመሠርተው ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"ምን የቀን ገደብ ያስፈልገዋል ? "አልኳቸው ።

አሁንም ምንም ቃል ሳይተነፍሱ እንደቀድሞው ፊ ቴን ትክ ብለው ይመለከቱኝ ጀመር ። እኔም በናፍቆትና በጉጉት አይን ተመለከትኳቸው በእለቱ እኔ በእሳቸው ፊት ላይ እሳቸው በእኔ ፊት ላይ የምንመለከተው ከሌ ላው ቀን የተለየ አዲስና ውብ ነገር ምን እንደሆነ ለማ ወቅ አልቻልኩም ።

ወዲያው ከመቀመጫው ብድግ አሉ ፤ በሁለት እጃ ቸው ጭንቅላቴን አቀፍ እንደማረግ ሳብ አድርገው ግንባ

ባሬን ደግሞ እንደ ሳሙኤ—በቃቸው ፣ ከዚህ የበለጠ አል ተጓዙም ። ድፍረትም አላገኙም ። በእሳቸው ብቻ ምን ይፈረዳል ? እኔም አልደፈርኩም ። ተመልሰው ተቀመጡና እንደገና ወሬ ጀመሩ ።

ከዚያን ዕለት ወዲህ ያለው ነገር ስንቱ ተወርቶ ። ትግናኝነተን በተለያየን ቁጥር ናፍቆት ነው ። ጥቂት ጊዜም ቢሆን መጫወት የምንችለው በሻይ ሰዓት ስለሆነ በሥራ ጊዜ ለተራ ወሬዎች አያመችንም ። ማታ ማታም የተለ ያየ ቤት ስለምንገባ በቅሬታ መለያየት ብቻ ሆነ ። በእ ሁድ የዕረፍት ቀናችን እኔ ነፃ ብሆንም ዶክተር ገድሉ ጊዜ አልነበራቸውም ። አንዳንድ ጊዜ እበሳጭና "እንዲህ እይንቱን በሥራ የተጠመዱ ሰው ወድጄ ለምን እማቅቃ ለሁ ?" ብዬ ራሴን ስጠይቀው "ግድ የለም ፣ ሁሉንም ቻይ፣ ለሥራ ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ነው ፤ ለፍቅሩ ትደርሱ በታላችሁ ፤ ወደፊት ብዙ ጊዜ ይኖራችኋል" የሚል መልስ ከህሊናዬ ይሰነዘርብኛል ።

ከጊዜ በኋላ የትዳር መመስረቻችንን ጊዜ ለማቃረብ ወስነን ዶክተር ገድሉም ሆኑ እኔ በግላችን አንዳንድ የቤት እቃዎችን እየገዛን ከቤት ማስቀመጥ ጀመርን ። ቤተ ሰቦቻችንም ስለዚሁ ጉዳይ ሳያውቁ አልቀሩም ። ሰፋ ያለ ጨዋታ እንጫወት እንጂ አልፎ አልፎ እኔ እሳቸው ቤት እሳቸው እኔ ቤት እየመጡ ምሳ እንገባበዛለን ። በሽ

ታዩም ሁሉ ለቅቆኝ ሄደ ። ከማንኛውም ሰው ጋር በአግ ባቡ መቃለድ ጀመርኩ ። ያለፈውን ግብዝነቴን ትቼ ለያ ዝኩት ፍቅርና ለምመስርተው ትዳር የሚያስፈልጉኝን ሁሉ ጠንከሬ አከናወ ን ጀመር ።

## 14

አንድ ቀን ጠዋት ቀደም ብዬ ሥራ ገባሁ ። የሥራ ልብሴን አጠለቅሁና ምድብ ሥራዬን እያከናወንኩ ቆይቼ ሰዓቴን አየት ባደርግ አራት ሰዓት አልፏል ። ዶክተር ገድሉ አልገቡም ። መቅረታቸው መሆኑ ስለታወቀኝ በምትካቸው ሕመምተኞችን እየጐበኘሁ እርዳታ አደር ግላቸው ጀመር ። መቼም ዶክተር ገድሉ ያልገቡ እለት ሥራውም ይሰለችኛል ። መንገላወድ አበዛለሁ ። ሥራዬን ጨርሼ ቢሮዬ እንደተመለሰሁ አምስት ሰዓት አካባቢ ስልክ ተደወለ ። “ አዜቢና በምሳ ሰዓት በእኔ በኩል ትመጪ የለ ? ” ብሎ በመጀመር ! ዶክተር ገድሉ ነበሩ ።

“ምን ችግርኝ እመጣለሁ እርስዎ ግን ምን ሆነው ነው ከሥራ የቀሩት? ---” አልኳቸው ።

“ ትቀልጂያለሽ እውነትሽን ነው? በመሥሪያ ቤት ውስጥ ስለ እኔ ምንም ሲወራ አልሰማሽም ?”

“ እረ አልሰማሁም ፣ ምን ገጠመዎት ዶክተር? ”

“ እንግዲያው ስትመጪ ትሰሚያለሽ ፤ አሁን በጣም እቸኩላለሁ ፣ ዝግጅት ላይ ነኝ ፣ በምሳ ሰዓት እንዳትቀሪ ። ቻዎ ! ” አሉኝና ጥያቄ ለማቅረብ እንኳ ዕድል ሳይሰጡኝ ስልኩን ዘጉብኝ ።

ከዚያ በኋላ የምሠራው ሁሉ በድኔን ሆነ ። ሁለመናዬ በሃሳብ ተመሰጠ “ ዝግጅት ላይ ነኝ” ያሉኝ ነገር ይከነክነኝ ጀመር “ወዴት ለመሄድ ምን ለማድረግ ? ” የሚለውን ጥያቄም እያነሳሁ ሕሊናዬን አስጨነኩት ። ነገሩ ምን እንደሆነ የማውቅበት ሰዓት በጣም ራቀኝ ። ከነበርኩበት ክፍል ወጣ ብዬ ከሠራተኞቹ ወሬ ለመልቀም አሰብኩና ከመቀመጫዬ ብድግ ስል “ ትደርሺበታለሽ ፣ አሁን አርፈሽ ተቀመጭ ፣ መጥፎ ወሬስ ቢሆን ቶና ከአሁኑ ለመቃጠል ነው ? ለወሬ ምን ያስቸኩላል ?” አለኝ ሕሊናዬ ። መውጣቴን ተውኩትና ተመልሼ ተቀመጥኩ - - ምን የከፋ ነገር አጋጥሞአቸው ይሆን ? ወይስ ደግሞ ምን ጥሩ እድል አጋጥሞአቸው ይሆን ? ብዙ ነገር አሰብኩ ፣ ማሠሪያም ባላበጀለት - - - - - - - - - - -

እንደማይደርስ የለም ፡ የምሳ ሰዓቱም ደረሰና ወደ ዶክተር ገድሉ ቤት ጉዞዬን ቀጠልኩ ። በየመንገዱ አዲስ ነገር ይኖር ይሆናል በሚል ስሜት ወሬ ባለበት አካባቢ ጆሮዬን ጣል ማድረጌ አልቀረም ። ነገር ግን ከዶክተር ገድሉ ሥራ ጋር የሚዛምደው ምንም ወሬ አላገኘሁም ። ከቤታቸው አካባቢ እንደ ደረስኩ የዶክ ተር ገድሉን እናት ከሩቅ አየኋቸው ፣ ሽርጥ አገልድመው ከቆናው ክፍል ወደ ማድ ቤት ይሄዳሉ ። አረማመዳቸው ሁሉ የችኮላ ነው ። ሥራ ላይ መሆናቸው ስለገባኝ ምሳ ለማድረስ እየተንጎዳጎዱ ይሆናል አልኩኝ ። እንዳጋጣሚ ገልመጥ ሲሉ ስለተመለከቱኝ ቆሙና ጠበቁኝ ። ከአጠ ገባቸውም እንደደረስሁ ስላምታ እንኳ ሳይሰጡኝ አስ ቀድመው ፡—

"ሲስተር ፣ አንቺም ትሄጃለሽ ወይስ የእኔ ልጅ ብቻ ነው ?" አሉ አነጋገራቸው ሀዘን የተመላ ስለነበር ከመጠን በላይ ደነገጥኩኝ ። ወዲያውም ፈጠን ብዬ "ወዴት ?" አልኩና ጠየቅኋቸው ።

"አልሰማሽም እንዴ ? በዚያው በመሥሪያ ቤታ ችሁ በኩል እኮ ነው የታዘዘው" በተፈጥሮአቸው ቢና ገሩ ቀዝቀዝ ያሉ ናቸው ። በዚያ ላይ ሐዘን ስለተጫና ቸው ንግግራቸው በጣም ተጓተተብኝ ። እኔ ደግሞ ወሬ ውን ለመስማት በጣም ቸኩያለሁ ። ምንኛ አናደዱኝ —

"እኮ ንገሩኝ ፣ ምንም ነገር አልሰማሁም አልኩዎት"
አልኳቸው ።

" ይኸውልሽ ፣ ወደ ምሥራቅ ጦር ግንባር እንዲ ሄድ ታዘዘ" አሉኝና ሳያውቁት እንባቸው እርግፍ እርግፍ አለ ። " በደህና ይመለሱ እንጂ ቢሄዱ ምናለበት ፣ ለእሳቸው ብቻ የመጣ ነገር አይደለም " አልኩኝ ።

እናትየዋን ለማፅናናት ያህል የተናገርኩት ነበር ። ካለፈ በኋላ ሳስበው ግን በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ቃል ከእኔ አንደበት የወጣ መሆኑ ያጠራጥረኛል ። ለዚያች ደቂቃ ያህል የነበረኝ ጥንካሬ ከየት እንደመጣ አላው ቅም ።

አነጋገሬ በማስተዛዘን ዓይነት ሳይሆን ቆጣ ባለ መልክ ነበር ። ፊቴንም ኮስተር አድርጌዋለሁ ። ይህ ሁሉ ከንቱ ነው ። ድካም ነው ። እናትየዋ እንደሆን የተናገ ርኩት እሳቸውን ለማፅናናት ያህል መሆኑ በደንብ ገብ ቷቸዋል ።

ፊቴ ፍም መስሎ የቆምኩበት ቦታ የጨው ሐውልት ሆኜ ቀረሁ ። በሰውነቴም ብርድ አይሉት ትኩሳት የማይታወቅ ወጀብ ተነሳብኝ። ስለዘመቻው ሰሞኑን ይወራ ነበር ። በዚያን እለት ጠዋትም ከመሥሪያ ቤት እንደገ ባሁ ሠራተኞቹ በቡድን በቡድን ቆመው በሚያወሩበት

ጊዜ ፤ “ ከእኛ መሥሪያ ቤትስ እነማን ታዘዙ ?” የሚል ቃል ከአንዱ ግለሰብ አፍ ሲወጣ ሰምቻለሁ ። ወሬው ስለዘመቻው ጉዳይ መሆኑን አውቄዋለሁ ። ነገር ግን ጉዳዩ ብዙ አላዳመጥኳቸውም ። ዶክተር ገድሉ ይሄዳሉ ብዬ መቼ ገመትኩ ? በኋላም ስልክ ደውለው ---“ ዝግጅት ላይ ነኝ ” ሲሉኝ ለዘመቻው መሆኑን መጠርጠር የአባት ነበር ፤ ነገር ግን አልጠረጠርኩኝም ። ያን ያህል ኃላፊነት የነበረባቸው ሰው ወደ ጦር ግንባር ይሄዳሉ ብዬ እንዴት ልጠርጥር ---? በሕልሜም በውኔም አልነበረም------ምን ዘጋኝ ልበል ። ---?

እናትየዋ “ በይ እቤት ግቢና ጠብቂው ፤ አሁን ይመጣል ፤ አንቺም እንደምትመጪ ቀድሞ ነገሮኛል ” አሉኝና ወደ ቤት ካስገቡኝ በኋላ ፤ ”እመንገድ ላይ እንኳን ቢሆን ትንሽ ስንቅ ብጤ ላዘጋጅለት ብዬ እየተንደፋደፍኩ ነው ፤ መቼም የግብር ይውጣ ሥራ መሆኑ አል ቀረም” ብለው ተመለሱና ወደ ማድቤት ሄዱ ።

የመሄጃቸውን ጊዜ ለማወቅ ከመንጓጓቴ የተነሳ ተመልሰው የማይመጡ ይመስል ተከትያቸው ወደ ማድቤቱ ሄድኩና ፤ “ እማማ ፤ ለመሆኑ የዶክተር መንቀሳቀሻ ጊዜ መቼ ነው ? ” ብዬ ጠየቅኋቸው ።

“አይ ልጄ ጦርነት ቀጠሮ ይሰጣል ብለሽ ነው ፤ በነገው እለት ነዋ ! እንደሚወራው ከሆነ በጦር ሜዳው አካባቢ

የሐኪሞች እጥረት ስላለ በጠላት ጦር የቆሰሉ ወገኖ ቻችንን በፍጥነት ሕክምና እንዲያገኙ ብዙ ሐኪሞች ከከተማው ይወሰዳሉ ይባላል ። ሎሂዱስ ካልቀረ የእኔም ልጅ በፍጥነት ቢደርስላቸው ይሻላል” አሉ ።

ከአነጋገራቸው እንደተረዳሁት ፣ በአንድ በኩል የሀገር ፍቅር ስሜት ስላላቸው በሁኔታው ቅር እንዳል ተሰኙ ለመግለጽ ጠንክር ማለት ይፈልጋሉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የእናት ሆድ ነውና ልጃቸው ጦር ሜዳ ሂዶ በሚያክምበት ጊዜ ሊያጋጥመው ይችላል ብለው የሚያ ስቡት ሁሉ ከፊታቸው ድቅን ሲልባቸው ትካዜ ይጫጫ ናቸውና ንግግራቸውም ቅልስልስ ይላል ።

የጉዞአቸው መቻኮል እኔንም ብዙ አላስደነቀኝም ። የጦር ሜዳው ጉዳይ ፋታ የማይሰጥ መሆኑንና የጠላት ጦር እየገፋ መምጣቱን በዜና ማሰራጫዎች ሰምቻለሁ ። ደግሞም ጊዜ የሚሰጥ ጉዳ ትርፉ ሃሳብ ብቻ ነው ። በመሸ በነጋ ቁጥር ቀን መቁጠሩስ ሌላ ጭንቀት መፍጠር አይ ደል ! ከዚህ ሁሉ በአጭር ቀን መሄዳቸው ን መርጫለሁ ።

“አሁን ከጭሱ ዘወር በይ ፣ ሳሎን ሆነሽ ጠብቂው”

“አይ እማማ ፣ ያደግሁበት አይደል የርሱ ፣ መች ቸገ ረኝ ብለው ነው” ብዬ ከማድቤት ወጣ ስል ዶክተር ገድሉም በፈጣን ርምጃቸው ተፍ ፣ ተፍ እያሉ ሲመጡ

አየኋቸው ። ገና ከሩቅ ሲመለከቱኝ ፊታቸውን ፈገግ አደረጉትና ወዲያው መልሰው ወደ መሬት አቀረቀሩ ። አንድ ነገር እንደተሰማቸው አወቅሁኝ ። ከሩቅ እኔን ማየ ታቸው ደስ ሲላቸው በጉዞ ምክንያት ሊለዩኝ በመሆኑ ደግሞ ቅሬታ እንደተሰማቸው ገባኝ ። ፊታቸውን በፍጥ ነት ወደ መሬት የመለሱት ይኸው የጉዞ ሁኔታ ትውስ ሲላቸው መሆኑ ተሰማኝ ።

አጠገቡም እንደደረሱ እጃቸውን ትከሻዬ ላይ ጣል አደረጉና ፣ "ታዲያስ አዜቢና ፣ ሥራ እንዴት ነበር?" ሲሉ ጠየቁኝ ፡፡

ሊጠይቁኝ የሚገባ ፣ ልጠይቃቸው የሚገባኝ ብዙ አጣዳፊ ነገሮች እያሉ እንዲህ ዓይነቱን ዘወትራዊ ጥያቄ ለምን እንዳመጡት አይገባኝም ። ምናልባት የዘመቻውን ወሬ ያዘናጉኝ መስሏቸው ይሆናል ። እንዳልጨነቅባቸው ሌላ ወሬ እያነሱ የጉዞውን ወሬ ችላ ለማለት እንደፈለጉ ተረዳሁ ። ግን እንዲያው ድከሙ ሲላቸው ነው እንጂ ፊታቸው ላይ የሚያንገዋብበው ደመና ምንኛ እንደተጨነቁ ይገልጽባቸዋል ።

መቼም "የሚዋደድ ሰው ልብ ለልብ ይተዋወቃል" ይባል የለ ፣ ያለቦታው ያቀረቡትን ጥያቄ መልስም ሳይ ጠብቁለት ተወት አደረጉና ፤

“ አሁን ያሳሰበሽ የእኔው ዘመቻ ጉዳይ መሆኑ ይገ ባኛል ። ግን ፈጽሞ አትጨነቂ፤ በጣም ቀላል ነገር ነው ። እንኳንስ የሕክምና ርዳታ ለማድረግ ቀርቶ ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ለመታኮስ የሚሄደው ወታደር እንኳ ይህን ያህል አይጨነቅም ። የእኔ ከዚህ ሁሉ የተለየ ነው ። ፈጽ ሞ ሃሳብ አይግባሽ ” አሉ ።

እንዴት ነገሩን ሁሉ ቀላል አድርገው አቀረቡት ፤ ይህ ሁሉ አባባል እኔን ለማጽናናት ነው ። እንዲህ አር ጎም ማጽናናት የለም ። “ ሃሳብ አይግባሽ ” ብሎ ነገር ፤ ዓይኔን ብዘጋው ፤ ጆሮዬን ብደፍ ነው ሃሳብ የት ይቀር ልኛል ?።

“ ለመሆኑ የሚያርፉበትን ቦታ ያውቁታል ? ”

“ የተነገረኝ ነገር ወደ ምሥራቅ ጦር ግንባር መሄድ እንዳለብኝ ብቻ ነው ፤ የሕክምና መስጫ ሥፍራ ግን በየት አካባቢ እንደሆነ አላወቅሁትም ፤ በጦርነቱ አካባቢ ቀረብ ብሎ ሳይሆን ይቀራል ? ” ይህን ሲናገሩ የባሰ መን ፈሴን ረበሹት ። በጦር ሜዳ የሚደረገው ውጊያ በመንፈሴ ታየኝ ።

በጠላት ጦር የቆሰሉ ወታደሮች እያቃሰቱ ርዳታ ሰጪዎችን ሲፈልጉ -- ዶክተር ገድሉ እዚያ ጥይት እን ደበረዶ የሚዘንብበት ቦታ ገብተው እየተሯሯጡ በተለመ ደው አነጋገራቸው ፤ “አይዞችሁ ፤ ምንም አትሉ ፤ ቀላል

ነው ፤ ትድናላችሁ” እያሉ በማጽናናት የሕክምና ርዳታ ሲያደርጉላቸው ---

ዓይኔ እንባ እንዳዘለ ትክ ብዬ እየተመለከትኳቸው ፤ “ደብዳቤም ልጽፍልዎት አልችልም ማሬት ነዋ ?” ብዬ ጠየቅኋቸው ።

በፍጥነት መልስ ሊሰጡኝ አልቻሉም ። ስለዚህ ጉዳይ በማሰብ ግንባራቸውን ኮስተር አደረጉና በዓይና ቸው ወደሩቅ ይመለከቱ ጀመር ። ልባቸውም እንደዚያው ርቆ መሄዱ ገባኝ ።

ይህንን ሁሉ የምንጫወተው ወደ ቤት ሳንገባ ገና ከውጪ እንደተቀበሉኳቸው ቆመን ነበር ። እናትዮዋ የልጃቸውን ድምጽ ሲሰሙ ከማድቤት ወጡና በሽርጣ ቸው ጫፍ ጭስ የሸፈነውን ዓይናቸውን እየጠራረጉ “እንዴት ነው ? የሄድክበት ተሳካልህ ?” ሲሉ ጠየቋ ቸው ።

ዶክተር ገድሉም ራሳቸውን በመነቅነቅ ጉዳዩ እንደ ተሳካላቸው ገለጹላቸው ። ይሄኔ እናትዮዋ የትካዜ ሳቅ እየሳቁ ወደ እኔ ተመለከቱ ። እንደገና ልጃቸውንም አት ኩረው አዩአቸው ። በፊታቸው ላይ የሚታየው ፈገግታ ደስታና ቅሬታን ያዘለ ነበር ። እኔም አንድ ያላወቅሁት ነገር እንዳለ ጠረጠርኩ ።

" በሉ ወደቤት ግቡ፣ እኔም ሥራዬን ጨርሻለሁ፣ መጣሁ " ብለው እያመነቃቁ ወደ ምድጃቸው ተመለሱ ፤ አኳኋናቸው ዓላማው ግቡን ያልመታለትን ሰው ይመስላል ።

እኔና ዶክተር ገድሉም ከቤት ገብተን ረዥሙ ፎቴ ላይ ጐን ለጐን ተቀመጥን ። ገና አረፍ ስንልስታችንም "ለጎጆ መውጫ" ብለን የገዛነውን ሙሉ የሻይ ስኒ ከነ ማስቀመጫው (ከነማንቆርቆሪያው) ከፊት ለፊታችን በነ በረው ቁም ሣጥን በመስታወት ውስጥ ታየን ። እኔ ልሁን እሳቸው ማንኛችን ቀድመን እንደተመለከትነው አላስታውስም ። ነገሩ ግን ለሁለታችንም ስለገባን የሁለታችንም ፊት ለአንድ አፍታ ያህል በትካዜ ጉም ተሸፈነ ። ዶክተር ገድሉ ወደ ትከሻዬ ጠጋ ብለው ከሹራቤ እጅጌ ላይ የጋቢ ጥጥ መሳይ እየለቃቀሙ፣ " አይዞሽ ፣ ስለትዳሩ እን ደሆን ከጦር ሜዳ ስመለስ እንጸርስበታለን " አሉኝ ።

ሰው መቼም ተስፋ አይቆርጥም ። እቆያለሁ እንጂ እሞታለሁ አይልም ። አሁን እስቲ እንዲህ ዓይነቱን የማ ይጨበጥ ተስፋ መናገራቸው ከምን ሊያድን ይሆን ? ለጠ ርነት ሳይሆን ለተመልካችነት የሚሄዱ ይመስል " ከጦር ሜዳ ስመለስ" ማለትን ምን አመጣው ? በእርሳቸው ቤት እኔን ቅር እንዳይለኝ ማባበላቸው ነው ። ዳሩ ምን ያድ ርጉ ፣ ጦር ሜዳ የሚሄድ እየሸለለ እንጂ እየተከዘ እንዳል ሆነ ሲነገር ይሰሙ የለ ? እኔም በአነጋገራቸው በመገረም

ራሴን ነቀነቅኩና "እሺ እስቲ ያድርሰን" አልኳቸው ።
እነጋገሬ የተስፋ መቁረጥና የማመንታት ነበር ።

እናትዮዋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሻችንን አድርሰው ከተፍ አሉ ። እንጀራ ያቀረቡበት ትሪ አዲስ ነበር ። ይህ ንንም ዶክተር ገድሉ በቅርቡ ለጎጆ መውጫችን የገዙት ሳይሆን እንዳልቀረ ገመትኩ ። ግን ቢሆንስ እናትዮዋ ምን ቢያስቡ ያወጡታል ። ለተንኮል ፣ ለማበሳጨት ፣ ትዝታ ውስጥ ለመጨመር ካልሆነ በስተቀር ------

ዶክተር ገድሉ ሐሳቤን የተከታተሉት ዓይነት ቆጣ ብለው ወደ ትሪው እያዩ ፣ አሁን "ይህን ምን ሊያደርግልሽ አወጣሽው ?" አሏቸው ።

"አይ ! ብሉበት እባክህ ፣ ለሙቼ ቀን ይቀመጣል ? የት ዳሩ ነገር እንደሆን --" ንግግራቸውን አቋረጡና ለጥ ቂት ሴኮንዶች ፀጥ ካሉ በኋላ ፣ "ብቻ አምላክ ያውቃል ፣ ሁሉንም መልሶ ያስተካክለው ይሆናል " አሉ ።

ዶክተር ገድሉ የእናታቸውን ከፉኛ ተስፋ መቁ ረጥ ከአነጋገራቸው ስለተረዱ ፣ ለማጽናናት ያህል ፣ "አይ

ዞሽ ያስብሽው ሁሉ ጊዜ ይፈጃል እንጂ መፈጸሙ አይ ቀርም ፣ ተስፋ አትቁረጪ'' አሏቸው ።

"እንዳፍህ ያድርገኖ ! " ብለው ወደጓዳ ተመ ልሰው ገቡ ። ይህን ሁሉ የሚያናግራቸው ልጃቸው ፍሬአቸውን ሳያሳዩአቸው ገና በዕትድ ላይ እንዳሉ ሊዘ ምቱ በመሆኑ ነው ። ፈጽሞ ተመልሰው የሚመጡ አል መሰላቸውም ። ወይም ደግሞ ተመልሰው እስኪመጡ ድረስ እኔ እሞት ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ሳያድርባቸው አልቀረም ። ትልቅ ተስፋ መቁረጥ ይታይባቸዋል ። ይው ጣላቸው ብለው ነው መሰል ዶክተር ገድሉ የገዙአቸውን ዕቃዎች ሁሉ እያወጡ ፊታችን ይደኑቅሩብን ጀመር ። በዚህ ሁኔታ የእኔንም ሆድ ይበልጥ አባቡት ።

ጨዋታ ያለቀብን ይመስል በሁለታችንም በኩል ፀጥታ ሰፈነ ። ምግቡን ብቻ አቀርቅረን እንጕስጉስ ጀመር ። እሱንስ ምን ያህል ስንበላ ፣ እንዲያው ብቻ የማይናገረውን ተያያዝነው ለማለት ያህል ነው ። ዶክ ተር ገድሉ ቆየት ይሉና ፣ "ብይ እንጂ'' ሲሉኝ "ይገ ዋለሁ'' ከማለት ሌላ ምንም የሰፋ ጨዋታ ጠፋ ።

ጀማሪው ጠፍቶ ነው እንጂ ወሬስ ሞልቶ ነበር ። መተፋፈር አይሉት መደባበቅ ስለ ዘመቻው እንዳናወራ የተከለከልን ይመስል ዳር ዳር ማለታችን ለምን እንደሚ

በጅ አልገባኝም ። የሁለታችንንም ሆድ የረበሸው ይኸው ጉዳይ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ዶክተር ገድሉ በድንገት ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ቆጣ ብለው ፥ "መተከዝ ምንድነው ? ከእኛ የሚጠበቅ እኮ አይደለም" አሉ ።

" በአፍዎስ ተናገሩ ፥ ለመሆኑ ልብዎ ይህን ማድረግ ችሎአል ዶክተር?" "በደንብ ነዋ ፥ ራሴን የምቆጣጠር ራሴ ነኝ" አሉ ።

የሚያታልሉት እኔን ሳይሆን ራሳቸውን ነበር ። ባይታወቃቸው ነው እንጂ የሩቁንና የቅርቡን እያስላሰሉ መተከዛቸውንና መጨነቃቸውን የሚያመለክተው የተገታተረው ስራስራቸውና ጥቅርሻ የመሰለው ፊታቸው ፥ እንዲሁም እኔን - እኔን እያዩ የሚንቀዋለለው ዓይናቸው አሳጥቷቸው ነበር ።

ምሳችንን በልተን ስንጨርስ ገበታው ተነሳና ታጥበን ወደ መቀመጫችን ስንመለስ ዶክተር ገድሉ ኪሳቸው ውስጥ እጃቸውን አስገቡና አንድ የወርቅ ቀለበት አወጡ ። እናትዮዋም ጠረጴዛው ጋ ያስተካከሉት የነበረውን ዕቃ ትተው ወደ እኛ መጡና "ልጆቼ ፥ እስኪ ያሰባችሁት ይሙላላችሁ --ለሁሉም አንተ በደህና ተመለስ ገድሉዬ!" ብለው ምርቃታቸውን ሰጡ ።

ቀለበቱ የመጣው ለእኔ መሆኑ ገባኝ ። ከዚያ በፊት ዶኮተር ገድሉ እጅ ላይ አይቼው አላውቅም ።

"አዜቢና ፣ ዛሬ ይህንን ለመፈለግ ስንት ቦታ ተዟ ዟርኩ መሰለሽ" ሲሉኝ ገና የዛን ዕለት የተገዛ መሆኑን አወቅሁ ። እናትዮዋ ገና ከበር ላይ ፣ "የሄድክበት ተሳካልህ ?" ብለው የጠየቋቸውና እኔም ያልገባኝ ነገር ይኸው መሆኑንም ተረዳሁ ።

ዶክተር ገድሉ ወደ ጦር ግንባር እንዲሄዱ የታዘዙት የቤት ዕቃ እያሰናዳን ጋብቻችንን ለመፈጸም ጥቂት ቀናት ሲቀሩን ነው ። በባሕላችን መሠረት የቀለበቱ ጊዜ አልፎአል ። ቀደም ብሎ መደረግ ነበረበት ። እኛም የተውነው አስፈላጊ መስሎ ስላልታየን ነበር ። አሁን ታዲያ ቀለበት ይዘው መምጣታቸው ምን ይባላል ? - - - ማስታወሻ ጥለውልኝ ሲሄዱ አስበው ይሆን ? በግዳጅ ላይ እንዳሉ እንዳልከዳቸው ተጠራጥረው ይሆን ? የሚደ ፍረኝ ቢኖር ቀለበቱን አይቶ እንዲመለስ ይሆን ? - - እን ደቆረቆረኝ አልቀረሁም ጠየቅኳቸው ፤

" ድሮ የተውነው ቀለበት አሁን ለምን አስፈለገ?"

"ለማስታወሻነት ብቻ ነው ፣ ለሌላ እንዳይመስልሽ ፣ እኔም የአንቺን ቀለበት ወስጄ ነው የምሄደው ፣ በምሠራ በት ጊዜ ፣ በምበላበት ጊዜ - - ሁልጊዜ አንቺን ማስታ ወሻ ይሆነኛል " ካሉ በኋላ ትካዜ ስለተጫናቸው እኔን

ሳለማባባት ፊታቸውን ወደ መሬት አቀረቀሩና ፣ "ቀለበትሽን ካደረግሁኝ ምን ጊዜም ከጐኔ እንዳለሽ ሆኖ ነው የሚሰማኝ ፣ ሥራው ሁሉ እንደሚቀላጠፍልኝ አልጠራጠርም" አሉ ።

ዓይኔ እንባ አቀረረ ። በእርግጥ ሊለዩኝ መሆኑ እየቆየ ይሰማኝ ጀመር ። መሥሪያ ቤትም ከእርሳቸው ተለይቶ የምሠራው ሥራ ምን ያህል አስጠሊ እንደሚሆን ተሰማኝ ። ፈጠን ያለው አረማመዳቸው ፣ ከእኔ በስተቀር ለማንም የማይገባው ጽሑፋቸው ፣ ትብብርን የሚጠይቀው አነጋገራቸው -- ሁሉም ፊቴ ላይ ድቅን አለብኝ ። ሳላውቀው እንባዬ ጠብ - ጠብ አለ ። እናትዮዋም እኔኑ ተከትለው ያነቡ ጀመር ።

ዶክተር በይቅርታዊ አነጋገር ፣ "እረፊ እንጂ አዜብ ፣ ምን ዓይነቱ ደካማነት ነው ?" አሉኝና ፀጉሬን ወደኋላ መለስ እያደረጉ እያሻሹልኝ እንደ ሕፃን ልጅ ማባበል ያዙ ። "መባባትና ማልቀስ መች በሕፃንነት ብቻ ይወሰናል ፣ ይልቅ ብዙ ነገር ባየነው በእኛ አይብስም ? --"

እናትዮዋ ነሸጥ አድርጓአቸው ተሳቡና እንባቸውን እየጠራረጉ ፣ "ምናልባት አሁን ተረሳና ነው እንጂ ጥንት አባቶቻችን የሚኖሩት በዱር በገደሉ እየተዘዋወሩ ---- አልነበረም ። ድንበርን ማስከበርም ከእነሱ ወዲያ ነው ። ግድ የለም ፣ ብቻ ይቅናችሁና ድል አድርጋችሁ ተመለሱ " አሉ ።

እውነት ከልብ የመነጨ ጥንካሬ ይሆን? በፊትማ እኔም ጠንካራ ነበርኩ። አሁን ማፍቀሬ አደከመኝ እንጂ፣ ወንድንስ ቢሆን መች ይህን ያህል ጉዳዩ እለው ነበር?

ዶክተር ገድሉ ግራ እጄን ሳብ አደረጉና፣ "ቀለበትሽን ልውሰደዋ?" አሉኝ። "ለእርስዎ ከጠቀመዎት ምን ቅር ሊለኝ" አልኩና አውልቀው እንዲወስዱት አመቻችቼ ሰጠኋቸው። ቀለበቱን ያሠራሁት ትምህርቴን ጨርሼ ሥራ በያዝኩ በሶስተኛው ወሬ ነበር።

ቀለበቷን ከእጃቸው ተቀብዬ ከጣታቸው ሳጠልቅላቸው በፈገግታ ትክ ብለው ተመለከቷት። ያሠራሁት በስሜ ስለነበር በላይዋ ላይ የተቀረፀውን የስሜን የመጀመሪያ ፊደል "አ"ን ለማየት እያሿሿሩ። እኔም ስመለከታት እኔ ጣት ላይ የነበረች ሳይሆን አዲስ ቀለበት መሰለችኝ። ዶክተር ገድሉ ከዚያ በፊት ቀለበት አድርገው ስለማያውቁ ይህችው የእኔ ቀለበት ለጣታቸው ልዩ ድምቀት ሰጠቻቸው።

እሳቸውም በተራቸው ያመጡትን ቀለበት ሊያጠልቁልኝ ጣቴን ሳብ ሲያደርጉ "መጨረሻውን ያሳምረዋ!" የሚል ቃል ከእናትዮዋ ተሰነዘረ።

ዶክተር ደግሞ "ለዚህ ምን ጥርጥር አለው" ብለው በቀለበት ጣቴ ላይ ሊያጠልቁልኝ ሲሞክሩ ቀለበቱ በአ

ጋጣሚና በማምት የተገዛ ስለነበር ሰፋና ውልቅ ውልቅ ማለት ጀመረ ። ወፈር በሚለው የመሐል ጣቴ ላይ ማጥ ለቅ ግድ ሆነ ። ይህ ሁኔታ እኔንም ሆነ ዶክተር ገድሉን ቅር አላሰኘንም ። እናትዮዋ ግን በጣም እንደከፋቸው ለሙግለጽ ፊታቸውን አጨማደዱትና ፣ " አይ ገድሉ፣ የልጅ ሥራ ሠራህ - - " አሏቸው ።

ዶክተር ገድሉም ነገሩ ስለገባቸው " አአይ፣ ምንም አይደል " በሚል አጭር መልስ ዘጋቸውና ወደእኔ ዘወር ብለው የእናትዮዋ ቅሬታ ምን ላይ እንደሆነ በእንግሊዝኛ ነገሩኝ ። በእናትዮዋ አመለካከት ቀለበት የተለመደው ጣት ላይ ካልተደረገ እጮኛነቱ አስተማማኝ እንዳልሆነ ሆኖ ነው የሚታያቸው ።

ከልኩ ለማያልፍ ነገር ማውጣት ማውረዱ ምንም እነደማይጠቅመኝ ተረዳሁ ። ወደ ጦር ግንባር የሚጓዙትም የኔው ዶክተር ገድሉ ብቻ ሳይሆኑ አያሌ ሰዎች በመሆናቸውና በሀገር አንፃርም ማየው የርሣቸው መሄድ የሚያስገኘውን ድጋፍ አሰላሰልኩ ------ ልቤ መጽናናት ጀመረ ። ብዙውም ልጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ጥለው እንደሚሄዱ ገመትኩ ። የእኔና የዶክተር ግዴለሽነቴንም ለማሳየት ትክሻየን ነቅነቅ አደረግሁና፣ "በርስዎ አልተጀመረ " አልኳቸው ። ከእኔ አልፌ ለእርሳቸውም ከፍተኛ ጥንካሬ ሰጠኋቸው ። ከመሥሪያ ቤታችንና ከአካባቢያ

ችን የዘመቱትን ሰዎች ስምና የቤተሰቦቻቸውን ሁኔታ እያነሳን ከእኛ ጋር በማነጻጸር ፍጹም ጥንካሬ አገኘን ።

እናቲቱ በመሀል ጣልቃ እየገቡ " በጣሊያን ጊዜ " የነበረውን የጦርነት ሁኔታና ሟቹ ባለቤታቸው የዘመቱባቸውን የጦር ሜዳዎች ፣ በአጠቃላይም ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠላት ላይ የተጐናጸፋቸውን አኩሪ ድሎች በሰፊው አጫወቱን ። በቤት ውስጥ ይህ ነው የማይባል ጥንካሬ ሰፈነ ። ታዲያ ምን ይሆናል ፣ እስከመ ጨረሻው እንዲሁ አልገፋንበትም ። ዶክተር ገድሉ ከጦር ሜዳ እስኪመለሱ ድረስ ለትዳራችን የሚያስፈልጉንን ነገሮች በሙሉ አሟልቼ እንደምጠብቃቸው ቃል ኪዳን ስገባላቸው አንድ ነገር ትውስ አለኝና "ለመሆኑ መቼ ይመለሱ ይመስልዎታል ? " ብዬ ጠየኳቸው ።

"እንዴት ላውቀው እችላለሁ አዜቢና" አሉኝና በትካዜ እየተመለከቱኝ " የጦር ሜዳ ጉዳይ እኮ መመ ለስንም ሌላውንም የያዘ ነው " አሉ ።

መልሱን ራሴ እያወቅሁ መጠየቄ ለምን እንደሆነ አልገባኝም ። ለመረበሽ ካልሆነ በስተቀር ፤ ጭራሽ እንደ ዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ምን አመጣው ? የጦር ሜዳ እን ደሆነ የጊዜ ገደብ የሚሰጥ ነገር አይደለም ። "በዚህ ጊዜ እመለሳለሁ " ማለት አይቻልም ። መመለስ የሚቻለው

ጦርነቱ አልቆ ሀገር ሲረጋጋ ብቻ ነው ። ይህንንም የሚ ያገኝ የታደለ ነው ። እዚያው ወድቆ መቀረትስ አለ አይደለ?

ይህንን ጥያቄ በማንሳቴ በጥንካሬ የተሞላውን ቤት እንደገና ትካዜ ውስጥ እንዲገባ አደረገው ። ዶክተ ርም ፣ "ወድቆ መቅረት" የሚለውን ቃል ሲጠቅሱ ስላ ልፈለጉ እንጂያው በደፈናው "ሁመለስንም ፣ ሌላውንም" ብለው አለፉት ። በዚህ ጊዜ ነበር ፊታችን በትካዜ ተሸ ፍኖ ስለ "ሞት" ማሰባችንን በግልጽ የሚያሳየው ።

--ሞት እንደሆን ለማንም አይቀርም ። ሆኖም "ደ ህና ሁኑ" እያሉ እየተሳሳሙ ተለያይቶ መቅረት ምንኛ ሰውነት ይረብሻል? ለዚህ ሁሉ መንስኤ የሆነው "ጦር ነት" ከምድረ ገጽ የሚጠፋበት ጊዜ መቼ ይሆን? ሰው ሰውን የሚያጠቃበት ፣ ሰው ከሰው ጋር የሚቧጨቅበት ነገር ሁሉ ቀርቶ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ተፋቅሮ ፣ እኩል ሠርቶ ፣ እኩል በልቶ ፣ የሚኖርበት ጊዜ መቼ ይሆን? በዓለም ላይ ሰላም ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት ፣ ሰፍኖ እስከፊው ጦርነት የሚቀርበት ጊዜ ርቀቱ ምን ያህል ይሆን?—— በልቤ ብዙ ሀሳብ ተመላለሰብኝ ።

ከቀትር በኋላ ሥራ ሳልገባ ዋልኩ ፣ ብገባም ልቤ እየተንጠለጠለ ምንም ዓይነት ሥራ እንደማልሠራ ስለ ማውቅ እንደኛዎን ሸኝቼ ከጨረስኩ በኋላ ቁርጡን አውቄ እሠራለሁ ብዬ ነው ።

አንዲሁ የቅርብ የሩቁን እያነሳን ስንጫወት እንደ ስንደሰት ፣ እንደም ስንተክዝ ጊዜው መምሸት ያዘ ። ወላጆቼ እንዳይሰጉ ስልክ ደውዬ ነገርኳቸውና እዚያው አድሬ ጠዋት ልሸኛቸው ወሰንኩ ። በምሽቱም አንዳንድ ዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው መጥተው “ ደህና ተመ ለሱ ” እያሉ ተሰናበቷቸው ። እኔም የዶክተር ገድሉ መሆኔን ለብዙ ሰዎች ያስመረቅኩት ያን ዕለት ነበር ።

ሌሊቱም ነጋና ዶክተር ገድሉ የጉዞ ሻንጣቸውን ይዘው ተነሱ ። የመሥሪያ ቤት ጓደኛቸው እስከ መንቀሳ ቀሻው ሥፍራ ድረስ ለመሸኘት በጥዋት መኪናውን ይዞ ከተፍ አለ ።

“ እንግዲህ ምን ቀረኝ አዜቢና ? ሁሉንም ነገር ሻን ጣዬ ውስጥ ከተሽልኝ የለ ? ”

“እዎ ሁሉም ገብቷል ምንም የቀረ ነገር የለም”

ወደ መኪናው እያመለከቱ “ይኸውልሽ ዶክተር ፍስሀ ጥብቅ ጓደኛዬ ነው ። የሚቸግርሽን ነገር ሁሉ ይረዳሻል ፣ ልክ እንደወንድምሽ ተመልከቺው ” ካሉ በኋላ እንድንተዋወቅ አደረጉ ።

እናትዮዋ ጋቢያቸውን ለብሰው እስከ መንቀሳቀሻው ሥፍራ ድረስ አብሬ መሄድ አለብኝ ብለው ተነስተ ዋል ። ዶክተር ገድሉ ደግሞ ማንም ሰው እንዲከተ ላቸው ስላልፈለጉ ከዚያው ለመሰናበት “ ደህና ሁኚ ”

እያሉ ሳሙአቸው ፥ ወደ እኔም መጥተው ጒንጭና ጉን ጩን እያገላበጡ ሳሙኝ ። እንባዬ ቢተናነቀኝም ቅሉ ከንፈሬን ነክሼ እንደ ምንም ጠንክሬ ያዝኩት ። እናትዮዋ ግን እየተንሰቀሰቁ ያነቡት ጀመር ።

በዚህ ጊዜ ነው ዶክተር ገድሉ ቆጣ ብለው ፥ “እን ዲህ መሆን ምንድነው ? አዜብን አታያትም እንዴ ፥ አንቺ ይልቅ ከእሱዋ የተሻልሽ መሆን አለብሽ ። ብዙ ነገር ያሳለፍሽ ሰው ነሽ ። ወልደሻል ፥ ከብደሻል ፥ ደስታ ውንም ስቃዩንም አሳልፈሻል ። አሁን አዲስ መሆን ምን ድነው? ለዚያውስ ደግሞ የሕክምና ሙግሪያ ይገኘ ለም ሄደው ነው እንዴ የምታለቅሺው ? በዚህ ዓይነትማ ልጆ ቻቸውን ጠብመንጃ እያስያዙ የሚሸኙ እናቶች እንዴት ይሁኑ ፥ ጦርነቱ ረኸምና ከባድ ከሆነ አንቺም ሳትቀሪ ጠብመንጃ ይዘሽ መነሳት አለብሽ ፥ በእኔ ብቻ አያበቃም” ያሉት ።

ዶክተር ገድሉም ቢሆን ይህን ያህል የሚያደፋፍ ሩት ሁሉንም ነገር በሆዳቸው አምቀው ይዘው ነው እንጂ መለያየት ምንኛ ሆድን እንደሚያባባ ሳያውቁት ቀርተው አይደለም ።

በመጨረሻም ሁላችንንም ተሰናብተው ወደ መኪ ናው ሲገቡ በናፍቆት አንጋገር ፥ “እንግዲህ ደህና ሁኑ ገዶ ! ” አልኳቸው ።

"ገዴ" ማለቱ ለእሳቸውም ገርሞአቸው እንደገና ወደኋላ ዘወር አሉና እያዩኝ ፣ "ግድ የለም ፣ ከጦር ሜዳ ስመለስ በደንብ እያቆላመጥሽ ትጠሪኛለሽ ፣ ይህንን "አንቱ" ማለትሽንም ትተሽ እንደምትጠብቂኝ አል ጠራጠርም" አሉኝ ።

ለእኔውም ገረመኝ ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ አቆላምጬ ጠርቼአቸው አላውቅም ። ያን ዕለት ግን አፌ ላይ ምን እንዳመጣልኝ አልገባኝም ። አንድ ቀን እንኳ አቆላምጬ ጠርቻቸው ቢለዩኝ ወደ ፊት የማይቆረቁረኝ መስሎኝ ይሆን ---

መኪናዋ ለመንቀሳቀስ ድምፅ አሰማች ። ዶክተር ፍስሃም በመስኮት በኩል አንገታቸውን ብቅ አደረጉና "ሽኝታቸው ስመለስ በዚሁ በኩል አልፋለሁ" አሉኝ ። ራሴን በመነቅነቅ እሽታዬን ገለጽኩላቸው ።

ወዲያውኑ የረሳነው ነገር ትዝ አለኝና ፈንጠር ብዬ እንደቆምኩ "ዶክተር ገድሉ የደብዳቤውስ ነገር እንዴት ነው ? እንዴት ልልክልዎት እችላለሁ ?" አልኳቸው ።

እሳቸውም "እመቺ ሁኔታ ካለ እኔ እጽፍልሻለሁ ፣ አንቺ ግን አድራሻውን ልታገኚ ስለማትችይ --- ባንቺ በኩል አይሆንም" የሚል መልስ ሰጡኝ

በትካዜ የልጃቸውን ፊት እየተመለከቱ ድንጋይ ላይ ኩርምት ብለው የተቀመጡት እናታቸው ፣ "ቤታቸው በጦርነት ፈራርሶ ካልሆነ እዚያም አገር ዘመዶች ነበሩን እኮ !" የሚል ድምፅ አሰሙ ።

ዶክተር ገድሉ የረሱት ነገር ትዝ ያላቸው ይመስል
ወደ መኪናዋ እንድጠጋ ጠሩኝና በእጃቸው አንገቴን
ይዘው በቀስታ "እንግዲህ የእናቴን ነገር አደራ ፣ እንደ
ፀባይዋ ያዥርአት ፣ ዘመዶቻችን እንደሆኑ ብዙ አይጨነ
ቁላትም" አሉኝ ።

እረስተውት ነው እንጂ ገና ከቤት ሳንወጣ ደጋግ
መው ነግረውኝ ነበር ። ለማንኛውም እዚያው ፊት ፊታ
ቸውን እያየሁ "እሺ" የሚል ድምፅ አሰማሁ ። ወዲያው
ግን እንባዬ መውረድ ጀመረ ፣ በዚያን ጊዜ ነው ዶክተር
"እኔ ነኝ ጥፋተኛ ፣ ፍስሃ እባክህ ወደፊት በል ፣ መኪና
ዋን ንዳ" ያሉት ፤ ወዲያው ተነስተው ከፊታችን የበረሩ
ሩት ፤ እኔም እናትዮዋም አይናችን አብሮ የበረረው —

እናትዮዋን አፅናንቼ ወደ ቤት ካስገባኋቸው በኋላ
የሥራ ሰዓቱ እስኪደርስ እዚያው አብሬአቸው ቆዬ
አልኩ ። ትካዜውና ናፍቆቱ ገና ያን ጊዜውን ሌላ ነገር ሆን
ብኝ ። በተይለም ለመጨረሻ ጊዜ ሲሰናበቱኝና የእናታቸ
ውን አደራ ሲነግሩኝ በመስኮቱ አንገቴን ያስገባሁ ጊዜ
የነበረው ሁኔታ ፊቴ ላይ ድቅን እያለ ማስጨነቁን ቀጠለ—

# 15

እኔ ላለሁበት ክልል በዶክተር ገድሉ ምትክ ለተቆጣ
ጣሪነት የተመደቡት ከአሁን በፊት ለጥቂት ቀናት መጥ
ተው የነበሩት ዶክተር አብርሃም ናቸው ፡፡ ምንም እንኳ ስለ
ጠባያቸውም ሆነ ትጉህ ሠራተኛ ስለመሆናቸው ወይም ስላ
ለመሆናቸው ጠንቅቄ ባላውቅም እንዲሁ ሁኔታቸው ሁሉ
ደስ አይለኝም ነበር ፡፡ አነጋገራቸው እንዳኮረፈ ሰው ብስ
ጭት የተቀላቀለበት የሚመስልና የመሳብ ችሎታ የሌለ
ለው ነው ፤ ጭራሽ የመስማት ስሜትን ይዘጋል ፡፡ ማወቅ
ብቻ ምን ዋጋ አለው? ትልቅ ነገር ዕውቀትን በጥሩ ሁኔ
ኔታ ላላወቁት መግለፅ መቻሉ ነው ፡፡ ዕድሜአቸውም
በግምት ወደ አርባ ሦስት ገደማ ይሆናል ፡፡ የሚኖሩት
ከሕግ ሚስታቸው ጋር ሲሆን ሁለት ከፍ ከፍ ያሉ ልጆ
ችም እንዳሉዋቸው ሰምቻለሁ ፡፡

ወደድኩም ጠላሁ ዶክተር ገድሉን እንደሆን አላገ
ኘሁም ፡፡ ከእኚሁ ከአዲሱ ዶክተር ጋር ሥራዬን እከና
ውን ጀመር ፡፡ ለጥቂት ሰሞን መሥሪያ ቤቱም ፣ መንገ
ዱም ፣ መኖሪያ ቤቴም ፣ ሁሉም የተራራ ያህል ከበደኝ ፤
አስጠላኝ ፡፡ ከምነቃነቅ ከምሠራ ይልቅ ተኝቼ ብውል እመ
ርጥ ጀመር ፡፡ የማይለመድ ነገር የለምና ከቀን ወደ ቀን እየ
ለመድኩት መጣሁ ፡፡ የዶክተር አብርሃምን ንጭንጭና ዘገ
ንግግርም ተላመድኩት ፡፡ ደግነቱ “ ሳይደግስ አይጣላም ”
እንደሚባለው ሁሉ የአማርኛም ሆነ የእንግሊዝኛ ጽሑ

ፈታቸው ለማንኛውም ሰው ቁልጭ ብሎ የሚነበብ ዓይነት ነበር ። እኔንም ከሚያነጋግሩኝ ይልቅ በጽሑፍ የፈለጉትን ጥለውልኝ ቢሄዱ እመርጥ ነበር ። ትብብር የሚጠይቅ ፅሁፍ እንደሆነ በዶክተር ገድሉ ጊዜ ቀርቷል ። የአሁኑ "እንዲህ አድርጊ" የሚል ትዕዛዝ ነው ።

ሕመምተኞቹን ልጐበኛቸው በገባሁ ቁጥር ስለ ዶክተር ገድሉ እያነሱ ናፍቆቴን ይቀሰቅሱብኛል ።

"ሲስተር ፣ ዶክተር ገድሉ እኮ አባታችን ነበሩ ፤ እንደ ሳቸው የሚያጽናናንና የሚያከመን አሁን ከየት እናገኛለን፣ ብቻ—ጥሎ አልጣለንም ፣ እርስዎን ያቆይልን" ሲሉኝ ያ ለዛ ያለው አፅናኝ አንደበታቸውና የሕመምተኞቹን ራስ ነካ ነካ የሚያደርጉበት እጃቸው ትውስ ይለኛል ። ታዲያ ምን ማድረግ ይቻላል? እኔም እንደጠንካራዎቹ ሆኜ "ይሂዱ እንጂ ጦር ሜዳም እኮ በጠላት ጦር እየቆሰሉ የሚወድቁት ሁሉ የእኛው ወንድሞች ናቸው ።እንዲያውም እንደ ዶክተር ገድሉ ዓይነቱን ሥራ ወዳድ ሰው ወደዚሁ ከባድ ሥራ ወዳለበት ቦታ መላኩ ትልቅ እርዳታ ነው ።" እያልኩ ሕመምተኞቹን አፅናና እገባለሁ ።

በአምስት ሰዓት አካባቢም ወደ ቢሮዬ እየሄድኩ ሻይ ማፍላቱን ተውኩት ። በሽታዬን ከመቀስቀስ ሌላ ምንም አልረዳኝም ። ገና ማንቆርቆሪያውን ሳነሳው "አዜቢና ፣ ሻይ ደረሰ?" የሚለው ጥያቄ ይናፍቀኛል ። ሱስ ሲይዘኝ እንኳ እያስገዛሁ ሆነ የምጠጣው ።

በዚህን ጊዜ ትዝታዬን የሚያስረሳኝ ይብዛም ይነስም በድርሻ ሥራዬ መጠመዴ ነበር ። ይልቁንም በጦርነቱ ያለምክንያት የሚያልቁትን ሰዎችና ቤት ንብረታቸው ወድሞባቸው መግቢያ አጥተው የሚንከራተቱትን ጭቁኖች እያስታወስኩ የኔውን ችግር ቀላል አደረግኩት ፤ ያንን በመሰለው አስከፊ ጊዜ የሁለት ፍቅረኞች መራራቅም ሆነ ሙለያየት እንደ ከባድ ነገር መቆጠር እንደሌለበት እያደር የገባኝ ።

እቤት በምገባበት ጊዜም እምብዛም ስራ አልፈታም ነበር ። መጽሐፍ ማንበብ ከፍተኛው ስራዬ ሆነ ። ቢያንስ ቢያንስ በየወሩ ሁለትና ሶስት መጽሐፍ ሳልገዛ አልቀርም ። ከዚያ በተረፈ ከመሥሪያ ቤቴም ቤተ መጻሕፍት መዋሴ አልቀረም ። ሥራ ፈትቼ የምገኘው በእንቅልፍ ላይ ስሆን ብቻ ነበር ። መጽሐፍ ለማንበብ የመጀመሪያ ጊዜዬ ባይሆንም እንኳ በዚያ ጊዜ ያገኘሁት ላቅ ያለ እውቀት ከፍተኛ ሕብረተሰባዊ አመለካከት እንዲያድርብኝ አድርጎኛል ።

የዶክተር ገድሉን እናትም ከሳምንት ሦስት ቀን ያህል እየሄድኩ እጠይቃቸዋለሁ ፤ አስፈላጊውን ርዳታና እንክብካቤም አደርግላቸዋለሁ ። በእኔ በኩል ብቻቸውን ከሚኖሩ ይልቅ አብሬአቸው ብሆን ፈቃዴ ነበር ። ሆኖም ፀባያቸው እንኳንስ ይህን ያህል ተቀራርበው ቀርቶ ሩቅ ለሩ

ቅም ሆነው የሚቻል ዓይነት አልሆነም ። የእርጅና ፀባይ ነው እንዳይባል እርጅናቸው ይህን ያህል አይደለም ። በመ ጠኑም ቢሆን "እርጅተው ተንዛዝተዋል" ከሚባሉ ሰዎች የተሻሉ ናቸው ። ነገር ግን የፀባያቸው ዓይነት ምን እን ደሆነ አይታወቅም ። ሰዎችን የሚያስደስታቸው ነገር እሳቸውን አያስደስታቸውም ። የሚፈልጉትንም ነገር ግልፅ አድርገው አይናገሩም ። በዚያ ላይ አሽሙርና ሐሜት ቋሚ ተግባራቸው ነው ። ከዘመዶቻቸው ሁሉ የተራራቁት በዚሁ ፀባያቸው እንደሆነ ዶክተር ገድሉ አጫውተውኛል ። ብቻ በአጭሩ ፣ በጣም ከተቀራረብን ልን ጣጣም ስለማንችል ተራርቆ መጠያየቁን መረጥኩ ።

16

በዚህ ሁኔታ አንድ ወር ያህል ቆየሁ ። የዶክተር ገድሉ ወሬ ግን ምኑም ምኑም የለ ። ስለጦርነቱም የሚ ወራው የጠላት ጦር ማየሉ ነበር ። ምንም ቆራጥ ነኝ ቢሉ ፣ ምን ቢደፍሩ ፣ ሃሳብና ትዝታ መች ይለቃሉ ፣ እኔም አን ዳንድ ወሬዎች በሰማሁ ቁጥር መሸጋቴና ማሰቤ አልቀ ረም ። ግን ምን ልጨምር ! ከምንስ ላድን ! ላስቻለውስ ሁሉንም ዋጥ አድርጎ መቻል መድሐኒት ነው ።

በእሁድ የእረፍት ቀኔ ከአልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ መጽሐፍ በማንበብ ላይ ሳለሁ የቀበሌአችን የቤቶች ማኅ በር ሊቀመንበር የአካባቢውን ቤቶች ለስራ ለማስወጣት

በድምፅ ማጉያ ቅስቀሳ ሲታደርግ አዳመጥኩ ። በነዚያ ሳምንታት ውስጥ በየቀበሌው ወደ ጦር ሜዳ የሚሄድ ስንቅ ማዘጋጀቱ ተጧጡፎ ስለነበር የዚሁ ዕለት ቅስቀ ሳም ለዚሁ ተግባር መሆኑ ገባኝ። ወዲያውም የስራ ሱሪ ዬን አጥልቄ ከላይ ቀለል ያለ ሸሚዝ መሳይ ደርቤ ወደ መሰብሰቢያው ስፍራ ሄድኩ ። ከቦታው ስደርስም የሴቶች ማኅበር ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ካልሆኑ በስተቀር ከኔ ቀድሞ የተገኘ ሴት አልነበረም ። ከጽሕፈት ቤቱ ሠራተ ኞች ጋር ሰላምታ ተለዋውጬ ገና ቆም ከማለቴም ከመሐ ከላቸው አንዷ ፣

"ሲስተር አዜብ ፣ ሴቶቻችን ሁሉ እንዳንቺ ሰዓት ቢያከብሩልን ስራችን ምንኛ በተቀላጠፈ ነበር" አለችኝ ።

አነጋገሯ አክብሮት የተሞላበት ከመሆኑም በላይ በሰ ዓት ያለመከበር ጉዳይ ክፉኛ መመርቀዟን ያሳይ ነበር ። በወቅቱ ግን የሰጠኋት አስተያየት "ምን ይደረግ ትያለሽ ጓዲት ፣ እንደሚታወቀው በቁጥር የበዙ ሴቶቻችን በቤት ውስጥ አሰልቺ ስራ የተጠመዱ ናቸው ። ሕፃናት ማሳደ ጉም የእነሱው ሥራ ነው ። ስለዚህ እንደኛ ቀልጠፍ ብለው መውጣቱ ላይሳካላቸው ይችላል ።" የሚል ነበር ።

ሌላዋ የማኅበሩ አባል ደግሞ በዚሁ ላይ አስተያየ ቷን አከለችበት " በእርግጥ ይህ የተናገርሽው ችግር በብዙ ሴቶች ላይ ያለ ነው ።

ሊቃለል የሚችለውም በእኛው የጠነከረ ትግል ነው ። ነገር ግን ለሰዓት ያለመከበር ምክንያቱ ይሄ ብቻ አይደ ለም ። ካለፈው ስርዓት የተወረሰ ግዴለሽነትና ዝርክርክ ነትም አለ ። ይህን በከፍተኛ ደረጃ መዋጋት ይኖርብናል።"

"በሉ እሺ የሚሰራውን ስራ እኛው እንጀምረዋ፣ ስለሥራ ሰዓት ያለመከበር እያወጋን እኛምኮ በወሬ ጊዜውን ገደልነው" ከማለቴ ሁሉም ወደኋላቸው መለስ ብለው በየክፍሉ ተፍ ተፍ ማለታቸውን ቀጠሉ ።

ከማኅበሩ ዕቃ ክፍል ውስጥ እህሉን በማውጣት የሚ ወቀጠውንና የሚሸከሸከውን ወደሚጻ ፣ የሚታመሰው ውንና የሚቆላውን ደግሞ በጊዜያዊነት ወደ ተሰራው ዳስ ውስጥ በማመላለስ ላይ እንዳለን ሴቶቹ ጠብ ጠብ እያሉ መምጣት ጀመሩ ። ከፊሎቹ ሙቀጫ የተሸከሙ ወንዶችን አስቀድመዋል ። አንዳንዶቹ ደግሞ መቁያና ብረት ምጣድ የመሳሰሉትን ዕቃዎች ይዘዋል ። ከግቢው እንደደረሱም ከፊሎቹን ወደ ዳስ ውስጥ ሥራ የተቀሩትንም ለወቀጣና ለማበጠር ሥራ ወደ ሚጻ ድልድሉ ከተካሄደ በኋላ ሁሉም በየረድፉ ሥራውን ማከናወን ጀመሩ ። እኔም ያለ እረ ፍት እህል የማመላለሱን፣ የመውቀጡንና የማበጠሩን ሥራ ሳሂካድ ቆይቼ ድካም ስለተሰማኝ አንድ አፍታ እረፍ አልኩና ወገቤን ይዤ የሥራውን ትርኢት እመለከት ጀመር ።

ከፊሉ ይወቅጣል ፣ ከፊሉ ያበጥራል ፣ ገና ተራ ያልደ ረሰው ደግሞ ቆሞ በማጨብጨብ ድጋፍ ይሰጣል ። ጭብ ጨባው "እሸነፈች ፣ እሸነፈ ፣ "በሚለው ዜማ እዘል እን ጋር የተቀነባበረ ስለነበር ወቃጮቹ ከስሜት ብዛት የሚ ሸከሸከውን ሳያደቁትም አልቀሩም ። ሕፃናት በአካባቢው ተገኝተው ይንጫጫሉ ፣ ይሯሯጣሉ ። እናቶቻቸው እግር ስር እየገቡ ፣ "እንቺ እማዬ እስጥይኝ ፣ ይሄ እንትና ሊማ ታ ነው" ይላሉ ። የሥራ ዘመቻቸው አላማ የገባቸውና በሰል ያሉት ደግሞ ለዘማቹ ሠራዊት የተዘመሩ አንዳንድ ሕዝባዊ ዜማዎችን ያሰማሉ ። በዚያን ላይ ደግሞ መወራ ረፍና መቃለዱ ራሱ ለሚዳው ድምቀት ሰጥቶታል ። በእድሜ ገፋ ያሉትና ከቤት የማይውሉ ሴቶች ከመሥሪያ ቤት የሚውሉ ሲቶችን ስም ይጠሩና "ነይ እስኪ ዘንዘና ውን ጨብጪው ፣ ሥራ ማለት እስክርቢቶ መያዝ ብቻ መሰለሽ "እያሉ ይቀልዱባቸዋል ። ጥቂት ወቅጣ እጇዋ የሚቆስል ስትገኝማ ደንበኛ መቀለጃ ትሆናለች ።

ታዲያ ይህን ሁሉ ትርኢት የሚመለከት ሰው በሃ ሳብ መርከብ ወደ ጦር ሜዳ ቢጓዝ ምን ይፈረድበታል ––

"ሲስተር አዜብ ፣ እስቲ ወገብሽን ለቀቅ አድርጊና ስፌዱን አቅርቢልን ፣ ይሄ ነገር ወደ መድቀቁ ነው" የሚል ቀልድ አዘል ንግግር በቅርቤ ይወቅጡ ከነበ ሩት ሴትዮ አፍ ሲወጣ ልክ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ከተዘፈቅሁበት የሃሳብ ባሕር ወጥቼ ሥራውን ቀጠልኩ ።

እንደታዘዝኩትም ኀፈዱን አቅርቤ የደቀቀውን እህል ካወጣሁ በኋላ ወደ ዱቄት መገልበጫው ይዤ ሄድኩ ።

መቼም ሰው በተሰበሰበበት ወሬ አይጠፋም ። የወቀጣው ሥራ ጋብ እንዳለ የሚቆላ ጥሬ ለማቀበል ወደ ዳሱ ውስጥ እንገቴን ሰደድ ከማድረጌ በአንድነት ተሰብ ስበው የሚሰሩ ሴቶች ወደ ጦር ሜዳ ስለዘመቱ ሰዎች ሲያ ወሩ መርዶአቸው ለዘመዶቻቸው ስለደረሰና ለሕክምና ስለመጡት ዘማቾች እንዲሁም ስለጦርነቱ እየከፋ መም ጣት ሲጫዋወቱ ቆዩና ወደ ጦር ሜዳ ከሄደ ሰው ጋር በስልክ መገናኘት እንደሚቻልም ሰማሁ ። ጉዳዩ ፥ ስለ ሆነ ፥ ማዳመጡን አቆምሁና ጠጋ ብዬ መንገዱን እንዲ ጠቁሙኝ ጠየቅኋቸው ።

ሴቶቹም ረጋ ብለው ወደ ጦር ሜዳው ለሥራ አገል ግሎት የሄዱትን ሰዎች ለምሳሌም እንደ መንገድ ሥራ ሠራተኞች ፥ ሐኪሞች፥ ጋዜጠኞች የመሳሰሉትን ፥ በአጠቃ ላይ ከተዋጊው ሠራዊት ጎን ቆመው የተለያዩ እርዳታ ዎች የሚያደርጉትን ሁሉ ፥ ከጦር ሜዳው ወደ ከተማው እየተመላለሱ አንዳንድ ዕቃዎችን ስለሚወስዱ ፥ በዚሁ አጋ ጣሚ በስልክ መገናኘት እንደሚቻል አስረዱኝ ። ይህን ማድረግ የሚቻለውም ሙጀመሪያ እተንቀሳቀሱበት ሥፍራ በመሄድ መሆኑን አረጋገጥኩ ።

# 17

ነገሩ እርግጠኛ ነበር ። ወደማንቀሳቀሻው ቦታ ሄድሁ ። ከቦታው እንደደረስኩም ብዙ ሰዎች አሰፍስፈው ተራቸውን ሲጠባበቁ አየሁ ። በስልክ ውስጥ ተገናኝተው የሚሳሳሙ ይመስል ህፃን ልጆቻቸውን ሳይቀር ይዘው መጥተዋል ። በስልክ ለመነጋገር የሚፈቀደው ለአንድ ሰው ብቻ መሆኑ ቢታወቅም አነጋጋሪውን በማጀብ ከእያንዳንዱ ቤት ከሰባት እስከ ዘጠኝ ያህል ሰዎች መጥተዋል ።

እንደኔ ነጠላቸውን የመጡ ቢኖሩ በጣም ጥቂት ናቸው ። ወታደሮቹ ተራ ጠባቂዎቹን ስነ ስርዓት ለማስያዝ ወዲያ ወዲህ ይሯሯጣሉ ። ተራዬን ይዤ ተሰለፍሁ ። ቆመን በምንጠብቅበት ወቅት ወደ ስልከኛው ሄደው ዕድላቸውን ሞክረው የሚመለሱትን “እንዴት ሆናችሁ ? ተገናኛችሁ”? እያልን መጠየቃችን አልቀረም ። የግማሾቹ ፊት ፈገግ ብሎ እየተሳሳቁና እያወሩ ይሄዳሉ ። እንዳንዶቹ ደግሞ በትካዜ ተመስጠው ይመለሳሉ ። እንዲህ ዓይነቶቹ የሚፈልጉትን ዘመድ ሳያገኙ የቀሩ መሆን አለባቸው ። ከነርሱ አልፎ የሌላውንም ሆድ ያንቦጫቡጫሉ ። በተስፋ ተራውን የሚጠብቀው ሕዝብ በትካዜ የሚመለሱትን በሚመለከትበት ጊዜ ስለራሱም መጣ

ኙት ይጠራጠርና ለአንድ አፍታ ይተክዛል ። ወዲያው ደግሞ መገናኘታቸውን ለመግለጽ እየሳቁና እየተደሰቱ የሚወጡትን ሲመለከት የሁሉም ፊት ይፈካል ። "አገ ኛለሁ" የሚል ተስፋም ያድርበታል ። በአጠቃላይ ልክ እንደ ሎተሪ ዕድልን መጠበቅ ሆነ ። በስልክ የሚያገናኘ ውም ሠራተኛ ከድካሙና ከፍጥነቱ የተነሳ ላቡ በሰው ነቱ ላይ ይንጠፈጠፋል ። የዚያን ዕለት መቼም የእሱን ቦታ ያልተመኘው የለም ። እንኳን ማላብ ቀርቶ ያለ ደመወዝም ሥራ ቢባል እዚያ ቦታ ከተሰበሰበው ውስጥ እምቢ የሚል ያለ አይመስለኝ ። ተራዬ ሊደርስ ስድስት ሰዎች ያህል ሲቀሩኝ የሚያሳዝን ነገር ተመለከትኩ ። አንድ ጠና ያሉ ቤትዮ ተራቸውን ከጨረሱ በኋላ የስ ልክ መነጋገሪያውን ሥፍራ አለቅም ብለው ቆሙ ፣ የሚ ፈልጉትን ሰው ሳያገኙ የቀሩ መሆናቸውንና መበሳጨታ ቸውን ለማወቅ ቀላል ነበር ። በአካባቢው ያሉት ሠራ ተኞችም "እባክዎት ለተረኞች ይልቀቁ" እያሉ ደጋግ መው ሲናገሩ ሰማሁ ። ቤትዮዋ ግን ጭራሽ እንባቸውን እያጎረፉ የመነጋገሪያውን ሥፍራ አለቅም ብለው ቆሙ ። በመጨረሻ ከሥነ ሥርዓት አስከባሪዎች አንዱ እየተን ደረደረ መጥቶ "ቦታውን ልቀቂ!" አላቸውና ገፍተር ሲያደርጋቸው ሁለቱን ደረጃ ተንከባለው ወደቁ ። ከዚያ በኋላማ ያለው የለቅሶ ነገር አይነገርም ። ሥነ ሥርዓት አስከባሪው አገፈታተሩ ይህን ያህል ለጉዳት ይሰጣል

ብሎ ስላልገመተ መውደቃቸውን በተመለከተ ጊዜ ከመ ጠን በላይ ደነገጠ ። እኔም የቤትየዋ ነገር በጣም አሳ ዘነኝና "ምን ክፉው ነው ? ቤት ልጅ እንዴት እንደዚህ ይገፈትራል ?" በማለት በሃዘን ስሜት ተናገርኩ ። ከፊቴ የተሰለፈችው ቤትዮዋም ስለሰማችኝ ፊቷን ወደ እኔ ሳታ ዞር በፊት እንደነበረችው ሆና "ዋ ልጄ ! ስዎቹስ ቢሆኑ መች እንዳሏቸው ይሆናሉ ብለሽ ነው ? ሠራተኞቹም ሊመረሩ ይገባል" አለች በቁጣ ቃል ፤ "ታዲያ የአሁኑ ሥራ ልክ ነው ?" አልኩ "እይ እሱማ —" አለችና ንግግሩን ሳትጨርስ አቋረጠችው ። በእርግጥ ሠራተኞቹ ብዙ ችግር ይገጥማቸዋል ። አብሶም እንዲህ ዓይነቱ ብዙ ሕዝብ የተሰበሰበበት ቦታ መላቅጡ የጠፋና የሚያስመ ርር መሆኑ ግልጽ ነው ። ታዲያ ምንስ ቢሆን እኒህን ዓይ ነት ቤትዮ መገፍተር ይገባል ? የዘማች እናት በመሆናቸው እንኳ ሊከበሩ አይገባቸውም? መቼም ጥፋታቸው ሁሉ ከመሐይምነትና ከአላዋቂነት የመጣ ነው ። ስልኩንም አንቀው ይዘው አልለቅም ያሉት ከመቆየት ብዛት የሚ ገናኙ መስሏቸው ይሆናል ። ስለሚቀጥሉት ተረኞች አለ ማሰባቸውም ቢሆን ከንቃተ ሕሊናቸው ዝቅተኝነት የመጣ መሆኑ አያጠራጥርም ። ይህን ሁሉ በማስተዋል ከመገፍተር ይልቅ ቀስ ብሎ በትህትና ቦታውን ማስለቀቅ ይቀል ነበር ። የስልኩን መነጋገሪያ መቀማትም ይቻላል ። ምንም ይሁን ምንም እኒህን የስንቶች እናት የሚሆኑ ቤትዮ መገፍተሩ ትልቅ ስህተት ነው ። እንዲህ ዓይነት

ቦታ የሚሰማሩ ሠራተኞችም ከሥራው በፊት ትህትናን ፣ አክብሮትን ፣ ማስተናገድን መማር አለባቸው ።

ከመበሳጨቱ የተነሳ እንዲህ ዓይነቱን ሃሣብ በሆዴ ውስጥ ሳመላልስ ቆየሁ ። ሴትዮዋንም ሰዎች ደጋግፈው አነሷቸውና "በሌላ ጊዜ ሊገናኙ ይችላሉ ተበሳጩ ፣ አትቆረጡ" በማለት እያጽናኗቸው ወደ ቤታቸው ይዘዋቸው ሄዱ ። ተራው እየተቃረበ መጥቶ ከእኔ ፊት ያለችው ሴትዮ ወደ ስልኩ ሄደች ። የምቀጥለው እኔው መሆኔ ነው ። ልቤ እንደ መደንገጥም እንደ መደሰትም እያለ ትርታው እየጨመረ መጣ ። ከፊቴ የነበረችው ሴትዮ የምትፈልገውን ሰው ተገናኝታ ወሬዋን በሠፊው ዘረጋች ። እንዴት ዕድለኛ ናት ። ሠራተኞቹም ሳይቸገሩ በቀላሉ መገናኘት የቻለችው እሷ ሳትሆን አትቀርም ። በስልክ የምታነጋግረው ዘማች በግ ምት ባሏ መሰለኝ ። እሱ የሚናገረውን መስማት ባልች ልም ከሷ መልስና ጥያቄ ለመረዳት ችያለሁ ። ስለቤቷ ፣ ስለ ኑሮዋ ፣ ስለልጆቿ በደንብ ትዘረዝርለታለች ። አጠገቧም የነበሩት ሁለቱ ልጆቿ በምትነጋገርበት ጊዜ በደስታ ፈን ድቀው ስልኩን ሊቀሟት ምንም አልቀራቸውም ። የእና ታቸውን ዓይን ዓይን እየተመለከቱ በማስተዛዘን "እማማ እኛስ፣ እኛም እናነጋግረው" እያሉ ይወተውቷት ጀመር ። እሷም ይህን ለማድረግ ፈቃድዋ ቢሆንም ሠራተኞቹ ይቆጣሉ ብላ በመፍራት በዓይኗ ልመናዋን አቀረበች ፣

ሠራተኞቹም ሁኔታዋን በማየት ፈቃዳቸውን ገለጹላት ። ልጆቹ እየፈነደቁ ወደ ስልኩ መነጋገሪያ ተጠጉ ። ትናንሾች ቢሆኑም ብልጣ ብልጦች ይመስላሉ ። ሁሉ ቱም በተራ በተራ መነጋገሪያውን በሁለት እጃቸው እየያዙ "አባባ ፣ እንደምነህ —? ቻው" የሚለውን ቃል ካሰሙ በኋላ ቶሎ መነጋገሪያውን ለቀቁ ። አነስተኛው ልጅ የረሳው ነገር ትዝ አለውና እንደገና ሠራተኛ ውን በመለመን መነጋገሪያውን ከያዘ በኋላ "አባባ መቼ ትመጣለህ? " የሚል ጥያቄ አቀረበ ። አባትየው ምን እን ደመለሰለት እንጃ ፣ እኔ ግን ይህንን ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ ሆዴ ባባ ። አንዳንዴም ልጅነት ጥሩ ነው ብዬ ገመ ትኩ ። ጦር ሜዳ የሄደን ሰው መቼ ትመጣለህ ብሎ መጠ የቁ ልጅ በመሆኑ አይደለ ፣ ወጺያው እናትዬዋና ልጆቹ ተያይዘው እየተደሰቱና እየሳቁ ወደ ቤታቸው አመሩ ።

እኔም ተራዬን ወደ መነጋገሪያው ተጠጋሁ ፤ የምፈ ልገውን ሰውና ሙያውንም መስመር ለሚፈልገው ሠራ ተኛ ገለጽኩለት ። ሰውየውም መስመሩን በመፈለግ ጥቂ ት ከደከመ በኋላ ተስፋ በመቁረጥ ዓይነት "እባክዎት የሚቀበል ሰው የለም "አለኝ ።

"ታዲያ እንዴት ላድርግ ? ምንም ሌላ መገናኛ መን ገድ የለም? " አልኩትና በትካዜ ዓይን ዓይኑን ተመለከ

ትኩት "እስቲ እርስዎ ይሞክሩ" አለና የስልክ መነጋገሪ ያውን ሰጠኝ ።

ስልኩ የጥሪ ድወሉን ያሰማል ። ልቤም ከአሁን አሁን አነሱት በሚል ግምት ትር ትር ይላል ። ነገር ግን የሚያነ ሳው ሰው አልተገኘም ። ለጥቂት ጊዜ እንዲሁ ይገፍ ቆየሁ ። ሥነ ሥርዓት አስከባሪው ትክ ብሎ ሲመለከተኝ ፈራሁት። "በቃሽ ቦታውን ልቀቂ" ይለኛል የሚል ሥጋት ያዘኝ ። ከዚህ ንግግር እንዲቀጠብ ያባበልኩት እየመሰለኝ በሃዘ ዘንና በትካዜ ተመስጬ ይቅርታ በተሞላበት አቀራረብ ዓይን ዓይኑን ተመለከትኩ ። እሱም ፣ ኃዘኔ ተሰምቶትም ይሁን በሌላ ምክንያት ሳይቆጣ ቀረ ። እስከመጨረሻው ዝም ብሎ ተመለከተኝ ። ታዲያ ምን ይሆናል ስልኩ ጠርቶ የሚያነሳው ስላጣ ጥሪውን አቆመ ። ያን ጊዜ ልቤ ምን ያህል እርር ድብን እንዳለ በቃላት መግለጽ አልች ልም ። ምን ልፈጥር እንደሆን እንጃ ፣ ስልኩ መጥራት ካቆመ በኋላም አለቀቅሁትም ። የሌሎቹን ተራ ከማቃጠል ሌላ ምንም የማገኘው ነገር አልነበረም ። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ደግሞ ከእኔ የሚጠበቅ አልነበረም ። ይህን ሁሉ ሕሊናዬ ቢያውቀውም መነጋገሪያውን ለመልቀቅ እጄ አልደፍር አለ ። ስልኩ ለእኔ ሲል እንደገና መጥራቱን የሚቀጥል መስሎ ታየኝ ። መቼም እንደያዝኩት መኖር አልችልምና የኋላ ኋላ ሳልወድ በግዴ መነጋገሪያውን አስ ረከብኩ ። ሠራተኞቹም ብዙ ታግሰውኛል ። በሚቻላቸ ቸው መጠን ረድተውኛል ።

ከመሐከላቸው አንዱ "ከወዲያ ይጠራ ነበር?" ሲል ጠየቀኝ "እዎ ለብዙ ጊዜ ጠርቷል ። ግን የሚያነሳው አላ ገኝሁም" አልኩ "እንግዲያው ትንሽ ይጠብቁ ፤ ከሁ ለት ሰዎች በኋላ እንደገና ደውለው ይሞክራሉ" አለኝ ።

በእውነቱ ይህ ሰው ለዘለዓለሙ ከልቤ የማይወጣ ባለውለታዬ ነው ። ተስፋ ቆርጬ ዝም ብዬ ብሄድማ ጭንቀቱና ሃሳቡ በየት በኩል ያስቀምጠኝ ኑሯል ?

"እሺ በምን ዕድሌ" አልኩና እጠባበቅ ጀመር ። እዚ ያው ቆሜ ሦስት ሰዎች የሚፈልጓቸውን እያገኙ ተነጋግ ረው ሄዱ ። አራተኛዋ ግን የእኔው ዕጣ ደረሳት ። እንዲ ያውም የእኔ የተሻለ ነው ። የእሷ ጭራሽ ስልኩም አይ ጠራ ፤ መስመሩም ሳይበላሽ አልቀረም ። የምትፈልገው ባለቤቷን ሲሆን የዘመተውም በመንገድ ሥራ ድርጅት በኩል መሆኑን ለሠራተኛው ስትገልጽ ሰማሁ ። ሠራ ተኛውም ብዙ ደከመላት ። ነገር ግን ጭራሽ ቦታው ሊገኝ አልቻለም ። እሷም እየተከዘች ወደ ቤቷ ከማም ራት ሌላ ምንም አማራጭ አላገኘችም ። "እስቲ እርስዎ ይሞጡ" ተባልኩና እንደገና ለመሞከር ወደ መነጋገሪ ያው ተጠጋሁ ። አሁንም ስልኩ ጥሪውን ቀጠለ ። የእኔም ልብ ትርታ የዚያን ያህል ሆነ ። ሦስት ጊዜ እንደ ደወለ (ጥሪውን እንዳሰማ) ተቀባይ አገኘሁ ። መንፈሴ በመጠኑ

እረፍት አገኘ ። ስልኩን የተቀበለኝ ወጣት የጤና መኰንን ነበር ።

“ ሃሎ ፣ ዶክተር ገድሉን ታቀርብልኛለህ?”

“ ዶክተር ገድሉ የሉም ። ራቅ ወዳለ ሥፍራ ሄደዋል”

“ ብጠብቅ ላገኛቸው አልችልም ?”

“ አይመስለኝም ፣ ከሦስት ቀን በፊት እዚሁ ነበሩ ። አሁን ግን ለከፍተኛ ሥራ ስለተፈለጉ ራቅ ወዳለ ሥፍራ ሄደዋል” ስለሄዱበት ሥፍራ አጥብቄ ብጠይቀውም “ራቅ ወዳለ ሥፍራ ” ከማለት ሌላ ትክክለኛ ቦታ ሊነግረኝ አልፈለገም ።

“ግን ጤንነታቸውን ደህና ናቸው ?”

“በዚህ በኩል አትስጊ ፣ ምንም አልደረሰባቸውም ። እንዲያውም የእሳቸው ሥራ የሚያሰጋ አይደለም ። ”

“እሺ እንግዲያው መደወሌን በሰው አስልከህም ቢሆን ንገርልኝ ። ሰላምታም ስጥልኝ ፤ ሲስተር አዜብ እባላለሁ ”

በዚህ ሁኔታ ተነጋግሬ ስጨርስ መነጋገሪያውን መለስኩና የተባበሩኝን ሁሉ አመስግኜ ወደ ቤት አመራሁ ።

እንግዲህ ይህ ዓይነቱ ነገር ምን ይባላል ? ዕድል ወይስ አጋጣሚ ? ከሦስት ቀን በፊት ብሄድ አገኛቸው ነበር ማለት ነው ፤ ወሬውን ቀድሜ ባለመስማቴ ነው እንጂ በስ

ልክ ማገናኘት ከተጀመረም ሰንበት ብሏል ። ለማንኛውም "አለመታደል ነው" ብዬ ደመደምኩት ። በሌላ በኩል ደግሞ የጤና መኩንንን አግኝቼ ስለጤንነታቸው መስማቴም አጽናናኝ ። ጭራሽ አድራሻቸው ሳይገኝ ቀርቶ እንዲሁ የተሙለሉ ቤተሰቦችስ አሉ አይደል ።

ከቤቴ እንደደረስኩ እንዳጋጣሚ ሆኖ ዶክተር ፍስሐን አገኘኋቸው ። አመጣጣቸው እኔው ጋ ነው ። ዶክትተር ገድሉ ከሄዱ ወዲህ አልፎ አልፎ እየመጡ ያጫውቱኛል ። ሆኖም በእኔ በኩል ጠንከር ያለ ጓደኝነት መፍጠር ስላልፈለግኩ ከሰላምታ ወዲያ የሚኖረውን ጨዋታ ችላ እላለሁ ። እሳቸው እንኳ ተጫዋች ብጤ ናቸው ። ቤትንብረትም የላቸውም ። ብቻ በአጭር ቀን ውስጥ ስለፀባያቸው መናገር ባልችልም ፣ አንዳንድ አዝማሚያዎቻቸው ስላላማረኝ ግንኙነታችንን በመጠኑ ለማድረግ ሞክሬአለሁ ።

በዚህ ዕለትም ስንገናኝ ፈገግ ብለው ሞቅ ያለ ሰላምታ ቢሰጡኝም ከእኔ የተመለሰላቸው ሰላምታ ያን ያህል አልነበረም ።

"ጤና ይስጥልኝ ሲስተር ፣ ስለ ዶክተር ገድሉ የሰማሽው ወሬ አለ? "

"ስለጤንነታቸው ሰምቻለሁ ፣ እሳቸውን ግን አላገኘኋቸውም" "ታዲያ ምነው የከፋሽ ትመስያለሽ? ደህንን

ታቸው ይያዝ እንጂ እንኳን ጦር ሜዳና --" ካሉ በኋላ ስለ አሜሪካንና ሶቭየት ኅብረት ጠፈርተኞች ችግርና ስቃይ፣ ሞትም ጭምር ገለጹልኝና፣ "ለጥሩ ዓላማ መሞት ምንም አይደለምኮ" አሉኝ ።

"አዎ እኔም አምንበታለሁ ።" አልኳቸውና ጨዋታ ውን በአጭሩ ማቋረጥ ስለፈለግኩ "ነገሩ ብዙ የሚያሳ ስብ አይመስለኝም" አልኩ ።

ጭውውቱን ለማሳጠር የሞከርኩበት ምክንያት አለኝ። ዶክተር ፍስኃ ሊያሜውቱኝ የሞከሩት የጦርነቶችም ሆነ የሌላ ራሳቸውን ለጥሩ ዓላማ ያሳለፉ ሰዎች ታሪክ እው ነተኛነት ነበረው ። ሆኖም ከአሳቸው አፍ ልሰማው አል ፈለግሁም ። በተግባር መፈጸሙ እንጂ መናገሩ ቀላል ነው ። ዶክተር ፍስሐ ባሉበት ደረጃ እንኳን ብዙ መሥ ራት ሲችሉ ደመወዝ ከሚያገኙበት መደበኛ ሥራቸው ሌላ ምንም ነገር ንክች አያደርጉም ። እውቀታቸውን የበ ለጠ የማዳበርና እርቆ በመመራመር ለሕዝብ ታላቅ ነገር ጥሎ የማለፍ ስሜትማ ጨርሶ የላቸውም ። በአጠቃላይ ይህን ያህል የተማሩትም የግል ኑሮአቸውን ማሩጭ ለማ ድረግ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም ። ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ከተግባር ጋር የተራራቀ ሰው ለወሬ ያህል ሲለ ፈልፍ መስማት ምን ሊጠቅም ?።

እሳቸውም በጨዋታው መሰልቸቴን ስላወቁ መሰለኝ ሌላ ወሬ ቀይረው ትንሽ ከተጫወትን በኋላ ወጥተው ሄዱ ።

መቼም በቀልድና ከሰው ጋር በመግባባት የሚያክላቸው የለም ። ያገኙትን ሁሉ ጓደኛ ማድረግ ነው ። ለማንም ሰው ጥርሳቸው አይከደንም ። ማንንም ሰው በቀላሉ ይቀርባሉ ። ከዚህ ፀባያቸው ጋር ሕዝባዊ አመለካከት ቢጨመርበት ምንኛ ውጤት ባስገኙ ነበር ። እኔም ጠንክሬ ሥራዬን ቀጠልኩ ። ስጋት ፣ ሃሳብ ፣ ትካዜ ቢደራረቡብኝም በሥራዬ ሸፈንኳቸው ። ካለፈው ይበልጥ ትጋትና ንቃት እያገኘሁ መጣሁ ። ከዶክተር አብርሃም ጋርም ከመላመድ ብዛት በመጠኑ እየተስማማን መጣን ። የማይለመድ ነገር የለምና ነው እንጂ የእሳቸው ፀባይ እንደሆነ አልተለወጠም ። የአቀራረባቸው አለማማር እስከዘለዓለሙም የሚለወጥ ዓይነት አይመስልም ። መጽሐፍን ጓደኛ ማድረጋቸውንና ለበለጠ እውቀት መጣራቸውን ግን ወድጄላቸዋለሁ ። ደግሞም ባለቤተሰብ ናቸው ። እንደ አንዳንዶቹ የመቅበጥበጥና አዘውትሮ የመቀለድ ፍላጎት የላቸውም ። ከእኔም ጋር ከሥራችን ሌላ የሚያገናኘን ነገር ስለሌለ ፀባይ ለፀባይ ተዋውቀን እናከናውን ጀመር ። አንዳንዴም ማመናጨቅና መቆጣት ሲፈልጉ እኔ ጉዳዩ ብዩ አላዳምጣቸውም ። ለቁጣው እኔ ብሺ ቁጭ እላለሁ ። አልፎ አልፎ በሆዴ ፣ እስኪ ሥራቸው ሳያንሳቸው እንዲህ ዓይነቱን ኘክኛካ ፀባይ ከምን አገኙት እያልኩ አዝንላቸዋለሁ ።

## 18

ቀጥታ ግንኙነታችን ከተቋረጠ ከሁለት ወር ያህል በኋላ በመሥሪያ ቤቴ በኩል ደብዳቤ መጣልኝ ። መቼም ያልታሰበ ነገር በድንገት ከተፍ ሲል ማስደንገጡ የማይቀር ነው፣ እኔም ደስታ ይቀላቀልበት እንጂ ድንጋጤ አልቀረልኝም ። ከዶክተር ገድሉ መሆን አለበት ብዬ ገመትኩ ። ከእሳቸው ሌላ ርቆ የሚጠይቀኝ ዘመድ አልነበረኝም ። በእርግጥ ከእሳቸው የመጣ ነበር ። ቦታ አግኝቼ እስካነበው ደስታው እንቅዠቀዠኝ — እንዲህ የሚል ነበር ።

"አዜቢና! ይህን ደብዳቤ የፃፍኩልሽ አንድ አፍታ ቁጭ ብዬ እንዳይመስልሽ ። ከአንቺ ከተለየሁ ጀምሮ በየእረፍት ሰዓቶቼ ሶስት መስመር ያህል እየፃፍኩ ያጠራቀምኩት ነው ። ደግሞም ጥሩ ዘዴ መሆኑን ተረዳሁ ። በአንድ ቀን ተነሳስቶ ወረቀትና ብዕር ይዞ ከመጨነቅ ይልቅ ይኸኛው ቀላል ሙንገድ ነው ። ለራሴም ቢሆን በየእለቱ ያጋጠመኝን ጫር ጫር እያደረግሁ ማስቀመጤ እቀነባብሬ በማነብበት ሰዓት ምን ያህል ደስታ ይሰጠኝ መሰለሽ ፤ ያሳለፍናቸው ነገሮች በፊልም ተቀርጸው የቀረቡልኝ ይመስለኛል ። ወደፊትማ ግዳጄን ሁሉ ፈጽሜ ተመልሼ ከአንቺ ጋር ጐን ለጐን ተቀምጠን ያሳለፍኩትን ጊዜና ያጋጠሙኝን ሁኔታዎች ስናነብ ምንኛ ኩራትና ደስታ እንደ

ሚሰጠኝ ገና ከአሁኑ መገመት ትችያለሽ ። ለማንኛውም የምጽፍልሽን ደብዳቤዎች በጥንቃቄ ጥሩ ቦታ አስቀም ጫቸው ።

ይኸውልሽ —ለመጀመሪያ ጊዜ የተመደብኩት ሐረር ሐኪም ቤት ውስጥ እንዳገለግል ነው ። ይህ ቦታ ጦር ነቱ ከሚካሄድበት ትንሽ ራቅ ያለ በመሆኑ ምንም የሚ ያሰጋኝ ነገር የለም ። ሆኖም "እያሰጋኝም" ማለቴ ጦር ሜዳ መሐል አልገባሁም ለማለት ያህል ነው እንጂ በዚህ አካባቢ አደጋ ከተሰነዘረ የተለየ ማምለጫ የለኝም ። በሐ ኪም ቤቱ ውስጥ የሚገኙት ስድስት ዶክተሮች ብቻ ናቸው ፤ እኔ ሰባተኛ ነኝ ። በእውነቱ በጦር ሜዳ አቅራቢያ ላለ ሐኪም ቤት እንኳን ሰባትና ሃያም ዶክተሮች በቂው አይደሉም ። ይህንን ስልሽ በከተማው ከሚገኙት ትናንሽ ሐኪም ቤቶች ጋር እንዳታነፃጽሪ ፤ ይኸኛው ፍጹም የተለየ ነው ። በየእለቱ ከጦር ሜዳው እየቆሰሉ የሚ መጡትን ታካሚዎች ሁሉ የሚያስተናግደው ይኸው ሆስፒ ታል ነው ። በግቢው ውስጥ የሚገኙት ነርሶችና ድሬሰ ሮች እንዲሁም ሌሎች ረዳቶች ተዳምረው ወደ ሃያ ሁለት ገደማ ናቸው ፤ በጠቅላላው በሐኪም ቤቱ ውስጥ ሠላሣ ያህል ሠራተኞች እንገኛለን ።

የሥራው ነገር አይነሣ ፤ እንዲያው መዋከብ ብቻ ነው ። አንዱን ስንይዝ አንዱን ስንለቅ ከመቼው መሸቶ ከመቼው እንደሚነጋ አናውቀውም ። የእኔ ነገርማ እን

ደምታውቂው ጥንቱንም ለእረፍት አልተፈጠርኩም ። መሥራት ! መሥራት ! መሥራት ! የእንቅልፍ ጊዜዬ ከስ ስት ሰዓት አይበልጥም ብልሽ አታምኚኝም ። ደስ የሚ ለው ነገር ደግሞ ረዳቶቼም እውነተኛ የሥራ ሰው መሆ ናቸው ነው ። በቀዳም ጥገናው ክፍል ረዳቴ የሆነው ዶክተር ዘውገ በሥራው ላይ ትጉህ ከመሆኑም በላይ ከሰው የመግባባትና የማጽናናት ችሎታው ከፍ ያለ ነው ። ውሎአችንም አዳራችንም አንድ ላይ ነው ። ለቁስለኞች የበለጠ ርዳታ የምንሰጥበትን መንገድ አብረን እንተል ማለን ፤ ምን አደከመሽ ! ጥብቅ ጓደኛዬ ሆኗል ።

ከጦር ሜዳ ተመተው ከሚመጡት ቁስለኞች ሰው ነት ውስጥ ጥይት መልቀም ምድብ ሥራዬ ሆኗል ።ካጋ ጠሙኝ ቁስለኞች ብዙዎቹ ጥይቱ ሰውነታቸው ውስጥ የቀረባቸው ነበሩ ። የሚገርምሽ ነገር ትንሽ ሻል ሲላ ቸው ጠመንጃቸውን ይዘው መነሣት ነው ። "ቤቴ ንብ ረቴ" የሚለውን ቃል የሚተነፍስ እንዲያውም አላጋጠ መኝ። ሁሉም ተቀዳሚ አላማው አድርጎ የያዘው "ድልን" ነው ። እኔም ሃሳብ ፣ ትካዜ ለሚባለው ነገር ቦታ አል ሰጠሁትም ። ሥራዬን ብቻ በጥድፊያ ማከናወን ሆነ ። በዚህ ላይማ አንቺም ከጐኔ ብትሆኚልኝ ኖሮ ምን ያህል ሥራው በተቀላጠፈልኝ ነበር ። አንዳንድ ጊዜ የእጅ ጽህ ፈቴ ለረዳቶቼ አልገባ ሲላቸው ፣ እንኳን ጽሕፈቴና ስሜ ቴም ሳይቀር የሚገባሽ አንቺው ፍቅሬ ትዝ ትይኚ ለሽ ።

መልዕክትሽንም ፥ መልክሽንም ፥ ስሜትሽንም ፥ ሁለመና ሽንም የምታሳየኝ ቀለበትሽን አንድ አፍታ አገላብጬ እመለከታትና ውጤት እንዳገኘ ሰው በመደሰት ወዳያውኑ ሥራዬን እቀጥላለሁ ። አልፎ አልፎም ብዙ ነገሮች በጣ ስታውስበት ጊዜ ናፍቆትና ትካዜ ውስጥ መዘፈቁ አል ቀረም ። ይህን ሁሉ የሚያስረሳኝ ግን ያው ሥራ ነው ። ለጭንቅላቴ ፋታ ሳልሰጥ ሥራ ላይ ካተኮርኩ ሌላ ሌላ ውን ለማሰብ ጊዜውም አይገኝ ። የኔዋ አዜቢና ! ያጋጠ መኝን ሁሉ ላንቺ መፃፍ ለእኔ ትልቁ ደስታዬ ሆኖ አግኝ ቼዋለሁ ። መቼም ሰው ፀባይ ለፀባይ የሚተዋወቀው እያ ደር ነው ። በቅርቡ ያጋጠሙችኝን ጓደኛዬን ደግሞ ሳስተ ዋውቅሽ እወዳለሁ ።

ናኔ ይላታል የሚያውቃት ሰው ሁሉ ፤ እናቱን የሚ ጠራ በሚመስል አንደበት ። ከሥራ ረዳቶቼ ውስጥ አንዷ ናት ። የሥራ ፍቅር አላት ፤ ከወንድም ሆነ ከሴት ጋር ቀልድ አታዘወትርም ፤ ከእኔም ጋር ያቀራረበን ያው የሥራ ነገር ነው ፥ ሰው በሥራ የሚመሳሰለውን ሲያገኝ በጣም ደስ ይለ ኛል። ምን ሩቅ አስኬደሽ ። የእኔና አንቺስ እንደዚህ አልነ በረም? ! ይችኛዋም ከመልኳ በስተቀር በምኗም በምኗም ከአንቺ አትለይም ። ሌላው ቀርቶ በአረማመድ እን ኳን ትመሳሰላላችሁ ።

በእዚሁ ሆስፒታል ውስጥ ከእኔ ቀድማ ስትሰራ ቆይ ታለች ። ከርሷው ጋር ሌሎች ሁለት ነርሶች አብረውኝ

ይሠራሉ ። እነርሱም ታታሪዎች ናቸው ። ግን እንደ ናኒ አይሆኑም ። ናኒን ባየሁ ቁጥር እንቺን ማስታወሴ አልቀ ረም ። በእንቺ ፀባይና ሁኔታ የምደሰተውን ያህል በእ ሷም እደሰታለሁ ፤ ማንኛውንም ሥራ ስታከናውን ከልቧ በመነጨ የወንድማማችነትና የእትማማችነት ፍቅር ነው ።

ስለ ቆራጥነትዋማ ምን እነግርሻለሁ ። ከዚህ ጦር ሜዳው አቅራቢያ ካለው ሐኪም ቤት የመጣችው ማንም ሰው ሳያዛት በገዛ ፍላጐቷ ነው ። ለምን እንዲህ እንዳደ ረገችም ጠይቄአት ነበር ። "የሐገርና የወገን ስሜት ነዋ !" በማለት ነበር የመለሰችልኝ ። እኔም በመጠየቄ አፍሬበ ታለሁ ። ቁስለኞችን ስታክምም የሚሰማት ጥንካሬና ድፍ ረት ሌላ ጉዳይ ነው ። በእርግጥ ሥራው ያለድፍረት የሚሠራ አልነበረም ። በጥይት የተበጫጨቀ አካልን በርህራሄ ለማከም መሞከር የባሰ ሕመምተኛውን መጉ ዳት ነው ።

እግራቸው ወይም እጃቸው ተቆርጦ የሚመጡትን ቁስለኞች "አይዞአችሁ ፣ እናንተ ቆስላችሁ ትኛ ሙሉ እካ ላችንን ይዘን ስትመለከቱ ሐዘን እንዳይገባችሁ ፤ እኛም ነገ የጠላትን ጦር ለመቋቋም ጠመንጃችንን ይዘን መነሣ ታችን አይቀርም " እያለች ታጽናናቸዋለች ። እነጋገ ርዋም ለአፍ ያህል ብቻ ሳይሆን ከሙሉ ስሜት የመነ ጩና ቆራጥነት የተሞላበት ነው ።

በሆስፒታሉ ውስጥ ጥብቅ የሥራ ጓደኛዬ ሆናለች ። ቢሮዬ በገባሁ ቁጥር ሕመምተኞች በጐበኘሁ ቁጥር ፣ የእሷ ከጐኔ መቆም ለሥራዬ ቅልጥፍና ረድቶኛል ። ያኔ –ገና እኔና አንቺ እንደተዋወቅን ለሥራ በገባሁ ቁጥር"አዜቢና አልገባችም?" እያልኩ እንደምጠይቀው ሁሉ አሁንም ናኒን ለአንድ አፍታ እንኳ ከሥራዬ ቦታ ብትለየኝ አልፈቅድም ። በህመምተኞቹም ያላት ተወዳጅነት ይህ ነው አይባልም ። ከሠራተኞቹም ጋር ያላት መግባባት የዚያኑ ያህል ነው ። እኔንም ከብዙ ሰዎች ያስተዋወቀችኝ እሷው ናት ። አዜቢና ፣ ስለእሷ ስዘበዝብ እስቀንቼሽ እንዳይሆን - - -

አ ! ያኗኗራችንን ሁኔታ አልገለፅኩልሽም ። በእርግጥ ወደ ጦር ሜዳ የተላከ ሰው ቤቱ ዱር ገደሉ ሁሉ ነው ። የእኛ ግን እንዲህ ዓይነት ስላልሆነ "ወደጦር ሜዳ ዘመቱ" የሚለው አነጋገር ቀርቶ በሥራ " ዝውውር ከተማውን ለቀው ሄዱ" ማለቱ ይቀላል ። ጉዳት ሊደርስብን የሚችለው ነዋሪውን ሕዝብ የሚነካ ከፍተኛ አደጋ ሲጣል ብቻ ነው —

መኖሪያ ቤት የተሰጠን እዚያው ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ው።የምኖረውም አንዲት ክፍል ውስጥ ከሥራ ጓደኛዬ ከዶክተር ዘውገ ጋር ሲሆን ከጎናችን ደግሞ ሦስቱ ቤት ነርሶች የሚኖሩበት ተመሳሳይ ክፍል አለ ። ከእነዚህ ነርሶች ጋር በመኖሪያ ክፍል ብንለያይም ቅሉ ማብሰያ ክፍላችን አንድ

ላይ በመሆኑ እየተረዳዳን አብስለን በአንድነት እንመ ገባለን ። ለሥራ ከሙውጣታችን በፊት ተነስቶ ቁርስ የሚያሰናዳው የዕለቱ ተረኛ የሆነ ሰው ነው ። አምስታች ንም በተራ በተራ መሥራት ማህበራዊ ግዴታችን ነው ። ይህም አይነቱ አኗኗር እንዴት ደስ የሚል መሰለሽ ፤ የመጎራረሱና የመጨዋወቱ ነገርማ አይነሳ ፤ በሥራ ብዛት ከመሀከላችን ደከም ያለ ሰው ሲኖር የሚደረግለት እን ክብካቤ ለብቻው ነው ። በሥራ በኩል መትም እኔና ዶክ ተር ዘውገ ትልቅ ውጥረት ላይ ነን ። ነገር ግን የሶስት እህቶቻችን ትብብርና ርዳታ ስለሚጨመርበት ከምንም አንቆጥረው ። በአጠቃላይ አንቺ ከጎኔ ከሙጥፋትሽ በቀር የኑሮው ሁኔታ የከተማውን ኑሮ የሚያስንቅ ሆኖ አግኝ ቼዋለሁ ።

ውዷ አዜብ ፤ ያንችስ የኑሮ ሁኔታ እንዴት ነው ? የራሴን ታሪክ ብቻ የማነበንበው ያንቺን ረስቼ አይደለም — እኔ ከአጠገብሽ በምርቅበት ጊዜ የሚሰማሽን ስሜት አውቀዋለሁ ። ይህንኑ በማንሳት "ሥራሽ እንዴት ነው? ጥሩ አለቃ አጋጠመሽ ወይ? —" ብሎ መጠየቁ አላቃ ተኝም ። ግን ምን ይሆናል ፣ መልስ የማይገኝለት ነገር ማተቱ ፋይዳ አይኖረውም ። ጦርነቱ እየባሰ ከመጣ ከእኔ በኩል የሚላክልሽም ሙቅረቱ የማያጠራጥር ነው ። ለማ ንኛውም ሃሳብ ፣ ትካዜ የሚባለውን ነገር አስወግደሽ ጠንክረሽ ሥራሽን ሥሪ ። እኔም ብዙ ፈተናዎችን አልፌ

የሚጠብቀኝን ሁሉ አበርክቼ ከአንቺ ጋር የምንገናኝበት ጊዜ ይቃረብልኝ ይሆናል ።

አዜቢና ! እንግዲህ ደህና ጠብቂኝ ። ደብዳቤዩ እንኳን አላለቀም ነበር ! ሆኖም ብዙዎቹን አሰባስቦ እንዲ ለመላክ አላስችል ስላለኝ ይህንን ቆርጨ ልኬልሻለሁ ። ለወደፊቱ ግን ጠንከር ብዬ ቆይቼ ቁርጥራጭ ጽሑፎቼን ሁሉ ባንድነት ሰብስቤ ልልክልሽ እሞክራለሁ ። የተወላገደው የእጅ ጽሕፈቴን ስታይ ከወዲሁ ደስታ እንደሚሰማሽ ይገባኛል ! ተስፋ እንደሚሰጥሽ ! እልፍ እልፍ እረፍት ላይ ስትሆኚ እየገለጥሽ ለፈግታ ያህል ስትመለከችው - - - -

ያንችው ገድሉ በሪሁን (ዶ/ር)

ያብዳቤውን እንደ ጣፋጭ መጽሐፍ ደጋግሜ አነበብኩት ። አጻጻፋቸው በሙሉ በትክክል የራሳቸውን ስዕል የሚያሳይ ነበር ። በተለይ በሥራ መወጠራቸውንና ማህበራዊ አኗኗራቸውን በማነብበት ጊዜ እኔ ከማውቀው እውን ተግባራቸው ጋር ስለገጠመልኝ ፣ ያሠራራቸውተፍተፍ ማለትና ህመምተኞችን የመፈወስ ጥበባቸው ቁልጭ ብሎ ታየኝ ። መንፈሴም በመጠኑም ቢሆን እረፍት አገኘ።

በደብዳቤው ውስጥ ናኒ ስለሚሏት የሥራ ጓደኛቸው ሁኔታ የሚገልጸውን ጽሑፍ ባነበብኩበት ጊዜ ፣ ዶክተር ገድሉ የሚፈልጉትን አይነት ሥራ ወዳድና መልካም ረዳት እህት በማግኘታቸው በጣም ደስ አለኝ ። በአንጻሩ ግን ፣

የማይለቅ ፍርሃት ዓይነት ነገር በልቤ ተሸንቅሮብኝ እቆይ እቆይና ሰውነቴ ሲረበሽ በልቤ ላይ ተንጠልጥሎ ውሳኔ ያላ ገኘ ሀሳብ እንዳስጨነቀኝ ይሰማኝና ምንድነው ነገሩ ብዬ ሳስብ የናኔ ነገር መሆኑን እደርስበታለሁ ። ምን ይሆናል ደብዳቤው ባገላብጠው ከተወሰነው በላይ ሊገልጽልኝ አልቻለም ሰው ቢሆን ደጋግሜ ስጨነቅ መልስ በሰጠኝ ነበር ።

ደብዳቤው ልቤን በደስታ ፣ በናፍቆትና በፍርሃት አተ ራመሰው ። ለናትዮዋ ፣ ለጓደኞቼ ፣ ለእኔ ቤተሰቦች ፣ ለሀ መምተኞቼና ለሚያውቁኝ ሁሉ ደስታዬን ገለጽኩ ። በጣም የምቀራረበው ሰው ባገኘሁ ቁጥር "ዶክተር ገድሉ እኮ ደብዳቤ ላኩ" ማለት የአፍ ልማድ ሆነብኝ ። የሚ ቻል ቢሆን ኖሮ በዜና ማሰራጫዎች እንዲነገርልኝ ሳላ ደርግ ባልቀረሁም ።

ከዚህን እለት ጀምሮ እንደገና መገናኘቱ ተስፋዬ ስለተጠናከረ በፊት ጀምረነው የነበረውን የቤት እቃ ማሟላትም እንደገና ተያያዝኩት ። የዶክተር ገድሉ እናት አዘውትሬ እቃዎች መግዛቴን በመመልከት "ገድሉ በአ ጭር ጊዜ ይመጣ ይሆን ?" እያሉ ይጠይቁኛል ።"አዎ ግፋ ቢል ከሁለት ወር በኋላ ይመጣሉ" እያልኩ እመልስላቸ ዋለሁ ። ለዚያች ሰሞን ያህል እንዲህ ዓይነቱ ሙሉ ተስፋ ከወደፊት መጥቶ እንዳበረታታኝ አይገባኝም ። ከእኔም አልፎ ለሌሎች ሁሉ ተስፋ መስጠቴ እስኪ ምን ይባላል ?

እውነትም ዶክተር ገድሉ እንደገለጹት የተወለጋገ ደውን ጽሁፋቸውን ባየሁት ቁጥር ተስፋ እየሰጠኝ ይሄድ ጀመረ። በዕረፍት ጊዜዬ መጽሐፍ እነብና እንደመሰል ቸት ሲለኝ ያንኑ ደብዳቤ ከሳጥን ውስጥ አውጥቼ አነበ ዋለሁ። እንደ ስዕል ትኩር ብዬ እመለከተዋለሁ። በዚህ ጊዜ መደፋፈር እጀምርና እንደገና ጥንካሬና ብርታት ይሰ ማኛል። ደጋግሜ ከማንበቤ የተነሳም በቃሌ መያዝ ጀም ሬያለሁ። ለማስታወሻ ሰጥተውኝ የሄዱትንም ቀለበት ስማቸውን እላዩ ላይ አስቀርጬ በጥሩ ሁኔታና በልኬ አስበጅቼ እትክክለኛው የቀለበት ጣቴ ላይ አድርጌዋለሁ። ማን ያውቃል ህልማችን እውነት ቢሆን ——

ደብዳቤውን ባነበበሁት ቁጥር ስለናኔ እሰላስላለሁ። ስለእሷ ለማወቅ ያለኝ ጉጉት ከጭንቅላቴ አልጠፋም ብሎኛል። የቅናት መከጃጀል ይሆን -/-

# 19

የዶክተር ገድሉን እናት መንስኤው ያልታወቀ በሽታ ስላመጣቸው ከአልጋቸው ላይ መነቃነቅ አቃታቸው ። የህመሙ አይነት በጣም ግራ የሚያገባ ነበር ። መብላት መጠጣት የማያውከ ፣ መነጋገር ፣ እንደልብ ማጫወት የማ ይከለክል ፣ ነገር ግን እግራቸውን አሳስሮ ከአልጋ ላይ የሚያውል ነበር ። በቤታቸው ውስጥ ሌላ ማንም ረዳት ስለሌላቸው ማስታመምና ምግባቸውን ማብሰል የእኔው ግዴታ ሆነ ፣ ስለዚህ ሁኔታውን ለወላጆቼ አማክሬአቸው ይህንኑ ግዴታዬን ለመወጣት ከእሳቸው ጋር መኖር ጀመ ርኩ ።

በሐኪም ቤት በኩልም ብዙ ደከምኩላቸው ። የማ ውቃቸውን ኀበዝ ዶክተሮችም ባማከራቸው "ሙቀት ይውሰዱ" ከማለት ሌላ ለበሽታው ሙሉ መፍትሔ አላ ገኙለትም ። በቀዶ ጥገናም ሊሰራ የሚቻል ነገር አልነበ ረም ። ዶክተር ፍስሃ በመኪናቸው እያመላለሱልኝ በየ እለቱ ሙቀት እንዲወስዱ አደረግን ። ሆኖም ይህም ርዳታ ምንም ያህል አልጠቀማቸውም ። ከሙቀቱ ሲወጡ ለጥ ቂት ጊዜ ሻል ይላቸውና አስር ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ እንደገና ይጠዘጥዛቸዋል ። እግራቸው ለመራመድ ቀርቶ አንድ ቦታ ለመቆም እንኳን አልቻሉም ። ወደ

ውጪም ሲወጡ ያው ሰው ተሸከሞአቸው ነው ። ምን ብደ ክም የበሽታውን መነሻም ሆነ መጥፊያ ማግኘት አልቻለም ። እሳቸው እንደሚናገሩት ከሆነ ፣

"—ጥንት ግራ እግሬን እየሸመቀቀ ስላስቸገረኝ ወደ አዋቂ (ጠንቋይ) ዘንድ ሄጄ መድኃኒት ከቀመመልኝ በኋላ እዚሁ በሽተኛው እግሬ ውስጥ እንዲቀበርልኝ አድርጌ አለሁ ። ነገር ግን ይህም ሆኖ ህመሙ ስላልተሻለኝ እን ደገና ወደ አዋቂው ሰው በምሄድበት ጊዜ "የእግርሽ ቅርፅ ቆንጆ ስለሆነ ቡዳ በልቶሽ ነው" ካለኝ በኋላ በሁ ለቱም እግሬ ውስጥ መድኃኒቱን ቀበረልኝ ። መድሐኒቱ የተቀበረበት የተረከዜ አካባቢ ለጥቂት ጊዜ አብጦ ቢቆ ይም አሁን የትጋ እንደሆን እንኳ አያስታውቅም ። ታዲያ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ህመሙ በጣም ተሽሎኝ ነበር —" ይላሉ ።

ይኸንኑ በመመርኮዝ ስለህመማቸው ጥናት ለማ ድረግ ራጂ ብናስነሳቸውም ውጤት አላገኘንም ። በተ ረከዛቸው በኩል ተቀዶ የነበረውንም ቦታ ብንመረ ምር እሳቸው እንዳሉት ሁሉ ቁስሉ ደፍኖ ጭራሽ የተ ነካም አይመስልም ።

የደም ጥናቱን ውጤት እንዳየነው ከሆነ ግን በእግ ራቸው አካባቢ ረግቶ የተቀመጠና መልኩን የቀየረ ደም ሲገኝ ፤ የበላይ አካላቸው ግን እንደማንኛውም ሰው

ጤነኛ መሆኑን ያስረዳል። ሆኖም ከታች እየረጋ የሚመጣው ደም ወደላይ አካባቢ ያለውን ሰውነታቸውን እንዳይበክል መከላከያ እየተደረገ ስለህመሙ አይነት ሰፋ ወቅ የሚደረገው ጥናት ቀጠለ።

ወደደኩም ጠላሁም እንደፀባያቸው ይገፔ ማስታመሙ አልቀረልኝም። ከሥራዬ ጋር ይህ ሁኔታ ስለተደራረበብኝ በጣም ውጥረት ላይ ሆንኩኝ። መጽሐፍ የማንበቡ ነገርማ የማይቻል ሆነ። ገና ከሥራዬ እንደገባሁ ልብሴን ቀይሬ የሚበስለውን ሳበስልና ቤቱን ሳጸዳዳ ይመሻል። እንዲሁም አድርጌ ሥራው ጠብ አይልልኝም። በዚያ ላይ እኔ መስሪያ ቤት በምሆንበት ጊዜ እሳቸው ብቻቸውን መሆናቸው ስለሚያሳስበኝ ልቤ ይሰቀላል። እኔ በሌለሁበት ጊዜ እንኳ ወንድሜና እህቴ መጥተው እንዲረዷቸው አስብና የፀባያቸው ነገር ማንንም እንደማያስቀምጥ ስለማውቅ ሁሉንም ትቼ እኔው እሳደፍራለሁ። የኋላ ኋላ ግን ብቻዬን መቋቋም ስላልቻልኩ የምትረዳኝ አንድ ሠራተኛ ቀጥሬ ነበር። እሷንም እንዲሁ እየነዘነዙ ስላስቸገሯት ሳምንት ሳይሞላ ቤቱን ለቃ ሄደች። ምን እንደሚፈልጉ፣ ምን እንደሚያስቡ፣ ምን እንደሚያስደስታቸው ማወቅ አይቻልም። ተጨንቄ፣ ተጠብቤ አጣፍጬ ያቀረብኩትን ምግብ “ኢዲያ”እያሉ ፊታቸውን አጨማደው ሲያንቋሽሹብኝ ጭራሽ ተስፋ ያስቆርጡኛል። የሚያዙትን ነገር ቶሎ ካላደረስኩላቸውማ ቁጣቸውን ማን ችሎ

“እይ ፈጣሪዬ ! ስንቱን አሳልፌ አሁን የልጆች እጅ ልመ ልከት ፣ የልጆች መጫወቻ ልሁን !” ይሉና ወደእኔ ዘወር ብለው ፣ ዋ እዜብ ያሳለፍኩትን ጊዜ ማን በነገረሽ ! ወን ዶችን የማስንቅ ነበርኩ —እንገድሉን እንኳ ያሳደግኳቸው በመጫኛ ጠፍሬ እየገረፍኩ ነበር —አሁንማ ምን አፍ አለኝ - - - ይህንን ሁሉ የሚያሳየኝ ፈጣሪዬ አልወስድ ብሎኝ ነው —” እያሉ ይበሳጫሉ ።

መቼውንም እንዲህ አይነት ፀባይ አጋጥሞኝ አያው ቅም ። የወለደችኝ እናቴ እንኳን እንዲህ ልትንቀባረርብኝ ቀርቶ ሥራ ልታዘኝ እንኳ አትደፍርም ። ይህን አይነት ፀባይ ያላቸውን አሮጊት እንደአመላቸው መያዝ ትልቅ ጥንካሬን ይጠይቃል ። እኔም ይህንን ጉዳይ “ዶክተር ገድሉ እንደመፈተኛ አድርገው ያቀረቡልኝ ይሆናል ” ብዬ ገመትኩ ። ይህን ሁሉ የሚያሠራኝ ለአባቸው ያለኝ ፍቅር ሞራላዊ ግዴታ እንጂ ከአሮጊቷ ጋር ከአንድ ቀን በላይ ባላደርኩም ነበር ። ደግሞ ከሁሉ የሚገርመው እግራቸው ተሳስሮ ከአልጋ መንቃንቅ በማይችሉበት ሰዓት እንኳ አፋቸው አለማረፉ ነው ።

20

አንድ ቀን ከምሳ በኋላ ቡና ፈልቶ ጎረቤቶቻችንም ተጠርተው እየተጫወቱ ሳለ ዶክተር ፍስሀ በድንገት ከተፍ አሉ ። ያ ቀን የመጀመሪያ ጊዜአቸው አልነበረም ።

ዶክተር ገድሉ ከሔዱ ጀምሮ አልፎ አልፎ እየመጡ አሮጊቷን ይጠይቋቸዋል ። ሴትዮዋ ግን ምን ቢጨነ ቁላቸው መወረፋቸው የማይቀር ተለምዶ በመሆኑ ዶክ ተር ፍስኃ ገና ከበሩ ብቅ ሲሉ "አለህ እንዴ ? አንተም የዘመትክ መስሎኝ ነበር እኮ ----ብቻ አሮ ት ምን ያደ ርግላችኋል" ብለው አሽሟጠጧቸው ።

ዶክተር ፍስኃ የፀባያቸውን ልክ ስለሚያውቁ ፈገግታ እያሳዩ "እንደምን ሰነበቱልኝ የዶክተር እናት ፣ መጠየቅ እናንተን ነው እንጂ ወጣት ምን ያደርጋል" አሏቸው ።

አሮጊቷ በስማቸው የሚጠራቸውን አይወዱም ። ሁሉም ሰው የዶክተር "እናት" ይላቸዋል ። ዶክተር ፍስ ኃም በዚሁ አይነት ስለጠሯቸው ትንሽ ደስ አላቸው ።

"በል እኮ አረፍ በልና አውጋ ፣ እኔማ ይኸውልህ የአልጋ ቁራኛ ሆኜ ቀርቻለሁ ።"

"ምንም አይደለም ዋናው ነገር ሲስተር አዜብን ያህል ጧሪ ማግኘትዎ ነው ።"

"ኸ ! ኸ ! ምን ተደረገልኝና? ብቻ አለማወቅህ ነው እንጂ --- " ካሉ በኋላ ወደ እኔ በቁጭት መልከ እየተመለ ከቱ "ብዙ የሚደረግልኝ ሰው ነበርኩ ምን ይሆናል ! ዛሬ የልጅ እጅ እያየሁ ማላገጫ ሆንኩ" አሉ ።

እኔም በብስጭት "ከዚህ የበለጠ ምን እንዳደርግልዎት ይፈልጋሉ ? በሽታውን እኔ አላመጣሁብዎት ፤ እርጅናውንም እኔ አላመጣሁብዎት ፤ ለምን አረጀሁ ብሎ ብስጭት ምንድነው? አሁንስ በዛ" ብዬ ልናገር ካሰብኩ በኋላ ከአፌ መለስኩት ። ብናገርስ ምን ሊጠቅመኝ ፤ እሳቸው እንደሆኑ ይህ ፀባያቸው የሚለቃቸው አይነት አይደሉም ። ብዙ ሰዎች ሲያረጁ ፀባያቸው ይለዋወጣል ። የእሳቸው ግን ከማንም የተለየ ነው ። አብሶ አልጋ ላይ ከዋሉ ጀምሮ የሚያደርጉትን አሳጥቶአቸዋል ።

ዶክተር ፍስኃ በቀልድ መልክ "አይዞዎት ብዙም ይበሳጫሉ? የሚቸግርዎትን ሁሉ እኛ እናደርግልዎታለን ፈጽሞ ቅሬታ አይሰማዎት ። እኛም እኮ ልጆችዎ ነን "አሉ

በዚህ ጊዜ አሮጊቷ እያለቀሱ ፣ "ውሸት! ቢሆንማ ኖሮ እግሬም እንዲህ ተበላሽቶ አይቀርም ነበር ። ይህን ሁሉ የሚጫወትብኝ ፈጣሪዬ ነው ። አንድ ልጅ ሰጥቶኝ መልሶ ወሰደብኝ ፣ ሌላማ ምን ዘመድ አለኝ ? ሥጋዎቼ ሁሉ ከድተውኛል ።---" እያሉ ያማርሩ ጀመር ።

ዶክተር ፍስኃ የሚያነሱት ጨዋታ ሁሉ አሮጊቷን የሚያስቆጣቸው ሆኖ ስለተገኘ ከእኔ ጋር ሌላ ጨዋታ እናወራ ጀመር ። አሮጊቷም ከጎረቤታቸው ጋር ቀደም ሲል ጀምረውት የነበረውን ጭዋታ ቀጠሉ ።

በዚህ አይነት ጥቂት ከቆየን በኋላ ዶክተር የስራ ሰዓት ስለደረሰባቸው አሮጊቷን ተሰናበቷቸውና ሊወጡ ሲሉ እኔም ለመሸኘት ተከተልኳቸው ። ዶክተር ፍስሐ ቀልድ ስለሚያዘወትሩ ፣ ግራ ከንዴን ያዝ አድርገውኝ ተራ ጨዋታዎች እየተጫወትን በቀስታ ርምጃ በሩን ወጣ ስንል ፣

"እንዲህ ተጓተቱ እንጂ ፣ ምን አለ አለፈላችሁ !" የሚል ድምፅ ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ አለ ።

ይህ ቃል ከአሮጊቷ የሚሰነዘር መሆኑ ስለገባኝ ዶክተር ፍስኀን "ቆዩ አድምጡ" አልኳቸውና እንደገና ወደ በሩ ጠጋ ብዬ ግድግዳውን ከለላ በማድረግ የሚናገ ሩትን ሁሉ አዳምጥ ጀመር ።

ከጎረቤቶቻቸው አንዷ " አሁን የመጡት የልጅዎ ጓደኛ ናቸውን?" ሲሉ ጠየቁ ። አሮጊቷም "አዎ ለነገሩማ ጓደ ኛው ነው ! ሴቷም የልጁ እጮኛ ነች። ታዲያ ምን ያደ ርጋል —— እንደምታዩት ዘለአለም እንደተጓተቱ ነው ። እነሱ ድሪያ የጀመሩት ልጁ ጦር ሜዳ ሳይደርስ ነው !እዩ ጉድ ! ያ ሞኝ ልጁ እጮኛ አለችኝ ብሎ ያስብ ይሆናል--" ሲሉ ተሰማኝ ።

የአሮጊቷ ንግግር ገና አላለቀም ነበር ። እኔ ግን ከዚህ የበለጠ መስማት አልፈለግኩም ። በሰውነቴ እሳቱን ለቀቀ ብኝ ። ከመጠን ያለፈ ተበሳጨሁ ። ለመሳደብም ቃጣኝ ፣

እጇን በወገቤ ላይ አድርጌ "ይህች አሮጊት እኮ አበዛ ችው" አልኩ ።

ዶክተር ፍስጎ ለዘብ ባለ አነጋገር ፣ "ተወት ማድረ ረግ ነው እባክሽ ፤ እማትሽ መሆናቸው ቀረ? ከዚህ የበለ ጠስ ቢናገሩ ምን ያስደንቃል ብለሽ ነው" አሉኝ ።

"እማት የሆኑ እንደሆን ታዲያ ምንድነው? እንዲህ አድርጎ መሳደብ ይገባል እንዴ? ይህ ከአሮጊት አፍ የሚ ወጣ ንግግር አይደለም ። በጣም ነውረኛ ናቸው ።"

"እይ ሲስተር አዜብ ፣ ሁሉን ስታውቂው ለምን አዲስ ትሆኝለሽ? ይህ እኮ በሁሉም ዘንድ ባይሆንም እንኳ አልፎ አልፎ የሚታይ ነገር ነው ። እማት የልጅዋን ሚስት ስታ መናጭቅና ስታማ ሰምተሽ አታውቂም? በእርግጥ አዲሱ ትውልድ ይህን የመሳሰሉትን ነገሮች ከጭንቅላቱ ማስወ ጣት አለበት"

እኔ በምናገርበት ጊዜ በብስጭትና በቁጣ ቃል ሙክ ብዬ ስለነበርና አሮጊቷ ስለሰሙኝ "ሰምተሻል እንዴ? ልክ ነውና ምን ውሸት ተናገርኩ? የምታደርጊውን ነው ።" አሉና ጭራሽ ጩኸታቸውን ቀጠሉ ።

እኔም እልህ ቢተናነቀኝም ቅሉ ፣ የዶክተር ገድሉ አደራ ስለታወሰኝ ነገሩን ሰምቼ እንዳልሰማ ሆኜ አለፍ

ኩት ። ብዙውን ጊዜ በአሮጊቷ ፀባይ ተበሳጭቼ በማረር ፊቴ ላይ ድቅን እያለ የሚገስፀኝ፤ ዶክተር ገድሉ ለመጨ ረሻ ጊዜ ሲሰናበቱኝ አንገቴን ያዝ አድርገው በጆሮዬ "የእ ናቴን ነገር አደራ" ያሉኝ ነው ። ከዚያ በፊትም ስለአ ሮጊቷ ፀባይ የገለጹልኝን ሁሉ አስታውስና እፅናናለሁ

ዶክተር ፍስኀን እስከ መኪናቸው ድረስ ከሸኘኋቸው በኋላ ወደ ቤት ተመልሼ እንጎዳጎድ ጀመር ። አሮጊቷ መነጫነጫቸውንና ማሽሟጠጣቸውን ባያቋርጡም እኔ ችላ ብያቸው ስራዬን ቀጠልኩ ። እየሰነበትኩ ስሄድማ፤ ቁጣቸውንም ፣ ስድባቸውንም ተላመድኩት ። እሳቸው ሲጮሁ ቢውሉ እኔ ከምንም አልቆጥራቸው ። የሚያስፈ ልጋቸውን ነገሮች እያሟላሁ አቀርብላቸዋለሁ ። መቼም ሰው ከጠነከረ ምንም የማይለመድ ነገር የለም ። ሁሉ ንም ችዬ እያስታመምኳቸው ቆየሁ ።

እሳቸውም ለብዙ ጊዜ አልቆዩም ። የህመሙ ነገር እየ ፀናባቸው ስለሄደ ሀኪም ቤት አስተኛኋቸው ። የተበላሸው ደም ቀስ በቀስ ወደ መላ አካላታቸው እየተሰራጨ መጣ ። ምንም አይነት መድሐኒት ሊያግደው አልቻለም ። እያደ ርስ ነው ! በኋላማ ሽንታቸውንም ከለከላቸው ። በእጃቸው ምግብ መጉረሱም አቃታቸው ። መላ ሰውነታቸው እስር ስር አለ ። ብዙ ጊዜ "እሚሚቴን አሳምርልኝ" እያሉ ሲፀ ልዩ እሰማ ነበር ። ነገር ግን አልሰመረላቸውም ። ብዙ

ከማቀቁና ከተሰቃዩ በኋላ ህመሙ በጀመራቸው በስድስ ተኛው ሳምንት እከባቢ አረፉ ።

ህመሙ ከፀናባቸው ጊዜ ጀምሮ ዶክተር ገድሉ እስፈች ደውም ቢሆን እንዲመጡ ለመንገር በስልክና ወደዚያ በሚሄዱ ሰዎች በኩል ሞክሬ ነበር ። ነገር ግን የሁኔታው መጥበብ ሊያሳካው አልቻለም ።

"ሰው ሲሞት እየተዘፈነ አይቀበርም —"የሚለው አነጋገር በትክክል የሰራው እዚህ ቦታ ነበር ። እንደዚያ ማቅቀው ለሞቱት አሮጊት ደረት እየተመታ ተለቀሰላ ቸው ። እንደማንኛውም ሰው ሁሉ ሥነ ስርዓቱ ተከብሮ ተቀበሩ ። እኔም እንደሰው "እናቴ እናቴ" ማለቴ አልቀ ረም ። ከሰው ላለመለየት እንጂ ሞታቸውስ የሚያሳዝን አልነበረም ። የሚያስለቅሰው በቁማቸው ሲማቅቁ ማየት ነበር ። ምን ያደርጋል ? መጥፎ ተለምዶ ነው ። ተጣልተዋ ቸው የነበሩት ዘመዶቻቸው ሁሉ እየመጡ አለቀሱላቸው ። እኔም ይሉኝታ ይዞኝ ነው እንጂ "ዝም በሉ ምን ታለቅ ሳላችሁ? እኒህን አሮጊት በቁማቸው ሲማቅቁ ዘወር ብላ ችሁ አይታችኋቸዋል ? የምን ማስመሰል ነው" ብላቸው ምንም ስህተት አልነበረበትም ። ለማንኛውም ፣ ምኑም ምኑም ሳይቀርባቸው እንደተለምዶአችን በደንብ ተለቀ ሰላቸው ።

የዶክተር ገድሉን እናት እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ በማስታመሜ ትልቅ የመንፈስ ኩራት ተሰማኝ ።

ከዚያ በኋላ የቀረኝ ነገር ወደ ወላጆቼ መመለስ ነበር ። ግን ቤቱን ለማን አስረክቤ? ዶክተር ገድሉ እስኪመጡ ድረስ ቤቱን መጠበቅ የእኔው ግዴታ ሆነ ።

ወላጆቼ የእኔ ሲገርማቸው ፤ ታናሽ እህቴንም ወደዚሁ ቤት አመጧት ። ከብቸኛ ኑሮ ሁለት መሆን ይሻላል በሚል ሐሳብ እንጂ ሌላ ምክንያት አልነበረውም ። ለኑሮአችን የተለየ ሠራተኛም አላስፈለገንም ። እህቴ ከትምህርት ቤቷ ስትመለስ ማንኛውንም ነገር አስናድታ ትጠብቀኛለች ። እኔም ከስራዬ ስመጣ የቀረ የቤት ሥራ ካለ አጠናቅቃ ለሁ ። በዚህ ላይ ዶክተር ገድሉ መጥተው ቢሆን ኖር የገዛናቸውን የቤት ዕቃዎች ከሳጥን አውጥተን በደንብ በደንቡ በመደርደር የተሟላ ኑሮአችንን ባስኬድነው ነበር ። ሆኖም በቅርቡ ማድረግ አልተቻለም ። የወደፊቱንስ ማን ያውቃል ---

የዶክተር ገድሉን ወሬ ከሰማሁ ብዙ ጊዜ ሆነኝ ። ደብዳቤአቸው ከደረሰኝ ሁለተኛው ወር አለፈ ። ሰዎችን ባጠያይቅም ስለእሳቸው ሰማሁ የሚለኝ አጣሁ ። እንዳለፈው ጊዜ በስልክ የመገናኘቱ እድል ካለ በማለት ወደ መገናኛው ሥፍራ ብሄድም የተሰጠኝ መልስ "ተቋርጧል" የሚል ነበር ። ለምን እንደሆነ ግን የሚነግረኝ አላገኘሁም ። በየአካባቢውም ከጦር ሜዳ በተለያዩ ምክንያቶች ተሚመለሱትን ሰዎች እያገኘሁ ለማጣራት ሞከርኩ ። ግን ማንም

ከእሳቸው አካባቢ የመጣ ሰው አጣሁ ። የጦርነቱ ሁኔታ ግን ከመጠን በላይ እንደተፋፋመ በየጊዜው በዜና ማሠራጫ ይነገራል ። ይህንንም ለመቋቋም ይረዳ ዘንድ በየጊዜው ወደ ጦር ሜዳ ለመሄድ የሚንቀሳቀሰው ኃይል ብዛት እየጨመረ ሄዷል ። በአጭሩ ፣ ስለዶክተር ገድሉ ወሬ ሳልሰማ በሀሳብና በስጋት ወደ ሶስት ወር ያህል ቆየሁ ።

# 21

በጦርነቱ ከፍ ያለ ጉዳት የደረሰባቸው ቁስለኞች በቂ ርዳታ ለማግኘት እኔ ወደ ምሰራበት ሐኪም ቤት ድረስ ይመጡ ጀመር ። ከእለታት አንድ ቀን ጠዋት ወደ ስራዬ ስገባ ብዙ ቁስለኞች የያዘ ትልቅ መኪና ከግቢው ውስጥ ቆሞ አየሁ ። ቀደም ብለጡ የገቡትና አዳሪ የነበሩት ሠራተኞች ቁስለኞችን ከመኪናው እያወጡ በማመላለ ሻው አልጋ ወደ የክፍሉ በመውሰድ ይጣደፋሉ ። ቁስለ ኞቹ እንደዚያ ሲማቅቁ ማየቱ የሚያሳዝን አልፎም የሚ ያስለቅስ ቢሆንም ቅሉ ፣ እንዲህ የሆኑት በጀግንነትና የብዙኃኑን ፍላጐት ለማስጠበቅ ባደረጉት ተጋድሎ መሆ ኑን አርቆ ለተመለከተ ደግሞ በወገኖቹ ምን ያህል በተ መካና በኩራም ነበር ። እኔም በጀመጀመሪያ እንደተመለ ከትኳቸው ማዘኔ ፣ ሆዴ መባባቱና እንባዬ ማቅረሩ አል ቀረም ። ሆኖም ቁስለኞቹን እያየሁ ህሊናዬ ወደ ዶክ ተር ገድሉ ይሄድ ነበር ። በዚህም ራሴን ታዝቤዋለሁ--- "ይህ ሁሉ ቁስለኛ ወገንሽ አይደለምን? ስለአንድ ሰው ብቻ ማሰብሽ ለምንድነው ?"የሚለው ወቀሳ አዘል ጥያ ቄም በተደጋጋሚ ከህሊናዬ ቀርቦልኛል ። ራስን ከግላ ዊና ወነናዊ ስሜት ማጽዳት እጅግ ያስቸግራል ።

ለማንኛውም እኔም ወዲያው ልብሴን ለወጥሁና መሯ ሯጥ ጀመርሁ ። አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዳይጓደልባቸው

በማገዝ ። ብዙም አልቆዩ እንጂ የድረሱልኝ ዋይ ዋይውታ መስማት ሲጀምር ። አንድ አምቡላንስ መንገድ ልቀቁ እያለ ከተፍ አለ ። አስቸኳይ እርዳታ የሚያስፈልገው መሆኑን በመረዳት ተሽከርካሪ አልጋውን ይገፉ ተጠጋሁ ። አራት ሰዎች በሽተኛውን ከአምቡላንሱ አወረዱና እየተ ንገዳገዱ በአስጠጋሁት አልጋ ላይ በጥንቃቄ ዘረጓቸው ። ለሽክም እንደከበዷቸው አየሁ ። አንዲት ያለእድሜዋ ያረ ጀች የምትመስል እንደሰውየው ወፍራም ሴትዮ እያለቀ ሰች ተከትላለች "እሚቸውም አያውቅኮ ፣ ድንገት ነው እቆ ሙበት ክልትምትም ያሉት" እያለች ። በሽተኛው እምብ ዛም እንቅስቃሴ አይታይባቸውም ።

ባስቸኳይ ድንገተኛው ክፍል ውስጥ አስገባናቸ ውና ዶክተሩ እስኪመጡ አንዳንድ የመጀመሪያ ዝግጅ ቶችን ለማሟላት ፣ የትኩሳት መለኪያየን ይዤ ገለጥ አደ ረግኋቸው ––

ልገልፀው ልሞክር እንጂ የተሰማኝ ስሜት ለቃላት ያስቸግራል ። ባንዴ ሰውነቴ ተለዋወጠ ፤ አላበኝ ፣ አንቀጠ ቀጠኝ ፣ አቅለሸለሸኝ ። ትኩሳት መለኪያውን እንደያዝሁ ወደ መፀዳጃ ቤት ሰርጥ እነዶክተር አብርሃም ላይ ወጥቸባቸው ነበር ። ክፋቱ ከሻይ በስተቀር የበላሁት ቁ ርስ እምብዛም ስለነበር ፉጣ አትውጣ ትንንቅ ፣ ከሆዴ የሚወጣው አሞት ፊቴን እንባ በእንባ አደረገው እንጂ

የሆዶ ትርምስ አልወጣልሽ አለኝ ። --- የስራው ጉዳይ ግዴታየ በመሆኑ ብቻ ትንሽ ፋታ እንዳገኘሁ ተመለስሁ።

ዶክተር አብርሃም ተቆጥተዋል ። አይናቸው ተለዋ ውጧል ። ሰውዬው " ኮማ " ውስጥ ገብቶ ፣ ሰውነቱን ስቶ የት ጥለሽ ትፈረጥጫለሽ —እያሉ ያንቀጠቅጣቸዋል ። እኔ ብሆን አሁንም አልተመለሰልኝ —"ትልልልልቅ ሰው ነኝ---ኮ አትጫ---ጫጫ---ወቱ— ብኝ— ቀ— ላላላ— ል— አይ-- —አይ—— "ይላል ፤ ታሪከኛው ።

"የደም ብዛቱ ስንት በስንት እንደሆነ ታውቂያለሽ፤ እጭንቅላቱ ውስጥ ፈሶኮ ሊሞት ይችላል --- በኛ ንዝህላ ልነት ---" ይላሉ ዶክተር አብርሃም ። ቢቸግራቸው"— ዛሬ በውነት ልክ አይደለሽም ---" በማለት አስፈላጊ ውን እርዳታ ራሳቸው ካደረጉለት በኋላ "ልዩ ክፍል ውስጥ አስገቡት" ብለው ድሬሰሮቹን አዘዙ ። ይዘውት ሲወጡ መልከት አልኩት ። አሁንም ከንፈሩ ይንቀሳቀ ሳል ፣ ቃላቱም ባይሰሙ ---አልፎ አልፎም ልምጭጭ ሳቁ ብቅ ጥልቅ ይላል —ትሩፋት ብትሆን ኖሮስ ፣ በኔ ቦታ --- ምን ይል ነበር ልጧ ብዬ ራሴን ጠየቅሁት ።

ቁስለኞቹ በየክልሉ ተከፋፍለው እንዲተኙ ተደረገ ። እኔ በምሰራበት "ክፍል 3" ውስጥ ስድስት ቁስለኞች አልጋ ያዙ ። ልቤ ግን ከነሱ አልፎ እየዘመተ አስቸገ ረኝ ። ረሳሁት ያልሁት ጥርጣሬ ተመለሰብኝ ። ዶክተር

ገድሉስ ቢከዱኝ፣ ሌላ ቤትስ ቢወዱ፣--- ትናፋት ኖራ ኖራ ባዲስ መልክ ታወሰችኝ ። እኔ በይሆናል እንዲህ የሆንኩ፣ ቢሆንማ ምን ይውጠኛል፣ — ያ ከመሬት ያደባለቃት ሀዘኗ እንዴት እንደነበር ታወቀኝ --- ትኖር ይሆን በህይወት፣ ---

እንዲያም ሆኖ ታዲያ ልቤ አልችል ብሎኛል ። የሥራ ድርሻዬን ለማከናወን በምንደፋደፍበት ወቅት ሁሉ የዶክተር ገድሉን ወሬ ለመጠየቅ አፌን እሾላለሁ ። ቁስለኞቹ በጉዞ ላይ ብዙ ስለቆዩና የደረሰባቸውም አደጋ ቀላል ስላልነበር ከመድከማቸው የተነሣ እንደልብ መነጋገር አልቻሉም ። ስለዚህ የምጠይቃቸውን ሁሉ አቅማቸው በፈቀደው መጠን ከመመለስ ወደ ኋላ ባይሉም ማስቸገሬ ሳይሰማኝ አልቀረም ። ከብዙዎቹም የተሰጠኝ መልስ "ጦር ሜዳ ላይ ብዙ ሐኪሞች አሉ ። ስማቸውን ግን አናውቅም" የሚል ነበር ። በተረፈ ስለብዙ ነገሮች የሚያውቅ ከጦሩ ውስጥ የአንድ ቡድን መሪ የሆነና ከእነሱ ጋር ቆስሎ የመጣ የመቶ አለቃ መኖሩን ጠቆሙኝ ። እንዳጋጣሚ ሆኖ የጠቆሙኝ ሰው እኔ በምሰራበት ክፍል ውስጥ አልነበረም ። ግቢንው አስሼ ፈልጌ የተኛበትን ክፍል አገኘሁት ። ግን እንዴት አድርጌ ልጠይቀው፣ የእኔው ህመምተኛ ቢሆን ኖሮ ህክምና ሳደርግለት ላነጋግረው እችላለሁ ። ከቀን ወደ ቀን እየቀረብኩት መጥቼ እንዳላነጋግረው ደግሞ አላስችል አለኝ ። ወዲያውኑ ለማወቅ ጓጓሁ ።

ጉዳዩን በክፍሉ ለምትገኘው ነርስ አስረዳኋትና አብረን ወደ ሰውየው ሄድን ። ከዚያም የክፍሉ ነርስ ቁስ ሉን ገለጥ አድርጋ በማየት "አይዞህ እየዳፈነልህ ነው" አለችው ። እኔም ነገሩን ለማቅለል ይሄ ትንሽ ነው እኮ በእኔ ክፍል ወ ስጥ ያለውን ብታይ ምን ትያለሽ" አልኩና እግረ መንገዴን እራሴን አስተዋወቅሁ። መቶ አለቃው ባን ዶበታችን መደሰቱን ተመለከትሁ --- ከዚያም ፣

"ዶክተር ገድሉ የሚባሉ ሐኪም ታውቃለህ ?" የሚል ጥያቄ ሰነዘርኩለት ፣ ቀስ ብዬ ። መቶ አለቃው በመልካም ስሜትና በደስታ ፊቱ ፈካ ብሎ አንገቱን ቀና በማድረግ ወደ እኔ እየተመለከተ በደካማ ድምፅ " አዎ አ - ዎ " ሲለኝ የደረቱ ቁስል ተቀሰቀሰበትና ያቃስት ጀመር ። መልስ ሊሰጠኝ ቢጓጓም ቁስሉ አላናግርህ አለው ። በጣቱ ወደ ጠረጴዛው ሲያመለከተኝ ወረቀቱን እንዳቀብለው መሆኑ ገባኝና ከብዕር ጋር አቀረብኩለት። " ቆዩ - - " የሚል ጽሑፍ ካሰፈረ በኋላ አሁንም እጁን ስለነዘረው መጻፉን አቋርጦ "እርጋታ ይስጥሽ" ለማለት እጁን እየነቀነቀ አሳየኝ ።

"-----ግን ጤንነታቸውን ደህና ናቸው ?" የሚል ጥያቄ እንደገና አቀረብኩ ። አጠያየቄ በትካዜ መልክ ነበር።

መቶ አለቃው በአፉም ፣ በእጁም ፣ በመላ ሰውነቱ ሊያስረዳኝ ቢሞክርም ቋሰሉ አላነቃነቅ በላለው ፊቱን ትራሱ ላይ ደፋና ዝም አለ ።

የክፍሉ ነርስ ኃላፊነትዋ ስለተሰማት "ተይ እንጂ ሲስተር አዜብ ፣ እንዲህ ታሞ እያየን እንዴት እንጠይቀዋለን ፤ ሻል ሲለው ብትመለሺ ይሻላል" አለችኝ ። ይህን ያህል ታሞ የሚማቅቅን ሰው በግድ ለማናገር መሞከር እንኳንስ ከእኛ ከነርሶች ቀርቶ ምንም ከማያውቅ መሐይምም የሚጠበቅ አልነበረም ።

በሶስተኛው ቀን ገደማ ህመሙ ሻል ብሎት ትንሽ ትንሽ መነጋገር ሲጀምር "አይዞሽ ደህና ናችው ። ህመሜ ሲሻለኝ ሁኔታቸውን ሁሉ በደንብ እጫውትሻለሁ" በማለት ተስፋ ሰጠኝ ። አሁንም የበለጠ ለማወቅ መጓጓቴ አልቀረም ። እሱ መመለስ እቃተው እንጂ ጥያቄ ለማቅረብም ወደ ኋላ አላልኩም ። በኋላማ የቅርብ ዘመዴ አደረግሁት ። ቀን ሁለት ሶስት ጊዜ ሳልጎበኘው አልውልም ። አልፎ አልፎም ሙዝና ብርቱካን እወስድለት ጀመር ። በአጠገቡ የተኙት ህመምተኞችም ፣ ከረዥም ጊዜ በኋላ እንደተገናኘን ዘመዳሞች አድርገው ሳይመለከቱን አልቀሩም ።

በዚህ ሁኔታ መቶ አለቃው እየተሻለው ሄደ ፣ አንድ ቀንም እኔ ሳልጠይቀው በገዛ ራሱ እንዲህ እያለ ሊያጫውተኝ ጀመረ ።

"—ዶክተር ገድሉን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘኋቸው በእኔ የሚመራውን ጦር ይገኑ ባቢሌ ወደ ተባለው ስፍራ በደረስኩበት ወቅት ነበር ። ሁሉ በሥራ እንደተወጠሩ ናቸው ። በባቢሌ ውስጥ የሚካሄደው ጦርነት በጣም የከፋ ቢሆንም ዶክተር ገድሉንና እሳቸውን መሰል ትጉህ ሐኪሞችን በማስከተላችን ጥንካሬ ተሰምቶናል ። በእኔ ከሚመራው ጦር ውስጥ በህክምና ዕጦት የወደቀ ማንም ሰው አልነበረም ። ከልብ የመነጨ እርዳታ አልተለየንም ምን ጊዜም ቃላቸው "እይዞችሁ በርቱ ፣ ወደፊት ግፉ ፣ ድል የእኛ ነው " የሚል ነበር ። ቁስለኛ በታየበት ሁሉ ቀድመው ደራሽ እሳቸው ናቸው ---"

በመሐል ንግግሩን አቋረጥኩትና "ዶክተር ገድሉ ጦርነቱ መሃል ገብተዋል ማለት ነዋ ?" የሚል ጥያቄ አቀረብኩለት ። እጠያየቁ በድንጋጤ የተመላ መሆኑ ገብቶት ኖሮ እሱም ወዲያው "ሲስተር ይህ ሁኔታ ፈጽሞ ሊያስጨንቅሽና ሊረብሽሽ አይገባም " ብሎ በመጀመር ፣ በእንዲህ አይነቱ ታሪካዊ ቦታ ጊዜንና ግላዊ ምቾትን ፣ አልፎም ራስን መስዋዕት ማድረግ በጣም የሚያኮራ ነው ። የሚገርምሽ ነገር ዶክተር ገድሉ የተመደቡበትን ሐኪም ቤት ለቀው ጦር ሜዳው መሐል የገቡት በራሳቸው ፍላጐት ነው ። የጠላት ጦር እያየለ በመጣ ቁጥር ቁስለኛው ስለጨመረ በቀላሉ የቆሰሉትን እንኳን ወዲያው የሚያክምልን ሰው ማግኘት አጣዳፊው ጥያቄ

እችን ነበር ። ለእንዲህ አይነቱ ተግባር በቆራጥነትና በሙሉ ፈቃደኝነት የቀረቡት ዶክተር ገድሉ በእርግጥ የህዝብ ወገን መሆናቸውን አሳይተዋል ። ትልቅ ጀብዱ ፈጽመዋል ። የግል ኑሮ ለሚያንሰፈስፈው ሁሉ ትልቅ ትምህርት ሰጥተዋል ። በአጭሩ ፣ የዶክተር ገድሉን ህዝ ባዊ ጠባይ በንግግር ብቻ መግለፅ አይቻልም ። እኔ ይህን ሁሉ ለመታዘብ የበቃሁት በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው ። በጠላት ጥይት ቆስዬ ወደዚህ ከመጣሁ በኋላም የበለጠ ስራ ሰርተው ሊሆን ይችላል ---" እያለ ካጫወተኝ በኋላ የሚፈልግበትን እንዳጠናቀቀ ሰው በሰፊው ተነፈ ሰና ፈገግ ብሎ እየተመለከተኝ "ለመሆኑ ምንሽ ናቸው ሲስተር ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"ዘመዴ" የምትለዋን ቃል ብቻ ተነፈስኩ ።

"በጣም ልትኮሪባቸው ይገባል ፤ ግሩም ሰው ናቸው" አለኝ ።

አልጋው ላይ እንደተቀመጥኩ የሩቅ የቅርቡን አሰላስል ጀመር ። በሩቁ እየተመለከትሁ ። በእርግጥ መቶ አለቃው ሳይታዘበኝ አልቀረም ። አልፎ አልፎ "እንዲህ አይነቱ መ ጨነቅ ከአንቺ የሚጠበቅ አይደለም" ማለቱ ትዝ ይለ ኛል ። ነገር ግን ለጊዜው እአምሮዬ ይህን ሁሉ ማስተዋል አልቻለም ።

"ሲስተር ይፈለጋሉ ! የፀናበት ህመምተኛ ይፈልግ ዋታል" የሚል ድምፅ በድንገት ከወደበሩ አካባቢ ስሰማ

ነው ከሀሳቤ የነቃሁት ። ዘወር ብዬ ስመለከት ፣ እኔኑ መሆኑ ገባኝ ።

ከክፍሌም እንደደረስኩ ቁስለኞች ወደ ተኙበት ሰፋ ያለ ክፍል ገባሁና "ህመሙ ጠንቶበት ያስጠራኝ ማነው?" ብዬ ጠየቅሁ ። ከሁሉም ራቅ ብሎ ወደ ጥግ የተኛው ቁስለኛ "እኔ ነኝ እኔ ነኝ" በማለት ከአንገቱ ቀና አለ ፤ በመቀጠልም ድክምክም ባለ ሁኔታ "ምነው ሲስተር ዛሬስ--" ብሎ ሳይጨርስ መወራጨት ጀመረ ። ጥፋቴ ተሰማኝ እጅግም አሳፈረኝ ፤ ያን ያህል ጊዜ ማጥፋቴ ።

የሰውየው ቁስል በጣም ከባድ ስለነበረ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ አራት ጊዜ እንዲታጠብና ፋሻው እንዲለወጥለት ታዞለታል ። የምሽቱ ተረኞች ረስተውት ስለሄዱ ርዳታ እንዳደርግለት እኔን የጠየቀኝ በጠዋቱ ነበር ። ሆኖም የማወቅ ጉጉቴ የሥራ ኃላፊነቴን አስረሳኝ ። በሽተኛው ሥራዬን በመደሌ የፀፀተኝ መሆኑ የገባው ይመስላል ። ቁስሉ ቢቆጠቁጠውም እኔን ላለማስከፋት ፈገግታ እያሳየኝ "እስከዚህም አይደል ―" ብሎ በመጀመር ሊያፅናናኝ ሞከረ ። ከዚህስ ቢወቅሰኝ በተሻለ ። ፈገግታ ሲያሳየኝ ከዱላ የበለጠ ተሰማኝ ። ሲጎዱት የሚስቅ ምን አይነት ፍጡር ነው?

የዶክተር ገድሉን ሁናቴ ከሰማሁበት ጊዜ ጀምሮ መንፈሴ እረፍት አጣ ። ቀለበቷም ማፅናናቷ ቀርቶ ጭራሽ

ታስተከዘኝ ጀመር ። የቅዠቱ ነገርማ ለብቻው ነው ፤ አንዴ እኔው እራሴ ጦር ሜዳ ሄጄ ሳገኛቸው ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ መርዶ ሲመጣልኝ — እንዲሁ የሆነ ያልሆነውን ስቃዥ አድራለሁ ። ያለምክንያት ከእንቅልፌ መባነን የጀመርኩትም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ነበር ።

"በእርግጥ ዶክተር ገድሉ ጦር ሜዳው መሐል የገቡት በራሳቸው ፍላጎት ይሆን?" በማለት ራሴን ደጋግሜ ጠየቅኩት ። ለጊዜው ትክክለኛውን መልስ ባላገኝለትም ይህንን ካደረጉ የእኔ ነገር ተረስቷቸዋል ማለት ነው ብዬ ደመደምኩ ። የዶክተር ገድሉ ጦር ሜዳ መሐል ገብቶ መፋለም ትልቅ አስተዋጽኦ መሆኑን ብረዳውም በእፌ ሙሉ "ለእናት ሐገራቸው የፈለጉትን ይሁኑ" ለማለት ልቤ አልደፈረም ። የሀገር ፍቅር ስሜቴ ቁራጥ ሲያደርገኝ የዶክተር ገድሉ ፍቅር ደግሞ ሲያንገበግበኝ ለብዙ ጊዜ ቆየሁ ። ታናሽ እህቴም ይኸው ሁኔታዬ ስለገባት "እህት አበባ ፤ ከልኩ ለማያልፍ ነገር እንዲህ መጨነቅሽ ለምንድነው? የጥንቱ ጥንካሬሽ የት ደረሰ?" እያለች ማጽናናቷ አልቀረም ። ግን ማን ቢሰማ ፣ ለእፌ ያህል "ሀሳብ የሚባል ነገር ትቻለሁ" ብልም መንፈሴ እረፍት አልሰጠኝም ። ሰው በድን ካልሆነ በስተቀር ማሰቡ የት ይቀራል ! ።

የዶክተር ገድሉ ጓደኞች አልፎ አልፎ እቤቴ ድረስ እየመጡ ያጫውቱኛል ። አብሶ እሁድ ቀን ከቀትር በኋላ ያለውን ጊዜ የሚያሳልፉት ከእኔው ጋር ነው ። ይህም የሚሆነው (የያንዳንዳቸውን አስተሳሰብ ባላውቅም እንኳ) በእኔ በኩል ከልብ በመነጨ የእህትነት መንፈስ ነው ። አንዳንዶቹ ገደቡን የሳተ ቀልድ ይቃጣቸዋል ፣ በተለይ ዶክተር ፍስሐ —

አንድ ቅድሜ ከቀትር በኋላ ዶክተር ፍስን ብቻ ቸውን መጡ ። እኔም ከስራ ገብቼ አረፍ ማለቴ ነበር ።

"እንደምን ሰንብተሻል ሲስተር? ይህ የቀን መኝታ አይቀርብሽም እንዴ?" አሉና ከአልጋው ግርጌ ጠርዝ ላይ ተቀመጡ ።

"ከዛሬ በፊት ቀን ተኝቼ አጋጥሞዎታል እንዴ?" ይህንን ጥያቄ ሳይመልሱ ወደሌላ ጨዋታ በመዝለል "እግርሽ እንዴት ያተኩሳል? ጋቢውን አልፎ ይሰማል" አሉና በእጃቸው ነካ አደረጉት ።

እኔም የቅንነቴን" ለመቀመጥ አስቸገረዎት? ልሰብ ስብልዎታ " አልኩና እግሬን ለመሰብሰብ አጠፍ ሳደር ገው "ይሁን ይሁን" ብለው በእጃቸው ያዙት ።

ወዲያውም እየቀላለዱ እግሬን ያሻሹልኝ ጀመር ። የሆነ ነገር ሰውነቴን ሲወረው ተሰማኝ ። "እረፉ እንጂ" ለማለት እያሰብሁ ምላሴን ያሳሰረኝን ነገር አላውቀውም ፤ ዝም አልኳቸው ። በኋላ ግን ትኩሳቴ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የዶክተር ፍስኃ አዝማሚያ ደረጃውን ጠብቆ ከፍ እንደሚል ስለተሰማኝ "ምን ማድረግዎት ነው? የእ ርስዎ ቀልድ ደግሞ መላ ቅጡን አጣ" አልኩና እግሬን መንጭቄ ሰበሰብኩት ። በዚህ ጊዜ የዶክተር ፍስሐ ፊት በድንጋጤ ጥቁር አለ ። ፍላጎታቸውን በዚህ እንኳ ለ መረዳት ይቻል ነበር ።

ታናሽ እህቴ ከጓዳ ወጣችና "እህት አበባ ፥ ምሳ ደር ሷልና ወደ ሳሎን ብትመጡ ይሻላል" አለች ።

እኔም እላዩ ላይ ጣል አድርጌው የነበረውን ጋቢ እመኝታው ላይ ተውኩትና ወደ ሳሎን ሄድኩ ። ዶክተር ፍስሐም ተከትለውኝ መጥተው ፊት ለፊቴ ካለው ፎቴ ላይ ተቀመጡና ምግብ ቀርቦ መብላት ጀመርን ። ድንጋጤው ግን እስከዚያ ሰዓት ድረስ አለቀቃቸውም ።

"የዶክተር ገድሉን ወሬ በቅርቡ ሰምተዋል? ደብ ዳቤአቸውም ቆየብኝ" የሚል ጥያቄ አቀረብሁ ።

"እንዲያውም አልሰማሁም ሲሉ —"ካሉ በኋላ ጥቂት አሰብ አደረጉና "—ምን ዋጋ አለው ብለሽ ነው ፤

ጦር ሜዳ የሄደን ሰው በሙሉ ልብ መጠበቅ አይቻልም እኮ" አሉኝ ።

"እንዴትነ አገላለጽዎ አልገባኝም"

"ማለቴ —ጦር ሜዳ ሄደው የሚመለሱ ጥቂቶች ናቸው ። ስለሆነም የዘመተን ሰው መናፈቅና ስለእሱው አዘወትሮ ማሰብ ኋላ አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል ። ደግሞ እንዲህ አይነት ደካማነት ከእንቺ የሚጠበቅ አይደለም ። ሰው እንኳን ለእናት ሀገሩ ቀርቶ በእንቅፋትም ይሞታል ። ያንቺ በየወቅቱ ስለዶክተር ገድሉ ማሰብ ከምንም አያድነውም ። ከመጣ ይመጣል ፤ ከቀረም ይቀራል ። እንግዲያውማ ለእኔስ ጓደኛዬ አይደል"

"ይህ ሁሉ ከጥያቄዬ ውጪ ነው ፣ የእኔ ጥያቄ የዶክተር ገድሉን ወሬ ሰምተዋል?" የሚል ብቻ ነበር ። ንግግሬን አቋረጡና "እንዴት ከጥያቄሽ ውጪ ?" አሉ ። "ቢቃ በቃ ምን ጊዜም ጨዋታዎ —"አልኩና ልናገረው የፈለግሁትን መልሼ ዋጥሁት ።

ዶክተር ፍስሐ የሚናገሩት እውነትን አንተርሰው ቢሆንም ከተግባሩ ላይ የሉበትም ። ሌላው ቢቀር በሀኪምና ዶክተርነታቸው እንኳ ለህዝብ የሚሰጡትን አገልግሎት እንደግዴታ ይቆጥሩታል ። ራሳቸውን ለማሻሻልም ሆነ ሌሎችን ለመርዳት ያላቸው ምኞትም ሆነ ፍላጎት በጣም

የቀዘቀዘ ነው ። እኔም የሚያስቆጣኝ የማይሰሩትን ነገር ሲያነበንቡ መስማቱ ነው ። አብሶ ስለዶክተር ገድሉ ጨዋታ ባነሳን ቁጥር የሚያወሩልኝ ሁሉ እንደማይመለሱ እድርገው ነው ። አንድ ጊዜማ በአፋቸው ሙሉ "ገድሉ ይመለሳል ብለሽ መጠበቅ ጅልነት ነው" ብለውኛል ። ወዲያው ነገሩን በቀልድ ባይሽፍኑት ኖሮ መጣያችን ይህ ዕለት ነበር ።

በዚህ ዕለት ምሳ በልተን እንደጨረስን "በይ እንግዲህ ደህና ዋይ ፤ አንቺ መቼም ቀልድ አልዋጥልሽ ብሎሻል" በማለት ተሰናበቱኝ ።

እኔ ግን በእሳቸው ላይ ያለኝ ጥርጣሬ ከፍ እያለ በአፋቸው ከመቀለድ አልፈው እግሬን አሻሹልኝ ። ይህም አልበቃ ብሏቸው የዶክተር ገድሉን ነገር "ተይው"ሊሉኝ ቃጣቸው ። እንግዲህ ምን እስኪሉኝ እጠብቃለሁ ? ነገሩ ትልቅ ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት እቅጩን ልነግራቸው አሰብኩ ። ግን ደግሞ ፍላጎታቸውን ግልፅ እስካላመጡልኝ ድረስ እንደዚያ መናገሩ ሊያቃቅረን ይችላልየሚል ግምት አደረብኝ ። ነገሩ ደረጃውን ጠብቆ መፈንዳቱ ላይ ቀር የእኔ መጨነቅ እንዲያው ትርፉ መጨረሻው እንዲህ ሆነ ፤

በማግስቱ እሁድ ስለነበር የዶክተር ገድሉ ጓደኞች እንደወትሮው ሁሉ ሊያጫውቱኝ መጡ ፤ ዶክተር ፍስሐ

ቀደም ቀደም እያሉ ሌሎቹ ተከትለው ። ከቤቱም በራፍ እንደደረሱ ሞልቀቅ ባለ አነጋገር“ እንደምን አድረሻል ሲስተር ” አሉ ዶክተር ፍስሐ ።

ጊዜው ከቀትር በኋላ ስለነበር “እንደምን ውለሻል ማለትህ ነወ? ” በማለት አጠገባቸው የነበሩት ጓደኞቸው ተናገሩ ።

“ለእኔ የሁላችሁም ይሆነኛል ፤ ይልቅ ከርከሩን ትታችሁ ወደ ቤት ግቡ ” አልኩና ቀድሜ ወደ ፎቴው አመራሁ ።

ዶክተር ፍስሐ ለአነጋገሬ ልዩ ትርጉም በመስጠት “የሁላችሁም ይሆነኛል ? —” በማለት ብልግና አዘል ንግግር አሰሙ ።

“መቀለድዎት ነው? ” ከማለት ሌላ ምንም አልተና ገርኩም ። አብረዋቸው የነበሩት ግን በድንጋጤ ፊታቸው ሲጠቁር ታየኝ ። ነገሩን ለማቅለል ያህል “ተቀመጡአባ ካችሁ ፤ እንዲህ አይነት የአፍ ልምድ ምን ያደርጋል ብላ ችሁ ነው ” አልኩ ።

ዶክተር ፍስሐ “ማ?—” እያሉ ነገሩ ላይ ችክ ቢሉም መልስ የሚሰጣቸው አላገኙም ። ዝም ብዬ ከሌ ሎቹ ጋር ጨዋታዬን ቀጠልኩ ። ከእንግዶቹ መሐል ሶስቱ ጤነኞች ሲሆኑ ፤ ዶክተር ፍስሐና አንዱ ሌላ እን

ግዳ ከሞቅታም አልፎ መስከራቸውን ከንግግራቸው አረ ጋገጥኩ ። ጨዋታቸው ሁሉ በእንግሊዝኛ ሆነ ። በጨዋ ታችን መሀል "ስለዶክተር ገድሉ ምን ወሬ ሰምተሻል?" የሚል ጥያቄ ከአንደኛው ቀረበልኝ ።

የተጠየቅሁት እኔ ብሆንም የዶክተር ፍስሐ ጨኸት አላናገረኝም ። እሳቸው ቀድመው "ዘለአለም ስለ ዶክተ ገድሉ መጠየቅ ምንድነው? የጦርነቱ ነገር እንደሆን እሱ ባለበት አካባቢ እየተጧጧፈ ነው ። በዚህ ብቻ የእሱን ሁኔታ መረዳት ይቻላል ። ይልቅ እዚሁ በቅርብ ስላለነው እንጫወት ----"በማለት የፈለጉትን ተናገሩ ።

ዶክተር ፍስሐ በተናገሩ ቁጥር ሌሎቹ መሳቀቃቸው አልቀረም ። ጥያቄው በመደመም "ምን አይነት ንግ ግር ነው? "Sorry ! አዝናለሁ" ካሉ በኋላ ወደእኔ ዘወር ብለው "እባክሽ አንቺ አጫውቺኝ" አሉ ።

እኔም የዶክተር ፍስሐ ንግግር ስለከነከነኝ ሆዴ ቢያ ርርም ላይ ላዩን እየሳቅሁ " ---ይኸው ዶክተር ፍስሐ እንዳጫ ወቱን ይሆናል! ---"አልኩ ።

ዶክተር ፍስሐ "No No No !!! በመጥፎ አትተር ጉሚው " በማለት ነገሩን ለማስተባባል ቢሞክሩም ፤ ትተናቸው ሌላ ጨዋታ ቀጠልን ።

እየመጡ ከሚጠይቁኝ ውስጥ ሁለቱ በጣም ግሩም ሰዎች ናቸው ። ከእኔ ጋር የሚጫወቱትም ፍጹም በወንድምነት መንፈስ ነው ። በመጡ ቁጥርም ስለዶክተር ገድሉ መጠየቃቸውና እኔንም ማበረታታቸው የተለመደ ነው ። ታዲያ ሁሌም በዶክተር ፍስሐ ቀልድና ቧልት እንደተሳቀቁ ነው ። የዛሬውም ጨዋታ ቢሆን ሁሉንም አሳዝኗቸዋል ። እኔም ይህ ሁኔታ ስላታወቀኝ ቅር እንዳይለኝ "ተጫወቱ እንጂ" ማለቴ አልቀረም ።

ዶክተር ፍሥሐ ኪሳቸውን ዳበስ ዳበስ ካደረጉ በኋላ " ለካ ሲጋራዬን ጨርሻለሁ ፤ የሚላከኝ ሰው የለም እንዴ ፣ ሲስተር" አሉ ።

"ማንም የለም ፤ እህቴም ወላጆቿን ጥየቃ ሄዳለች"

"እንቺላ ብትሄጂ (ብትላኪኝ) ምናለበት፤ የእድሜው ነገር ቀርቶ በማዕረግ እንኳ አልበልጥሽም እንዴ ?" አነጋገራቸው በቀልድ ዓይነት ነበር ። ለማንኛውም ከመሳቅ በስተቀር ምንም አልመለስኩም "

"ገዝቼ እመለሳለሁ" ብለው ብድግ ሲሉ እንገዳገዳቸውና የፎቴውን ጠርዝ ተደግፈው ሳይወድቁ ቀሩ ።ስካ ራቸውን ለማስተባበልም "ብዙ ጊዜ ተቀምጨ ስነሳ እግ ግሬ ደንዝዞ እኮ ነው" አሉ ፤ ሁሉም ከንፈሩን ከድና ከመሳቅ ሌላ እንዳችም ቃል የተነፈሰ የለም ።

-ወጥተው እንደሄዱም የመገረም ሳቅ እየሳቅሁ "ያሳዝናል —" አልኩና ራሴን ነቀነቅሁ። እንደኛው ፣ "በጣም! በጣም! ልክ ነሽ፣ አብሶ በእኛ በሐኪሞች ዘንድ ይህ ሁኔታ እየታየ ሲላው ሕዝብ አትጠጣ አታጭስ ማለቱ ምንም ያህል ተቀባይነት እያገኝም" አሉ።

እኔም "እስኪ ይታያችሁ —" በማለት ንግግሬን ቀጠልኩ አንድ ሰው ሀ ብሎ ፊደል መቁጠር ከሚጀምርበት ጊዜ አንስቶ "ዶክተር" የሚባለውን መጠሪያ እስኪያገኝ ጊዜ ድረስ ብዙ ውጣ ውረዶች ማለፉ የማያጠራጥር ነው። ታዲያ ብዙ እውቀትን እንዳልሰበሰበ ሁሉ ጥሩና መጥፎ ነገሮቹን እንዳላገናዘበ ሁሉ የበሰጠ ጠልቶ በመመራመሪያው ጊዜ እንደገና ወደ ጥፋት መመለስ ምን ይባላል? ለመማር ለመመራመር የሚገንገውን መሣሪያ እንኳ ተስፋ ማስቆረጥ አይሆንም?

በዝምታ የቆዩት የጤና መኰንን ነገሩን በአንክሮ እንዳዳመጠ ሰው በሰፊው ተንፈሱና "ነገሩስ ልክ ነሽ ግን ትምህርት የሚጀምር ሁሉ ለከፍተኛ ምርምርና ለሕዝብ አገልግሎት እንዳይመስልሽ "ከመቼው ትምህርቱን ጨርሼ ገንዘብ ላይ ተቀምጬ" የሚል አለ። በአንፃሩ ደግሞ ትምህርትና ምርምር ገደብ እንደሌለው በማወቅ ለሕዝቡ ትልቅ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚደክም አለ"

በመሐል ዶክተር ፍስሐ ተመልሰው ስለመጡ ጨዋታችንን አቋረጥንና ለጥቂት ደቂቃዎች ፀጥታ ሰፈነ ። ውይይታችን ትምህርት ሰጭነቱ ቢታመንበትም ከምንነ ጋገርባቸው አብዛኛዎቹ በዶክተር ፍስን ላይ የሚታዩት ስለነበሩ ፊት ለፊታቸው ለማውጋት የደፈረ አልተገ ኘም ፤ ሁላችንም ዝም ብለን እንዳችን እንዳችንን መመ ልከት ብቻ ሆነ ።

ዶክተር ፍስሐ ሲጋራቸውን እያቦነኑ "ምነው ፀጥታ ሰፈነ? ተሟሟቱ እንጂ "ካሉ በኋላ ወደ እኔ ዘወር በማለት "ዝም ስትይ ደስ አይለኝም ፤ በይ እባክሽ ወሬ አምጪ ፤ መቼም ሲወራ ቢያድር የማይሰለችሽ የዶክተር ገድሉ ወሬ ነው"አሉኝ ።

"ይልቅ የእርስዎ ደጋግሞ ስለ ዶክተር ገድሉ ማን ሳት የፍቅር ይሁን የጥላቻ አልገባኝም "

ይህ አነጋገሬ በዝግታና በግዴለሽነት ነበር ። ወዲያ ያው ግን ግልፍ አለኝና በቁጣ ቃል ፤ "እንደ ፍላጎትዎ ምንድነው ? ምን ያስነውራል ? ባወራስ ?— በውነቱ ይህ ከእርስዎ የሚጠበቅ አይደለም —" አልኩ ።

ዶክተር መሐሪ "የዛሬው ጨዋታሽ ለዛውን አጣ" በማለት ለመሄድ ከመቀመጫቸው ተነሱ ፤ ሌሎቹም ተከትለው ብድግ አሉ "ምነው? ተሟሟቱ እንጂ" እንኳ አላልኳቸውም ።

ሆዴ እየተቃጠለ በፊቴ ላይ የመገረም ፈገግታ ማሳ የቴን አልገፋሁበትም ። እንዲያውም ብዙ ነገሮች በማሰ ላሰሌ እንባዬ ሲመጣ ተሰማኝ ፣ የእልህ እንባ በመሆኑም አይኔን አደፍርሶ ከመበጥበጥ ሌላ በጠብታ መልክ አልወ ረደም ። ዶክተሩን ዘልዬ ማንቁርታቸውን ማነቅ አሰኘኝ ፣ በጥርሴ ልቦጫጭቃቸው ፣ በጥፍሬም ልቦጫጭራቸው ፈለ ግሁ ፤ የሴትነትና የደካማነት ስሜት ፈጽሞ ከአጠገቤ ራቀ ። "አንቱ" የሚለውን አክብሮት ትቼ "አንተ" ያልኳቸውም በዚሁ ጊዜ ነው ።

"አንተ ! አንተ ! እውነት የዶክተር ገድሉ ጓደኛ ነህ ? በፍጹም በፍጹም ---- አይደለህም ---- የሰማይና የምድር ያህል የምትራራቁ ናችሁ --- በል አሁን ውጣልኝ ። መልክ ስክሉን የለመድክበት አድርገው" በማለት ጩኸቴን የለቀ ቅሁት ። በዚህም አልበቃኝ ። እሱም ወንድነቱን ለማሳየት ስለተጋበዘ እዚህ ላይ ልገልፀው የማይገባ የብልግና ስድብ ጭምር አወረድኩበት ። ይህ ሁሉ አላረካኝም ። የበለጠም ብናገር እሺሁ አለቀቀኝም ፤ ጭራሽ ያንቀጠቅጠኝጀመር ።

እህቴ ከጓዳ መጥታ የምታደርገው ጠፍቷት ዝምብላ ቆማለች ። ከይኳኋኗ እንደገባኝ ከሆነ አንድ ተራ ነርስ ዶክተሩን ስታዋርድ በማየቷ በጣም ሳትሸማቀቅ አልቀ ረችም ። እቋምም ለመወ ሰድ ያልደፈረችው በዚሁ ምክ ንያት ነው ።

## 23

በዚህ አይነት ከተለያየን በኋላ ባዶ ቤት ቁጭ ብዬ የቅርብ የሩቁን ሳሰላስል ታናሽ እህቴ ከተፍ አለች። የወላጆቼን ሁኔታም እያጫወተችኝ ንዴቴን ሁሉ አስረሳችኝ።

ጊዜው ጨለምለም ማለት ሲጀምር ዶክተር ፍስሐ ተመልሰው መጡ። ከተለያየን ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ ነው። ስካራቸው ከበፊቱ ጨምሯል። ለድፍረት እንዲየረዳቸው እንድ ሁለት መለኪያ ቀንዶ አረቄ በቁማቸው መጠጣታቸውን ለመገመት ያስቻለኝ መኮላተፍ የጀመረው ምላሳቸውና ቤቱን የአወደው የአረቄ ሽታ ነው።

የአማርኛ ቋንቋ ለጊዜው ተረስቷቸዋል ፤ ገና በሩቀን ገባ ሲሉ በእንግሊዝኛ "እንደምን አመሸሽልኝ ሲስተር" አሉ። ሁሉንም በሆዴ ይገር ቁጣም ሆነ ፈገግታ ሳላሳይ "ደህና ነኝ። የእኔ ጤንነት ይህን ያህል አሳሳቢ ከሆነ" አልኩ።

"እንዴት"

"እንደዚህ"

በዚህ ጊዜ ታናሽ እህቴ ከፍሉን ለቃልን ወጣች። ምን አስባ እንደሆነ ግን አልገባኝም። በጣም ግራ ተጋባሁ። ነገሩ ሁሉ ልዩ ምስጢር ያለው መሰለኝ።

“በእሁኑ ሰዓት ለምን መጡ፣ቀን አይተውኝ የለም እንዴ?” “ነውር ነው፤እንግዳ እንዲህ አይባልም” ካሉኝ በኋላ በእነጋገሬ ማዘናቸውን በእግሊዝኛ ገለጹ ።

በዚህ ስካራቸው ላይ ምንም ብናገራቸው ጉዳዩ እን ደማይሉት ስለማውቅ ዝም አልኩ ። በሁለታችንም በኩል ጸጥታ ሰፈነ ። የማልፈልጋቸው እንግዳዩ መሆናቸውን ለመረዳት ይህ ብቻ ነበር ። ለእሳቸው ግን ሁሉም አልተሰ ማማቸውም ። እንዲያውም ይውጣላት ብለው ነው መሰል ፣

“ሲስተር ፤ መውደድ ሐጢአት ነው እንዴ?” ብለው ጠየቁኝ ። ለጥቂት ደቂቃዎች ፀጥ ብለው ካሰቡ በኋላ ደግሞ “– መቼም እንደምወድሽ ታውቂያለሽ ፣ ታዲያ ይህን ያህል ሰው ማስጨነቅ ምንድነው ? ዛሬስ ሁሉንም ቁርጥ አድርጌ ነው የምነግርሽ” ካሉ በኋላ አሁንም በእ ንግሊዝኛ“በሴት ስቻገር እንቺ የመጀመሪያዬ ነሽ” አሉ ።

እንዳንዴ “መናደድ ሲበዛ ያስቃል” የሚለው አነ ጋገር ትክክል ነው ። እኔም ልቤ በንዴት ቅጥል እያለ ላይ ላዩን እስቅ ጀመር ። ቢገባቸውማ የሽሙጥ ሳቅ መሳቄ ለእሳቸው ከዱላ የበለጠ በተሰማቸው ነበር ፤ ሆኖም ከም ንም አልቆጠሩትም ፤ ያንኑ የንዴትና የመደነቅ ሳቅ እየሳ ቅሁ “እህህ” ከማለት ሌላ ምንም አልተናገርኩም ፤ ጭራሽ አዘንኩላቸው ። ከውስጣቸው በል በል ተናገር እያለ የሚ

ገፉፉቸው ነገር ያለ መሰለኝ ። ይህ ባይሆንማ ፣ እንዴት መጀመሪያውኑ መቆጣቱን የተመለከተ ሰው የባሰ ጥያቄ ያቀርባል?

አሁንም እንደገና ለመናገር ጭንቅ ጭንቅ ቢላቸውም በሰካር ላይ ፍርሃት በተጨመረበት የተኮላተፈ አንደበታ ቸው "ነውሩ ምንድነው ? እሙኛሽ እንደሆን በቅርብ የለም ደግሞም ከዶክተር ገድሉ አልቆረብሽም ። እኔ እውነቱን ልነገርሽ እፈልጋለሁ ። አፍቅሬሻለሁ ! ከዶክተር ገድሉ ሌላ አልፈልግም የምትይ ከሆነም በሕይወት ከተመለሰ የሱው ነሽ ። እስከዚያው ግን —አታስቀይሚኝ አደራ እስ ከመቼም ተደብቆ የሚቻል ነገር አይደለምና እንዲህ ቁር ጡን መነጋገሩ የተሻለ ነው"

ለብዙ ጊዜ ሲያብሰለስሉት የቆዩትን ሀሳብ በሰካር መንፈስ አስመስለው ዘከዘኩት ። እንዲህ ዓይነቱን ጉድ ምን ማድረግ ይቻላል ? ጓደኛቸው ትላንት ጦር ሜዳ ሂደው ዛሬ ከእኔ ጋር ድሪያ አማሯቸው ። በምን ዓይነት ልክ ልካቸውን ብነግራቸው እጠግብ ይሆን ? እልህ እየተ ናነቀኝ፣ በእውነቱ በዚህ ጊዜ ያሳዩሁትን ትእግሥት መቼም አድርጌው አላውቅም ። ንግግራቸውንም በዝምታ ማስጨ ረሴ ከበፊቱ ሁኔታዬ አንፃር በጣም ትልቅ ለውጥ ማሳየ ቴን ያመለክታል። ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላም ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ቤቱ ፀጥ አለ ። ።

ሌባን ሌባ ሲሉት የሚሸማቀቀውን ያህል ዶክተር ፍስሀም ያን ስድብ ሳወርድባቸው ሥራቸው ስላሳፈራቸው ብዙም ለመቆጣት አልሞከሩም ። “ ለንዴት ማብረጃ ” ሲጋራ ቸውን ለኰሱና ከቤት ውስጥ ፈትለክ አሉ ። እኔ የውጪውን በር እስኪያልፍ እየተከታተልኩ “ሁለተኛ እዚህ እንዳትደርስ ! አንተ ብሎ ዶክተር ፣ ሰውን የሚያስከ ብረው ሥራው እንጂ ስሙ አይደለም ። ደግሞ ለጓደኞች ህም ንገራቸው ። በራፌን እንዲረግጡ አልፈልግም ! ነገም እነሱ እንዳንተው ይሆናሉ—”እያልኩ ተወ ረገረግሁበት ። ብዙ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በጣም ሲበሳጩ ከመጠን በላይ ሲውረገረጉ ስመለከት ለማስመሰልና ለጉራ ይመስለኝ ነበር ። ዛሬ ግን በእኔም ላይ የደረሰው ይህ ሁኔታ እርግ ጠኛነቱን አሳወቀኝ ። የማደርገውን አሳጣኝ ። አጠገቤ ብር ጭቆ ወይም ሌላ እቃ ቢኖር ወርውሬ ከመፈንከት ወደ ኋላ አልልም ነበር ። ምን ብናገር ፃን ብሳደብ አልበርድ ልሽ አለኝ ። ወደቤትም ተመልሼ ገብቼ እየተንሰቀሰቅሁ አለቅስ ጀመር ። ሌላ ሰው በተናገረኝ ይህን ያህል ባላስቆ ጣኝም ነበር ። ነገር ግን የዶክተር ገድሉ ጓደኛ ተብለው አደራ የተሰጣቸው ዶክተር ፍስኅ እንዲህ ሆነው በማግ ኘቴ ሀዘኔ ፍፁም ገደብ አጣ ።

እንደገና ዶክተር ገድሉን እያስታወስሁ መንሰቅሰ ቁን ቀጠልኩ ። መናደዴን በማየት ለማነጋገር የፈራችኝ ታናሽ እህቴ ስትፈራ ስትቸር ወደ እኔ ቀረበችና “እባ

ክሽ ሁሉንም አርሺው ። አሁን ራት ላቅርብና ብይ ፤ እረ እንዲህ አትሁኚ እት አበባ” አለችኝ።

ከአጠገቤ እንድትሄድልኝ ያህል “እሺ አቅርቢ”አል ኳትና ምግቡን ለማቅረብ ወደ ጓዳ ገባች ። በዚህ ጊዜ የራ ሴን ሁሉ ተወት አደረግሁትና ስለ እርሷ አስብ ጀመር ። በሆዴም “ወደፊት እንቺም እህቴ ብዙ ችግር ይገጥምሽ ይሆን?” በማለት ስትወጣና ስትገባ በትካዜ አይን አይኗን ተመለከትኳት ። ወዲያውም ደግሞ በቤተኛ አዳሪነት የም ትኖር ዘመንዷ ያስጠጋች ቤት ሁናቴ ፊቴ ላይ ድቅን አለ ብኝ ። ይህን ሁናቴ ከእኔ ጋር ያዛመድኩበትን መንገድ ግን አላውቅውም ። ከብቸኝነታችን ሌላ ኑሮአችን ከቤተኛ አዳሪ ጋር የሚመሳሰልበት ምንም ሁኔታ አልነበረም ። ብቻ በማላውቀውና ባልጠበቅሁት መንገድ ብዙ ነገሮች እየታወሱኝ መተከዜን ቀጠልኩ ። እንባዬም ለዚህ እለት የተጠራቀመ ይመስል በሰፊው ጎረፈ ። ምግቡም ቀርቦ ሳይበላ እንዲሁ ተመለሰ ።

ለወጉ ያህል መኝታዬ ላይ ወጣሁ ። እንቅልፍ ከየት ይምጣ? የቆጥ የባጡን እያሰብኩ መገላበጥ ብቻ ሆነ ። ዓይኔን ጨፍኜ ተሸፋፍኜ በመተኛት ከሃሳብ ለመገላገል ሞከርኩ ። ይህም ከንቱ ድካም ሆነ ። በምንም መንገድ እንቅልፍ አልመጣልሽም አለኝ ። ቢቸግረኝ መብራቱን አበራሁና ጋደም ብዬ መጽሐፍ ለማንበብ ጀመርኩ ። እን ዱንም ሳላውቀው አራትና አስራአምስት ገጾች ከመጓዝ

በስተቀር ምንም ፍሬ አላገኘሁበትም ። እንደገና ወደኋላ እየተመለስኩ ባነበውም “እዚያው ሞላ እዚያው ፈላ” እንደሚባለው ሁሉ መስመሮችን ደጋግሜ ከማየት በስተ ቀር በደንብ ማስተዋል አልቻልኩም ። ሃሳቤ ሁሉ በፀቡ ጊዜ የነበረውን ሁናቴ ማስታወስ ብቻ ሆነ ። የእኔና የዶክተር ፍስሓ ፀብ መጽሐፍ ላይ የቀረበ ይመስል በዓይኔ ላይ እየሄደ እልህ ይተናነቀኝ ጀመር ። መጽሐፉን ከደን ኩና ተመልሼ ተኛሁ ። መቼም መድከም አይቀርምና ከብዙ ሃሳብ በኋላ ተረታሁ ። እንቅልፍ ወሰደኝ ።

24

ጠዋት ስንቃ ከወትሮ የመነሻ ሰዓቴ አሳልፌ ነበር ። የመሥሪያ ቤታችንም መኪና (ሰርቪስ) ጥሎኝ ሄዶአል ። እየከነፍኩ የሕዝብ አውቶቡስ ወደሚገኝበት ሄድኩ ።

የአውቶቡሱን መምጣት ቆሞ የሚጠባበቀው ሕዝብ ብዛት ይህ ነው አይባልም ። ሁሉም ደግሞ ለየጉዳያቸው የተጣደፉ ናቸው ። አንድ ታክሲ የመጣች እንደሆን ለማ ስቆም ሲረባረቡባት የጉድ ነው ። ባለታክሲዎቹም የሕዝ ቡን ችግር በማየት የሚናገሩትን ዋጋ አሳድገውታል ። አብዛኛዎቹ ሰዎች ከገንዘቡ ይልቅ ጉዳያቸውን ይቅደም በማለት የተጠየቁትን ከፍለው እየተሳፈሩ ይሄዳሉ ። እኔም ያለኝ አማራጭ ይህ ብቻ ነበር ። የተጠየቅኩትን ከፍዬ

መሥሪያ ቤቴ ለመድረስ ወሰንኩ ። በዚህ ጊዜ ደግሞ ታክሲ የሚባል ነገር ጠፋ ። አልፎ አልፎ አንዳንድ ብቅ ቢሉም የሞሉ ብቻ ነበሩ ። ሕዝቡ ለሽሚያ መሀል መንገድ ድረስ ገብቷል ። የሰዓቱ መርፌ ድ የሚያጠያይቅ ነው። የማታው ብስጭት ሳይለቀኝ እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ተጨመረበት ። ከብስጭቴ የተነሳ ፀጉሬን ልነጨው ምንም አልቀረኝ ። ተስፋ ቆርጬ ወደ ቤት ለመመለስ አሰብኩ ። ወድያው ግን አውቶቡሱ ሲመጣ ከሩቅ ታየኝ ። እሱም ጢቅ ብሎ ሞልቷል ። ሕዝቡ ግን ከወዲሁ መጋፋቱን ቀጠለ ። አውቶቡሱን እንደሚልፈግ ሰው ከዳር ቆሚ እመለከት ጀመር ። በአውቶቡሱ ውስጥ ባለው በታና መሬት በተኮለኮለው ሕዝብ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ ። ሹፌሩ ሳያቆም ሊሄድ ሳያስብ አልቀረም ። ሆኖም ሕዝቡ መሀል መንገድ ድረስ ገብቶ በእጁም በእፉም ስለለመነ ለማቆም ተገደደ ።

በዚህ ጊዜ የነበረውማ ጭራሽ አይነሳ ! ዱላ ቀረሽ ሆነ ። መተዛዘን ፣ መከባበር የሚባል ነገር ፈጽሞ ጠፋ ። የፈረደባት ትኬት ቆራጭ "እባካችሁ ቀስ በሉ ። ግማሽ ቻችሁ በመሀል በር ግቡ ። ማንቲሙን በእጅ በእጃችሁ ያዙ" እያለች ጩኸቷን ቀጠለች ። የተሳፋሪውም ቁጣ የዛኑ ያህል ነበር "በሰዓታችሁ ለምን አትደርሱም ? ምን ያህል እንደተገተርን ታውቂያለሽ ?" የሚለው የቁጣ ቃል በሰፊው አስተጋባ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ለመሳፈር ምንም ሙከራ አላደረግ ሁም ፤ ጎዴቴም ቀረና የተሳፋሪውን መረባረብ እንደ ቴያትር እመለከት ጀመር ። ስለችግሩም በማሰብ ሐዘን ተሰማኝ ። ማዘኑ ብቻ ግን ምንም ዋጋ እንደሌለው ተገንዘብኩ ። ይህን ሁሉ ማሻሻል የሚቻለው ሕዝቡ ራሱ ከቀን ወደቀን እያደገ እያሳደገ በሚሄደው የሥራና የዕውቀት መጠን መሆኑን ተረዳሁ ።

አውቶቡሱ ቀድሞውኑ ስለሞላ ከስምንት ሰው በላይ ማሳፈር አልቻለም ። ስለሆነም ፣ በትንንቅ በሩ ተዘግቶ የተቀሩትንም እዚያው ጥሏቸው ሄደ ። ለዚህስ እንኳን ያልተጋፋሁ በማለት ራሴን አጽናናሁ ። አሁንም ሌላ አውቶቡስ መጣ ። ከፊተኛው ጋር በሶስት ደቂቃ ያህል ቢለያዩ ነው ። ይኸኛው ግን የያዘው የሰው መጠን አነስ ያለ ስለነበር እኔም በዚሁ ለመሄድ ግፊያው መሀል ገባሁ ። እንደምንም እየተገፋፋን ተሳፈርን ። አሁንም አውቶቡሱ ጢቅ ብሎ ሞላ ፤ መሬት ግን አንድም ሰው አልቀረም ።

በዚህ ዓይነት ጉዞአችንን ቀጠልን ። በድምጽ ማጉያው "ተጠንቀቁ ኪሳችሁን ጠብቁ !" የሚል ቃል ከሾፌሩ ሲነገር ተሰማ ። ሁሉም ኮቱን ሰብሰብ እያደረገ "እባካችሁ ወደ ፊት ተላለፉ !" በማለት ራሱን ይጠብቅ ጀመር ። እኔም በግራ እጄ አንዱን ወንበር ብረት ጨብጬ ቆምኩ ። የሥራው ሰዓት መርፈድ ስለታወቀኝ መንፈሴ

ተረበሽ ። እውቶቡሱን እየገፋሁ በፍጥነት ማስኬድ የም
ችል ቢሆን ኖሮ ባደረግሁት ነበር ። በአጭሩ በጣም የተ
ቻኮለ ሰው ከሚሰማው የመቁነጥነጥና የመቆጣት ስሜት
ጋር ማገናዘብ ይቻላል ።

በጉዞአችን ላይ እኔ በቆምኩበት አካባቢ ጥጉን ይዞ
የተቀመጠ አንድ ሰው ከመቀመሪያ ጀምሮ በስርቆት ይመ
ለከተኝ ነበር ። ዓይን ለዓይን ስንገጣጠም ወደ ሌላ ይመ
ለከታል ፤ ወዲያው ደግሞ ዘወር ብሎ በመቅለስለስና በጉ
ጉት ዓይን ይመለከተኛል ። ለአንድ አፍታ ያህል እኔም ዓይ
ኔን ከርሱ ሳልነቅል ትኩር ብዬ ብመለከተው ፣ ሀፍረትም
ድንጋጤም ተጫጫነውና ፊቱን አዙሮ በመስታወቱ በኩል
ወደ ውጭ ይመለከት ጀመር ። ሆኖም ጥቂት ሳይቆይ
ወደ እኔ ዞሮ በመቅለስለስ መመልከቱን ቀጠለ ። ነገሩ
ግራ ገባኝ ። በአንድ በኩልም የሰውዬው ስሜት ገባኝ ፤

የጥንቱ በሽታዬ (ወንድ ሲያየኝ የምሳደበው) ተቀሰ
ቀሰብኝ ። ይህ የሆነው የማታው ብስጭትም በጭንቅላቴ
ውስጥ ስላለ መሰለኝ ። ፊቴን ኮስቴር አድርጌ "ምን ፈለ
ግህ ?" እልኩና ተቆጣሁ ። የሰውዬው ፊት በድንጋጤ
ተዋወጠ ። ወዲያውም ወደ ሌላ ይመለከት ጀመር ።
በአካባቢዬ የነበሩትም ሰዎች "ምን ገጠማት ?" በማለት
ወደ እኔና ወደ ሰውዬው አተኩረው ተመለከቱ ።

“ምን ሊሆን እምርት ይሆን?--” የሚለውን ቃል ደገምኩ። በዚህ ጊዜ እሱም በቁጣ መልክ “መታየትን የሚጠላ ከቤቱ አለመውጣት ነው!” አለና አፈጠጠብኝ። በእሱው ብሶ ቁጭ አለ። የግልምጫው ዓይነትማ ከአፈር ይደባልቃል። በማጉረምረም እየተሳደብኩ ከዚያ ቦታ አልፌ ወደ ፊት ሄጄ ቆምኩ። የሰውዬው ዓይን ግን እስከዚያ ድረስ እንደተከተለኝ ነበር። አስተያየቱ እንደ በፊቱ በመቅለስለስና በጉጉት ሳይሆን ቁጣ ባዘለ መልክ ነው። እኔም መውረጃዬ ስለደረሰ አውቶቡሱን ለቅቄ ወጣሁ።

በኋላ ግን የራሴ ሥራ እስገረመኝ። እንዲያው ተናደጂ ቢለኝ ነው እንጂ አንዳንድ ወንዶች ሥራዬ ብለው ሴቶችን በዓይን መቃኘታቸው እንደሆን የተለመደ ነገር ሆኗል። በማየት ይጠግቡ ይመስል ትንኮል ባዘለ መልክ የሚያዩ ወንዶች ጥቂት አይደሉም። አንዳንዶቹም ሆን ብለው የሴቶቹን ቅርጽ እየተመለከቱ “እንትኗ በዛ፣ እንትኗ አነሰ---” በማለት አቃቂር ሲያወጡ ይውላሉ። በእኔም ላይ ያለ ምክንያት አትኩሮ መመልከት ሲደርስብኝ የመጀመሪያ ጊዜዬ አልነበረም። ሆኖም በብስጭቱ ተደራቢ ሆኖ በመምጣቱ ሊያስቆጣኝ ቻለ።

ከመግቢያው ሰዓት አርባ ደቂቃ ያህል አሳልፌ ከመሥሪያ ቤት ደረስኩ። ደግነቱ በሥራዬ ላይ ስለማላለምጥ ማንም ሰው መዘግየቴን በትንኮል አልተረጐመብኝም። የሥራ ሽርጤን አጥልቄ ሕሙማኑን ከጐበኘሁ በኋላ ለአንድ

አፍታ ያህል መቶ አለቃውን እንጋግሬ መመለስ ዘወትራዊ ተግባሬ ሆኗል ። በዛሬው እለትም ሄጄ አነጋገርኩት ።

ወደ ሥራ ክፍሌ ተመልሼ ከዶክተር አብርሃም ጋር ሕመምተኞቹን በምጐበኝበት ጊዜ ከዶክተር ፍስኀ ጋር የነበረው ግጭት ፊቴ ላይ እየተደቀነብኝ መቃጠሌን አልተውኩም ። አብሶ አንዳንድ የሥራ አለመግባባቶችና ድክመቶች ሲፈጠሩ ዶክተር ገድሉን እያስታወስኩ ትካዜዬ እየባሰ መጣ ። እያደር ፣ ከዚህ ሁሉ ለመውጣት ራሴን በሥራና መጽሐፍ በማንበብ ለማጥመድ ብሞክርም ከንቱ ሙከራ ሆነ ። የእስከአሁኑስ እንዲያው ነው ። ትዝታ ፣ ናፍቆት ፣ ትካዜ ተደራርበው ያስቃዩኝ አሁን ነው ። ከጓደኛ አይሉት ጓደኛ የለኝ ። ከፍቅር አይሉት ፍቅረኛ ርቆኝ ፣ ወይ ለወላጆቼ አልሆንኩ ፣ ባለእደራነቴ ከብዶኝ ብቻዬን ቀረሁኝ ። ደህንነቴን ጠያቂዎቼም እየመነመኑ ሄዱ ። ዶክተር ፍስሃም ድራሻቸው ጠፋ ። ከዚያች ዕለት በኋላ ምንስ ሊያደርጉ ይምጡ ? የእሳቸው አልገረመኝም ፣ ሌሎች ጓደኞቻችውም ራቁኝ ። ምን ሰምተው ይሆን - - - ? ናፍቆት ፣ ብቸኝነት ተነባበሩብኝ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሰውነቴም ሁኔታ እየተሰዋ ወጣ መጣ ።

የዶክተር ገድሉ ወሬም ጠፋ ። አንዳንድ ጥያቄዎችን ባስታወስኩ ቁጥር እየሄድኩ የምጠይቀውና ትንሽ የመንፈስ እረፍት የሚሰጠኝ መቶ አለቃም ቁስሉ እየሻረለት በመሄዱ ከሐኪም ቤት ወጣ ። እንዳንዴም ስተክዝ አንዴም ስጽናና ከዶክተር ገድሉ ደብዳቤ ሳይደርሰኝ ስምንት ወር ያህል ቆየሁ ።

25

ማንኛው ነገር ከልኩ ሳያልፍ መጨነቅና መተከዙ ዋጋ አልነበረውም ። ጊዜውን ይጠብቃል ። የዶክተር ገድሉ ደብዳቤም ጊዜውን ጠብቆ ደረሰኝ ።

መጋቢት 1970

እዜቢና ! የጽሑፉን ብዛት ስትመለከቺ በእኔ እጅ መጻፉን ትጠራጠሪ ይሆናል ። ግን ፈጽሞ አትጠራጠሪ ፤ የኔው እሥረኛሽ ጽሕፈት ነው ። ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆንሽ ያው የተወላጋገደው የፊደል አጣጣሌ ነው ። በየጊዜው ያጋጠመኝን ስሜቴን ፣ ትዝታዬን ፣ ያየሁት ፣ የሰማሁትን ሁሉ እንደመጣልኝ የጫጫርኩት ትውስታዬ ነው --- ፋታ ባገኘሁ ቁጥር ። እኔም የፃፍኩት ሁሉ ትርጉሙ አይገባኝ --- እስቲ አንቺ ጭራና ቀንድ አውጭለት - - ዝግት አርገሽ ቤትሽን ደጋግመሽ በማንበብ --- እና የገባሽን ያህል ጻፊልኝ ---

ጥቅምት 1970

አራተኛው ሳምንት ላይ የጦርነቱ ሁኔታ በጣም አስ ከፊ እየሆነ መጣ ። እኛም ሌት እንቅልፍ ቀን እረፍት ሳንል በሥራ ተወጠርን ። እንዲህም ሆኖ የቁስለኞችን ብዛት መቋቋም አልቻልንም ። ይህንኑ ችግር በመመልከት አራት ዶክተሮች ተጨመሩልን ። እረፍት ሳይሆን ፋታ አገኘን ። ስለ ዶክተሮቹ ፀባይና የሥራ ሁኔታ እምብዛም አላውቅም ፤ አብረውኝ የቆዩት አራት ቀን ብቻ ስለሆነ ፤ ቁስለኞቹን ከጦር ሜዳ ወደ ሐኪም ቤቱ የሚያመላል ሰው መኪና ቁጥር ጥቂት ነው ። አንዳንዴ ቁስሉ የጸና ባቸው ሐኪም ቤት ሳይደርሱ እዚያው መኪናው ውስጥ የሚሞቱበት ጊዜ አለ ። አንዳንዴም መኪናው ቁስለኞ ቹን እንደያዘ በጠላት ፈንጂ የሚጋይበትም ጊዜ አለ --- መፍትሔውን እየፈለግን ነው ።

ህ ዳ ር 1970

መፍትሔውን ያገኘን መሰለኝ ፤ በቅርባችው ተገ ኝተን ለመርዳት ወሰንናል ፤ በዚህም መሠረት ከዚያው ካለነው ውስጥ ጥቂቶቹን በሆስፒታሉ እንዲቀሩ አድር ገን ጥቂቶቻችን ወደ ግንባሩ ለመዝመትተዘጋጅተናል ።

በሙሉ ልባችንም ቆርጠን ስለተነሳን አገልግሎታ ችን መልካም ውጤት እንዲኖረው እንጠራጠርም --- ይህ ንንም ስል አንዳንዴ ጥርጣሬ አይገባንም ማለቴ አይደ

ለም ። ጦር ሜዳ የዘመተ ሁሉ በሙሉ ልቡ ቆርጦ የተነሳ እንዳይመስልሽ ! ግዳጇን ለመወጣት ያህል ብቻ የግብር ይውጣ የሚሠራው ጥቂት አይደለም ። ያኑ ያህል ደም በሚፈስበት ፣ ያን ያህል ሕዝብ በሚዋደቅበት የተግል ሜዳ እንዲህ ዓይነት አዝማሚያና አቋም ማሳየት እጅግ አስከፊ ነው ።

ህዳር 1970

ሳንውል ሳናድር የሕክምና መሣሪያዎች የተከተተበ ትን ቦርሣ በቀኝ ክንዳችን ፣ ጠመንጃውን በግራ ትክሻችን አንግበን ጉዞአችንን ቀጠልን ። ፍርሃት የለ ። ወደ ኋላ ማሰብ የለ ። ሶስታችን ናኒን ከመካከላችን አድርገን ። ምን ዓይነቷ ቆራጥ መሰለችሽ ! የተኩስ ድምጽ ከሩቅ ሲያስ ተጋባ እንኳንስ እንደሱዋ ዓይነቷ ወጣት ይቅርና ብዙ ችግር አልፈናል የሚሉትን ጆግኖች እንኳ ያስበረግጋል። እሱዋ ግን ከምንም አትቆጥረውም ፊቷ ላይ መደናገጥ አይታይባት ፣ ጭንቀት አይሰማትም ፣ ቤትነቷ አያሸማ ቅቃትም--- ምንንም ምንንም እርግፍ አድርጋ ትታ የፊት የፊቷን ብቻ የምታስብ ፣ በወገናቹዋ መድማትና በድንበሯ መደፈር የምትቃጠል ፣ ልበ ሰፊና ቆራጥ ኢትዮ ጵያዊ ናት--- መንገዱን ተያያዝነው ። አንዳንዴ ግራ ቀኝ መልከት ትልና "--- ጠንቀቅ በሉ! ጦርነቱ እኮ የሚጀመረው ከዚሁ ነው" ትለናለች ---እዬ ናኒ!

ሚሊሺያ ይዞ ወደ ጦር ሜዳ የሚሄድ ትልቅ መኪና ሲመጣ ከሩቅ ተመለከትን ። አጠገባችን እንደደረሰ ሹፌሩ በመስኮት በኩል አንገቱን ብቅ አደረገና "ወደ ጦር ሜዳው ነው ፤ ጓዶች" ሲል ጠየቀን ። ለተጠየቅ ነው ጥያቄ "አዎ" የሚል መልስ ሰጠንና ከኋላ በኩል ለመሳፈር ቦርሳችንን አንገታችን ውስጥ እያጠለቅን ስን መቻች ከሹፌሩ አጠገብ የተቀመጠው ወታደር "ታዲያ ብቻችሁን እንዴት መጣችሁ ፤" የሚል ጥያቄ አቀረበ ልን ።

እንደተጠራጠሩን ስለገባን መታወቂያችንን አሳየና ቸውና የተነቃነቅንበትን ሆስፒታልና ምክንያቱን በአጭ ሩ ገለጽንላቸው ። መቀመጫዎቹ በሚሊሺያው ሠራዊት ተሞልተው ስለነበር ፣ የሸራ ማሳረፊያውን ተሳሳፊ ብረት ይዘን ቆምን ። ዘማቾች ጨዋታቸውን ቀጠሉ ። ዜማ ውም ሆነ ጨዋታው በተለያዩ ብሔረሰቦች ቋንቋ ቢሆ ንም ሁኔታቸው ስለነሸጠን በጭብጨባ አጀብናቸው ።

ናኒን በፈገግታ እየተመለከትኋት "በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው ፣ ሞቅ ፣ አድርገሽ አጨብጭቢ !" አልኩ ። እሱዋም በቀልድ መልክ "አዎ ! የጥይቱን ድምጽ ለመ ዋጥ የእኛ ጭብጨባ ከፍ ማለት አለበት" አለች ።

"ኧረ ቀልዱ ቀርቶ ፣ ለወገኖቻችን በፍጥነት መድ ረሳችንን ማመልከቻ ይሆነናል ። ለሞራሉስ ቢሆን ፣ ይልቅ

ሆ በሉ አጨብጭቡ ! ” በማለት ዶክተር ዘውገ ተና ገሩ ። ዘውገ ከሆስፒታሉ አብሮን የተንቀሳቀሰ ዶክተር ነው ።

ሆሆታው ቀጠለ ፣ ማንደፍሮን ባይኑቱ በጩኸት በእልልታ ተሰማ ። ጠመንጃውና የሚሊሺያው ልብስ አጠገባችን ባይኖርማ ጦር ሜዳ መሄዳችንን ሳንዘነጋው እንቀርም ነበር ። በዚህ ዓይነትም ፥ ወደ ጦርነቱ እየተቃረ ብን ስንሄድ እንኳ ፥ ድምፃችን በፍርሃት አልተቀነሰም ፣ ጭራሽ ፋከራውና ሽለላው ብሶበት ነበር ።

--- መኪናው በድንገት ቀጥ አለ ። እኛም ጨዋታ ችንን አቆምን ። ጋቢና ውስጥ የተቀመጠው አዝማች ወደ ኋላ በምታሳየው ቀዳዳ አንገቱን ብቅ አደረገና “እዚህ ቦታ ተጠንቀቁ ! ሽፍቶች በተደጋጋሚ አደጋ የጣሉበት ቦታ ነው ” አለ ። አማርኛ ለማያውቁትም ተተረጐመላቸ ውና መኪናው እንደገና በዝግታ ተንቀሳሰቀሰ ። ከሞተሩ ጩኸት በስተቀር የሰው ድምጽ የሚባል ነገር ጠፋ ። ለአንድ አፍታ ያህል ፀጥ ረጭ አለ ። ፍርሃትና ድንጋጤ በአንዳንዶቻችን ፊት ላይ ይነበብ ጀመር ። የዚች የነፍስ ጉጉት ምን ቢያደርጉት ይለቃል ፣ ስንጮህ ስንጨፍር መጥተን ተግባሩ ላይ ስንደርስ መደናገጣችን ራሳችንን መልሶ አስገረመን ። ብዙዎቻችን ፊታችንን በማኮሳተር ለጠላት የማንበገር መሆናችንን ለማሳየት ብንሞክርም ፣

ከውስጣችን የሚመነጨውን የድንጋጤ ስሜት መግታት አልቻልንም ። የጠመንጃችንን አፈሙዝ ገትረን ግራና ቀኙን ማየት ብቻ ሆነ ።

ምድር ሰማዩን የሚያደባልቅ የሚመስለው የተኩስ ድምጽ ጦርነቱ ግንባር መድረሳችንን አበሰረልን ። ከተ ሳፈርንበትም መኪና ዱብ ዱብ እያልን ወረድን ። ዓይና ቻችን ጠላት ባደረሰው ጉዳት ላይ አረፍ ። ---- ልባችን በኃይል መምታት ጀመረ --ስሜታችን ተቀሰቀሰ----- በገዛ አገራችን ተፈሩ ሥር እየወደቁ እየተነሱ ከጠላት ጋር በመፋለም ላይ ያሉትን ወገኖቻችንን ተመለከትን ። ለአንድ አፍታ ያህል ቆም ብለን አካባቢውን ወደ ግራም ወደ ቀኝም ወደ ኋላም ወደ ፊትም ማተርነው ። የሚጠ ብቀንንም ረዥም ጉዞ ተገንዘብነው ፤ እጆቻችንን እያጣ ጠፍን ፣ በቆራጥነትና በሙሉ ልብ ገባንበት ----

ህዳር 1970

የኔዋ አዜብ ፣ ባለፈው ደብዳቤዬ--ካንቺ ጋር የምንገ ናኝበት ጊዜ ይቃረብልኝ ይሆናል ብዬ መጻፌ ትዝ ይለ ኛል ። ግን አሁን ሳየው ከንቱ ማጓጓት መሰለኝ ። ያንጊ ዜም በምጽፍበት ጊዜ ቢሆን እየተጠራጠርሁ ነበር ። እያ ደር ነው ሁሉ ነገር የሚከሰተው --- እና እኔም አሁን እያደር ተሰማኝ ፤ ገና ረዥምና መራራ ትግል እንደሚጠ ብቀኝ--ጥንቱንም ቢሆን አነሳሴ ጦር ሜዳውን ተሳልሜ ለመመለስ አልነበረም ፤ ሆኖም በደበልቀ ግልጽልጽ ብሎ

የታየኝ አሁን ነው ፤ ጠላትን አባርሮ መመለሱም ብቻ በቂ እንዳልሆነ --- በጠላት ድራሹ የጠፋው ደናችን ፣ ወድቀውና ተበታትነው የቀሩት ወገኖቻችን ፣ በእሳትና በአይሮፕላን የተደበደቡት ቤቶችና ዘር አጥተው የተቀመጡት ለም መሬቶቻችን ሁሉ የእኛኑ እጆች እንደሚጠብቁ --- ትግላችንን በዚህ መስመር ማጠናከር እንዳለብን --- የአንቺና የእኔም መገናኘት ይህን ሁሉ አልፌ በሕይወት የቆየሁ እንደሆን ብቻ እንደሆነ -- ይህን በም ጽፍበት ጊዜ በአንቺ ላይ የሚወድቀውን ትካዜና ሐዘን አልዘነጋሁትም ፤ ግን ምን ማድረግ ይቻላል ? አንቺም በእኔ ቦታ ብትሆኚ ከዚህ የተለየ አቋም አትወስጂም -- ጠላት ካልሆነ በስተቀር ያንን ሁሉ እልቂትና ጭካኔ እያየ በቸልተኝነት የሚያልፍ ከቶስ ማን ይገኛል ?---

ግንባር ላይ እንደተሰለፍን ወደ ማታ ገደማ አንድ ከባድ አደጋ የደረሰበት ወታደር አጋጠመን ። ሕክምና የጀመርነው በዚሁ ሰው ነው ። ቁስሉ ከባድ ቢሆንም ቅሉ በትኩስነቱ እርዳታ በማግኘቱ ትንፋሹ ሊመለስ ቻለ ። በዚህ ጊዜ ሶስታችንንም ዓይኑን ገለጥ በማድረግ ተመለከተና "እባካችሁ ወደፊት ሂዱና ርዷቸው ፣ ብዙ ጓዶቻችን እየቆሰሉ ነው ፤ ቶሎ ድረሱላቸው" በማለት ተናገረ ።

ናኒ በሁኔታው በመገረም " ያንተ ሕክምና በቃ ማለት ነው ?" ብላ ጠየቀችው ፤ በእናታዊ አንደበት ።

"እኔስ እንደ ነኝ ። ማሰብ ከፊታችሁ ላሉት ለብዙ ዎቹ ነው እንጂ ፣ ብሞትም ደግሞ አይቆጨኝም ፤ የልቤን አድርገሻለሁ" እያለ ሲቃ ተናነቀው ። በእሱ ሁኔታ እኛም ሲቃ ያዘን ። የሁላችንም ፊት ተለዋወጠ ። ከራሱ ነፍስ ይልቅ ለተቀሩት ወገኖቹ ያደላው የእንዲህ ዓይነቱ ሰው ጥንካሬ ለእኛም ተረፈን ። በዚህ ጊዜ በድንገት ተኩስ ተከፈተብን ። ቁስለኛው " እኔን እዚሁ ጨርሱኝና ሂዱ ። ጠላቶቼ እንዳያገኙኝ --- " እያለ መጮህ ጀመረ ። ደፍሮ ይህን የፈጸመ ግን የለም ። ሶስታችንም እየ ተወረወርን በመውደቅ ትላልቅ ድንጋዮችን ከለላ አድር ገን ተኛን ። ወደ ተተኮሰበት አጠፋውን እንመልስ ጀመር ። የመጀመሪያ ጊዜያችን በመሆኑ መደናገጣችን አልቀረም ።

ተኩስ ከፋቾቹ አከታትለው ተኩሱና ወዲያው አቆሙ ፤ እኛም አድፍጠን ፀጥ አልን ። መሬት ለመሬት እየተንከባለልንም ደህና ደህና ምሽጉች ወዳሉበት ስፍራ አመራን ። ከሁለታችንም በኩል የተኩስ ድምጽ ጠፋ ። ቀና ብሎ የሚመለከት አልተገኘም ።ወዲያውኑ የኛ ወገኖች ከአካባቢው እየተሯሯጡ ሲደርሱ አየናቸው ፤ ተኩስ የከ ፈቱብንም በሽሽት ላይ የነበሩ የጠላት ወታደሮች መሆ ናቸው ገባን ። ወታደሮቻችን እየወደቁ እየተነሱ በሄዱ በት ተከተሏቸው ። እኛም በዚሁ አጋጣሚ ካደፈጥንበት ቀና አልን ። በአካባቢው ሁሉ ፀጥታ ሰፈነ ። የጥይቱም

ፉጨት በረደ ፤ እኔ ገና ቀና ከማለቴ የተመለከትኳት ናኒን ነበር ። ዓይኖቹዋ የጠላት ወታደሮች ወደሸሹበት እንደተተከለ ነው ። ጠመንጃዋንም ወደ ኋላ አላደረገችውም ። ዶክተር ዘውገም እንደ እኔው ሳይገረምባት የቀረ አይመስልም እንዳመለካከቱ ።

ወደ ቁስለኛው ተመለስን ፤ እሱ ግን አልጠበቀንም ፤ ከውጥረቱ ጋር ፤ የነበረበት ሁኔታ ፋታ አልሰጠውም ። "የልቤን አድርሻለሁ" እንዳለው ሁሉ አብዮታዊ ግዳጁን ፈጽሞ አለፈ ፤ አደራውን ለኛ አስተላልፎ ።

ታህሣሥ 1970

መልካም ዜና ! መልካም ዜና ! ከቆምንበት ሁለት መቶ ሜትር ያህል ርቆ ሕዝባዊ ሠራዊታችን እልልታውንና ጭፈራውን ሲያቀልጠው ተመለከትን ። መቼም የድል እልልታ መሆኑን ለመገመት አያስቸግርም ። ሁላችንም ወደ ውካታው አቅጣጫ ተሯሯጥን ። አምቡላንሶች፣ የጦር መኪናዎች ፣ ምግብ ማመላለሻዎች እየተግተለተሉ እኛ ወዳለንበት ደረሱ ። ለአንድ አፍታ ያህል ቢሆንም ድል ያስፈነጥዛል --በተለይ ከፍተኛ ትንቅንቅና ታላቅ መስዋዕትነት የታየበት ድል ።

የጦር አዝማቹ የመቶ አለቃ በኮፍያው ፊቱን እያራገበ ከተቀመጠበት ተነሳና “ እንግዲህ ጓዶች! ጭብጨባውም እልልታውም ይብቃ! በቀላል ድል መፈንጠዝ የለብንም፣ ብዙ ያላስለቀቅናቸው ቦታዎች ስላሉ-- ወደ ፊት!” በማለት ተናገረ። ሁሉም በሩቁ እየተመለከቱ እርጭ አሉ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ፋታ አግኝቶ የተቀመጠው ሕዝባዊ ሠራዊት ለሚቀጥለው ፍልሚያ ጠመንጃውንና የውሃ ኮዳውን እየያዘ ብድግ ብድግ ማለት ጀመረ። እኛም አብረን ።

ሰኔ 1970

ዛሬ ጠዋት ተጨማሪ የሕክምና መሣሪያ ደረሰን። መሣሪያውን ያመጣልንን ሹፌር ሌላ ያመጣልን ነገር እንዳለ ብንጠይቀው ስለኛ እከተማ ስለሚወራው አንስቶ ሞራላችንን በይበልጥ አጠናከረልን ።

አንቺ ደውለሽ ስለ እኔ መጠየቅሽንም የገለጸልኝ በዚሁ ጊዜ ነው ። እኔም አጸፋውን ሰላምታዬን ልኬልሻለሁ ። ሹፌሩ ግን ከዚያ ወዲህ ስላልተመለሱ መልእክቴን ማድረስ አለማድረሳቸውን ማወቅ አልቻልኩም ፣ ይገርምሻል ፣ አንዳንዴ ፋታ ሲገኝ አሳብ እየዘምቱ ዘመቻ እየዘመቱ ያስቸግራል -- ለጎጆ መውጫ የገዛና

ቸው ዕቃዎች ፣ ያንቺ የብቸኝነት ኑሮና በሥራሽ ላይ የሚ ያጋጥሙሽ ችግሮች ፣ ከእናቱ ጋር የሚኖራችሁ ግንኙ ነት --- ጓደኞችሽ ይጠይቋት ይሆን --- ኮስታራ ገጽታ ሽ --- ሥራሽን ስታከናውኚ ተፍ ተፍ ማለትሽ --- በሻይ ሰዓት እኔን ለማስተናገድ የነበረው ዝግጅት ፤ -- ከአንድ ቀን በላይ ያልደገምነው የእሁዱ ቀን ትግሥታሽ -- ለመ ጨረሻ ጊዜ ስሰናበትሽ ድንገት ገደ ፤ ብለሽ የጠራሽኝ --- ስንቱ ፣ ስንቱ ፣ ስንቱ ----

ናኒ ነገሩን ለማወቅ የጓጓች መሆኗ ያስታውቅባታል ። ሹፌሩን ስለ አንቺ ስጠይቀው አዳምጣለች ። በኋላም ትካ ዜዬን በመመልከት "እንዲህ የምታስብላት ምንህ ነች?" ብላ ለመጠየቅ ሳይቃጣት አልቀረም ። ጥያቄዋንም ተጠ ባብቄው ነበር ። ነገር ግን እሱዋ ሁሉንም ዋጥ አድርጋ "ዶክተር ፣ ነቃ ይበሉ የምን ሃሳብ ነው ፤ ሁሉንም ከድል ኋላ ይደርሱበታል" አለችኝ ።

የአንቺ ነገር ለዶክተር ዘውገም ግራ ሆኖበታል ። የሚገርምሽ ከእሱ ጋር አብረን ስለምንተኛ ብዙ ጨዋታ ዎች አጫውቼዋለሁ ። ስለአንቺ ግን አንስቼለት አላውቅም ። ማንሳቱንም አልፈለግሁም ። ለምን እንደሆነ አላውቅም ። ደብዳቤ እንኳ ስጽፍልሽ ሰውሬ ነው --- ብቻ ማንም ሰው ስለ አንቺ እንዲያውቅብኝ አልፈለግሁም ።

ታህሣሥ - 1970

-- ከጦሩ ጋር ፣ የሚያጋጥመንን ሁሉ እየተጋተርን ወደ ፊት አመራን ። አንዳንድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ስለተሟሉልን የእርዳታ አሰጣጣችንም ከፍ አለ ። ቀላል የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸውን እዚያው እያከምናቸው ተመልሰው ወደውጊያው ይገቡ ጀመር ። ለከፍተኛ ሕክምና ወደ ከተማ መላኩም ከበፊቱ ሁኔታ ቀጠለ ። ለትንሽ ቀናት ያህል የከፋ ጦርነት አላጋጠመንም ። ጥቃቅን ውጊያዎችን ቢሆን በድል አድራጊነት እየተወጣን ቀጥለናል ። ጦሩም ከፍተኛ ሞራልና ጥንካሬ አግኝቷል ። በሌሎቹ አካባቢዎች የሚደረገው ውጊያ የእኛው ሕዝባዊ ሠራዊት ብዙ ሥፍራዎችን እያስለቀቀ መሆኑን ሬድዮ አገናኛችን ባደረሰው ሪፖርት መሠረት ባስተላለፈልንማ ጊዜ የሰጠን ጥንካሬ ልዩ ነበር ። "ግፋ በርታ !" ሆነ ከእያንዳንዱ አንደበት የሚፈልቀው ።

---- ይገርምሻል ! የሚያጋጥሙን የጠላት ወታደሮች ሁሉ ያለ የሌለ ጥይታቸውን እያርከፈከፉ ወደ ኋላ ከመሸሽ በስተቀር ሥልት ይዘው አይዋጉም ። አንዳንዴማ ሁኔታቸው በድንጋይ ፈንክተህ ቶሎ ተመለስ ! የሚቻል ከሆነማ ቤቱ ድረስ ገብተህ ደብድበው ! ልጅነትህ ለመቼ ነው ? ተብሎ በአባቱ የታዘዘና ግዴታውን ለመወጣት የሞከረ ፈሪ ልጅን ይመስላል ። ለማንኛውም ለወሳኙ ትግል እየተዘጋጀን ነው ---

ታህሣሥ 1970

ውዱዋ አዜብ ፣ ባለፈው ጊዜ እንደገለጽኩልሽ ሁሉ ልክ እንዳቺው በመሆን እንዳላስብና እንዳልተከዝ የምታጽናናኝ ናኒ ነች ። ቅድም እንዲህ ዓይነቱ ሃሳብ ውስጥ ገብቼ ስዋኝ ሁኔታዬ ስለገባት ፣ በድንገት እጇዋን ዘረጋችና "ይህችን ጉረስልኝ ፣ ግሩም በሶ ነች ። ቤቷ ግን ትሆን ? " በማለት አጐረሰችኝ ። ከጉርሻዋ ይብስ አቀራረብዋ ለዛና ጣዕም ስለነበረው ከሃሳቤ ወጣሁና ከእሷው ጋር ጨዋታ ቀጠልኩ ። ናኒ ስላጎረሰችኝም ብድሬን ለመመለስ ፣ እኔም ከድርሻዬ ጨበጥኩና "ይህችን ጉረሺልኝ" አልኩ ፤ የእኛን ሁኔታ ያጤኑት ሚሲሺያዎች በፈገግታ እየተመለከቱን ፤ ሁኔታችን እንዳስደሰታቸው ገባን ።

ዶክተር ዘውገ በቀልድ አነጋገር "ለእኔ የሚያጐርሰኝ የለም ማለትነዋ ?" ሲል ናኒ በእጇዋ እያዘጋጀች ስለነበር "ይኸው ወደ እርስዎም መምጣቴ ነው" አለችና አጐረሰችው ።

በዚህ ጊዜ ሁሉቱንም ትኩር ብዬ እየተመለከትኩ እንደገና ሃሳብ ውስጥ ገባሁ ። ስለእያንዳንዳቸውም መመራመር ጀመርኩ ። ዶክተር ዘውገ ትምህርቱንም ያጠናቀቀው በቅርቡ ስለሆነ ሚስትም ሆነ እጮኛም እንደሌለው ከአሁን በፊት አጫውቶኛል ። ስለ ናኒ ግን ምንም የማውቀው ነገር የለም ። ከሁኔታዋ እንደተረዳሁት ከሆነ ወደ ኋላዋ የሚስባት ነገር ያለባት አትመስልም ። ምንም ጠን

ካራ ብትሆን ፍቅረኛ ካላት ማስታወሱዋ አይቀርም፣እና የላትም ብዬ ደመደምኩ ። እና ታዲያ ለእኔ እስከመቼ ውም የማይለወጥ ፀባይ ያለሽ አንቺው ፍቅሬ አለሽልኝ ዶክተር ዘውገስ ---ከናኒ ጋር--እምልሽ በሃሳቤ የተመ ላለሰውን ነው ። ምናልባት ስለራሴ ባሜወ ታቸው እነር ሱም ስለራሳቸው ያስቡ ይሆን ? ምን እልሻለሁ ብቻ ስለ እነርሱ ብዙ ሳስብ ቆየሁ ። ሆኖም ግን እኔው ሆድ ውስጥ እንደታመቀ ቀረ ። የምግቡ ጊዜ አለቀና ጉዟ ችንን ጀመርን ።

ጥር 1970

የኔዋ አዜብ፤ ትልቅ ችግር ያጋጠመን ዛሬ ነው ።የእ ስከዛሬው ቀልድ ነበር ለማለት ያስደፍራል፤ብዙ ቦታ በቀላሉ እያስለቀቅን አልፈን ነበር ። የአሁኑ ግን እንደሚያ ዳክመን እሙን ነው ። እንዲሁ ለሚያየው እንኳ የጠላት ጦር ብዛት ከእኛ በብዙ እጅ ይበልጣል፤በዚያ ላይ የመሣ ሪያው ዓይነትና ይዘውት የጠበቁን ተራራማ ሥፍራ ከወ ዲሁ ተስፋ ያስቆርጣል ። እና ይህንን ከተወጣነው ወደፊት ምንም የሚበግረን ኃይል እንደማይኖር እተማመናለሁ ።

አዜቢና፤ በጣም አዝናለሁ ከዚህ በላይ ልጽፍልሽ አልቻልኩም ። የጠላት ጥይት እንደዝናብ እየተርከፈከፈ ብን ነው ---

ጥር ---- 1970

ውዷ አዜብ ፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ጊዜው ይርዘም እንጂ መገናኘታችን አይቀርም ። እስከፊ ከነበረው የሰሞኑ ጦርነት ተረፍኩልሽ ፤ ይህን ደብዳቤ የምጽፍልሽ እስ ከፊና መራራ የሆነውን ና ያለእረፍት ሶስት ሳምንት የፈ ጀብንን የሰሞኑን ጦርነት በድል አድራጊነት ተወጥተ ነው እረፍት ባገኘሁበት ሰዓት ነው ።

ይኸውልሽ ከፍተኛው የጠላት ጦር የገጠመን ለው ጊያ አስቸጋሪ ከነበረው ተራራማ ሥፍራ ነው ። ገና ከሩቅ ሲያዩን መተኮስ ጀመሩ ። እኛም በየቦታው ተበታትነን ምሽግ በመያዝ መታኮሳችንን ቀጠልን ፤ ሆኖም የእነሱ ቁጥር በጣም ስለበዛና የእኛ አነስተኛ ስለሆነ ያለን አማ ራጭ መከላከል ብቻ ነበር ። በዚህ በኩል ጠንካራ የሆነ ውንና ግሩም የጦር ሥልት ያለውን አዝማች መቶ አለቃ ሳላነሳልሽ ማለፍ አልወድም "ተኙ ተነሱ" ወደፊት ሂዱ ወደኋላ ተመለሱ ፤ አድፍጡ" በማለት ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ፀጉሩ የታጠቀውንና በቁጥር የበዛውን የጠ ላት ጦር እንድንቋቋም ትልቅ ለስተዋጽኦ አበርክቷል ። በዚህም የጦር ጥበባችን ለማጥቃት ባንችል እንኳ ያለንበትን ላለመልቀቅ በመከላከል ትልቅ ተጋድሎ አደ ረግን ። የጠላት ጦርም ስተት ብሎ እንዳይገባ እንቅ ፋት ስለሆንንበት የፈንጂ ናዳ ያወርድብን ጀመር ። ወይ ፍንከች የፈለጉትን ያህል ቢፍጨረጨሩ ንቅንቅ አላል ንም ፤ ብዙ ጓዶችን ግን አጣን ። እኛም ቢሆን እንዳስፈ

ላጊንቱ የቆሰሉትንም ተንስተን ለማከም አልቻልንም ፣ ከደፈጥንበት ቀና ከልን ለጠላት ሲሳይ መሆን ይከተላል። ሆኖም ቁስለኞቹ እየተበራከቱ ከመሄዳቸው በፊት ዘዴ እየፈለግን ማከም ጀመርን ።

ናኒ የሕክምና ቦርሳዋንና መመንጃዋን እንደያዘች መሬት ለመሬት በመንከባለል ወደ ቁስለኞቹ አመራች። እኛም እንዲሁ እንድናደርግ በዓይኗ ጠቀሰችንና ተከተል ናት ። ከቦታ ቦታ እየተንከባለልን ማከማችንንም በሰፊው ቀጥለን ፣ ብዙዎችንም እየረዳናቸው ውጊያውን እንዲቀ ጥሉ አደረግን ። የእኛ ሥራ በአንድ በኩል ሕክምና መስ ጠት ፣ በሌላ በኩል አልፎም ደግሞ ለጦሩ ሞራል መስጠትና ማበረታታትም ጭምር ስለ ነበር ለሴኮንድ ያህል እንኳ ፋታ አልነበረንም ። ሌሊት ከቀን እንዲሁ በንቃትስ ሰነ በትን ። ያቺን ቦታ ላለመልቀቅም ትልቅ ተጋድሎ አደ ረግን ። "ከብዛት ይልቅ ጥራት" የሚለውን አነጋገር ትክ ክለኛነት በተግባር አስመሰከርን ፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የጠላት ወታደሮች ቢጐርፉም ፤ ታንኩ ቢግተለተልም ፣ የፈንጂ ናዳ ቢወርድንብንም ፣ አልተበገርንላቸውም ። ለት ክክለኛና ሕዝባዊ ዓላማ የቆመው ሕዝባዊ ጀግና ቆራጥ ታጋይነቱን አሳያቸው ።

ከሌሎች ቦታዎች እርዳታ እንዲመጣልን የጠየቅነው ቀደም ብለን ቢሆንም ትሉ እስካሁን የደረሰልን ምንም

ኃይል አልነበረም ። ከማግሥት በኋላ ግን ብዙ የሰው፡ና የመሣሪያ ኃይል ደረሰልን ። ከዚህ በኋላ ያለውን ስን ቱን እገልጽልሻለሁ ። አድፍጦ በመከላከል መወሰናችን ቀረና ለማጥቃት ከንዳችንን አጠንክረን ፣ ኃይላችንን አሰ ተባብረን ተነሳን ። መድረሻችንን የኢትዮጵያ ድንበር ከሩቅ በዓይናችን እየመተርን መፋለም ብቻ ሆነ ። በእር ግጥ እንዲህም ሆኖ የጠላት ኃይል አልተበገረልንም። የያ ዘወን ቦታ ላለመልቀቅ ትንንቅ ያዘ ። እንዳለፈው ሳም ንት ኃይላችን አነስተኛ ባለመሆኑ ወደ ፊት ገፍቶ ለመ ግባት ያለው ዕቅድ እንደከሸፈበትም አወቀ ። በኛ በኩል ግን ጥንካሬአችን ከፍ እያለ ስለሄደ ማጥቃት ቀጠልን ። ታንኩን ከለላ እያደረገ የሚጕርፈው፦ የጠላት ጦርም በፈንጂ እያጋየን መግቢያ መውጫ አሳጣነው ።

ጠላትም የመጨረሻ መፍጨርጨሩን አደረገ ። በተ ዋጊ አይሮፕላኖች ፣ በአዳዲስ ታንኮች መድፎችን በመ ጨመር ኢትዮጵያችንን ለማጋየት ተነሳ ። እንደ አሰላለፋ ቸው ከሆነ በምድር ላይ ሰውም ባልተረፋቸው ነበር ። ሕዝባዊው ወታደር ግን በሙሉ ልቦና በቆራጥነት ተጋተ ራቸው ። በእኛም በኩል ቢሆን ለእነሱ የጕረፈውን ታንክ ፣ አይሮፕላን ፣ መድፍ በእጥፍ የሚያስከነዳ መሣሪ ያና ኃይል ወዳያው፦ ደረሰልን ። ወዳጆቻችን ሁሉ ለም ናደርገውም ሕዝባዊ ጦርነት ድጋፋቸውን ገለጹልን ። ጦርነቱ ከመቼውም ይበልጥ ተፋፋመ ።

ጥር 1970

በምድር በሰማይ የሚታየው የመጣሪያ ዓይነትና ብዛት ልብን ይሞላል ፤ በአይሮፕላን የሚደረገው ውጊያ በስሜት ያበራል ። ጦርነቱ እየተጧጧፈ መጥቷል ። በእኛ በኩል የውጥረቱ ነገር አይነሳ ። ገና የያዝነውን አክመን ሳንጨርስ ሌላ ቁስለኛ ይመጣል ። አብሶማ ጦርነቱ ጋብ በሚልበት ሰዓት ሥራችን እጅግ ከፍ ይላል ፤ በየቦታው የወደቁትን ወገኖቻችንን በወሳንሳ እየተሸከሙ ማምጫቸው ጊዜ ስለሆነ ። የቀዶ ጥገና ሕክምና መስጠቱንም እዚሁ ተያያዝነው ። ፀሐያማ በሆንና ሰዎች በበዙበት ሥፍራ እንዲህ ያለውን ሥራ ማከናወኑ ይገርምሽ ይሆናል ። ሆኖም ችግር ሁሉን ያስተምራል ። በተለይማ በር ከት ብንል ፤ ኖር ከዚህ በበለጠም ሥራችን በተቀጣ ። የሐኪምና የነርስ ችግር አለብን ፤ በተለይ ናኒ በየቦታው እንደተቀከበች ነው ። ሁለታችንም ሕክምና በምንሰጥበት ጊዜ የማድ ረዳት ስለሚያስፈልገን ፤ እኔን በምትረዳበት ጊዜ ዶክተር ዘውገም ችግር ይገጥመውና "እባክሽ ሲስተር ይህንን ነገር አርጂኝ" የሚል ጥሪ ያቀርባል ። የትኛውን ይዛ የትኛውን ትልቀቀው ? እንዲሁ እንዲሁ ከአንዳችን ወደ አንዳችን ትራወጣለች ። ታዲያ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ አንቺን ማስታወሴ አልቀረም ። አንቺ አጠገቤ ብትሆኚልኝ "አዜቢና እንዲህ ብናደርግስ" እያልኩ ችግራችንን በጋራ እንወጣው ነበር ።

የሆነው ሆኖ ይህ ሁኔታ እስከዚህም ሃሳብ ሊሆን ብሽ አይገባም ። በመጠኑም ቢሆን መፍትሔ እየፈለግን

ለት ነው፤ከሠራዊቱ ውስጥ ቀድሞ ትንሽ ትንሽ ልምድ የነበራቸውን የመንደር ወጌሻዎች ማለማመድ ጀመምረናል ። ከእኛው ጋር እየሠሩ በተግባር እንዲለማመዱ በማድረግ ። በዚህ ረገድ ረዳቶች ካገኘን ለየብቻችን በየቦታው እየተሰማራን ለማከም አቅደናል ። ከባድ መሣሪያ ዙሪያችንን እያደበላለቀው ነው ፤ እንደገና ጊዜ አግኝቼ ----

## ጥር 1970

ደጋግሜ እንደገለጽኩልሽ ሁሉ ጦርነቱ መራራ እንደመሆኑ መጠን ጥይቱ ከላይ ከታች ሲርከፈከፍ መስማቱ ጆሮአችንን አደንዝዞታል ። አብሶማ የተጧጧፈ ጦርነት በተካሄደባቸው ባለፉት ሁለት ቀኖች ውስጥ የመስማት ችሎታዬ ዝቅ ብሎ ነበር ። ጥይት እንደበረዶ ሲዘንብ ፣ ፈንጂ ዙሪያችንን ሲቦዳድሰው ፣ ስንቱ ጓዶች አጠገቤ ሲወድቁ፣ እኔ የተለየ መከላከያ ያለኝ ይመስል ፣ መትረፌም እጅግ ይገርመኛል ። የሥራው ክብደት ቢሆን እስከዚህም እንደበፊቱ አይሰማኝም ። ሚሊሺያው ሁሉ የቅርብ እረዳቴ ሆኗል ። ቁስለኞችን ከወደቁበት ቦታ እየተሸከሙ ያመጡአቸውና “ ደምስሩን ነው የተመታው ፤ የዚህኛው ሕክምና መቅደም አለበት ወዘተ --” እያሉ አስተያየታቸውን ሲሰጡ በሰፊው የሰለጠኑበትን ያህል ነበር ፤ ለእኔም መጠነኛ እፎይታ ሰጥቶኛል ። ከቦታ ቦታ

ብዙ መራመጤ ቀርቶልኛል ፤ እነሱም በወሳንሳና በትከሻቸው እየተሸከሙ የሚያመጧቸውን ቁስለኞች ማከሚን ቀጥያለሁ ። ሚሊሻ ወጌሻዎች ታላቅ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው ። ይብሱን ሴቶችማ ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ ቶሎ የመያዝ ችሎታ አላቸው ። ለማዳንቅ ያህል ያቀረብኩት እንዳይመ ስልሽ ። ያልሆነን ነገር ማድነቅ ጥንቱንም እንደማልወድ አንቺም ታውቂያለሽ ።

ጦር ሜዳው ከመጣሁ ጀምሮ ለማደርገው የሕክምና ርዳታ ከሚተባበሩኝና የምንግራቸውን ቶሎ ከሚቀበሉኝ መሀል አብዛኛዎቹ ሴቶች ናቸው ። በጦርነቱ ላይ ያላቸውን ተሳትፎና ሙሉ ቆራጥነትማ ለታሪክ አስቀምጦ ማለፉ የተሻለ ነው ።

መቼም የእንቅልፍ ነገር ቀን ከሌሊት ያንገደግደናል ። ቆመን መሄዳችንም ጦርነቱ ጋብ በሚልበት ወቅት በተራ በተራ ትንሽ በመተኛታችን ነው ። አንድ ቀንማ ማታ የሆነውን ባጫውትሽ ፤ በየተራ በምንተኛበት ወቅት የእኔ ድካም ከሁሉ ይበልጥ ከፍ ብሎ ስለነበር በቅድሚያ እንድተኛ ፈቀዱልኝ ። ገደባችን ሁለት ሰዓት ያህል ብቻ ስለነበረች በፍጥነት በሽርጤ ተጠቀለልኩና ተኛሁ ። ሽርጤ ከወገቤ በታች ሊሸፍንልኝ ስላልቻለ እግሬን አኮራምቼ አገጩ ድረስ አደረስኩት ። በዚህ ጊዜ የእንቅልፍ ተራቸው እስኪደርስ አባቢውን በመጠበቅ ላይ ካሉት

ወታደሮች አንዱ የጦር ሜዳ ጃኬቱን አውልቆ እግ
ሬን ሲያለብሰኝ ተሰማኝ ። ምን ዓይነቱ ፍቅር ነው ? ከእ
ራሱ ይበልጥ ለእኔ በማዘኑ ብዙ አሳሰበኝ ። ውስጥ ውስ
ጡን ለማልቀስም ቃጣኝ ፤ ለሁሉም ድካሙ ስለተሜኔኝ
ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰደኝ ።

ታዲያ ሁኔታዎች ያልታሰበ አቅጣጫ ይዘው ኖሯል ።
ገና ሠላሳ ደቂቃ ያህል እንኳ ሳልተኛ ወታደሮቹ ትከሻ
ዬን በጣም እየነቀነቁ ስለቀሰቀሱኝ ባነንኩ ። ተራ
ቸውን ለመተኛት የቀሰቀሱኝ መሰለኝና ሰዓቴን ተመ
ልክቼ "ገደቤን እኮ አልጨረስኩም ፤ ሰዓት መቼ ደረሰ?"
ስላቸው በድንጋጤ እንጋገር " ዶክተር ይነሱ ፤ የምንቀሰ
ቅስዎት ለመኝታ አይደለም ። ጠላት አካባቢያችን ደር
ሷል ፤ ይነሱ " አሉኝ ። እውነትም ተኩሱ ሌላ ጉዳይ
ሆኗል ። ያን ያህል የተኩስ ጩኸት ግን አልቀሰቀሰኝም ።
የድካሜን ልክ በዚሁ መገመት ትችያለሽ ፤ ወዲያውኑ
ዓይኔን ጠራርግሁና ብድግ አልኩ ። መቼም እንደዚች ቀን
ዓለም አስጠልቶኝ አያውቅም ። እቆምኩበት እየተንገዳ
ገድሁ ምርር ብዬ " ጦርነት ከምድረ ገጽ የሚጠፋው
መቼ ይሆን ? ሕዝቡ ሰላም አጥቶ እየተሳቀቀ የሚኖረው
እስከ መቼ ነው ? " በማለት ጮህሁ ። ያቺ የሰላሳ ደቂቃ
እንቅልፍ በጣም በጠፀጠችኝ ። ወይ መጀመሪያኑ ባልተ
ኛሁ እንዲህ ባልተረበሸሁ ነበር ። የጦር ሜዳን ፍዳ
ለማወቅ መቅመስ ያሻል ።

ገና ጮኬ ሳላባራ ሁለት ሚሊሺያ ሴቶች ቁስለኞች ተሸክመው ከተፍ አሉና "ቶሎ ይርዱት በጣም ተጐድቶአል" አሉኝ። ፈጠን ፈጠን እያልኩ ልረዳው ሞከርኩኝ። ነገር ግን ሶስት ቦታዎች ስለተመታ በጣም ደከመና ተንዘለፈለፈ። በጣም የጐዳው በሆዱ በኩል ገብቶ የቀረው ጥይት ስለነበር በቀዶ ጥገና ላወጣለት አሰብኩና መሣሪያዎቼን ላወጣ ቦርሳዬን ከፈትኩ።

ዓይኔ እንዳፈጠጠ ቀረ። ለካስ ማደንዘዣውን ጨርሼ ኖሯል! እርግጠኛ ለመሆን ቦርሳዬ ውስጥ ያለውን ዕቃ ሁሉ ዘቅዝቄ ፈተሽሁት። በእርግጥ የለም። እየታወቀኝ ከሚሞት ይልቅ እንዳይንፈራገጥ በሰዎች አስይዤ ለመቅደድ ወሰንኩ። እሱ ግን ለዚሁ ሁሉ ዋጋ አልሰጠውም። እንደማይተርፍ ስለታወቀው ደግፋ የያዘችውን ሚሊሺያ ጐንበስ ብላ እንድታዳምጠው ጠየቃትና፣

"ጓዲት እንግዲህ አደራሽን ለ--ለ--- ዘመዶቼ ማረፌን ላኪባቸው። የጀግና ሞት መሞቴንም ግለጭላቸው። ለሶስት ልጆቼ እናት ማስታወሻ እንዲሆናት ባለ እርማውን ኮፍያየን አውልቀሽ ላኪላት። ሕዝባዊ አሟ–" ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ አረፈ። መጨረሻ ሊናገር ያሰበው ምን ይሆን?-- ሁኔታው አንጀቴ ውስጥ ገብቶ አንገበገበኝ፤ የእሱ ትንፋሽ ተቋርጦ እንደቀረው ሁሉ እኔም ለጥቂት ሴኮንዶች ሳልተነፍስ ቆየሁ። ደግፋው የቆየ

ችው ሚሊሺያም ሳታስበው የወረደውን እንባዋን ጠራረገችና ጠመንጃዋን እንስታ በፍጥነት ርምጃ ወደ ጦርነቱ መሀል ገሰገሰች ። ቁጣና እልህ ተደባልቀው ፊቷን ፍም አስመስለውታል ። ወደ ተፋፋመው ግብግብ ውስጥ ።

እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ተነሳብኝ ። የሕክምና ርዳታዬ ጠቀሜታ ጨለመብኝ ። ቦርሳዬን ወረወርኩና "መሀል ገብቼ መዋጋት አለብኝ፣ አጠገቤ እንደተዘረረው ጓድ የእኔም ሞት ዛሬውኑ እዚሁ መሆን አለበት ፣ ከእንግዲህ ምን እስኪመጣ እጠብቃ ለሁ ?" በማለት እልህ እየተናነቀኝ ተናገርኩ ። ለካ ያላ ለቀ እንቅልፍና ብስጭት ሲደመር ሕሊናን ያስታል ።

በእርግጥ ከዚህ የበለጠ ብዙ ችግር አጋጥሞኛል ፤ ሕክምና እያደረግሁላቸው ባለሁ አስቃቂ ሞት የሞቱም ጥቂት አይደሉም ። ከሁሉ ይበልጥ ግን የዚህኛው ሰው አሟሟት አሳዘነኝ ። አብሶ የሶስቱ ልጆቹ እናት ለሆነ ችው ባለቤቱ መልዕክት ሲልክ ሆዴን በጣም ረበሸኝ ። የእኔም ፍቅር ፊቴ ላይ ድቅን አለሽብኝ ። እኔም የምልክ ልሽን አሰላስል ጀመር ። "ከአሁን በኋላ ፍቅር ትመሠ ርት ይሆን ?" የሚል ነገር አሰብኩና "ቀለበቷን መል ሳችሁላት ስለ እኔ ንገሯት" ብዬ ለመላክ አቀድኩ ። ወዲያው ደግሞ ከእኔ ጋር ለመፋቀር የፈጀብሽን ጊዜና

ያፋቀረንን ሁኔታ በማስታወስ በብቸኝነት ትኖራለች እንጂ ከአሁን በኋላስ አታፈቅርም እልኩና ካንቺ ከተለየሁ ጀምሮ የሠራሁትን ጀብዱና ያሳለፍኳቸውን ሁኔታዎች ያዘለውን ትውስታዬን የሚያደርስልኝን ታማኝ ሰው ማሰላሰል ጀመርኩ ።

ትውስታዬም ተጽፎ ተጽፎ (ተጭር ሳይሻል ይቀር ብለሽ) ተከምሮ ፣ ላንቺ ሳይደርስ ሊቀር እንደሚችል የገመትኩት በዚሁ ጊዜ ነው ። እየጻፍኩ ማንበቡ ራሴን ያጽናናኝ ቢሆንም ትልቁ ምኞቱ ወደ አንቺ የመድረሱ ጉዳይ ነው ። እናም ወደአንቺው ለመላክ ከመጠን በላይ ተቻኮልኩ ። አሁን ትሞታለህ እንደተባለ ሰው ራሴን እያስጨነቅሁ ወይኔ ፤ ለአዜቢና ደብዳቤዬ ሳይደርስ እንዲሁ ተበታትኖ መቅረቱ ነው” በማለት ተከዝኩ፣ ምን እልሻለሁ መቼውንም አሳይቼው የማላውቀው ደካማነትና የተስፋ መቁረጥ ስሜት ታየብኝ ። ደግነቱ በዚህ ዓይነት ብዙ አልቆየሁም ። ቁስለኛው እየተከታተለ መድረስ ጀመረ ፤ የእኔን እጅ እንደሚጠብቁ ተሰማኝ ። የወረወርኩትን የሕክምና ቦርሣ አንሳሁና ጠመንጃዬንም አንግቤ ወደ ወትሮው ተግባሬ ተመለስሁ ።

ሌሊቱን እንዲሁ ስንታኮስ አደርን ። ሊነጋጋ አካባቢ በጣም ቀርበው የመጡ የጠላት ወታደሮች ስላጋጠሙን በቁጥጥራችን ሥር አዋልናቸው ። እጃቸውን ለመ

ስጠት ያልፈለጉትንም ደመሰስናቸው ። ጦርነቱ ቀኑንም ቀጥሎ ዋለ ። ሰይጣና ምድሩን የሚያንቀጠቅጠውን የተኩስ ድምጽ ደጋግሜ መግለጽ ማሰልቸት ይሆንብኛል ። ነገር ግን እንደ ሳልፈው የማልፈልገው ነገር አለ ። "ትግላችን ረዥምና መራራ ነው" ሲባል ቃላቱን መናገሩ ምንም ያህል ክብደት አይሰጠውም ። በተግባር መራራነቱን መቅመስ ግን የአባባሉን ትልቅነትና እውነታ ለመረዳት ያስችላል ።

ጥር 1970

አዜቢና ! ይህ የመጨረሻውና ትልቁ ጦርነት ሳይሆን አይቀርም ። ኃይላችን በሚገባ ተጠናክሯል ። ብዙ ቦታዎችንም አስለቅቀናል ። ከእንግዲህ የሚቀረን ሥፍራ በጣም ጥቂት ነው ። ጠላትም የመጨረሻ መፍጨርጨር ለማሳየት በውድቅት ሌሊት መጥቶ ተኩስ ከከፈተብን ጀምሮ እስካሁን እንደቀጠለ ነው ። ጭለማና ብርሃን ሳንመርጥ ስንፋለም ይኸው አራት ቀን ሆነን ። ሌሎቹን አካባቢዎች አስለቅቆ የመጣው ጦር ሁሉ ተጨመረልን ። ውጊያው ኃያል በመሆኑ ብዙ መስዋዕትነት ከፈልን ። በጦር ሥልቱና በአመራሩ ዝናን ያተረፈው መቶ አለቃችንም ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ የደረሰበት በዚሁ ጊዜ ነው ። የዚህ ሰሞን ጦርነት ፈጽሞ ፋታ የሚሰጥ ስላልነበረ እዚያው ልረዳው አልቻልኩም ።

ተመላላሹን መኪና ጠብቀን ከሌሎች ቁስለኞች ጋር ወደ ከተማ ሐኪም ቤት እንዲሄድ አደረግን ። ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያቶች የሚቆስሉትን ሁሉ ወደ ከተማው ሐኪም ቤት መላክ አማራጭ የሌለው ነገር ነበር ። እሳት በጉንና በጉናችን እያለፈ እዚያው ለማከም መሞከር "እተርፍ ባይ እጉዳይ" እንደሚባለው ይሆናል ። ስለ ዚህ እኔም ከማከሙ ይልቅ ወደ መዋጋቱ አዘነበልኩ ።

የሰሞኑ ጦርነት በጀመርን በአምስተኛው ቀን ማለ ዳ እድፍጠው ከተኛሁበት ሥፍራ ሕዝባዊ ዜማ ሰማሁ ።

"የኛው ነው ድሉ --- የኛው ነው ድሉ --- በርቱና ታገሉ"

ይህ በብዙ ሰዎች ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፈ ሕዝ ባዊ ዜማ እንዲህ ዓይነቱ ሥፍራ ቢሰማ ምን ያህል ደስ ታና የመንፈስ ጥንካሬ እንደሚሰጥ ለመረዳት በፍልሚ ያው ላይ መገኘት ያሻል ። ዜማው ከየት አካባቢ እንደ መጣ እንኳ ዘወር ብዬ ሳላይ እኔም በቀጮት እንጉራጉር ጀመር ።

የዜማው ጣፋጭነት እስከ ልቤ ጠልቆ ተሰማኝ ፣ ደስታውንም ፣ ትካዜውንም ፣ ትዝታውንም ፣ ሁሉንም አስታወሰኝ ። ዘፋኙ ማ እንደሆነና የት አካባቢም እንዳለ እስከመጨረሻው ላውቀው አልቻልኩም ። ምን ይታወ

ቃል ! ፡፡ በንፋስ ኃይል ከከተማው ድረስ መጥቶልኝ ይሆናል ፡፡ እኔ ካለሁበት ስምንት ሜትር ያህል ርቆ ያደፈጠው መደበኛ ወታደርም ከእኔው ተቀብሎ ዝግ ባለ ቶጨት ያንጐራጉር ጀመር ፡፡ እንዲያም ሲል ወደ ብዙዎች ተዛመተና ይህ የድል ሙዚቃ በሰፊው አስተጋባ ፡፡ ሥራዩ ብለን ያቀነባበርነው ይመስል ልክ እንደጥሩ የሙዚቃ ጓድ በለሰለሰና ጣዕም ባለው ዜማ ሚዳውን አናወጥነው ፡፡

ተራራውም እያስተጋባ ሲመልስልን ይብሱን ልዩ ጣዕም ሰጠው ፡፡ የተኩስ ድምጽ በእኛ ዘፈን ተዋጠ፤ሠራዊታችን በከፍተኛ ሞራል ወደፊት መጓዙን ቀጠለ ፡፡ እያንዳንዱ የሕዝባዊ ሠራዊት አባል በያረቱ እየተሳበና እየተንከባለለ በመታኮስ ጠላቱን አርበደበደው ፡፡ ጦርነቱ እጅግ ተፋፋመ ፡፡ ‥ ሕዝባዊው ዜማ ያለ ምክንያት አላስተጋባም ፡፡ ድልን ለማብሰርና እኛን ለማበረታታት እንደነበረ ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደብንም ፡፡ አምስተኛ ቀን እስከ ሌሊቱ ከፍተኛ ፍልሚያ አድርገን በስድስተኛው ቀን ላይ ድልን ተጐናጸፍን ፡፡ የጠላትን ጦር እያንኮታኮትን ከድንበራችን አባረርን ፡፡ የተደመሰሱት ፡፡ ተደመሰሱ የተረፉትም የሀፍረት ሸማቸውን ተከናንበው ፈረጠጡ ፡፡

ድንበራችን ጫፍ ላይ በመቆም የድል መዝሙሮች ዘመርን ፡፡ ባለሶስቱን ቀለም ሰንደቅ ዓላማችንና ቀዩ ባንዲራችንን እዚሁ ድል ሥፍራ ተክልን ፡፡ ለትክክለኛና

ሕዝባዊ ዓላማ የሚታገል ሁሉ ድልን መጐናጸፉ እን ደማያጠራጥር አስመሰከርን ። የተበታተነው ሠራዊት የባ ንዳራችንን መውለብለብ በመመልከት ተሰበሰበ ። በየቦ ታው እየተዘዋወረ ሠራዊቱን ሲያንቃቃ የነበረው የኪነት ጓድም ወደዚሁ ሥፍራ በመምጣት እልልታውንና ፉከራ ውን አሰማ ፣ በእስክስታው ተምነሽነሸ ።

የካቲት 1970

የኪነት ጓድ በእኛ መካከል መገኘት በየቦታው ሲፋ ለም የቆየውን ጦር አሰባሰበው ፤ እኔም በዚህ ፋታ ተለ ይተውኝ የቆዩትን ሁለቱን የሕክምና ጓዶቼን ዶክተር ዘውገንና ናኒን ለመገናኘት ጓጓሁ ። በሕይወት የመቆየታ ቸውንም ነገር ተጠራጠርኩ ። ሰው ሁሉ የኪነት ጓዱን በማጀብ ሲያጨበጭብና እልልታውን ሲያቀልጠው እኔ ሃሳብ ውስጥ ገብቼ እተክዝ ጀመር ። መቼም በሕይወት ካሉ እዚሁ ሁሉም የተሰባሰበበት የድል ሥፍራ መገ ናኘት እንደምንችል ገመትኩ ።

---ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መሀል ለይቶ ማግኘት ስለ ማይቻል የሕክምና ቦርሳዬን አንጠለጠልኩና ነጭ ሻር ጤን ለብሼ የኪነት ጓዱ የሚነቃነቅበት መድረክ ላይ ወጣሁ ። ተሜዎቹችንም አንድ በአንድ ጨበጥኳቸው ።

ይህን ዓይነት ሁኔታ ብዙዎቹ በስሜት እየተነሱ የሚያደርጉት ስለሆነ በእነም ላይ ሌላ ትርጉም አልተሰጠውም - - - ዋናው አወጣጡ ግን እነ ዶክተር ዘውገ በአካባቢው ካሉ በሕይወት መኖሪያን እንዲያዩና ፈልገውኝ እንዲመጡ በማሰብ ነበር ።

ጥሩ ዘዴ ሆኖ አገኘሁት ። ተሜዋቾቹን ጨብጠው ስመለስ ናኒ እየሮጠች ስትመጣ አየኋት ። ለእንዳፍታም ቆመችና በዓይኗ ትፈልገኝ ጀመር ። ያለሁበት እንደጠፋት ስላወቅሁ ቦርሳዬን ከፍ አድርጌ አወዛወዝኩላት ። በዚህ ጊዜ በቀጥታ ወደ እኔው መጣችና ትከሻዬ ላይ ተጠምጥማ በጎዳዊ ስሜት ልትስመኝ ሲቃጣት አስቀድሜ ጉንጩን ሰጠኋት ። ይህን ያደረግሁት አፍሬ መሆኑ ስለገባት ሳቀችና ጉንጩን ሳመችኝ ። በኋላማ ነገሩ ለራሴም ገረመኝ ። ብዙ ትግሎችን አብረን ያለፍን ሰዎች ተቃቅፈን ብንሳሳም ነውሩ ምንድነው ? ሐፍረቱስ ማንን ነው ? ከእንዲህ ዓይነቱ ከንቱ አስ ተሳሰብ ባለ መላቀቄ ራሴን ወቀስኩት ።

ናኒ ከአጠገቤ ቆሞ አለችና "ያንን ሁሉ ጉድ ተወጣነው አይደለም ?" ብላ በመደነቅ ተናገረች ።

"እንዴታ ይኸው ለእልልታ በቅተናል ። ዘፈኑም ቀጥሏል" አልኩ ። "አዎ በመራራ ትግል የተገኘ ድል ጣፋጭ ነው ይባል የለ ?" ካለች በኋላ ጨዋታዋን በመቀየር

"የዶክተር ዘውገስ ነገር እንዴት ነው! አላገኙአቸ ውም እንዴ!" በማለት ጠየቀችኝ ።

"እንዲያውም አላገኘሁት" ከማለት ሌላ ምንም አል ተናገርኩም ። እሱዋም ሌላ ጥያቄ አላቀረበችልኝም ። ሁለ ታችንም ውስጥ ውስጡን ስለ ዶክተር ዘውገ ማሰባችንን የደነገጠው ፊታችን ይመሰክር ነበር ። በአካባቢያችን ካለ እኔን በሚያይበት ጊዜ ይመጣ ነበር ። ስለዚህ ትልቅ ጥር ጣሬ አደረብን ። ለማንኛውም ቁርጣችንን እስክናውቅ ድረስ ሌላ ጨዋታዎች ቀጠልን ። በተጓዘችበት ያጋጠማ ትን ሁሉ አጫወተችኝ ። እኔም ያጋጠመኝን ዘርዝሬ ነገ ርኳት ። በዚህ ሁኔታ ጥቂት እንደቆየን የየጦሩ አዝማች ወደ መድረኩ ሄደው በጦቆም የትግላችንን ፍሬዎች ከገ ለጹ በኋላ፣ ያለንበት ደረጃ የረገጠው ጉዞ ማብቂያ እንደ ልሆነ በመጠቆም ወደፊት ለሚጠብቀን ትግል እንድንዘ ጋጅ አሳሰቡ ። ከዚያም በማያያዝ ለእናት ሀገራቸው ሕይ ወታቸውን የሰውትን ጓዶች ስም ዝርዝር ከሞላ ጎደል በመጥራት መልካም አርአያነታቸውን ገለጹ ።

ዶክተር ዘውገም አብዮታዊ ግዳጁን ፈጽሞ አልፎ ኖሯል ። ስሙ እንደተነገረ እንደ ጀግና ጓደኛው ሆኜ "ይ ሁና"! ማለቱን አልቻልኩም ። ሰውነቴ ሁሉ ተረበሸ - - - ናኒስ ምን ይሰማት ይሆን? ቀና ብዬ ዓይን ዓይኗን እያ ኋት ። ከእኔ የተለየ ሀዘን አይታይባትም ። ሁለታችን በሀ

ዘን ተመሰጥን ። የተገኘው ድል በብዙ ሰዎች መስዋዕት ነት መሆኑን ቀደም ብለን ብንረዳውም እንደሌሎቹ ሁሉ ዋዋ አድርገን ማለፍ አልሆነልንም ። ከሆስፒታል ጀምሮ የነበረንን ግንኙነት በትዝታ ተመለከትነው ። አብረን በምንተኛበት ሰዓት የምንጫወታቸውን በማስታወስ በይ በልዋ ራሴን ረበሽኩት ። ናኒም ከተዋወቅኋት ጀምሮ እን ዲህ ተከዛ ሳያት የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ፤ በእርግዋ ለእ ንዲያ ዓይነቱ አርቆ አስተዋይ ፣ ትሁት ፣ ሰው ወዳድና መካሪ ሰው የበለጠም በተተከዘለት ነበር ። ግን ምን ልን ጨምር ?! ራሳችንን ለማጽናናት ያህል "ስማቸው የተ ዘረዘረው ሁሉ ወገኖቻችን አይደሉ እንዴ ? ሁሉም የሞ ቱት ለሕዝባዊ ዓላማ አይደለም እንዴ ? ታዲያ ለዶክተር ዘውገ ብቻ ይህን ያህል ማዘኑ ጠባብነት አልሆንም? ፈጽሞ ከእኛ የማይጠበቅ ነገር ነው" አልንና ከትካዜ ለመ ውጣት ሞከርን ።

የካቲት 1970

የድል ቀንን ምሽት እዚያው ድል ሥፍራ ስንጫ ወት ለማደር ወሰንን ። የተወሰኑ ቡድን ብቻ አካባቢውን ለማስከበርና የጠላት ሰላዮችን ለመጠበቅ በየቦታው ተሰ ራጭቶ እንዲቆም አደረግን ። የተቀረነው በሰሞኑ ጦር ተዳከመን ስለነበር በፍጥነት ለመተኛት ተራራማ የሆኑ ጥግ ቦታዎችን መፈለግ ጀመርን ።

በመሀሉ ኃይለኛ ንፋስ ከወደኋላችን እየነፈሰ መጣ ። በዚያ በምሽት ንፋስ ሲጨመርበት ምን ያህል እንደሚበርደን መገመት አያዳግትም ። ለብርዱ ሲገርምን የንፋሱ ኃያልነት ልብሳችንን ከላያችን ላይ ሊያወልቀው ምንም ያህል አልቀረው ።

በዚሁ ውስጥ ደህና ቦታ ለመፈለግ ስንፈራገጥ የተመለከተው ሚሊሺያ እጁን እያውለበለበ "ኑ ኑ ! ! እዚህ ጥሩ ቦታ አለ" በማለት ተጣራ ፤ በእርምጃችን ላይ የንፋስ ግፊት ተጨምሮበት በፍጥነት ወደ ተጠራንበት ቦታ ደረስን ። ግሩም ቦታ ነው ። ተፈጥሮ ራሱ ከቤት አስበልጦ ሠርቶታል ። ከላይ በኩል ሽፋን የለውም እንጂ ጉንና ጉን በተራራ ተከልሎ በጅምር የቀረ ቤትን ይመስላል ። በርከት ያሉ የሚሊሺያ አባሎች ከውስጡ ተቀምጠዋል ። እኛም እዚያው ውስጥ ያደገውን የግራር ግንድ ተደግፈን ተቀመጥን ። ወደዚሁ ቦታ እንድንመጣ የጠራን ሚሊሺያ ግን እስካሁን ድረስ ከዚያው አልተንቀሳቀሰም ። ከፍ ካለ ሥፍራ ቆሞ ቦታ ለመፈለግ የሚራራጡትን የሠራዊቱ አባሎች በመጥራት ላይ ነው ። የመዋደዱና የመተዛዘኑ ነገርማ ስንቱ ይወራል ፤ እሱም ቢሆን በዚያ በብርድ ቆሞ የሚያስተናግደው በማፍቀሩ እንጂ ምንም ግዴታ አልነበረበትም ። አላፊውን ሁሉ እየተጣራ በተከላተፈ አማርኛ "ቤት ለእንግዳ" ሲል ምን ያህል ያስደስት መሰለሽ ፣ መቼም ጣራና ግድግዳ ያለው ቤት ውስጥ ከገ

ባን ብዙ ጊዜ ሆኖናል ። ለእኛ ቤቶቻችን ተፈጥሮ እመ ቻችቶ የሠራቻው ዛፎችና ወጣ ገባ ሥፍራዎች ናቸው ። መብራታችንም ያቺው ጨረቃ ናት ። ሻማ ቢኖረንም ቅሉ በጦር ሜዳ መጠቀም አደገኛ ነው ። ባትሪም ያለን እኛ ሐኪሞቹና ሌሎች ጥቂት ሰዎች ብቻ ነን ።

ያ ሲበጠብጠን የቆየው የተኩስ ድምጽ በመቋረጡ ቦታው ፀጥታ ሰፈነበት ። ሁሉም ድካም ስለ ተጫጫ ነው፥ ሥንቁን በመፍታት እየጐራረሰ ጋደም ጋደም አለ ። እኔና ናኒም ቦርሳችንን በመዳበስ ከሁለት ቀን በፊት የታ ደለን ሥንቅ አገኘንና ተቃመስን ።

አብዛኛውን ጊዜ የዶክተር ኃዘን እየመጣ ፊታችን ላይ ቢደቀንም ሌላ ወሬ በመጫወት ለመርሳት ከመሞ ከር ሌላ አማራጭ አልነበረንም ። የንፋሱ ድምጽ ከፍ ከማለቱም ሌላ አቧራውንም እያነሳ እንደ እንዝርት ይጫወት ስለነበር እነፋፊሱም ከመቼውም የተለየ ስለ ነበር ብዙዎቹ በመደነቅ የየራሳቸውን አስተያየት ይሰጡ ነበር ።

አንዱ "የተኩሱን ድምጽ መተካቱ ነው" ሲል ፤ ሌላው "ድል አድራጊነታችንን በማየት ጠራርጐ ወደ ሰፈራችን ሊመልሰን መምጣቱ ነው ።" ናኒም ሳትቀር በቀልዳዊ አነጋገር "ወደ ጠላት መንደር ሄዶ የነበረውን አቧራና ቅጠላ ቅጠል ጠራርጐ ሊመልስልን ነዋ ። መቼም

አሸናፊ አጃቢ እያጣም'' በማለት ።

እኔም ተራዬን እንድናገር ዓይን ዓይኔን እያየች ብትጠባበቅም ምንም አልተናገርኩም ። ባላሰብኩት መንገድ ሃሳቤ ሁሉ ወደእንቺው ተሻግሮ ----

አይግረምሽና ብቻዬን እንዳልሆን ለትካዜዬ ረዳት አግኝቻለሁ ። እኔ ከተቀመጥኩበት አራት ሜትር ያህል ርቆ ጋደም ያለው አንድ ሚሊሼያ ረጋ ባለ ድምጽ እንዲህ እያለ ያንጎራጉራል !

ተራራው ዞር በል ቤቴን ልለይበት
ማዶ ማዶ እያየሁ መንፈሴን ላስደስት ።
ግዳጄን ፈጽሜ አረፍ ከማለቴ
ትዝ ትይኝ ጀመር ውዷ ባለቤቴ ።
በቅርቡ እመጣለሁ ሆኜ ከአጠገብሽ
ልጆቼ እንዴትናቸው ? ምን ችግር አለብሽ ? !
አይዞሽ ተናገሪ ብዬ ስጠይቅሽ
እኔን እንዳይከፋኝ ዓይን ዓይኔን እያየሽ ።
" ደህና ነን " ስትይኝ ችግርሽን ደብቀሽ
ፈገግታ ስትሰጪ ትካዜሽን ውጠሽ
ከአሁኑ ታውቀኝ ታየኝ ሁለመናሽ ።

ግጥሙን እዚያው እየፈጠረ ሳይሆን አይቀርም፤ዜማ ውን ግን ከአሁን በፊትም ባላገር ውስጥ በማሲንቆ ሲጫ ወቱት ሰምቼዋለሁ ። በጣም ግሩም ዜማ ነው ። በተለይ

የተሜዎቹ ድምጽና የቦታው ፀጥታማ መሆን ልዩ ጣዕም ሰጥቶታል ።

ሚሊሺያው ማንጐራጐር የጀመረው በቀስታ ድምጽ ነበር ። ቀስ በቀስ ግን በስሜት እየተገፋፋ ሳያውቀው ድምጹ ከፍ አለ ። በአካባቢው የተኙት የሠራዊቱ አባሎችም ቀና ቀና በማለት ዘፈኑን ያዳምጡ ጀመር ። ከፊሎቹም በትካዜ ተውጠው ራሳቸውን በማወዛወዝ ስሜታቸውን ይገልጹ ነበር ። አልታወቀኝም እንጂ እኔም ራሴን ሳልወዘውዘው አልቀረሁም ። ዘፈኑን በሙሉ ስሜት እያዳመጥኩ ወደ አንቺ የምመለስበትን የጊዜ ርቀት ማማተሬን ቀጠልኩ ።

የካቲት 1970

አዜቢና ! ደስታና ችግር በሰው ልጆች ላይ ተፈራርቀው የሚደርሱ ነገሮች መሆናቸውን በየደቂቃው በማስታወስ የሚደርስብሽን ችግር ሁሉ በቀላሉ ለመወጣት ሞክሪ ። ችግርሽን በማቃለል በምታገኚአቸው ድሎች አትፈንጥዢ ፣ በአጭር አነጋገር በኑሮሽ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥምሽን ጥሩም ሆኑ መጥፎ ነገሮች ያለብስጭትና ፣ ያለሐዘን ፣ ያለትካዜ ፣ እንዳመጣጣቸው በመቀበል ለማስተናገድ ሞክሪ ! ምክንያቱም ፣ የሰው ልጆች ጨቋኞቻች

ውን ሁሉ ደምስሰው ቢያበቁ እንኳ ተፈጥሮን በቁጥጥ ራቸው ሥር እስካዋሉ ድረስ በየአጋጣሚዎች መቸገራቸው የማይቀር ነገር ነውና። ይህ ደግሞ ሊጠፋ የሚችለው ጠን ክሮ መታገልና በመሥራት ለተረካቢያችን ትውልድ ጥሩ መሠረት ስንጥልለት ብቻ ነው ። ሥራ ምን ያህል የሙን ፈስ እረፍት እንደሚሰጥና እንደሚያስደስት አንቺም ታውቂያለሽ ። አሁንም በሚገጥሙሽ ጥሩና መጥፎ ሁኔ ታዎች ሳትለወጪ ሥራን መሠረት አድርገሽ ያዥው ። መጪውን ትውልድ ከችግር ለማላቀቅ፣ ምርምርንና ፈጠ ራን አዘውትሪ ። ጊዜሽን ሁሉ ለሕዝባዊ ሥራ መስዋዕት አድርጊ ። በዚህ ጊዜ ብቻ የማይለወጥ አንድ ደስታ እንደ ሚሰማሽ እርግጠኛ ነኝ ። የጻፍኩት ሁሉ የምታውቂውን ነገር ነው ፤ ምንም አዲስ ነገር እንዳልጨመርኩበት አም ናለሁ ።

ነገር ግን መጠነኛ ድል በማግኘታችን ብቻ ሃሳቤ ሁሉ ወደ ኋላዬ በተመለሰበት ሰዓት ከላይ የገለጽኳቸው ነገ ሮች ተደራርበው በመምጣት የሕሊና ወቀሳ ስላስከተሉ ብኝ ላንቺም ጫጭሬ ለማስቀመጥ ተገድጃለሁ ።

ውዷ አዜብ ፤ በዚሁ ምሽት ልተኛ ከተሰናዳሁ በኋ ላ አንድ ነገር ትዝ አለኝና ልጽፍልሽ ብዕርና ወረቀቴን አወጣሁ ። እንደተለመደው "የኔዋ አዜብ" በማለት ጽሁ ፌን ስጀምር በሁኔታዬ በመገረም "እንዴ" -- ስትል

ሰማኋት ። በዚህ ጊዜ የተደነቀችበትን ነገር ለመጠየቅ ዞርኩና ስሜወት ልጽፍልሽ ያሰብኩትን ሁሉ ረሳሁት ።

"ምን አስደቀሽ ። ናኒ?" አልኩ ረጋ ባለ አነጋገር
"እንቅልፍ ነስቶ የሚያጽፍዎት ነገር ነዋ" ብላ በፌዝ ዓይነት ከተናገረች በኋላ ፣
"ለመሆኑ አዜብ የሚሏት ምንዎ ነች?" በማለት ጠየቀችኝ ።

ከአጠያየቋ እንደተረዳሁት ከሆነ ከፍተኛ የማወቅ ጉጉት አድሮባታል ። የመልስ አጠባበቋ ሁኔታ ሁሉ ከወ ትሮው የተለየ ነበር ። የምጽፈው ላንቺ መሆኑን ማወቋና ስምሽን መለየቷም በነገሩ ያሰበችበት ቀደም ብላ መሆ ኑን ያመለክታል ። ምክንያቱም ፣ በዚያ በምሽት ውስጥ የጻፍኳቸውን ፊደሎች እንዳልለየች እርግጠኛ ነኝ ። እኔ ባትሪ ይገኙ የምጽፈው እንኳ እየተቸገርኩ መከራዬን አይቻለሁ ። ብቻ ነገሩ ሲከነክናት መቆየቱ የማያጠራጥር ነው ።

ይኸውልሽ ስለአንቺ በመጠየቁ በጣም ደስ እያለኝ ነገሩን ሁሉ ዝክዝክ አድርጌ አጫወትኳት ። ሌላው ቀርቶ የፍቅር አጀማመራችን ሁኔታ እንኳ አልቀረኝም ። እየጻፍኩ የማጠራቅመው ደብዳቤም ላንቺ መሆኑን ገለ ጽኩላት ። እንዲያውም ከደብዳቤዎቹ ውስጥ ስለአንቺ

ብዙ የሚያወራውን ፊልጌ ከመሀል በማውጣት አነበብ ኩላት ። ምን አደከመሽ ስለእኔና አንቺ ያላጫወትኋት ነገር ቢኖር የረሳሁትን ብቻ ነው ።

ይሆን ሁሉ የለፈለፍኩት ወድጂ እንዳይመስልሽ ፤ ናኒ ብዙ ችግሮች አብራኝ ያሳለፈች ውድ ጓደኛ ነች ። ስለሆነም በትግል ጓደኝነትዋና በጥንካሬዋ በጣም እወዳ ታለሁ ። እሱዋም በጣም ትወደኛለች ፤ ግን አፈታቀርዋ በምን ዓይነት እንደሆነ ማን ያውቃል ። የእሱዋን አስተሳሰብ እንዴት መለየት ይቻላል ? ። ከዚህ ሁሉ ስለ አንቺ በደንብ ብገልጽላት የተሻለ ይሆናል ብዬ ነው ። ነፃ ብሆንማ ኖሮ የምትፈልገው ነገር ካለ በሙሉ ስሜት ከመቀበል ሌላ አማራጭ አልነበረኝም ። ነገር ግን የአንቺ እስረኛ ነኝ ። ስለዚህ ከጥርጣሬ ዓለም ለመውጣት አንቺን ከናኒ ጋር በማስታዋወቄ በጣም ደስ አለኝ ። ከአሁን በኋላ እኔም ሆንኩ ናኒ ያለጥርጣሬ በጥሩ ወንድምነትና እህት መንፈስ ተዋደን እንድንቆይ መንገዳችንን ያስተካ ከልኩ መሰለኝ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ልቤ በጭንቀት ተሞላ ፤ እኔ ውድ ፍቅረኛ እንዳለኝ ግልጽልጽ አድርጌ መናገሬ ናኒን ቅር የሚያሰኛትና የሚያስተከዛት መስሎ ታየኝ ። ይሆን ሁሉ የሚያሳስበኝ ብዙ ትግሎችን በጋራ እየተወጣናቸው መምጣታችንና መቀራረባችን ከፍ እያለ መሄዱ ነው ።

መጀመሪያም ይህን ያህል የሚያሳስበኝ ምንም ነገር አልነበረም ። ስለዚህም ስላንቺ ሳልነግራት ይህን ያህል ጊዜ መቆየቴ ጸጸተኝ ።

ናኒ የምንነግራትን ሁሉ በጽሞናና በረጋ መንፈስ ካዳመጠችኝ በኋላ ስለመልክሽ ስለአለባበስሽና ስለሥራሽ ሁኔታ እንድገልጽላት ጠየቀችኝ ። ጥያቄዋ ምክንያታዊ ነበር ። መልክሽንና መኖሪያሽን እንዲሁም ሥራሽን እን ደገለጽኩላት በመደነቅና በተለየ ስሜት ፣ "እሱዋማ ጓደኛዬ ነበረች ። እርግጠኛ ነኝ እሱዋ ራስዋ ነች--" በማለት ለጥቂት ደቂቃዎች ተክዛ ቆየች ።

ናኒን ከተዋወቅኳት ጊዜ ጀምሮ የዛሬውን ዓይነት ስሜት አይቼባት አላውቅም ። ከገባችበት ትካዜ ለመው ጣት ትንሽ ጊዜ ፈጀባት ። እኔም በዚህ ለት አንዳንድ ያጫወተችኝ ጨዋታዎች ትዝ አሉኝና ትካዜም ገባኝ ።

ሰው ሁሉ ተኝቶ ግማሽ እንቅልፍ ወርዷል ። በት ዝታ ባቡር አንቺንና ከተማውን ከጐበኘን በኋላ ግማሽ ሌሊት ላይ ተኛን ። የእንቅልፍ ነገር ግን ፈጽሞ ከአጠገ ባችን ጠፋ ። ያ ሁሉ ድካም ቀረና አዲስ ጉልበት ስንቀ ጥል የዋልን ይመስል ቁልጭ አልን ። ናኒ ሽርጧን በመከናንነብ ፊቷን ሸፍና ለወጉ ያህል ዓይኗን ብትከድን ውም ቁንጫ እንደበላው ሰው በየደቂቃው በመገላበጥ

ከሃሳብ እንዳልተላቀቀች ይመስክር ነበር ። እኔም ለወጉ ያህል ጋደም ብዬ ማሰላሰል ብቻ ሆነ ።

ናኒ በብቸኝነቷ ምን ይሰማት ይሆን ? እስመታደሏ ነው እንጂ ዶክተር ዘውገ በሕይወት ቢቆይ ኖሮ ሊፋቀሩ ይችሉ ነበር ። ወደ ፊት ናኒ የምትኖረው ከማን ጋር ነው ? ፈቃዱዋ ከሆነ ከእኔና አዜብ ጋር ብትቀመጥ መልካም ነው ። ለአዜብ ጥብቅ ጓደኛዋ ከሆነችማ ምን ችግር አለ ። እሱዋም ትዳር እስክትይዝ ከእኛ ጋር ቆጭ ማለት ብቻ ነው ።

እኔ ከማሰላስለው ሃሳብ ከፊሉ ይህን ዓይነት ነበር ። ናኒስ የምታሰላስለው ስለምን ይሆን ? ማን ያውቃል ። ብዙ ነገር ትዝ ሊላት ይችላል --- በዚህ ሌሊት እጅግ ተሰማችው ለልቤ ።

የካቲት 1970

ገና ሲነጋጋ የጦር አዛዡ ከተኛንበት ድረስ መጥቶ ተነሱ ሜዳው ድረስ ትፈለጋላችሁ ” በማለት እኔና ናኒን ቀሰቀሰን ። በሁለታችንም ልብ ውስጥ ” ደግሞ ለምን ይሆን ? የሚለው ሃሳብ እየተመላለሰብን ወደ ተባለው ቦታ ሄድን ። የሚፈልጉን ሰዎች ከሐረር ሐኪም ቤት የመጡ ነበሩ ። አጠገባቸው እንደደረስን ከተጨባ

በጥን በኋላ እንደኛው ለከባድ ሥራ ወደ ከተማው ሐኪም ቤት ስለምንፈለግ ሊወስዱን መምጣታቸውን ገለጹልን ።

በምንጓዝበት ወቅት አንዳንድ ጨዋታዎች ቢነሱም የእኔ ልብ ወደ ከተማ በር ስለነበር አልተከታተልሁም ። ናኚ ነች የመለሰችኝ ፤ ትከሻዬን ነካ ነካ አደረገችና በጠላት የወደሙትን ቤቶች እያሣየች ‘ይህ ሁሉ እኮ የሚጠብቀው የእኛኑ እጅ ነው ። ” በማለት ።

እኔም “ አዎ ” አልኩና እጇን እገጩ ላይ አድርጌ አተኩሬ ከተመለከትኩ በኋላ ” “ የበለጠውን ተወጥተን ዋል ፤ ይሄ ምን ያህል ሲከብደን ብለሽ ’ አልኩ ። የሹፌሩ አነዳድ በጣም ፍጥነት ስለነበረው ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሐረር ሐኪም ቤት ደርሰን ከመኪናው እንደወረድን ለዓይናችን ርቀውን የነበሩትን ብዙ ነገሮች ወደ ላይና ወደታች እንዲሁም ወደ ጐን እየተመለከትን ሳለ በድንገት “ እፎይ - - - ይ ” አልኩና ተነፈስኩ ። ናኚም እኔኑ በፈገግታ እየተመለከተች “ እስ - - - ይ ” አለች ። የእሱዋ ለቀልድ ያህል የተደረገ ነው ። የእኔ ግን ከብዙ ነገሮች ማሰብና ማሰላሰል እንዲሁም ላይ ታቹን ከማስተዋል በኋላ የተገኘ ድካምን መግለጫ ትንፋሽ ነው ።

የሆስፒታሉ ሠራተኞች እየተሯሯጡ በመምጣት ተጠመጠሙብን ። እንደኳስ ጨዋታ ጀግናም ወደ ላይ እንስተው በመሸከም እልልታውን እያቀለጡ ወደ ማስተናገጃ ክፍል

ወስዱን ። ከዚህ በኋላ ያለውንማ ስንቱን እገልጽልሻለሁ። ሲስሳሳ መጠጡና ምግቡ ቀርቦ ጨዋታው ደራ ። ሁሉም ያጋጠመውን እንድናወራለት አስፈሰፈ ። በመሀከሉ ስለ ዶክተር ዘውገ ተጠየቅን --- ያለ መስዋዕትነት ድል የማ ይታለም ነገር ነው ። ሁሉም "ግድ የለም ብቻ እንኳን እናንተው ተረፋችሁ" በማለት ለማጽናናት ሞከሩ ።

ናኒም ፈገግታ እያሳየች "የእኛ መትረፍ ይህን ያህ ል ዋጋ ሊሰጠው አይገባም ። ይልቅ እንኳን ድል ተቀዳ ጃሁ በሉን " አለች ።

ይኸውልሽ በራሳችን አነሳሽነት የጦር ሜዳውን ፍልሚያ ተካፍለን የተመለስነው ሁለት ጓዶች በግቢው ውስጥ ተወዳጅነትንና አድናቆትን አተረፍን ። በአሁኑ ወቅት ከሆስፒታሉ ውጪ ሁለት የመኝታና አንድ የእ ንግዳ መቀበያ ሳሎን ያለው ቤት ተሰጥቶን ሥራችንን እንድንቀጥል ተደርጓል ። እንደ ጥንቱ ሥራውን ተያይዘ ነዋል ። የአኗኗራችንም ሁኔታ መልካም ባልና ሚስት የሚያደርጉትን ይመስላል ። እሱዋ ምግብ ስታበስል እኔ ቤቱን እያፀዳሁ ፣ ልብስ ስታጥብ ውሃ እያቀረብኩና በሌ ላውም ሁሉ እየተባበርን ሠርተን መኖር ዘወትራዊ ተግ ባራችን አድርገናል ።

በሆስፒታሉም ውስጥ ለቁስለኞች የምናደርገው እር ዳታ ከጥንቱ የበለጠ እንጂ ያነሰ አይደለም ። ስለ ሁለታ

ችን ፍቅርና ሥራ ሁሉንም ልዘረዝርልሽ አልችልም ። እንቺው ተገናኝተሽኝ ለማየት ያብቃሽ ፤ እስከዚያው ግን መልካም እህቴ መልካም ወንድሟ መሆናችንን ብቻ እወቂልኝ ።

መጋቢት 1970

ከጦር ሜዳው ተመልሼ አንድ ሳምንት ያህል ከቆየሁ በኋላ ይህንን ሳጠራቅመው የቆየሁትን ደብዳቤ ልል ከልሽ አሰብኩና በትልቅ የወረቀት ከረጢት ውስጥ ጨምሬ አሽግሁት ። ነገሩን ለናኒም አማከርኳት ። ሆኖም እሷ በመላኩ በኩል አልተስማማችም ። ለዚሁም ያቀረበችልኝ ጥያቄ "ለመሆኑ መደምደሚያውን ምን አሉት እርስዎ ሊሄዱ አሰቡ ወይስ እሷ እንድትመጣ ? "የሚል ነበር ። እኔም በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ነገር እንዳልፃፍኩልሽ ገለጽኩላት ። በዚህ ጊዜ ደብዳቤውን አሁን እንዳ ልልክልሽ በመቃወም ፤

"ምንም የሚያስቸኩልዎት ነገር የለም ።" እስከአሁንም ሳይሄድላት ቆይቷል ። ከአሁን በኋላማ ምን ችግር አለ ? እርስዎ አንድ ነገር ቢያጋጥምዎት እንኳ እኔ ልል ክላት እችላለሁ ። ይህን ሁሉ የምልበት ምክንያት አለኝ። መቼም እኛ ከአሁን በኋላ ወደ አዲስ አበባ የምንመለስ አይመስለኝም ። --- ተመልሰንስ ደግሞ ምን ልንሠራ ?

እዚሁ ብዙ ሥራ ይጠብቀናል ። ስለዚህ "እቅዳችንን" እንጀምርና እሱዋም እዚሁ እንድትመጣ እናድርግ ። እን ዲያውም ጥሩ መንገድ ይሆነናል ።"

አነጋገሩ ትክክልና አሳማኝ ስለነበር ልልከው ያዘጋ ጀሁትን ደብዳቤ ከፊትኩትና እንደገና መጻፌን ቀጠልኩ ፣ አዜቢና ፤ ናኒ "እቅዳችንን" ብላ ያቀረበችው ሃሳብ ት ንሽ ግር ሳይልሽ አልቀረም ። እኔም ቀደም ብዬ ሳልገል ጽልሽ መቅረቴ ስህተተኛ ነኝ ። ገና ከጦር ሜዳ እንደተ መለስን በመልሶ ማቋቋሙ ረገድ የምናደርገውን ተሳትፎ ስንነጋገር ከሕዝቡ ጋር በመተባበር መጠነኛ የጤና ጣቢያ ለመሥራት እቅድ አውጥተን ነበር ።

ናኒም "እቅዳችን" ብላ የተናገረችው ይህንኑ ነው። የጤና ጣቢያው ከተሠራ አንቺም እዚህ መጥተሽ እየሠ ራሽ ለመኖር እንችላለን ። ከአሁን በኋላ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተመልሰን የምንሠራው ምንም ከባድ ሥራ አይኖ ርም ። ናኒ እንደምትለው ብዙ ሥራ የሚጠብቀብን እዚሁ ነው ።

መጋቢት 1970

— ጦርነቱ አከተመ ለማለት ባያስደፍርም እንኳ መረ ጋጋቱን መጠቆም ይቻላል ። ስለዚህም ሕዝቡ በጠ ላት የወደሙትን ቤቶችና ንብረቶች በመገንባት ከተፈ

ጥሮ ጋር ትግሉን ተያይዞታል። የገንዘብና የሰው ኃይል ስለሚያስፈልግም ሕዝባውያን ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉ ተጠይቋል። በዚህ ዓይነት ሌላውና ከተፈጥሮ ጋር የሚደረገው ጦርነት ተጀምሯል።

እኔና ናኒም የክፍለ ሀገሩን አስተዳዳሪ በማማከር የጤና ጣቢያውን ሥራ ለመጀመር ተነስተናል። እንዲህ ዓይነቱን መልካም ተግባር የሚቃወም ሕዝባዊ ከቶ ሊኖር አይችልም። የክፍለ ሀገሩም አስተዳዳሪ በነገሩ ላይ ያላቸውን ሙሉ ድጋፍ ጠቁመው በዕቅዱ ላይ ሰፊና ጠለቅ ያለ ውይይት እንድናደርግ የሥራው ልምምድ ያላቸውን ሶስት ሰዎች ሰጥተውናል። እቅዱን በተግባር ለማዋል በአፈጻጸሙ ላይ የሚገጥሙንን ችግሮችና መፍትሔአቸውን ለአራት ቀናት ያህል ከነዚሁ ሰዎች ጋር ተወያይተናል።

በከተማው ውስጥ የሚገኘውን ሕዝብ በመቀስቀስ ለዚህ በጐ ዓላማ በገንዘቡና በኃይሉ እንዲተባበረን አድርገናል። የጤና ጣቢያው መሠረት የተጣለ ዕለት የተሰማንን ደስታ ምን ጊዜም አንዘነጋውም --- ለግባችን ፋና ሆኖ በልባችን ውስጥ ይኖራል።

መጋቢት 1970

ናኒ የቡታ ጋዙን ከፈተችና እሳት ካቀጣጠለች በኋላ “ዶክተር ወደዚህ ይምጡ ዛሬ ጎመኑን የሚቀቅሉት እር ስዎ ነዎት ፤ እኔ ሻይ አፈላለሁ” አለች ። ፍቅር የተሞላ በት ትዕዛዝዋን ተቀብዬ ጎመኑን መቀቀል ጀመርኩ ። ብዙ ጊዜ የእኔ ሥራ ሻይና ወተት ማፍላት ፣ ውሃ ማቅረ ብ ፣ አልፎ አልፎም እንቁላል መጥበስ ስለነበር ፣ ናኒ ይህ ንን ሥራ ያዘዘችኝ ልትስቅብኝ ፈልጋ ነው ።

እኔ ግን እሷዋ ስትሠራም አጥብቄ እመለከት ስለነ በር ሽንኩርቱንም ፣ ቅመማ ቅመሙንም በየተራው በመ ጨመር በጥሩ ሁኔታ አበሰልኩት ። ፈገግታ እያሳየች “ግሩም ነው ፣ ነገም ወጥ የሚሠሩት እርስዎ መሆን አለብዎት” አለች ።

እኔም በሥራዬ እየተኩራራሁ “በሚገባ ነዋ ምን ይጐለኛል” አልኩና ከቀቀልኩት ጐመን በሹካ አቀመ ስኳት ። በምላሱዋ እያጣጣመች “ግሩም ድንቅ” ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ የውጪው በር ስለተንኳኳ በፍጥ ነት ርምጃ ሄደችና ከፈተች። ወዲያውም “ይግቡ ይግቡ” ስትል ሰማኋት ።

ጐረቤታችን ናቸው ፤ የሚሠሩትም በቴሌኮሙኒኬሽን ውስጥ ነው ። ብዙ ጊዜ እየመጡ ከእኛው ጋር ያመሻሉ ። በዚህም ዕለት የመጡት እንደወትሮአቸው ተጫውተው ለመሄድ ነበር ። ገና ከቤት እንደገቡ ለመጀመሪያ ጊዜ

የጠቁኝ፣ “ዕቅዳችሁ ተጀመረ ሲባል ሰማሁ ፣ እርግጠኛ ነው ?” የሚል ነበር

“ አዎ ! ኑሮ ከተባለ እንዲሁም ይኖራል ፤ ለእናት ሀገር አልፎም ለዓለም ሕዝቦች አንድ አስተዋጽኦ ማበርከት ግን የመንፈስ ደስታን ከመስጠቱም በላይ ትልቅ ነገር ነው” በማለት ናኒ ተናገረች ። ይህ አነጋገሯ የጐረቤታችንን ልብ የነካ ይመስላል ፤ ለጥቂት ደቂቃ አቀርቅረው በነገሩ ሲያስቡበት ቆዩ ። ራት ቀርቦ በምንበላበትም ጊዜ ሁለታችንንም በአድናቆት ይመለከቱን ነበር ፤ በጋራ ሠርተን መብላታችንን በመመልከት “በጣም የሚስቀና ኑሮ ነው” ማለታቸው የተለመደ አነጋገር ሆኗል ። እንደተለመደውም ታዲያ ፣ የጤና ጣቢያው መጀመር ከሰጠን አዲስ ተስፋ ውጪ ፣ ጦርነቱ ቦላ ስከተለው ጉዳት ፣ ስለ መልሶ ማቋቋም ፣ ስለቤተሰብ መብታት ን ፣ ስለጋብቻና ስለመሳሰለው ስንጨዋወት አመሸን።

በዚህን ዕለት ናኒና እኔ ያለወትሮአችን ለብዙ ጊዜ ቁጭ ብለን ስናወራ ቆየን ። ደግመን ፣ ደጋግመን የምንጫወትውም ስለ ጤና ጣቢያው ሥራ ጉዳይ ነበር ። በሁለታችን ታቅዶ የተጀመረው ይኸው ተግባር እንዳሳሰበን እሙን ነው ። ከሁለታችንም በኩል “ እረ እንተኛ ” የሚል ጠፋ ። ሌሊቱ እየተጋመሰ ሲሄድ ደስታ አይሉት ትካዜ ሁለታችንም እየተጫጫነን ሄደ ። እንዲያው ብቻ

ቅዝዝ ቅዝዝ ብለን መተያየት ሆነ ። በዚህ ጊዜ ነው ናኒ በለሰለሰና ፍቅር በተሞላበት አነጋገር "መተኛቱ ሳይሻል አይቀርም ፤ ዶክተር" ብላ የተነሳችው ፤ ሁለታችንም ሜና እንደ ተሸከመ በኃይል ተነፈስን ፤ እሷም ወደ ክፍሏ እኔም ወደ ክፍሌ የሄድነው ። በዚህ ሌሊት አንቺ መምጣት እንዳለብሽ ወሰንሁ ።

መጋቢት 1970

ውዷ አዜብ ፤ ከአሁን በኋላ እምብዛም የሚገጥመኝ ከባድ ነገር የሚኖር አይመስለኝም ። ብዙ ትግሎችንም አልፌአለሁ ። በእርግጥ ወደ ኮሙኒዝም የሚወስደው ረዥሙ ጉዞ ገና መጀመሩ ነው ። ሆኖም ከአንቺ ጋር ለዚህ ዕውን መሆን ከአጠገቤ ሆነሽ አብረን እንድንጓዝ ወስኛለሁ ። ከአሁን በኋላ የሚያጋጥሙኝንም ሆነ የሚያጋጥሙሽን ነገሮች አብረን መቋቋም ይኖርብናል ። የዓላማ አንድነት ያለን ፍቅረኞች ተራርቀን የምንቆየው እስከመቼ ነው ? በእኔ ብኩል እዚሁ ድረስ መጥተሽ ብዙ ያልለሙ ሥፍራዎችን እያለማን የሚጠበቅብንን አስተዋጽኦ ሁሉ እያበረከትን ወደፊት የሚጠብቁንንም ትግሎች በጋራ እንድንወጣቸው ወስኜአለሁ ። አንቺም የመምጣቱ እድል ከተሳካልሽ ወደ ኋላ እንደማትይ እርግጠኛ ነኝ ። ስለዚህ የምትችይ ከሆነ በቅያሬ ሐረር ሐኪም ቤት ለመምጣት ሞክሪ ፤ ይህን የማይፈቅዱልሽ ከሆነም ከዚያ እንዲለቁሽ ጠይቀሽ መምጣቱ አይከፋም ። የሥራው ጉዳይ ብዙ እንዳያሳስብሽ ፤ እዚሁ

ከመጣሽ በኋላ ማስተካከል እንችላለን ። እንኳን እንዳንች ዓይነቱ ሥራ ወዳድና ታታሪ ቀርቶ መቀመጫ ለማሞቅ ብቻ የሚቀጠሩም ጥቂት አይደሉም ። ደግሞም ለእጭር ቀናት ያህል ነው እንጂ የአዲሱ ጤና ጣቢያ ሥራ ሲያ ልቅ እዚያው ድረስ እየሄድን በማጠናከር የምንሠራው እኛው ነን ። በገጠር አካባቢ ያለን ሆስፒታል የሚወደው ሠራተኛ ቁጥር እንደሆነ ዝቅተኛ ነው ፤ ባለሽበትም ቦታ የምትሠሪው ሥራ ቀላል እንዳልሆነ አውቃለሁ ። ሆኖም እዚያ አካባቢ ብዙ አዋቂዎች ስለሚገኙ ያንቺ መምጣ ት ይህን ያህል ጉዳት አያስከትልም ። እዚህ መምጣትሽ ግን እንደኛ ፣ እኔም ወዳንቺ አንቺም ወደ እኔ ማሰባችን ቀርቶ ተጣምረን በጠንከረ ሁኔታ እንድንሠራ ይረዳናል። በሌላ በኩል ደግሞ ምሁራን በተጠራቀሙበት አካባቢ ከማገልገል ይልቅ እዚህ ብዙ ኃይል በሚያስፈልግበት ቦታ መሥራቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ነው ። መቼም ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሚሆነው የእኔ ወደ አንቺ ለመምጣት ያለመቻል ነው ። በእርግጥም ለጥቂት ጊዜ ብቻ ሳይሆን እስከመቸውም ወደ አዲስ አበባ መመለሱን አልፈልገው ም ። ብዙ ሕዝባዊ ሥራዎች የተከማቹበት እዚህ ነውና ። እንግዲህ በሚመችሽ መንገድ ሁሉ ጥረት አድርገሽ እዚሁ ድረስ ለመምጣት ሞክሪ ።

ከቻልሽ አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ የቤት ዕቃዎችን ም ይዘሽ ነይ ፤ ካለዚያም እዚያው ለዘመዶችሽ ስጫቸው ።

ከአንቺ መምጣት በስተቀር ለምንም ነገር አትቸገሪ ፣ እናቴንም ቢሆን እዚሁ አምጥተሻት አብረን ብንቀመጥ የተሻለ ነው።---መቼም ከሌላ ሰው ጋር ተግባብታ ልት ኖር አትችልም። ቤቱን ግን በቀጥታ ለቀበሌው ማህበር አስረክበሽ ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውል አድርጊ። እኔም እዚህ የምኖረው አዲስ ጐጆ ሠርቼ ሳይሆን መን ግሥት በሰጠኝ የሕዝብ ቤት ውስጥ ነው። በተረፈ ማን ኛውንም ነገር ተሳክቶልሽ ወደ እኔው መጥተሽ እስክን ገናኝ ድረስ ደህና ሁኚልኝ።

ያንችው ገድሉ በሪሁን ( ዶ/ር )

ደብዳቤዎቹን በዝግታ አነበብኳቸው ፤ አንዳንዶቹን ደጋገምኳቸው። ብዙ ስሜቶችም ተፈራረቁብኝ። ስለጦ ረነቱ ሁኔታ ባነበብኩበት ጊዜ “እውነት ዶክተር ገድሉ ይህን ያህል ጀብዱ ፈጽመው ? በማለት ተገረምሁ። ስለናኒ ባነበብሁ ቁጥር ግን ሰውነቴ እየተረበሸ አስቸገረኝ---- ሳልወድ ሁለመናዬ ይነዳል---ደግሞ ናኒ ብሎ ጓደኛ-- ኖሮኝም አያውቅ ደግሞ የዶክተር አለማጤን---

## 26

ለማንኛውም እቅዴን አወጣሁ። እቅዴን ለማስፈ ጸም ከወዲያ ወዲህ መራወጤንና የማውቃቸውን ሰዎች ሁሉ ማማከሬን ቀጠልኩ። ለመሥሪያ ቤቴ አስተዳደርና

ለሚመለከተው ክፍልም ሁኔታውን በማስረዳት ወደ ሐረር ሐኪም ቤት እንድቀየር ጠየቅሁ ። ከገጠር ወደ አዲስ አበባ ለመቀየር የሚፈልጉ ሐኪሞች በርካታ መሆናቸውን ባውቅም "ከክፍለ ሀገር ወደዚህ የሚቀየሩ የሉም ።" እየ ተባለ ተደጋግሞ ተነገረኝ ። ሆኖም ደጋግሜ በመወትወ ትና ሌላ አማራጭ በመፈለግ ወደ ሐረር የሙቀየሩን ጉዳይ ለማሟላት መታገሌን ቀጠልኩ ። አንዳንዴ ተስፋ ሲያ ስቆርጠኝ አንዳንዴም ቀጠሮ ሲሰጠኝ የቅያሬው ጉዳይ ሳይሳካልኝ አስራ አምስት ቀን ያህል ቆየ ። ከዚያ ከናካ ቴውም ከመሥሪያ ቤቴ እንዲያሰናብቱኝ ጠየቅሁ፤ ይህም አልተቻለም ።

በዚሁ ሰሞን ውስጥ የእነ ዶክተር ገድሉ መልካም ተግባር እንደሚገለጽ ተነገረ ። እኔም በተባለው ቀን ቴሌ ቤዥን ከፍቼ ስጠባበቅ "እውቀታቸውንና ኃይላቸውን እንዲሁም ሕይወታቸውን ለሰፊው ሕዝብ ትክክለኛ ዓላማ መስዋዕት ያደረጉ ሕዝባውያን" በሚል ርእስ የሶስት የሕ ክምና ጓዶችና የአንድ ሕዝባዊ ተጋድሎ እንደሚቀርብ ተነገረ ። ዝርዝሩም መቅረብ ጀመረ ።

በዚህ እለት የደነገጥሁት ድንጋጤ እስካሁንም ከሰ ውነቴ አልወጣ ። ለጊዜው ዓይኔን አላመንኩትም ። ለካስ ከሶስቱ ባለታሪኮች አንደኛዋ ትሩፋት ኖራለች ። ዶክተር እንዴት ስለሲስተር ትሩፋት ሳይጽፉልኝ ቀሩ? ወይንስ

ናኒ እያሉ ሲጽፉልኝ የነበሩት ስለእሱዋ ነው ? ። ለምን እውነተኛ ስሟን ደበቁኝ ? ምነው ምን በደልኳቸው ? እሷ ንስ ቢሆን ምን በደልኳት ? ብቻ በሃሳቤ ያልመጣው አሁንም ቢሆን የማይመጣው አስተሳሰብ የለም - - - ደግሞ ቴሌቤዥን ላይ ሲያሳያት እንዴት አድርጋ ነበር ዶክተ ርን የምትመለከታቸው - - - -

- - እጃቸውን ያዝ አደረገቻቸው ፣ እሳቸውም በግራ ክንዳቸው አቀፍ እንደማድረግ - - -ምንስ ለቴሌቭዥን የቀ ረቡ ቢሆን ይኸን ያህል መቀራረብ - - ምናልባት እጮኛ ዋን ያስከዳሁባት መስሏት ይሆን ? ምን በደልኳት - - - አሁንም አሁንም ሳስበው እንዳንዘፈዘፈኝ ነው ያለሁት ።

ለሁሉም የዶክተር ገድሉ ስማቸውን ማስጠራት ለእ ኔም የቅያሬ ጥያቄ መልካም መንገድ ከፈተልኝ ። በእሳ ቸው ዝና እኔም ሰዎች ተዋወቅሁ ። ለአሥራ አምስት ቀን ያህል ከላይ ታች የደከምኩበትም ጥያቄ አሁን ተቀ ባይነት አገኘ ። ለጉዞዬም መሰናዳቴን ጀመርኩ ።

ቤቱን ለቀበሌ ማኅበር አስረከብሁ ። ታናሽ እህቴም ወደ ወላጆቼ ተመለሰች ። የወላጆቼ ምኞት አጠገባቸው ሆኜ ወግ ማዕረጌን ማየት ቢሆንም ቅሉ አልተሳካላቸ ውም ። በኑሮዬም ቢሆን ከእነሱ ጋር የተራራቅሁት ገና ነርሶች ማሠልጠኛ ት/ቤት ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ ነው ።

በጉዳዩ መቁረጤን ሲያውቁ “ በይ ደህና ሁኚ” ብለው ከመሸኘት ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም ። እኔም የሚያስፈልጉኝንና መያዝ የሚገባኝን ዕቃዎች ካሰናዳሁ በኋላ ስንብት ፣ መሸኛ ፣ ጨዋታ የሚባለውን ጣጣ ፈንጣጣ ሳላበዛ ከቤቴ ወጥቼ አልኩ ። ወላጆቼ እስከ ባቡር ጣቢያው ድረስ ለመሸኘት ቢከጅሉም “ ተመለሱ እንጂ የምን አጀብ ነው ። እየመጣሁ እጠይቃችኋለሁ” በማለት ስለተቆጣሁ ወደ ቤታቸው ተመለሱ ። ታናሽ ወንድሜ ብቻ ሻንጣዬን ተሸክሞልኝ እስከ ባቡር ጣቢያው ድረስ ሸኘኝ።

የምሄድበት ባቡር እዚያው ቆሞ ስላገኘሁት ከወንድሜ ላይ ሻንጣውን ተቀበልኩትና “ በል ደህና ሁን ፤ በእረፍት ጊዜዬ እየመጣሁ እጠይቃችኋለሁ” ብዬው ወደ ውስጥ ገባሁ ። ታናሽ ወንድሜ እት አበባ ፣ አትስሚኝም እንዴ ? ለማለት ፈርቶ በትካዜ ፊት ፊቴን ሲያየኝ ነገሩ ስለገባኝ ተመለስኩና ሳምሁት ። ምን ማድረግ ይቻላል ? መጥፎ ተለምዶ ነው ። በፊትም ሳልስመው የገባሁት ጉንጩን ሰስቼ አልነበረም ፤ ግን ሆድ ከማባባት በስተቀር ምን ሊጨምርለት ? ።

እንደዘመኑ ፋሽን ለጉዞ በምንሳበት ጊዜ ዘመድ አዝማዶቼንና ጓደኞቼን ጠርቼ በአጀብ መሸኘቱን አላጣሁ በትም ። ወላጆቼንም ደግሜ ደጋግሜ እየሳምኩ “ ደህና

ሁሉንልኝ'' ካልኩ በኋላ ባቡር ጣቢያው ድረስ መጥተው ከንዳቸውን እያውለበለቡ እንዲሸኙኝ ማድረጉ አልከበ ደኝም ። ግን ይህ ሁሉ ምን ሊጠቅም ? ከዚህ ሁሉ እኔም ቀራጥ ሆኜ ወላጆቼንም ለእንዲህ ዓይነቱ ነገር እንዳ ይጨነቁ ማድረጉ የተሻለ መሰለኝ ። ያልተለመደ ነገር በመሆኑ ነው እንጂ ፣ ወገኖቻችን ለመርዳትም ሆነ ፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ፣ በየክፍለ ሀገሩ እንደተዘዋወሩ እድሜ ያቸውን የገፉ ጥቂት አይደሉም ። ወደ ፊትም በስም ''ዘመድ'' በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ መቀመጥ የማይቻል ነገር ነው ። በየቦታው እየተዘዋወርን የምንሠራቸው ብዙ ሕዝባዊ ተግባሮች ይኖራሉ ፤ ታዲያ ያን ጊዜ እየተ ሳሳሙና እየተላቀሱ ለመለያየቱ ማን ቦታ ይሰጠዋል ?

ባቡሩ የመንቀሳቀሻው ሰዓት ስለደረሰ ድምጹን አሰማ ። ተሳፋሪዎችም ተመቻችተው በመቀመጥ እየተነ ቃንቁ ወደ ፊታቸው ይመለከቱ ጀመር ። ባቡሩ ተንቀሳ ቀሰ፤እኔም ነቃ ብዬ በመቀመጥ ፊት ፊቴን ማየት ጀመርኩ። ነፋሻማው የሌሊት አየር እኔኑ ለማስተናገድ ዛሬ ብቻ የመጣ መሰለኝ ። የተሳፋሪዎቹ ሆሆታና ጫጫታ ከባቡሩ ድምጽ ጋር ተዋህዶ እንደሙዚቃ አስተጋባ ። ሳላስ በውና ሳልፈልገው የሚያስደስት ነገር መንፈሴን እየቀ ሰቀሰው ፈገግ ማለት ጀመርሁ ። የምጠላው የሲጋራ ጢስ ሲሸተኝ ጥሩ ጣዕም እንዳለው ነገር ሆኖ ተሰማኝ ። ጫጫታውንም ቢሆን እንደሙዚቃ ስተረጉመው ይህ

የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ። በዚያ ምሽት ሁሉም ነገር እኔን ደስ የሚያሰኝና ለእኔ ብለው የማያደርጉ መሰለኝ ። ወደ እነ ዶክተር ገድሉ በሃሳቢም በባቡርም እየተጓዝኩ ፊቴ በደስታ ተሸፈነ ።

አንዳንዴ የማያደፈርስብኝ ነገር ቢኖር ትሩፋት ስትታወሰኝ ብቻ ነበር --- እስካሁንም ሁሉቱን ለያቼ ማሰብ አቅቶኛል ። ግማሽ ሌሊት አካባቢ ድሬስ ተኝቼ ስወራጭ ቆየሁ ። ስደሰትና ስተክዝ እምብዛም እንቅልፍ አልወሰደኝም ። አንገቴን በመስኮት ብቅ አድርጌ የደረ ስንበትን ለማወቅ ፈለግሁ ፤ በግምት ግማሽ መንገድ ሳን ጓዝ አልቀረንም ፤ ባቡሩ ከዚህ በበለጠ ፍጥነት ለመጓዝ ባይችልም እንኳ እኔ በሃሳቢ ቀድሜው ሄጃለሁ ።

በማግስቱ አስራ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ድሬዳዋ ከተማ ደረስን ። ከዚያም በታክሲ ወደ ሐረር ሐኪም ቤት አመራሁ ። ከሆስፒታሉ በራፍ እንደደረስሁ ልቢ በድን ንጋጤ ይመታ ጀመር ። ምን ይገጥመኝ ይሆን ? በእርግጥ ከእነ ዶክተር ገድሉ ጋር የምንገናኝ አልመሰለኝም ። ለማ ንኛውም ፤ መጀመሪያ ዘበኛውን ስጠይቃቸው "እንጃ ልጄ እስቲ ወደ ውስጥ ግቢና ጠይቂ" አሉኝ ፤ ስተት ብዬ ገባሁ ። ሽርጥ ለብሶ ወደ ክፍሉ በመሮጥ ላይ ሳለ ያየሁትን ሰው እጄን አውለብልቤ አስቆምኩና ጠየቅ ሁት "ሥራቸውን ጨርሰው ወደ ቤታቸው ተመልሰዋል"

በማለት ከመለሰልኝ በኋላ የያዝኩትን ሻንጣ ትክ ብሎ እየተመለከተ" ከሩቅ ነው የመጣሺው ?" ሲል ጠየቀኝ፣ እኔም "አዎ ከሩቅ ነው ፤ ወዴት ላገኛቸው እችላለሁ ?" ብዬ በማስተዛዘን ጠየቅሁት ። ሸርጡንም ሳያወልቅ "እኔ አሳይሻለሁ" አለና ሻንጣዬን ይዞልኝ ከግቢው ወጣን ።

የዶክተር ገድሉ ቤት ከሐኪም ቤቱ ስለማይርቅ በፍ ጥንት ደረስን ። በር ስናንኳኳም ትሩፋት ብቅ አለችና ስታ የኝ "አዜብ" ብላ ጮኸች ። በዚህ ጊዜ ዶክተር ገድሉም እየሮጡ ወጡ ። ሁለቱም እየተንደረደሩ መጥተው ተጠ መጠሙብኝ ። እኔም የሁለቱንም አንገት እቅፍ አድርጌ ፊቴን መሀከላቸው አስገባሁ ።

ዶክተር ገድሉ " አዜቢና ፣ ለዚህ ደረስን " ሲሉኝ ትሩፋት ደግሞ ቀኝ ጉንጬ ላይ ጥብቅ ብላ " --- እን ደገና ተገናኘን" አለችኝ ። ጥርጣሬዬ ሁሉ ከትከሻዬ ላይ ወረደልኝ ፤ ቅዠቴ ወደ አስደሳች ሕልም ተለወጠ ። ለጊዜው ለይቼ የማነጋግረውን አጣሁ ፤ እንዲሁ በደፈ ናው ሁለቱንም " ደህና ናችሁ ?" ማለቴን ቀጠልኩ ። በዚህ መሀል ሻንጣዬን ተሸክሞ የመጣው ሰው ትዝ አለ ኝና ዘወር ስል ፣ አሁንም ተሸክሞ እንደቆመ በአድናቆት ይመለከተናል ። "አውርደው እንጂ ፤ ኧረ እንዴት ዓይነቱ ትሁት ሰው ነው" አልኩና ልቀበለው ስል ዶክተር ገድሉ

ቀድመውኝ ተቀበሉት ። ልቤ ወደ እነ ትሩፋት ጨዋታ ሄዶ የረባ ምሥጋና እንኳ ሳላቀርብለት ወደ መሥሪያ ቤቱ ተመለሰ ።

## 27

ትሩፋት ተለውጣለች ፥ ፊቷ በጣም ጠቋቁሯል ፤ ገጽ ታዋ ሁሉ እንዳለፈው ጊዜ ሳይሆን የተኮማተረና ጥንካሬ የተሞላበት ሆኗል ። የዶክተር ገድሉም ፊት በጣም አፈ ርማ ሆኗል ሻካራ ዓይነት ።

ከተገናኘን ገና ሠላሳ ደቂቃ እንኳ ሳይሞላን ዶክተር ገድሉ ፈገግ ብለው በናፍቆት ዓይን እየተመለከቱኝ “ ይኸውልሽ ገና ከአሁኑ ያ -- ግልጽ ያልሆነልኝ ትካ ዜና ሃሳብ ለቀቀኝ ” አሉ ።

በፊት የተጨነቁበትንና እኔ ስመጣ መድህን የሆን ኩብትን ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ብዙ አሰላሰላለሁ ። ከእን ዲግሀ ብቸኛ ያለመሆናቸው ይሆን ? -- ወይስ የፍቅ ራቸው ሚዛን የደፋበትን ማወቃቸው -------

በዚህ ምሽት የቅርቡን የሩቁን እያነሳን ብዙ ተጫ ወትን ። ስለ አሮጊቷ በጠየቁኝ ቁጥር ግን “ደህና ናቸው ፥ ለመምጣት ግን አልቻሉም ” በማለት እየሸፋፈንኩት ቆየሁ ። በስንት ጊዜያችን የተገናኘን ሰዎች ጨዋታ ያለ ቀብን ይመስል “ በሉ እንተኛ ” ተባባልን ።

ናኒ ቀስ እያለች ብድግ አለች፤በለዘብታ አስተያየት እኛ እኛን እያየች ። እኔም ሳይታወቀኝ አብሬ ብድግ አልኩ፣ የአክብሮት እንሳስ ዓይነት ፤ እሱዋ እጇዋን ስታሰናዳና እኔ እቅፏ ውስጥ ስገባ አልታወቀኝም፤ ያ -- ቅፅበት የና ፍቆቴ ማሠሪያ እንደሆነ ተሰማኝ ።

እጆቹዋን ቀስ እያለች ከትከሻዎቼ አውርዳ መለስ አላለሁ ስትል "ናኒ" አልኳት ፤ ፊቷን ሳትመልስ ቆም እንደ ማለት ስትል ፣

"ጓዴ ደህና እደሪ" አሏት ዶክተር ፤ ፍቅር ፣ አክብሮትና ስሉነት በተመላበት እንደበት ፤ ዘወር ብላ አየችን ። እንደገና በዚህን ወቅት ፤ ልጆቹዋን ሳስማ አስተኝታ ደህና እደሩልኝ በሚል እናታዊ አስተያየት --- ናኒ ስሟ ብቻ አይደለም ለካ አዲሱ አልኩኝ በልቤ --- ተፈጥሮዋም እንጂ ፤

ከሄደች በኋላ እንኳ ያለች ያህል አብረን ብዙ ጊዜ ቆየን ፤

የልባቸውን እንጉልል ቀስ እያሉ በመተንፈስ "ማን ያውቃል ያለላትን--- " አሉ ዶክተር ፣በግራ ክንዳቸው አቀፍ እያደረጉኝ "ማን ያውቃል ---" ደረታቸውን ደገፍ ብዬ አሰላስል ገባሁ ።

ናኒ ከወጣች በኋላ ዝም ብሎ መተያየት ሆነ ። ዓይና ቸው ሁለመናየን እየደባበሰ ቀስ እያለ ቀለበት ጣቴ ላይ አረፈ ። በቅፅበትም ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቶ “ አስበ ጀሽው እንዴ ? ” አሉኝ ፤ እንገቴን አቀፍ አድርገውም እየተመለከቱኝ “ እንዲህ ተመልሰን እንደምንገናኝ እር ግጠኛ ነበርሽ ማለት ነው ? ” ቀጠሉ ።

“ እንዴታ ” አልኳቸው ። እንደበታችን እንደገና ተፈታ ።

መብራቱ ጠፍቶ ከተኛንም በኋላ የእኛ ወሬ አላ ለቀም ።

አንዳንዴ ልቤ እንጥልጥል ይላል በየጨዋታችን መካከል ፤ ማሰሪያ ያላገኘ ነገር ይጉላላብኝ ይመስል። መለ ስ ብዬ አስባለሁ ። ለብቻዋ አንድ ክፍል ወ ስጥ የተኛ ችው ትሩፋት ሁኔታ ይመጣብኛል ። በዚህን ዓይነት ስሜት በምዋዥቅበት ወቅት ነው ካንገቴ ቀና በማለት ፣

“ ለመሆኑ ፣ ለመሆኑ --- ” በማለት የጀመርኩት።

“ የሆናይ ሆይና ---- ” እያሉ አስተቃቀፋቸውን ያመቻቻሉ እሳቸው ።

“ የትሩፋትን ስም ያልገለጹልኝ ---

“ እ -----

“ የትሩፋትን ስም -----

“እ ------- የናኒን ------

"እ ---------
'a rose is a rose ----" በማንኛውም ሌላ ስም ብት ጠሪው -- ለዚያውም በቀውጢ ሰዓት ---

"---ቢሆንስ -----""

"ማን ጠይቆ --- ማን አጢኖ ብለሽ ---"

ሰውነቴ እየተመቻቸና እየተዝናና መሄድ ጀመረ ፤ እንቅልፍ እየተጫጫነኝ -- እስኪ ወስደኝ ስመመኜን ባት ለየውም ---ለመሆኑ ናኒ ምን ይሰማት ይሆን ? ያለፈውን ካሁኑ ጋር ስታስተያየው -- ምናልባት ዶክተር ዘውገ ናረው ቢሆን ---

ጥዋት እንደተነሳሁ ወደ ናኒ ክፍል ሄድሁ ። ዶክተር ገድሉም ወዲያው ተከትለውኝ መጡ ። እኔ ድሮ በሷ ያልቀናሁትን ያህል ሁኔታው የተገላቢጦሽ ሆነና የነገር ችን ሂደት በማስታወስ ልቤ ቢከብደኝም የተቻለኝን ያህል ልቋቋመው ሞከርሁ ። በበለጠ ብርቱ ሆናና ተጽቂ ማው ያገኘኋት ግን እሷን ነበር ። ምንም ዓይነት ትካዜ አለየሁባትም ። እንዲያውም እኔና ዶክተር ገድሉን በደስ ታና በፈገግታ እየተመለከተች የፍቅራችንን ጠንካራነት ገለጸች ።

ቁርስ ካደረግን በኋላ ዶክተር ገድሉ የትሩፋትን ትካሻ ያዝ አድርገው " ለአዜብ የእዲሱን የጤና ጣቢያ ሥራ እናሳያት " አሉ -- የሁለቱም ፊት በፈገግታና በኩራት ተሞላ ።

እኔም ስለ አዲሱ የጤና ጣቢያ ሥራ በማንሳት“ -- ከእርስዎ ደብዳቤ ሌላ በዜና ማሰራጫም ስለሥራችሁ ትልቅ እስተዋጽኦ ሰምቻለሁ” አልኩ ።

“ አሃ ! አሃ ! አንቱ ማለትሽን አሁንም አልተውሽም ከአሁን በኋላ መተው ይኖብርብሻል” አሉ ዶክተር ገድሉ ከተገናኘን ጀምሮ አንቱ በላቸው እድሬ አሁን በምን ትዝ እንዳላቸው አላውቅም ። ለማንኛውም ነገሩን በመቀበል አንተ አንተ እያልኩ ለመጫወት ሞከርኩ ። በእርግጥ ለጥቂት ጊዜ ያህል አፌ ላይ ቢያስቸግረኝም ቅሉ እያደር እንደምለምደው ስለገመትኩ ብዙም አልተጨነቅሁ በትም ።

## 28

በሃሳባቸው መሠረት ጤና ጣቢያ ወደ ሚሠራበት ሥፍራ ሄድን ። የሕንፃው ሥራ እየተገባደደ መሆኑንም ተመለከትኩ ። ሠራተኞቹ እኛ በሄድንበት ሰዓትም እየተ ራሩጡ ነበር ። የጠዋቱ ጤዛ እንኳን ለሠራተኛ ለመንገደ ኛም የሚያውክ ነበር ። ሆኖም ይህን ሁሉ ከምንም የቆ

ጠፉት አይመስሉም ። ከሠራተኞቹ ውስጥ ከፊሉ በነፃ አገልግሎት የሚሰጡ የሀገሬው ነዋሪዎች ናቸው ።

ዶክተር ገድሉ ወደ እኔና ትሩፋት እየተመለከቱ "ይህች ጤና ጣቢያ ሕክምና መስጠት ስትጀምር በግን ባር ቀደምትነት የምናደራጃት እኛው ነን" አሉ ።

ሲስተር ትሩፋትም " ለዚህ ምን ጥርጥር አለው " ስትል እኔም ፈገግታ በማሳየት ድጋፌን ገለጽኩ ። ይህንን ጉብኝት እንደጨረስን በቀጥታ ወደ ሐረር ሐኪም ቤት ሄድን ። በቅያሬ የመጣሁበትን ወረቀት ለሚመለከተው ክፍል አሳይቼ ወዲያውኑ ሥራዬን ቀጠልኩ ።

እስከ ዘለዓለሙ ተደብቆ የሚኖር ነገር የለምና ለዶ ክተር ገድሉም የእናታቸውን ሞት አረዳኋቸው ፤ ከዚያ በተረፈ የኑሮአችን ሁኔታ ከመቼውም ይልቅ እያማረ ሄደ ። በአካባቢው እንደ አዲስ ነገሮች የማይመለከተንና የማይቀናብን አልነበረም ። ትካዜ ፣ ጭንቀት ፣ መራራቅ --- ሁሉንም እርግፍ አድርገን በመተው ተግተን ሥራችንን ቀጠልን ። በቤትም ሆነ በውጭ ለሚገጥሙን ችግሮች መፍ ትሔ መፈለጊያችን ውይይት ሆነ ። ከትንሽ እስከ ትልቅ ሥራ ድረስ የሦስታችንም ከልብ የመነጨ ትብብር አልተ ለየንም ። እየሰነበትን በሄድን ቁጥር ስለ ትሩፋት ብቸኛ ነት መተከዛችንን አቆምን ። ራሷ ትሩፋት ለዚህ ሁሉ

ቦታ እንደማትሰጠውና እንደማትጨነቅበት ተረዳን ። ሌላው ቢቀር በሁኔታዋ --- የልቧን ባናውቅም ።

አንድ ወር ያህል በዚህ ዓይነት እንደቆየን ችግር የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን ለመርዳትና ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ሥር ለማድረግ የምርት ዘመቻ እንደሚያስፈልግ በዜና ማሰራጫዎች ተገለጸ ። ለዚሁም ዓላማ ሕዝባውያን ሁሉ ትብብራቸውን እንዲያሳዩና የዘመቻውን ጊዜ በተጠንቀቅ እንዲጠብቁ በዚያው አጋጣሚ ተነገረ ።

ይህንን የሰማነው የአዲሱ ጤና ጣቢያ ሥራ ሊያልቅ አካባቢ ነው ። እኛም በዚሁ በአዲሱ ጤና ጣቢያ የሕክምና ሥራችንን ለመጀመር እየተሰናዳን ቢሆንም እንኳ በምርት ዘመቻው መሳተፍ ግዴታችን ሆነ ።

ዶክተር ገድሉ ይህንኑ አዲስ ዜና በሰሙበት ወቅት “እንግዲህ የጤና ጣቢያውን የሕክምና ሥራ ለማስጀመርና ለማደራጀት አንዳችን ብቻ በቂ ነን ። በነገሩ ላይ እንወያይበትና ከመሀላችን ሁለት ሰው ወደ ምርቱ ዘመቻ ለመሄድ ቢሰናዳ መልካም ነው” በማለት ጉዳዩን አነሱት

ሲስተር ትሩፋት ፈጠን ባለ አነጋገር “ ለዚህ ምንም ውይይት አያስፈልገው ። እኔ እንደሆንኩ በፍጹም አልቀርም ። በጦርነቱ ወቅት ከእርስዎ ጋር ዘምቻለሁና አሁን ደግሞ ከውዷ ጓደኛዬ ከአዜብ ጋር ብዘምት ደስ ይለ

ኛል ። ደግሞም እርስዎ ለአዲሱ ጤና ጣቢያ በጣም ስለ ሚያስፈልጉ እዚሁ ቀርተው ማንቀሳቀስ አለብዎት ። እኔና አዜብ ግን ወደ ምርቱ ዘመቻ ለመጓዝ መዘጋጀት አለብን ” አለች ።

እኔም እንደ ከተነፈስኩ በኋላ “ይሁና --” የሚል ቃል ስናገር ተሰማኝ ፤ በመቀጠልም “አይ የጉዞው ጣጣ ” አልኩኝ ።

ዶክተር ገድሉ ንግግሬን በመቀማት “ምን ያህል ተጓዝንና–እኛ ጉዞውን የጀመር ነው ከመሀል ነው ። ከመጀ መሪያ ጀምሮ ያለመሰልቸት የሚጓዙት እንኳ “ጣጣ ” አላሉትም ” አሉኝ ።

“እሱስ ልክ ነዎት ፤ ብቻ የሰው ሁሉ አመለካከት አንድ ዓይነት ባለመሆኑ ቶሎ የሚሰለችና በግማሽ መን ገድ የሚቀር ሊኖር ይችላል ። በአንፃሩም ደግሞ በቆራ ጥነት እስከ መጨረሻው የሚጓዝም ይኖራል” ካልኩ በኋላ ግማሽ ቀልድ በተቀላቀለበት አነጋገር “የሆነስ ሆነና የጉዞው መድረሻ ወዴት ነው ? ” ብዬ ጠየቅሁ ።

ዶክተር ገድሉም በኩራት መንፈስ ፈገግ እያ ሉ ፤

“እዚያው ኮሙኒዝም ነዋ ! ” አሉኝ ።

# ማሞ ቢጩ

ከአውግቸው ተረፈ

ማሞ አዳራሽ አካባቢ የታወቀ ልብስ ነጋዴ ነበር ፤ መቸርቸሪያ ሳይሆን የጅምላ መሸጫ ሱቅ ያለው የሚመስል ፣ በአለባበሱ የሚሽቀረቀር ፣ ጫማውን እንኳ በቀን ሁለት ጊዜ የሚያስጠርግ ፤ አካባቢው "አባዝራው ማሞ" የሚል ቅፅል ያወጣለት ።

ማታ ከመርካቶ እስከ ውቤ በረሃ ገንዘቡን ሲዘራ ማምሸት ፣ ባንኮኒ ተደግፎ ውስኪ እንደ ውሃ ማስቀዳት ፣ መጠጣት ፣ መጋበዝ ሌላው የታወቀበት ተግባሩ ሲሆን እማይገባበት ቡና ቤት ፣ እማያውቃት ሴት አልነበረችም ። "መኪና ለምን አትገዛም?" ሲሉት እንኳ "መኪና ምን ያደርግልኛል ፤ እቤት አልገባ ፣ እኔ የማድረው እመሸብኝ" ነበር መልሱ ።

ደስ ባለው ቀን ሁሉቱን የሱቅ ሠራተኞቹን እያዞረ ያጠጣቸዋል ። ደሞዝ ግን ከሃያአምስት ብር በላይ አይከፍላቸውም ። ማታ ማታ እየዞረ የሚበትነው ገንዘብ እስካገኙ ድረስ ስንት ዕቃ ተሸጠ ምን ተገዛ እያለ ስለማይቆጣጠራቸው እነሱም በፈንታቸው ከማሞ ሱቅ የሚዘርፉትን ገንዘብ ውቤ በረሃ ባይደርሱም እንኳ ማታ ማታ መርካቶ ለመርካቶ ሲበትኑ ያመሻሉ ።

ማሞ ሚስት አልነበረውም ። መሀል አራዳ ፒያሳ አንድ እታወቀ ቡና ቤት ፍቅር እስኪይዘው ድረስ ሁልጊዜ ለማሞ ሥርግና ምላሽ ነበር ። ያራዳይቱ ቆንጆ ግን በፍቅር ገመድ ሸብባ ያዘችው ፤ እንዳሰኛትም ትመራው ጀመር ፤ ከዚህ ጊዜ አንስቶ መጠጣቱን ባያቋርጥም ብዙ ቡና ቤት ማዳረሱን ተወ ። ሆኖም እያደር መጠጥ አዘውታሪነቱም እያደገ መጣ ፥ ውስኪ ከበር ምላሽ ቅጅ ከማለት አልፎ "ኑ ወዳጄን እዩልኝ" እያለ ለሚያመጣቸው ጓደኞቹ ጠርሙስ ውስኪ ማስከፈት አዘወተረ ። መስከር ፥ መታመም መጣ ። ሱቅ ሄዶ ገንዘብ መረከቡን ተወና "አራዳ ድረስ አምጡልኝ" እያለ ሱቁን ሙሉ ለሙሉ ለሠራተኞቹ ተወ ።

ሠራተኞቹ እዩኝ አላዩኝ እያሉ መስረቃቸው ቀረና "እኛን በሃያአምስት ብር ይገዛናል እሱ ለማንም ውስኪ ይረጨዋል" እያሉ ሽያጩ ባነሰ ቀን ሸሚዝና ሹራብ ከሱቅ በንቃሽ መወርወር ጀመሩ ። "ጠንራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል" ባለቤትና ሠራተኞች ሱቁን መዘበሩት ፤ ማሞ ባዶ ሱቅ ታቅፎ ቀረ ።

የሱቁን ቁልፍ ሸጠ ። ኮንትሮባንድ እነግዳለሁ ብሎ ድሬዳዋ ወረደ ። እዚያም አልቀናውም ፥ በኮንትሮባንድ ያጋበሰው ዕቃ ከመቀጫ ጋር ተወረሰ ፤ የመጨረሻ መፈናፈኛውን አጣ ።

አዲስ አበባ ተመልሶ ደላላ ሆንኩ ብሎ ሲዞር ቢውል እሳት የላሱ ደላሎች መሀል "የባላገር መጤ" ሆኖ ለጥ ብስ አደረስኩት ያለው ቤትና ርስት ሽያጭ ሁሉ እየተፋ ረሰ ሳይሳካለት ቀረ ። በየቀኑ ይበትነው የነበረው ብር ቀረና ዛሬ በሳንቲም እንኳ የሚቆጠር ገንዘብ አረረ በት ። እነዚያን ያሽበርቅባቸው የነበሩ ልብሶቹን አንድ ባንድ መሸጥ ጀመረ ። ቀስ በቀስም የለበሰው ልብስ ብቻ ሲቀረው ሽጦ ጨረሰ ። ከሸሚዝ አቅም እንኳ መቀየሪያ አጥቶ ፣ ሲቆሸሽበት ማታ ማታ ጭፍጭፍ ማድ ረግ ነበረበት ።

በየሱቁ እየተቀጠረ መሥራት ጀምሮ ነበር ። ነገር ግን ማዘዝ የለመደ ጌታ ጎንበስ ብሎ ጫማ ለመለካት ሲኮራ ሲያውት ብዙም ሳይቆይ ያስወጡታል ። እያደ ርም እስከናካቴው የሚቀጥረው አጣ ። ኑሮ አቃተተው 1 ቀወሰና አማኑኤል ሆስፒታል ገባ ።

ከአማኑኤል ግማሽ ቀውስ ግማሽ ጤነኛ ሆኖ ሲወጣ የሚያውቃቸው ሰዎች መንገድ ላይ ሲያዩት እያዘኑ ለሲ ጋራና ለሻት እያሉ አንዷ ብርም ሁለት ብርም ሲሰጡት ለትንሽ ጊዜ እንደምንም ቆየና 1960 ዓ.ም. ሲብት ጨርሶ ወደቀ ። ሆኖም ተስፋ አልቆረጠም ። ቢያንስ ቢያንስ ተለ ጣፊ የዥራብ ሱቅ አዳራሽ አካባቢ እገዛለሁ ፣ ባጣ ባጣ ለሆዱ ያህል አላጣም በማለት መስከረም መጨረሻ ላይ ጨርቅ ተራ ድለላ ጀመረ ። ወግ ወጉማ ያገኘውን ያህል ሃምሳ ሳንቲም ሆነ ብር እቁብ ገብቶ ለማጠራ ቀም ነበር ።

የዚያን እለት ጠዋት መሐመድ ሳላ ሻይ ቤት ቁርሱን በሦስት ዳቦ ፈታ በልቶ ሦስት ሰዓት አካባቢ በኪኪያን ሱቅ መደዳ ያለውን መንገድ ይዞ ሄደና በመስተዋት ተራ ብቅ አለ ። መንገድ ዳር በር በሩን አንቀው የሚጠብቁት ጨርቅ ነጋዴዎች "ጀ" ምን ይዘሻል ? እምይ ያራዳ ልጅ ፣ ሰዓትም ይዘሽ እንደሆን አምጪው እንገዛሻለን ። መሀል ብትገቢም ለናትሽ ልጅ አትሽጭው እያሉ ያለባበሱን ንጹሕነት ፊቱ ላይ ከሚታየው የመቸገር መልክ ጋር አገናዝበው ሳይሸጥ አይቀርም የሚል ግምት በመውሰድ ከበብ ከበብ አደረጉት ፤ ለመልስ እኳን ጊዜ አልሰጡትም ። መልስ ያገኙ ያህል "ኮቱን ነው የሚሸጠው ፣ በቃ ! እኔ ቀድሜአለሁ" እያሉ አዋከቡት ፣ እንደ ቀልድ እያስመሰሉም አንዱ የማዋን እጅ ሲይዝ ሌላው ኮቱን ማስወለቅ ሲጀምር "ኧረ አልሸጠውም እኔ ራሴ ለመንገድ ነው የመጣሁ" ቢል ማንም አልሰማውም ።"እኔስ መሀል ገብታችሁ ምን እንደምታገኙ ነው ፣ የማይገባኝ ፤ እኛም የምንገዛችሁ በገንዘብ ፤ እነሱም የሚገዟችሁ በገንዘብ ፣ እኛን እምቢ እያላችሁ ውስጥ ስትደርሱ ትሸጣላችሁ" በማለት ፣ "ማውለቁን አፍረህ እንደሆን ና ወደ በረንዳው እንሂድ" እያለ ታደሰ የሚባለው ደላላ ማሞን በኮቱ አንቆ አጠገቡ ወደሚታየው በረንዳ እየጎተተ ወስዶ ለማውለቅ ይተናነቀው ጀመር ።

ማሞ የከበቡትን ሰዎች ብዙ መሆን አዩና አልሸ ጥም ቢል በግድ እንደሚነጥቁት በመጠራጠር በዋጋ አስ ፈራርቶ ለማፋረስ በማሰብ "እምሳ ብር" አላቸው ። ሆኖም ታደሰን በቀላሉ የሚላቀቀው አልሆነም ። ኮቱን በመመለ ካከት "ትቀልዳለህ መሰለኝ ፣ ያረጀ ፣ ብዙ የለፋ ኮት ነው ፤ እቅጩን ተናገር እባክህ -- ደግሞ ሱፍ ትምሰል እንጂ ቴትሮን መሆኗ ቁልጭ ብሎ ይታያል ። መቸስ ብዙም ባንግር ትንሽ ምካከረናል ። "ጨርቅ ተራ ከማትሪክ የወደቁ ተማሪዎች መሰብሰቢያ ነው" ሲሉ አልሰማህ ም ? እና ምንም ያራዳ ልጅ ብትሆን እምታትቼ እሄዳለሁ ማለትህን ትተህ አስር ብር ይበቃሀል" እያለ አስር ብር መዞ እንካ አለው ። ማሞ እምቢ አለ ። በዚህን ጊዜ ደላሎች እሚያዩ እየመሰሉ አንዱ ላንዱ ሲያቀብል ማሞ ሲከተል "ካንተ አልተቀበልንም ዞር በል" እያሉ ሲገፈት ፋት መጨረሻ ላይ ከታደሰ ጋር ተፋጠጠ ።

"እምጣ ኮቴን! እንኳን በአሥር ብር በሃምሣ ብር አልሸጥልህም "አለ ማሞ ።

"ትቀበላለህ ተቀበል ፤ አለበለዚያ ከነአስር ብሩም ታጠዋለህ ። ሲያዩህ አራዳ ትመስላለህ ፣ ግን እልም ያልክ ጥሬ ነህ ፤ አጉል አራዳ ልሁን ባይ !" ብሎ እሁ ንም አስር ብሩን ዘረጋለት ። ማሞም አሁን በባዶው ምን አጫጨኸኝ ? ኮቱ እንደሆን በጄ የለም ። ከነጭራሹስ አላየሁም ቢለኝ በየትኛው ምሥክር ረትቼ ልቀበለው ነው ? ብሎ ብሩን ተቀበለና እዚያው ውራጅ ተራ

ገብቶ ሲመራርጥ ከቆየ በኋላ አሮጌ ጃኬት በስምንት ብር ገዝቶ ለበሰ ።

የተረፈችውንም ሁለት ብር ይዞ ወደ ጠጅ ቤት ሄደ ። ለማታው መኝታ አምሳ ሣንቲም እንኳን አላስቀረም ።

ከዚያን እለት ጀምሮ የባሰ ሰካራም እየሆነ ሄደ ። አን ዳንዴማ ማን አሜሪካን ግቢ ወስዶ እንዳስተኛው እንኳ ትዝ አይለውም ። ከሁለት ብር ወደ አንድ ብር አልጋ ከዚያ ወደ አምሳ ሳንቲም ሲወርድ በመጠጥም ከውስኪ ወደ ቢራ ከዚያ ወደ ጠጅ አሽቆልቁሏል ።

ማዎ ጨርቅ ተራ እየሄደ መዋል ከጀመረ ሰነባብ ቷል ። ሆኖም ሌሎች ደላሎችና ነጋዴዎች በጉልበትም ፣ በብልሃትም ፣ በማጭበርበርም እየተጠቀሙ ሲገበያዩ ከማየት በስተቀር እሱ ሻጭና ገዥውን እንኳ ለይቶ ማወቅ አልቻለም ። ልብስ የወንድና የሴት ፣ ያዋቂና የልጅ ፣ አሮጌና አዲስ ፣ መሀረብና ካልሲ ፣ ሰዓት ፣ ሬዲዮ ፣ ወርቅ ፣ ጫማ ፣ ባርኔጣ ሳይቀር ይሸጣል ፣ ይገዛል ፤ ማዎ ግን ውራጅ እንጀራ ፣ ውራጅ ነፍስ ሳይቀር ሲገዙ ፣ ሲሸጡ ከሚውሉ ጮሌዎች መሀል ፈዞ ከመዋል በስተ ቀር መሀረብ እንኳ ገዝቶ መሸጥ አልቻለም ።

የታደሰና የጓደኞቹ ስድብ ሲያስለቸው መሳደብ ይጀምራል ። "አራዳው" እያሉ ያበሽቁት የነበረው አንቧ ቸው ፣ አግኝቶ ፣ ያጣ ፣ እንዲያውም አማኑኤል ገብቶ የወጣ

መሆኑን ሲሰሙ " ዕብዱ " "ቢጨው" እያሉ መቀለጃ አድርገውታል ። ማሞም ሌላ መሄጃ ስላጣ ጠዋት ማታ ከነሱ ጉያ የማይወጣ ሆነ ። ደስ ባላቸው ቀን " ለማሞ እናዋጣለት "እያሉ የማታ ማታ የሚሰጡትን የመዋጮ ሳንቲም ተስፋ አድርጎ ከጨርቅ ተራ ሀኪያ ይንቀለኝ አለ ።

ስራውና ጫማው ጃኬቱ አለቁበት ። ማሞ ስሙኒም ቢያገኝ ሽልንግ ጠጅ ከመጠጣት በስተቀር ሌላ ምንም እማይሠራ ሆነ ። ሳንቲም ካጣ አንድ ጥግ ቦታ ይፈልግና ፀሐይ እያንቃቃው እየተገላበጠ ይጋደማል ። አንዳንድ ጊዜ ከጠጅ የተረፈው ቀን አሜሪካን ግቢ ይሄዳል እንጂ ማደሪያው በረንዳ ሆኗል ። ፀጉሩን ስለማያበጥረው ተን ጨፍር የውነትዮ ዕብድ አስመስሎታል ።

እነ ታደሰ ገበያ በሌለበት ሰዓት እየተሰበሰቡ ማሞን በስድብና በጥፊ እየመቱ መጫወት ደስ ይላቸዋል ። "ያዋ ጣንልህ እንድትሰክር ነው ። ሰክረህ ካላጫወትከን ሁለ ተኛ ላንተ ዱዲ እሚያጭርህ የለም" ይሉታል ። ሞቅ ብሎት በመጣ ቀን ይዘፍናል ። ሊስትሮዎች ፣ አዟሪዎች ጭምር ከበው ያዳምጡታል ። እየቆነጠጡ ፣ እየጉነ ተሉ ፣ ከኋላው በኩል በጥፊ እየመቱ ጢሙን እየጐተቱ ።

ዱላውንም ስድቡንም የጀመረው ታደሰ ነው ። አርጌ ጨርቅ ተራ የተዋጣለት ዱለኛ ነው ። ከማንም

ጋር ሲቀጣቀጥ ይውላል ። ታዲያ የላይኞቹ ጥርሶቹ ረግፈው በብርና በወርቅ ጥርስ ተተክተዋል ። ታደሰ ዕቃ ሲገዛ ዋጋ ሰብሮ ነው ። ሌላው ነጋዴ ሃያ ብር የሚገዛውን ደህና ዋጋ ሰጠ በተባለ ቀን አስር ይገዘዋል ። ችግሮት ሲሸጥ ይምጣ ወይም ቤት ሰርስሮ ፣ ቁም ሣጥን ሰብሮ ይምጣ ለታደሰ ያው ነው ። ሕሊናውን ደስ የማ ይለው ገበያ ሲያጣ ብቻ ነው ። ሌባ እንኳ ከኪስ አው ልቆ ሲሮጥ ተከትሎ ሂዶ ምን ያህል ገንዘብ እንደሰረቀ አይቶ ፣ ትንሽ ካልሆነ በስተቀር አካፍለኝ ብሎ ድርቅ ይላል ። ማታ ማታ ማጅራት ይመታል እየተባለ በርጩቅ ተራ ይታማል ።

ማሞ የታደሰን ስድብና ጥፊ በሆዱ ችሎ ማታ የሚ ሰጠውን አሥር ሳንቲምና ስሙኒ በተስፋ ይጠብቃል ። ታደሰም ማሞን ሲያላግጥበት ይዋል እንጂ ሳንቲም ሳይሰ ጠው አይሄድም ። እንዲያውም እንደ ልማድ አድርጐ "ለማሞ እናዋጣለት እንጂ ዛሬ ምንም አልቀመሰ" ካለ ግማሹ ማሞ ሰክሮ እንዲያጫውተው ወይም ታደሰ እንዳይቆጣው ያዋጣለታል ። አንዳንዴም ደስ ያለው ቀን "አይዞህ አንድ ቀን በርከት ያለ ገንዘብ አዋጥተንልህ ተለጣፊ ሱቅ ይኖርህ ይሆናል ! ማን ያውቃል ?" እያለ ያበረታታዋል ።

ታደሰ ሊስትሮዎችን ጠርቶ "ማሞ ቢጨን ጭራ አስበቅሉት ፤ አሁን ጠጥቶ መቷል" ይላቸዋል ። ታዲያ

ሊስትሮዎች ክብብ ያደርጉና አንዱ ፀጉሩን ይነጩዋል ። ዞር ሲል ሌላው በጥፊ ይመቱዋል ። ባንደኛው ትክሻ አሳልፎ ስለሆነ የሚመታው የትኛው እንደሆን ለይቶ ማወቅ ያስቸግረዋል ። "እኔ አይደለሁም ማሞ" ይሉታል ። "እስቲ እንግዲህ ይህን ምን ትሉታላችሁ? እታዩትም እንደኔ ፀጉሬን ሲነጩኝ" ይላል ማሞ ። አንዱ ልጅ ከኋላው ይዞርና ኮቱን ገለጥ አድርጎ የሲጋራ ቁራጭ ጀርባው ላይ ይጥልበታል ። እሳቱ ሲፈጀው ይዘላል ። ልጆች ይስቁበታል ። አንዱን ልጅ ማባረር ይጀምራል ። እየተሽሎከለከ ያመልጠዋል ። ማሞ ከየመንገደኛው ጋር እየተጋጨ ሲሮጥ ካላሰበው ሰው ጋር ይጣላል ። ብዙ ጊዜ መኪና ሊገጨው ሲል ይተርፋል ። ከሩጫ ሲመለስ ጠጠር ይወረውሩበታል ። የደፈሩት ጢሙን ይዘው ይጎትቱታል ። ሊመታቸው ሲል ሮጠው ሄደው ታደሰን የሙጥኝ ይሉታል ። ማሞ ከታደሰ ጋር ብዙ ቀን ተደባድቧል ፤ ጩርቅ ተራ እንደጀመረ ሰሞን ። በኋላ ግን ገንዘብ የሚሰጠው እሱ መሆኑን አውቆ መጣላቱን ትቷል ።

ብዙ ጊዜ ግን ጉትቻው ፣ ቁንጥጫው ፣ ሩጫው ፣ ጥፊው ሲያደክመው ወጣ ይልና ፀሐይ ላይ ይጋደማል ፤ ሰውነቱን እያከከ ። "ማሞ አትክክ" ይለዋል አንዱ እንደአጋጣሚ ያየው ፣ "እከካም ሊስትሮ ሁሉ" ይላል ማሞ "ጫማዬን ለመጥረግ እንኳን አትበቁ የነበር ዛሬ ትስድቡኛላችሁ"

"ማሞ ዓይንህን አታፍጥ ትናንት እኔ ባዋጣሁልህ ሣን ቲም ነው ስክረህ የተደሰትክ ። ና ጠጅ ልግዛልህ" ብዙ ጊዜ ቢያሾፉበትም አንዳንዶ የምራቸውን ስለሚገዙለት ሲና ገሩት የውነታቸውንና የውሸታቸውን ለይቶ ስለማያውቅ እንትርክ ውስጥ ያስገቡታል ፣ እና " እሺ ግዛልኝ " ሲል ተናጋሪው "ደም ጠጣ" ይለዋል ወይም "ማሞ ና ዳቦ ልግዛልህ" "እሺ ግዛልኝ" "የማይጨውን ቦምብ ብላ" ወይም "ማሞ እግርህ ምን ሆኖ ነው ያበጠ? " "ጫማዬ አልቆብኝ በባዶ እግሬ ስሄድ ጠርሙስ ወጋ ቶኝ" ሲል "አይደለም ቁምጥና ሊጀምርህ ነው ።" አን ዳንዶ ሁኔታው ማሞንም ያስገርመዋል ፤ "እስቲ ይኸን ምን ትሉታላችሁ? ሰው ከሰው ልጅነት ወደ ውሻነት ይመ ለሳል? ትናንት ቅማል ላንሳልህ እያለ ፀጉሬን ሲነጨኝ ፣ ጀርባዬን ሲቆነጥጠኝ ዋለ ፣ ዛሬ ደግሞ ቁምጥና ያዘህ ይለኛል ፤ ይሄን ምን ትሉታላችሁ?" እያለ ያጉመተ ምታል ።

ማሞ ቀድሞ የመታውን ትንሽ ከቆየ አሁን ፊቴ አገ ኘሁት ልምታው አይልም ። አሁን የሚመታውና የሚ ሰድበውን ነው የሚጠላ ። ስለዚህ ልጆች መተውት ይሮጡና ከአምስት ደቂቃ በኋላ አጠገቡ መጥተው ይቆ ማሉ ።

" ማሞ እንካ እንጀራ "
" ወዲህ በል "
" አፈር ጠኔ ብላ "
አልፎ አልፎ "ማሞኮ ሰው በዓይኑ የማይሞላ

ትልቅ ሰው ነበር እሉ'' ይላል ታደሰ የማሞን ጢም እየ ጉታተተ ''ሱፍ ካለበሰ በስተቀር ነጭ በነጭ የሀበሻ ልብስ ለብሶ ፣ ነጭ ጭራ ይዞ ፣ ነጭ ባርኔጣ አድርጎ ውስኪ እንደውኃ ለማንም ሰው ያጠጣ የነበር የሞጃ ዘር ፣ ዛሬ እንዲህ ማንም ሊስትሮ ጢሙን እየጎተተ ሊጫወት በት'' ብሎ በይበልጥ ጢሙን ጎተት ሲያደርገው ''ልብ አድርጉ ምስክር በሌለበት ጢሜን ሲነጩኝ ፣ ቁመት ህን አስረዝሙህ የመጣህ ጢሜን ልትነጩኝ ነው ? እስቲ እንግዲህ ይሄን ምን ትሉታላችሁ ?'' በማለት ይጮሃል ማሞ ። ''ሌላ ምን እንለዋለን ? ጢም መንጩት ነዋ'' ይመልሱለታል ።

በጋውን እንዲህ ባጀና ሰኔ መጨረሻ ላይ ማሞ ፊቱ አባበጠ ። እግሮቹ አባበጡ ። ዓይኖቹ ቀሉ ። ሰውነቱ አመድ ወረሰው ። ቁርሱ ጠጅ ሆነ።ምሣና ራቱም ጠጅ ። ጠዋት ተነስቶ ጠጅ ካልቀመሰ እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ ። መናገርም አይችልም ።

አንዱ ጨርቅ ነጋዴ ለማሞ ኮትና ሱሪ ሸሚዝ ጭምር ሰጠው ። ማሞ ሸጠና ጠጅ ጠጣበት ። የጨርቅ ተራ ነጋዴ በሙሉ '' ቤተስኪያን የገባች ውሻ'' አደ ረገው ። ''ይህ ሽጦ በላ ፣ ለራሱ ሰውነት የማያዝን ርኩስ'' እያለ አዋከበው ። ሊስትሮዎች ሳይቀሩ የብረቱካን ልጣጭ በላስቲክ በማስፈንጠር እየመቱት ''ማሞ በጩ ፣ ተንበጫበጨ ፣ ተንገጫገጨ'' በማለት የሚገባበት አሳ

ጡት ። "ልብ አድርጉልኝ ምስክር በሌለበት ዓይኔን ሲያጠፉኝ" እያለ ዓይኑን ከመሸፈን ሌላ የሚያደርገው አልነበረም ።

የክረምቱ ብርድ እስከ አጥንቱ እየገባ ማሞን ያን ቀጠቅጠዋል ። ሁለት እጆቹን ሱሪው ኪስ ውስጥ ይከ ትና ሽምቅቅ ብሎ ቆሞ ወባ እንደያዘው ሰው ይንዘፈ ዘፋል ። ማንም አላዘነለትም ። ሽጦ በመብላቱ ከመናደድ በቀር ።

ማሞ ስለት ነገር በጣም ይፈራል ፤ ጩቤ ፣ ምላጭ፣ ቦንዳ ሳይቀር ስለሚፈራ ይህን ያወቁ ልጆች ጢሙን ይዘው ይጎትቱና ሊመታቸው ሲል ከኪሳቸው ምላጭ ወይ ቦንዳ አውጥተው "በልስቲ ወንድ ተጠጋኝ ፤ አንቻትህን እዘረግፍሀለሁ" ሲሉት "ምን እየሆንክ ነው አንተ ጩቤ ይዘህ የምትዞር ? አብደሃል ? ይሄን ምን ትሉታላችሁ ? ልብ አድርጉልኝ ብቻ ምስክር በሌለበት ሊያርደኝ" ይልና የመጣበትን ይቀበላል ።

"ኑ ማሞን ለሠፈሩ አድባር እንረደው ፣ እሱ ከመጣ ወዲህ የጩርቅ ተራን አድባር አስቀይሞ ገበያውን አዘግ ቶብናል ፤ ኑ ላድባሯ እንረደው" አለ አንድ ቀን ታደሰ ምላጭ ይዞ ወደ ማሞ እየመጣ ። ማሞም "ልብ አድር ጉልኝ ፣ ቁመቱን አስረዝሞ ሊያርደኝ ሲመጣ" እያለ ጨኸቱን አሰማ፤ ድንጋይ ለማንሳት እያጎነበሰ ።

"ጠብሰን ነው የምንበላው ወይስ ጥሬውን ?" ብሎ ጠየቀ እንዱ የታደሰ ጓደኛ ፤

"ጥሬ ሥጋውን ነው የምንበላው" "በማጅራቱ ነው ባን ገቱ የምናርደው ?" አለ ሌላው ።

ጥያቄውና መልሱ አስገርሟቸው ያዳምጡ የነ በሩ አንድ በመንገድ ያልፉ የነበሩ መነኩሴ ራሳቸ ውን እየነቀነቁ ሲሄዱ ታደስ አያቸውና ድምጹን የሴት አስመስሎ "ቄስ መሐመድ ?" ብሎ ጠራቸው ። ጥሪው አስደንግጦአቸው ይሁን አስገርሟቸው ዞር ሲሉ ታደስ ማሞን በጣቱ እየጠቆመ "እሱ ነው የጠራዎት አባቴ" አላቸው ። ሊስትሮዎች ሳይቀሩ « ማሞ ነው ፤ ማሞ ነው » እያሉ ተንጫጩ ። መንገዳቸውን ሲቀጥሉ "ቄስ መሐመድ" "ሙምሬ አብደላ" "መምሩ የሰው ሚስት አይምሩ" እያሉ የጩርቅ ተራ ነጋዴዎችና ሊስትሮዎች ቢንጫጩባቸው ፤ መነኩሴው "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዴት ያለ እተረገመ ቦታ አደረስከኝ ፈጣሪዩ" ብለው በማማተብ "በስመ አብ -- እኔ ቄስ መሐመድ !?" እያሉ ቆሙ ።

"አንቱ የውሸት ቄስ ፤ ዳባዎ ውስጥ የደበቁትን የተሰረቀ ልብስ ያውጡት ። አንቱ የተሰጣ ልብስ ሌባ" ሲል ቀጠለ ታደሰ በሴት ድምጽ በግልጽ እየታየ ። ቄሱ እንደ ጅብራ ተገትረዋል፤የሚያደርጉት የጠፋቸው ይመ ስላል ።

"ማሞ ! ግደል ፣ ግደል አለኝ በል ፤ አንተስ ሙት ፣ ሙት አላለህም ?"እያለ ቀረበው እንደገና ማሞን ፣ ታደሰ።

"ኧረግ የፈጣሪ ያለህ ። ምነው ይህን ሳታሰማኝ በገደልከኝ ። እኔ ሌባ ነኝ፤ እኔ የውሸት ቄስ ነኝ?" መሀል መንገድ ላይ ቆመው እብድ፣ ስከር ብለዋል ቄሱ "እንጀራ አይውጣላችሁ – አይውጣላችሁ --" እያሉ መራገም ጀምረዋል ። አንድ ሌላ መንገደኛ ባይገፋፋቸው ኑሮ እዚያው ቆመው እሚያድሩ ይመስሉ ነበር ።

ወዲያው ዝናቡ መጥቶ ሰውን በታተነው ። ታደሰ ማሞን ሻይ ቤት ይዞት ሄደና ሻይና ዳቦ ገዛለት ። ማሞ ምሳ በላሁ የሚል ዳቦ ሲበላ ነው ። "አንድ ዳቦና አንድ ብርጭቆ ሻይ ግጥም አድርጌ ምሳየን በላሁ" ይላል ።

ዝናቡ ሲያባራ ታደሰና ማሞ እጅ ለእጅ ተያይዘው ጨርቅ ተራ ሲቆሙ ነጋዴዎችና ሊስትሮዎች ከበቧቸው ። "በል ማሞ የሻይ ቤቱን ንግግራችንን አልረሳሁትም" አለና ወረቀት ላይ አንደኛ ተራ ቁጥር ሰሙን መዝግቦ "እኔ በበኩሌ ይኸውልህ አሥር ብር" ብሎ ለማሞ ሰጠው ። ከዚያን በኋላ ታደሰ ከማሞ ጋር እየዞረ ከነጋዴዎች አሰር አስር ብር መቀበል ጀመረ ። ታደሰ ለተነኮል እንጂ ለሙነት እንደማይሰበስብ ስላወቁ የተጠየቁት ሁሉ ዐይናቸውን ሳያሹ ማዋጣት ቀጠሉ ። ማሞም እንደታዘዘው ታደሰ እያንዳንዱን አስር ብር ተቀብሎ በጁ ወደታች ሲያመለክተው አስር ብር የሰጠውን ነጋዴ እግር ጎንበስ ብሎ ይስማል ። ማሞን ከኋላ ከኋላ እየተከተሉት ልጆች ለነደ ልማዳቸው ፀጉሩን ይነጩታል፣ይጎትቱታል ፣ ያንጓጥ

ጡታል ፤ ሆኖም በደስታ ስለተዋጠ ምንም ምንም የሚሰማው አይመስልም ። አንዳንዴ ብቻ እጁን ሲይዙትና ልብሱን ይዘው ሲጐትቱት ዞር ይልና "ምን እየሆንክ ነው አንተ ? አብደሃል ? እስቲ እንግዲህ ይሄን ምን ትሉታላችሁ ?" ሲል ከመስማቱ በስተቀር ።

"ለገሱን አይደለም እንዴ ?" አለ ታደሰ እጁ ላይ ያለውን ብር እየተመለከተ ። "እንግዲህ አሁን ለመጨረሻ ጊዜ አንድ ሰው እንጠይቅና ያሰብነው ልክ ደረሰ ማለት ነው ፤ ይብቃሃል"

"ንስኪ ለሻይ መጠጫ ስጠን ማሞ" አሉት ከኋላው ያጀቡት ልጆች ። ማሞ ወደዚህ ሰፈር የመጣበት ትንሽ ገንዘብ አጠራቅሞ ቢያንስ ተለጣፊ የሹራብ ሱቅ ለመግዛት የነበረው ምኞት ተቀሰቅሶበት ሲያሰላስል ። የዚህን ጊዜ ታደሰ አስር ብር መዘዘና ሲሰጣቸው እጁን ሲዘረጋ ማሞ የታደሰን እጅ ቶሎ አፈፍ አድርጎ "ምን እየሆንክ ነው በል ለኔ የተዋጣውን ብር ለማንም ዱርዬ እምትሰጥብኝ? አብደሃል እንዴ ? እስቲ እንግዲህ ይሄን ምን ትሉታላችሁ ? እንዲያውም አምጣው ልቁጠረው ?" እያለ አለቅም አለው ። ሆኖም "በቃ ከተቆጣህ ይቅር ። አሁን ዘጠና ብር ደርሶልሃል ፤ ካንድ ሰው አስር ብር ካገኘህ መቶ ብር ሆነልህ ማለት ነው ። ይበቃሃል" አለና ታደሰ ወዲያው አረጋጋው ።

እንደተለመደው ታደሰ የምሩን አልነበረም ገንዘቡን የሰበሰበው ። ማሞን ለትንሽ ጊዜ ገለል ካስደረገ

በኋላ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለየባለቤቶቹ መለሰላቸው ። ማሞ ተበሳጨ ፣ ተሳደበ ፣ ተራገመ--- ሁኔታው ለሱ አዲስ አልነበረም ።

በበነጋታው ታደሰ የራሱን አሮጌ ኮትና ሱሪ ሸሚዝ ጭምር ለማሞ ሰጠው ። "ልባድርግ ማሞ ፣ ጠ፺መሪያ የለበስከውን ቡትቶ እቃጥላለሁ ። ቀጥሎ ደግሞ ይህን የምሰጥህን ልብስ ብትሸጥ እያጋጩሁ ፣ እያንገጫገጭኩ ፖሊስ ጣቢያ ወስጄ እንዳሳስርህ ወይም እዚህ ጨርቅ ተራ በአምስት ሣንቲም ገመድ ላንጠለጥልህ ወደህ ትፈርማለህ ። አለበለዚያ አልሰጥህም ።"

ማሞ በታደሰ ሃሳብ ተስማማ ። አሮጌ ልብሱ ተቃጠለ ። ታደሰ የሰጠውን ለበሰ ። ለጠጅም ተዋጣለትና ሞቅ ብሎት መጣ ። "አዲሱ ልብስ ተስማምቶሃል!" እያሉ ልጆች ሲጎትቱት ፣ ሲገፈትሩት ዋሉ ። ማሞ ግንብ ተገን አድርጎ ካልቆመ እንዳ ከዚህ ሲገፋው ሌላው እንዳትወድቅብኝ ብሎ መልሶ ሲገፈትረው ይውላል ።

በነጋታው ማሞ ጨርቅ ተራ ሳይደርስ ዋለ ። በተ ነገወዳያው ፣ ሌሊት ሌሊት የሚለብሰውን ድሪቶ አን ገቱ ላይ ጠምጥሞና ፣ አንድ ሱሪ ታጥቆ መጣ ። ፊቱን ሸፍ ነው ሲመቱት ፣ እንገቱን በድሪቶው አንቀው ሲጎትቱት ዋሉ ። ታደሰም "በውላችን መሠረት እያጋጩሁ እያን ገጫገጭኩ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እወስድሃለሁ ፤ ያውም

በራስህ ድሪቶ አንቄ'' ብሎ ወደ ማሞ ሲጠጋ ማሞ ለመሸሽ እየሞከረ ''ልብ አድርጉልኝ ቁመቱን አስረዝሞ ሊመታኝ ሲመጣ ፤ የድሀ ልብሴን ፣ ወዜን አቃጥሎ ራቁቴን ማስቀረቱ አንሶት ፤ ሊደበድበኝ ሲመጣ ልባድርጉልኝ'' እያለ ሮሮውን አሰማ ። ''ወንድምህ እንቁላል ሰርቆ ዕድሜ ልኩን ወህኒ ቤት ይማቅቃል ። አንተማ የኔን ሰላሳ ብር የሚገመት ኩትና ሱሪ ከነሸሚዙ ሸጠህ ከበላህ ስቅላት አስፈርድብሃለሁ ። ፖሊስ ጣቢያ እንሂድ ።'' አለና አንገቱን በድሪቶ አነቀው ። ታደሰ ማምረሩ በሁኔታው ይታያል ።

''እኔን ነው ባሮጌ ልብስ ዕድሜ ልክ እሥራት የምታስፈርድብኝ ? ዳኞቹ ሁሉ እንዳንተ ዱርዬ መሰሉህ ? ደሞ ወንድሜን የት ታውቀዋለህ ? እንኳን ሊታሰር ሠርቆ አያውቅም '' አለ ማሞም ፣ እየተናነቀ ። '' ያው እንዳንተ ያለ ሸጦ በላ ዱርዬውን ማለቴ ነው '' ብሎ በመቀጠል ወደ ልጆቹ ዞረና '' ኑ ልጆች እያዳፋን ፣ እያጋጨን ፤ እያንገጫገጭን ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንውሰደው ''
አላቸው ። እየተጋገዙ የማሞን እጅ ጠመዘዙት ።

''እጄን ሰበራችሁኝ ፣ ልብሴን ቀደዳችሁብኝ ፣ እባካችሁ በወንድ ልጅ አምላክ በሳት አታቃጥሉኝ ! ማን ነው አንገቴን አሚያርደኝ ?'' እያለ እንባው እያቆረዘዘ ለመናቸው ፣ ማሞ ። እነሱ ግን ''ማሞ በሳት ሳቃጥልህ እኮ አይታወቀኝም''። ''ማሞ አንገትህን በምላጭ ሣርድህ

ደስ ይለኛል" እያሉ እጆቹን የኋሊት ጠምዘው እየገፈ ተሩ ፣ እየጎሸሙ ፣ እያንገላቱ ወደ ፖሊስ ጣቢያ መንገድ ሲጀምሩ ፣ ከመካከላቸው አንዳቸው "አሁን ፖሊስ ጣቢያ ብንወስደው አይቀበሉንም ። የምስክር ወረቀት ያለው እብድ ነው ። ለምን በውላችን መሠረት በሁለተኛው እማራጭ እዚሁ ባምስት ሳንቲም ገመድ አናንጠለጥለ ውም?" ብሎ ሀሳብ አቀረበ ። "ይሻላል ፣ ይሻላል" ብለው ተንጫጩ ሌሎቹም ። የጫት መጠቅለያ ቅጠልና ኮባ በጎርፍ ውሃ ነክረው እያመጡ ማሞ ራስ ላይ ጫኑበት ። ማሞ ራሱን ያነቃንቃል ፣ እጆቹ ስለታሰሩ በጁ ማስወገድ አልቻለም ። ከቅጠሉ የሚንጠፈጠፈው ውሃ ከእንባው ጋር እየተቀላቀለ በጉንጮቹ ላይ ቁልቁል ይወርዳል ።

"ገመድ አምጣ ፣ ገመድ አምጣ" ሲባባሉ አንድ ሊስትሮ ከቆመ የጭነት መኪና ላይ አንድ የናይለን ገመድ አምጥቶ ለታደስ ሰጠው ።

ታደስ አንዱን ጓደኛውን መሰላል እንዲያመጣ አዘ ዘው ። እንዳመጣም ገመዱን አጠገባቸው እነበረው የብ ረት ምሰሶ ባላ ላይ እንዲጠመጥመው ነገረው ። ከዚያም ቀስብሎ ፣ ፍላጐታቸው ማሞ ሌላ ቀን የተሰጠሰዉን ል ብስ እንዳይሸጥ ለማስፈራራትና ለማስደንገጥ መሆኑን ገልጾ ገመዱን ሲጠመጥም እንዳይቋጠር አስጠነቀቀው ።

"እና የምራችሁን ልትሰቅሉኝ ነው? ምን አደረኳ ችሁ? ኧረ በወንድ ልጅ አምላክ ተውኝ! እና ቁመታች

ሁን አስረዝማችሁ ምስክር በሌለበት ልትገድሉኝ ነው ?”
እያለ ሲለምናቸው አንድ በመንገድ የሚያልፍ ፖሊስ
አየ ። “ፖሊስ ! ፖሊስ ! አስጥለኝ” ! አለ ማሞ ተስፋ
በቆረጠ ድምጽ ። ወደ ተሰበሰበውም ሰው ዞሮ “ እስቲ
እንግዲህ ይህን ምን ትሉታላችሁ ? ” በማለት ሲቀጥል
ሲል “ ኑዛዜ ካለህ ሁለት ደቂቃ ሰጥተንሀል ። ረዘም
ያለ ከሆነም አምስት ደቂቃ እናደርግልሀለን” አለ ታደሰ
አቋረጠውና ።

ማሞ ፊቱ ተለዋወጠ ። ከንፈሮቹ ተንቀጠቀጡ ።
እንባና ሲቃ እየተናነቀው “የጨርቅ ተራ ዱርየዎች ፣ ገዳ
ዮች ፣ ሌቦች ናችሁ” ወደ ታደሰ ዞረና “አንተተ ከዚህ
በፊት ሰው በጩቤ ወግተህ ገድለህ ድሬዳዋ ከርመህ
ተመልሰህል አሉ ። ነፍሰ ገዳይ ነህ ” በማለት ጀመረ !

“እባክህ ኑዛዜ ካለህ ተናዘዝ ስድቡ በኋላም ይደ
ርሳል አለ ታደሰ ፣ የሀፍረት ፈገግታ ፈገግ እያለ ።

የማሞ ኃጢአት ፍቅር ነው ። በፍቅር የከሰረ በስቅ
ላት ይሞታል ! ለሌላ ጊዜ ትምህርት ይሆነዋል ፣ ፍቅር
እንዳያሞኘው ። ቶሎም እንጠራ ! ኑዛዜም አያስፈልገው”
አለ ሌላው ።

“ለሰማይ ቤት ስንቅህ ።” አለና አንድ ሊስትሮ
ጭቃ ዝቆ አምጥቶ ማሞን አጎረሰው ። ይህን ጊዜ ገመድ
አንጠልጣዩ ገመዱን እያይዞ ወረደ ።

“በሉ ተረዳዱ” አለ ታደሰ ዙሪያ የቆሙትን ሰዎች “እንገቱን ሸምቆቆ ውስጥ እናስገባው ፤ እንዳይፈራገጥ እግሩን ያዙት”

አንዱ አንድ እጁን ፣ ሌላው ሌላውን ፣ አንዱ ቀኝ እግሩን ፣ ሌላው ግራውን ፣ ወገቡን ፣ ብብቱን ይዘው አን ሱና እሸምቀቆው ውስጥ አንገቱን አስገብተው ለቀቁት ። የተጠመጠመው ገመድ ሲፈታ የማሞን አወዳደቅ ለማ የት ታደሰ በጉጉት ሲጠብቅ ማሞ እንደ ሰዓት አሚ ዋች በመንጠልጠል ወዲያና ወዲህ ተፈራግጦ ፀጥ አለ ።

“አንተ ቡሽቲ ገመዱን ቋጥረኸዋል ማለት ነው? ” አለና ዞር ቢመለከት ቋጣሪው እተሰበሰበው ሰው መሀል የለም ። ሌሎቹም እየተጋፉ በያቅጣጫው መሂዳቸውን ጀምረዋል ።

# ኀራው

ከሰለሞን ለማ

ጦር ሜዳ ውሎ አያውቅም ። ብቻ ስለጦር ሜዳ ሲወራ ብዙ ጊዜ ሰምቷል ። "በአምስቱ የወረራ ዘመን ዱር ቤቱ ብለው ፣ ቅጠል ለብሰው ጢሻ ለጢሻ ተንዘው መግቢያ መውጫ ሲያሳጡት ጠላትን ሲያርበደብዱት" እሚሉ ወሬ ከሰማ አፉን ከፍቶ ሲያዳምጥ ይውላል ። ሆኖም ደነቀው አገር ያደነቀው ዘመድ ወዳጅ እሚወደው ታታሪ ገበሬ ነው ። የአድዋ ድል ሲከበር ፣ የነፃነት ቀን ሲታወስ ፤ እሱም ያ ያላየው ፣ ያ ያልዋለበት ጦር ሜዳ ትውስ ይለውና ነሸጥ ያደርገዋል ። ወደ ኋላ ተመልሶ በወሬ የሰማውን ጀግንነትና ቆኛማች ደጀኔም ያጫውቱ ትን ታሪክ እያደነቀ ይገረማል ። በላይ ዘለቀ ሲባል ሰም ቷል ። ከበላይ ጋር ጦር ሜዳ ከዋለ ሰው እኩል ስለበላይ ያወራል ። እናቱ የወሬ ወሬ "የተወለድከው ደጃች በላይ በተያዙ በአምስተኛው ዓመት ነው ሲሉት" "ምነው ሳይ ያዙ ቀደም ብለሽ ወልደሽኝ በነበር" ብሎ ይጸጸታል ። ታዲያ ያ ሲተረክ እሚያስፈገዘው የጦር ሜዳ ወሬ ወሬ ሁኖ አልቀረም ። እናት ሀገር ጀግኖች ልጆቹዋን የምት ፈልግበት ለብዙ ልጆቹዋ ጥሪ የምታደርግበት ወቅት መጣለት ። "ጀግኖች ልጆች ያላት ሀገር ተደፍራ አት ቀርም" ብሎ ሁሉም በያለበት ሲነሳ ፣ በደነቀው ደም ውስጥ የሚፈላው ጀግንነትም አብሮ ተቀሰቀሰ ። የአባቱ ጓደኛ ቆኛማች ደጀኔ ያ ሚያጫውቱት ሁሉ ቅርብና እሚጨበጥ መስሎ ታየው ።

ቀኖማች ደጃኔ አንቱ፥ እሚባሉ አርበኛ ናቸው ። ከል ጃቸው ጎጆ በላይ ካለችው ኮረብታ ቁጭ ብለው በጭራ ቸው እየተጫወቱ፥ አላፊ አግዳሚውን ሲማትሩ ይውሉና ወደ ደነቀው ቤት ያመራሉ ። ለደነቀው የጀግና ምሣሌ ውና ምን ጊዜም እንግዳው ናቸው ። ምንጊዜም ደጃኔ ሌላም ወሬ የላቸው ፤ ወሬያቸው ሁሉ "የጠላት ዘመን" ወሬ ነው ።

"የሚያዝያ ጊዮርጊስ ዕለት ጠላት ብቻና ስፍሯል ማለትን ሰማንና አርበኛ ሁሉ ፎክሮ ወደ ብቻና መገስገስ ጀመርን ። እኔ አባትህ የያዝኩትን ውሃ መትረየስ አን ድዬ በግራዬ ፤ አንድዬ በቀኝ እጄ እያዞርኩ አንደዬ ትከ ሻየ ላይ እያስቀመጥኩ ፤ ያንዬ ድምጼ ደህና ነው ----

ሞትማ ምንድነው ጉንፋንም ይገላል ፤
ሞትማ ምንድነው ስርቅታም ይገላል --- ብዬ

ሳቅራራ አንዱ አንዱን ፤ አንዱ አንዱን እየተመለከተ ሲፎክር ምን ልበልህ መሬት ድብልቅ ትላለች ። አንድ ከኛ ጋር አንዱ ዓለም እሚባል ቆፍጣና ነበረልህ-ጀግና ። ዲማ ላይ ጠላትን ገጥመን ስናርበደብደው ዋልንና ወደ ማታ ላይ እግሬ አውጭኝ ብሎ ጠላት ሲፈረጥጥ የኛ ሰው የማረከውን መሣሪያ ሲሰበስብ አንዱ ዓለም ቢታይ የለም ፤ ለካስ ጠላት ሲፈረጥጥ አልመለስም ብሎ ጠላ ትን እያባረረ ሂዶ ኑሯል ። --- ምን ይሆናል ፣ ብቻውን መሆኑን አይቶ ጠላት እዛው አስቀርቶታል ።

"እና --- ታዲያ --- ታዲያልህ" ብለው ጭራቸውን ግራ ቀኝ ያወዛውዛሉ - የረሱትን ታስታውሳቸው ይመስል ። "አዎ አንዱ ዓለም ፤ ጀግና ነበር ። ጀንበር ስታሽ ቆለቆል ተነስተን የገሰገስን እንደሆነ ሳይጨልም ጠላት ሰፈር እንገባለን ። ጠላትም በመንጥር አይቶ ይጠነቀቃል ። አንዱ ዓለም እዚሁ ቆይተን ሌሊት ጉሮሮውን እንነቀው ይላል ። ልጅ በላይ ዘለቀም ደግ ነው ይለዋል ። ከዚያን ሁላችንም እንስማማለን ። ተሩቅ እንዳትተኩሱ ብሎ ልጅ በላይ ያስጠነቅቀንና በአራት ተከፍለን ምሽቱን ስንጠባበቅ ቅልጥጥ ያለ ጨረቃ ይወጣልህና ቁጭ ይላል ። እህ ሲባል ከፊሉ ቢያየንም እንግባበት ፤ ከፊሉ የለም እንደር ሲል "ተነስ" ጉበዝ ይላል ልጅ በለይ ። ምን ልበልህ ብቻ እኩለ ሌሊት ላይ ታለበት ደርሰን እንሰፍርበትና ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር ጠላት እዛው እምሽክ ብሎ ይቀራል

ደነቀው ፈዞ ይሰማቸውና "አየ" ይላል ። "ቀኛ ዝማች እንደው እማያቁት አገርና ሰው አይናፍቅም ይባላል እንጂ እኔስ በላይ ናፈቀኝ ።" ይላቸዋል ። ከት ብለው ይስቃሉ ። "እየው ምን አልከው ፤ እማያቁት አገር ሰው አይናፍቅም" መናፈቅ እኮ መ ወደድ ነው ። ሰው እሚወደውው በጀግንነቱ አይደለም እንዴ ? ታዲያማ በላይም ይናፈቃል ። ስንት አለ የበላይ ዓይነት ፤ እየው ልጅ ለምንድነው እሚወለድ ? አባቱን እያቱን ትንዲተካ አደለም እንዴ ? በላይ የዛን ዘመን ጀግና ነው ። በጀግንነቱ ሞተ ።

ጠላት ተመምጣቱ በፊት በላይ እንዲህ እንዳንተው ታታሪ ገበሬ ነበር ። ስማ በላይን መናፈቅህ ጥሩ ነው በአንድ ወገን ። መናፈቅህ የሱን ጀግንነት ለመውረስ የሱን ታሪክ በመውደድ ተሆነ ደግ ነው ። እንደ ልጅ ናፍቆት ተሆነ ግን ይቅርብህ ፥ አይናፍቅህ ።

"የልጅ ናፍቆትማ ሆደ ቡቡ ያደርጋል ፣ ጀግና አት ሆንም ። እየው ጀግናና ወርቅ አንድ ነው ። አሁን ወርቅ ወርቅነቱ እሚታወቅ እሳት ሲነካው አደል እንዴ? ታዲ ያማ - ጀግናም በክፉ ቀን እሚወጣ በእሳት ነው እሚፈ ተን ። አሁን ሰው "ፈሪ ለእናቱ" ይላል ። እየው "ጀግና ደግሞ ለአገሩ ነው ፤ ጀግና ቶሎ ይሰበራል" ይባላል እዎ ተሰነፉ ጋር ሲወዳደር እጭር ነው ዕድሜው ። ሞቱ ግን የጀግና ሞት ነው ።

"ደሞ ጀግና ቶሎ ይሰበራል ሲባል ጦር ሜዳ በገባ ማግሥት ይሞታል አደለም ። ጅግና ብረት ነው ። ቶሎ አይሰበርም ፤ ብዙ ሠርቶ ነው እሚሰበር ። ቶሎ ተተሰበረ ማ ጀግንነቱ እምኑ ላይ ነው ? ጦር ሜዳ ስለ ሄደ? ለዚ ያማ ሰነፉስ ይሄድ የለም እንዴ ? እየው ቶሎ እሚሰበር ሰነፍ ነው ። ያውም ጅል አሰባበር ። ጀግና ምድር ነው ። አሁን ምድር ስንቱን ትችላለች ? ጀግናም እንዲያ ነው ። ስንቱን ችለነው ኖርን ። አሁን እንኳ በአንተ ዕድሜ ስን ቱን ቻልነው ፣ ለጦቢያ የሞቱላት ሳይሆን ገሎ የቀበራት

ሲበላ እያየን አንገታችንን ደፍተን አልኖርንም ? አርበኛ ነን ማለትን እንኳ ፈርተን ተሸማቀን አልኖርንም ወይ? በልይ መልስ ? ስንት ዓመት ተቆራምጄ የሰው አሽከር ሆኜ ስኖር አላየህም ? እንዴያ አልቻልኩም ? ጀግና እኮ መመከት ብቻ አይደለም ፣ ጥቃትም ይችላል ። ቀኛማች ብሎ ስሜን አጠፋው እንጂ ለኔ ምንጠቀመኝ ? ። ኩርማን መሬት አልሰጠኝ ። ቀኛማች አባቱ ይጥፋና ይኸው ስንት ዓመት ስሜን አጥፍቶት ኖረ ። ኤዲያ አልቻልኩም ወይ" ይላሉ በተናገሩ ቁጥር ጀግንነት እየተሰማቸው ትናንት በዓባይ በረሃ የፈጸሙት በዓይነ ሕሊናቸው እየታያቸው ፣ ትውስ እያላቸው ፤ በዘመነ "ነፃነት" ም ያጋጠማቸው ውርደት እየታሰባቸው ።

ደነቀው የጀግንነት ወሬ ይወዳል ። እንኳንስ ከቤቱ ድረስ መጥቶለት ብዙውን ጊዜ የጀግና ወሬ ፍለጋ ይወጣል ። ቀኛማች ብዙ እንዲያወሩለት ጥቂት ወርወር አድርጐ መለስ ይላል ። ጥቂት ካስጨበጣቸው እሳቸውም አይመለሱ ። ደነቀው ያን ጊዜ ቀኛማች በነበሩበት ዘመን ኖሮ እንደዛሬው እንደ ቀኛማች ባወራ ደስ ባለው ። ባያወራም በዚያን ወቅት ኖሮ ጀብዱ ሠርቶ ባለፈ ደስ ባለው ።

---- ግን ዛሬም ዕድሉ ሊኖር ይችላል -- ሲል ወዲያውኑ ያስባል ።

የደነቀው አባት አወቀ ቸሬ እንደ ቀኛማች አይ ሁኑ እንጂ እሳቸውም አበርኛ ነበሩ ። በ1962 የብቸና ንቅናቄ ጊዜ ዱር ገብተው በቦምብ ተደብድበው ነው የሞቱት ። ያን ጊዜም ደነቀው ነፍስ ያወቀ ገበሬ ነበር። ቀኛማች የአወቀ ቸሬ ጥሩ ጓደኛ ነበሩ። ዛሬ ደግሞ የል ጃቸው የደነቀው ጥኑ ጓደኛ ሆነዋል ። ደነቀው ቀኝ እጁን በምሬት እያወዛወዘ፤ “ እኔስ ቶከራ ቀረርቶ! ሽለላ ስሰማ ልቤን ይነሳኛል ቀኛማች ። የሰው ሁሉ አመል ይገርመ ኛል ። አሁን ሰው ሲዘፍን ሲደልቅ ቢውል ምንም አይመስለኝ ። ቀረርቶ ሽለላ ተሰማሁ ግን እንደው ---- እንደው --- ምን ልበልሁ” ሲል ያቋርጡትና “ያቁነጠ ንጥሀል መቸ አጣሁት ። ታዲያ እኮ ይኸ የወንድ ልጅ ወጉ ነው ። ቀረርቶና ቶከራ መቸ እንዲህ ሆነና? አይ የልጅ ነገር! ይህ ሰው ሁሉ ወንዝ ወርዶ ሲመለስ ፣ ገና አሸንፎ ሲመጣ ፣ የጠፋ እህያ አግኝቶ ሲመለስ ፣ እን ቅፋት ሲመታው ፣ ሚዳቆ አቋርጣው ስትሮጥ ፣ ጅብ ሲያስ ደነግጠው እሚፎከረውን ነው እንዴ ቶከራ እምትለው? አይ የልጅ ነገር! መቸ እሱ ቶከራ ነውና ። ቶከራ ቀረርቶ ድሮ ቀረ ። ቶከራ አለይ! ቶከራ እሚያምረው በቦታው በወጉ በማዕረጉ ነው እይ ። ይኸ አ፤ ረገ ምቸው እንጂ ቶከራ አይደለም ። ብቻ ቶከራ መውደድህ ጥሩ ነው ። በአ ባትህ ነው የወጣኸው ። አባትህም እንዲሁ ነበር ። እሱማ ያቅራራ እንደሁ ፣ የፎከረ እንደሁ --- ኤዲያ -- እን

ኳን ወንድ ባልቴቷ እንኳ ሳትቀር ልሽፍት ነው እምትል ።
—እስቲ እወዳለሁ ብለሃል ካልህ ሲቅራራ ሲፎክር ክሰማ
ኸው እንድ እንኳን በልልኝ" ደነቀው እንደማፈር ይላል።
"እኮ በል እወዳለሁ እላልክም እንዴ ታዲያ የት አለ?
አይ የልጅ ነገር ። " ይላሉ ። " እንዴ ቀኛማች ታለቦ
ታው ታልሆነ በውጉ በማዕረጉ ታልሆነ እስረሽ ምችው
ነው እላሉም እንዴ" ፤ ይልና ደነቀው ሁለት ጊዜ
በረኸርሙ ተንፍሶ ድምጹን ለቀረርቶ ያመቻቻል - እንደ
መሳል እያለ ።

" እለ ነገር እለ ነገር
እቀበቱን ወጥተን
ቁልቁለቱን ወርደን
ወንዙን ስንሻገር - -(ያቆምና ድምጹን ያስ
ተካክላል )
የጉበዝ ወዳጅ ታስታውቃለች
የጅግና ወዳጅ ታስታውቃለች
እፋፍ ላይ ቆማ በለው ትላለች።"

" እይ ! እየሀ ስሟን ሲያጠፉት እየሀ ! "
"እንዴት ቀኛማች" እለ ደነቀው ፤
" ደሞ እፋፍ ላይ ቆማ? እፋፍ ላይ ቆማ በለው ለማ
ለትማ የሰነፍስ ወዳጅ ምን ይጉላታል? ። ተሩቅ ሁና አይ
ሃህ ለማስትማ ወላዲት እምላክን እሱዋም ብትሆን አይ
ቸግራት ። እየው የጅግና ወዳጅ እፋፍ ላይ አትቆምም ፤ እብ

ራ ወርዳ ነው እጭድ ከምር እያረገች በለው እምትል ። እፋፍ ተወጣችማ ምኑን የጀግና ወዳጅ ሆነች ? አላየንም እንዴ ? አልሞትን ፣ የአይን ምሥክሮች እኮ ነን ። ደሞ እፋፍ ላይ ቆማ ! ሁለተኛ እንዳይወጣህ ። " ይላሉ ቀኛ ማች ።

" ተለምዶአል ቀኛማች ! አገር ነው እሚለው "

" እወን ፣ ምን ታደርግ ? አንተማ የሰማኸውን ነው "

ለማንያውም ደህና እሚወትኩህ ፣ እምደርስባት አለችኝ " ብለው ጭራቸውን እያወዛወዙ ሊወጡ ሲዘጋጁ " ምነው መሄድዎ ነው እንዴ ? " ይላቸዋል ።

" እዎ --- እሚወትኩህ ፣ እስኪ ደሞ ወጣ ልበል ። እምጠይቀው አለኝ ። "

" አሁን ፣ ቀኛማች ዝመቱ ቢባሉ እውነት ይዘም ታሉ ? " ቀስ ብሎ ይጠይቃቸዋል ።

" እኔ ደጀኔ የቆፍጣናው ልጅ እንዴትሳ አልዘምት በል ! እንዴት ብትደፍረኝ በል ! ሳልውል ሳላ ድር ያኑለት ነዋ ። በእዛኙቱ "

" የለም አርጅተዋል ብየ ነው እኮ "

" ያረጀህስ አንተ ፣ ምኔ ነው ያረጀው ፣ ወጣት ብቻ ይዝመት ያለህ ማነው ? በልይ ንገረኝ ። የለም የለም አላማርከኝም ቀስ እያልክ እኮ ሰደብከኝ ። በል --- በል ደህና ሁን ። "

ይወጣሉ ደንቀም ቀኛማች ጭራቸውን እያወዛወዙ ሲሄዱ ከዓይኑ እስኪጠፉ ድረስ በፍቅር፣ በአክብሮት ከኋላቸው ይመለከታቸዋል ።

አዲስ አበባ አብዮትና ፀረ አብዮት ይፋለምባታል። ዛሬ ጋብ ያለው ፍልሚያ ነገ ይብሰበትና እንደገና በረድ ይላል ። ደሞ እንደገና ይብስበታል ። በየቀበሌው ሕዝቡ ይጣደፋል ። የውስጥ እልበቃ ብሎት የውጭ ወረራ የታከለበት አብዮት ልጆቹን አስተባብሮ ለሁለቱም ፍልሚያ ይዘጋጃል ። አገር ተወረረ፣ ድንበር ተቆረሰ ሲሉት እማ ይወደው፣ አብዮቱን አላስቀለብስም ከሚለው ጋር ተባብሮ ለሞት ሽረት ትግል ዝግጅቱን ያጣድፋል ። የውስጥና የውጭ ወራሪ እይዞህ እየተባባለ የውስጡ አንድ ድንጋይ ሲወረውር የውስጡም በቅርብ ሆኖ ሁለት ይወረውራል። አብዮቱን አገሬን ያለውም አጥፍ አርጐ ይመልሳል ። ፍልሚያው ዛሬ ጋብ ይልና ነገ ይብስበታል፣ ደሞ በረድ ይላል ። ሕዝቡ ግን በየቀበሌው ይጣደፋል ። ሥንቅ ዝግጅት፣ ምልመላ ቅስቀሳ የሀገር ፍቅር፣ የወገን ፍቅር፣ አብዮት በአንድ በኩል፤ አሻጥር፣ ግድያ፣ ፀረ አብዮት በሌላ በኩል ። ግብግብ፣ ነገም ግብ ግብ ። ጊዜው ወሳኝ ነበር ። አገር አትቆረስም፣ ድንበር አይደፈርም የብዙዎች ደም የፈሰሰበት አብዮት አይቀለበስም እሚለው ከዳር እስከ ዳር ግልብጥ ይልና ይነሳል ። ሁሉም "እዛው እድንበሬ ላይ" ይላል ። ዝግጅት-ሥንቅ-ምልመላ-ሰልፍ ። ነገም ዝግ

ጅት- ስንቅ-ምልመላ-ሰልፍ ። የአብዮቱ ወገን ክንድ ያይላል ። በቀበሌ ፣ በከፍተኛ፣ በፋብሪካ ፣ በገበሬ ማህበር፣ በከተማ በአገሪቱ በሞላ ስንቅ ዝግጅት፣ ሰልፍ ። "እዛው እድንበሬ ላይ" ይላል ሁሉም ። የውስጡ ፍልሚያ ጋብ ብሎ ያድርና ብሶበት ይውላል ። ሕዝቡ አሁንም በየቀበሌው ይጣደፋል ።

ደብረወርቅ ከተማ ውስጥም ዝግጅቱ ቀጥሏል ።ከየገበሬ ማህበሩ ሚሊሺያ ሲመለመል ቀኛማች ወኔ እሚቀሰቅስ ፉከራ እያሰሙ ፤

"ልብ አርግ አንድ ብለህ ማፈኝ እኔ ደጀኔ--በቁሜ እያለሁ ? ምቻለሁእ" ቃሉ ወዲህ ደብረወርቅ ውስጥ ተመዝጋቢው በዝቷል ።

መኮንኑም በኃዘንና በፍቅር እያስተዋላቸው ፤ "ቀኛማች አሁንም ያደረጉት አስተዋፅኦ ትልቅ ነው ። ቀላል ሥራ አይደለም የሠሩት ። አላስቀረንዎትም ፣ ሁሉንም ማንንዝ ስለማንችል ነው-- በደጀንነት ተጠባባቂ ሆነው ተመዝግበዋል ---" ሲላቸው ያቋርጡትና "ምን ምን ? በደጀንነት በአዛኙቱ ማሪያም ! ማነው ደጀን በል እኔ ደጀኔ አላደርገውም ማን ቀድሞኝ እኔ ደጀን ልሆን በል አሁንማ ጭራሹን ገደልከኝ በል ተወው" ይሉትና በክዘራቸው ምድሯን እየደበደቡ ይወጣሉ ።

ደነቀው ግን እንደሕልም ሲያየው የኖረው ዕድል እንዳያመልጠው አልፈለገም ። ከጓደኞቹ ጋር ሁኖ ታጠቅ ጦር ሠፈር ደረሰ ። ባለው የተፈጥሮ ጀግንነት ላይ ታጠቅ ያገኘው ትምህርት ሲታከልበት የወኔ ወኔ ሰጠው ። ትም ህርቱ ደስ እያለው ፤ ልቡ ግን ቶሎ ጦር ሜዳ መሄድን ይፈ ቅዳል።ሶስት ወር በሚገባ ሰልጥና "ነገ ወደ ጦር ሜዳ ጉዞ እናደርጋለን ።" የሚል ወሬ ሲሰማ ልቡ በደስታ ተሞላ ።

የጠዋት ፀሐይ በውል ሳትወጣ ደነቀውና ጓደኞቹ ከታጠቅ ተነስተው በየመንገዱ ጥግ ቆሞ እጁን ለሚያው ለበልብላቸው ሕዝብ አፀፋውን እየሰጡ የሐረርን መን ገድ ተያያዙት ። አሁንም በየዳሩ ቆሞ እጁን የሚያውለ በልብላቸውን ሕዝብ አፀፋውን እየመለሱ አዳዲስ መን ደርና ከተማ እያዩ እየፎከሩ ረዥሙን የሐረር ጉዞ ቀጥለው ጀንበር ከመጥለቋ በፊት ሐረር ከተማ ደረሱ ። ሐረር የግርግር ሀገር ሁና አገኙዋት ። አልፎ አልፎ የከባድ መሣሪያ ተኩስ ይሰማል ። ጀቶች ሐረርን ቁልቁል እያዩ አሻግረው ይሄዱና ይመለሳሉ ። የሐረር ሰው ሲሄዱም ሲመለሱም ያይና "እሰይ" ይላል ። ደነቀው ከቶም አል ተደናገጠ ። ውርውሩን አየና በረታ ። የጥይቱ ተጩት የመድፍ የታንኩ ጋጋታ ሳይፈታው የጀግንነት መንፈስ መላ ሰውነቱን ወረረው ። ቀኛማች "ጀግና በክፉ ቀን ነው እሚወጣ" እሚሉት ትውስ እያለው የባሰውን ጠን ከረ ።

እሱ ያለበት ጦር ሐረርን አላስነካም ብሎ ሲዋጋ ሰንበተ ። ገፍቶ የመጣው ጠላት ያሰበው አልሳካለት ብሎ ምስ ምሱን እየቀመሰ ፣ ይዞ የመጣውን እያስረከበ ቁል ቁል ወደመጣበት እግሬ አውጭኝ አለ ።

ጥቂት ቀናት ቆይቶ ጦሩ እንዲንቀሳቀስ ትዕዛዝ ደረ ሰውና የማለዳ ፀሐይ ቀጭን ብርሃን ዘንጓን ስትዘረጋ ሁሉም በየመኪናው ወጥቶ ጉዞ ተጀመረ ። ደነቀውም በ4ኛ ቁጥር ከተሰለፈው መኪና ላይ ነበር ። ጦሩ በትጠ ንቀቅ ሆኖ ብዙ እንደተጓዘ አዛዡ ትዕዛዝ ሰጥተው ጉዞው በእግር ሆነ ። እንደዚህ ያ ሁሉ ጀግና የሀገር የወገን ፍቅር እያቃጠለው አራስ ነብር ሆኖ በጀግንነት ሲጓዝ ጠላት ሳይታሰብ ተኩስ ከፈተ ። የደነቀው ልብ ቶሎ ቶሎ መም ታት ጀመረ ። ለዚህ ሁሉ አዲስ ስለነበር ያላሰበው የፍር ሃት ጃንጥላ አረበበበት ፣ ፍርሃት ጀግንነት ድካም ብር ታት ተፈራረቁበት ።

ቱኛ --ቱኛ እሚል ድምጽ ተሰማና ወዲያው ድብ ልቅልቁ ወጣ ። መሬት ቁና ሆነች ። "እይዞህ --በለው --" ይላል አንዱ ከመካከላቸው ። ደም ድብልቅልቁ ። ወጣ ደነቀው በጶረቱ እየተሳበ የጠላቱን ግንባር ሲበሳ ቆየና ድንገት ሳይታሰብ ፣

"ዘራፍ ብሎ --ወንዱ ሲነሳ ፣
የሌሊት አውሬ የቀን ጃዊሳ" ብሎ ፎክሮ

በቋሙ ሁለት ቦምብ አከታትሎ ይጥላል ። ወዲያው ከፊት ለፊት አቧራው ጨሰና በጢሱ ውስጥ ሰዎች ሲሮጡ ታዩ ።

"ተከተለው --- በለው -- በለው" የሚል ድምጽ ተሰማና እንደ ደንቀው በዚያ የአቧራ ጢስ ውስጥ እየተ ሽሎከለከ የፈረጠጠውን ጠላት ከኋላ ደርሰው አብዛኛ ውን አስቀሩት ። ጥቂቱ እግሬ አውጭኝ አለ ።

"አቤት አቤት እንዴት ይሮጣል በል" አለ ደንቀው ከጐኑ ለነበረው ሰው ። የሃምሳ አዛዡ ነበር ። "ደንቀው ተኩስ በሚከፈትበት ጊዜ ምሽግህን አትልቀቅ ፣ ቋመህ እንዳትተኩስ" አለው ። እየፎከረ ተነስቶ ቦምብ ሲወረ ውር አይቶት ነበር ። ደንቀው ሰላምታ ሰጠና "ሁሉቱም ቦምቦቼ ከመሬት ሳይረፉም ከነጠመንጃው አምሽከውታል" አለ ። ደንቀው የወረወራቸው ቦምቦች ፣ ጥይት እንደዝናም ያወርዱ የነበሩትን አምስት መትረየስ ተኳሾች ከነመትረ የሳቸው አመድ አድርጐአቸዋል ። የመትረየሶቹ ድምጽ ሲጠፋ ነው ሌላው መተኮሱን አቁሞ እግሬ አውጪኝ ያለው እርግጥ ጥቂት እግሬ አውጭኝ ማለቱ ለጊዜውም ቢሆን ደንደስ ደንደሱን እየቀመሰ ተዘረጋ ።

በቅርብ ያለው ተኩስ ጋብ አለና የከባድ መሣሪያ ዎች ድምጽ አከታትሎ ከሩቅ ተሰማ ፣ እነ ደንቀው እየቀ ረቡ ሲሄዱ የተኩሱም ድምጽ እያየለና እየቀረበ መጣ ።

አይሮፕላኖች በአሻገር ካለው ተራራ ላይ አቧራ ያጨሱና ተመልሰው ወደ ሐረር መስመር ይጓዛሉ ። እንደገና ይመጡና ያንኑ ተራራ በሚገባ ጉብኝተውት ይመለሳሉ ። እነ ደነቀው ሲሄዱም ሲመለሱም ያዩአቸውና ልባቸው በደስታ ይሞላል ። በተንጣለለው ሜዳ ላይ ያለው አቧራ እንደ ክረምት ጭጋግ ምድሯን ሸፍኖአታል ። ከፀሐይ እሚወርደው ሙቀት ምድር ላይ ካለው ሙቀት ጋር ይጋጭና ተመልሶ ወደ መጣበት እየተስለመለመ ሲሄድ ያን ከሩቅ እሚታይ ሜዳ የተንጣለለ ባሕር ያስመስለዋል ። አቧራው ምድሩ አልበቃው ብሎት ወደ ላይ እየበነነ አላፊ አግዳሚውን ያስቸግራል ። ሰውን ቀረብ ብለው ካላዩት በሩቅ ማንነቱም አይለይ ። ልብሱም ቀለሙን ቀይሮ ቋጭ ይላል ። የጠዋቱ ፀሐይ እንደቀትሯ ፀሐይ ታቃጥላለች ። ግራና ቀኝ ባሉት ተራሮች ጫፍ ላይ የተቀለለው ትልልቅ ድንጋይ ከሩቅ ሲያዩት የተሰለፈ ታንክ ይመስላል ፣ በየጊዜው የሚነፍሰው ኃይለኛ ንፋስ ዙሪያ እየሠራ አቧራውን ፣ ቅጠሉን ፣ ወረቀቱን ሰብስቦ ወደ ላይ ይበትነዋል ። እንደነቀው አሁንም በተጠንቀቅ ተኩሱ ወደ ተፋፋመበት ያመራሉ ። በተራራዎቹ መሀል ባለችዋ አቧራ በሸፈናት ሜዳ ሲጓዙ ቆዩና ከወገን ጋር እንደሚቀላቀሉ ተነግሮአቸው ፈጠን ፈጠን እያሉ ማምራት ጀመሩ ። ራሱን ለማበረታታት "አቦ ሞትም ጀግንነትም አንድ ቀን ነው" አለ ደነቀው በልቡ ። ጥቂት እንደተጓዙ ግራናቀኝ

ያለው የወገን ጦር ምልክት ሰጣቸውና ተቀላቀሉ ። ታንክ መትረየስ ፣ መድፍ ፣ እግረኛ ጉዞ ጀመረ ። ዓላማቸው እዚ ያ ተኩስ ከበዛበት ቦታ ለመድረስ ነው ። ድንገት ተኩስ ከፍቶ እግሬ አውጭኝ ካለው የጠላት ጦር ሌላ የገጠማ ቸው የለም ፤ ከፍቲኛው የጠላት ጦር የተከማቸው ከዚያ ተኩስ ከበዛበት ቦታ ነው ። አይሮፕላኖች አሁንም ደጋ ግመው እየመቱ ይመለሳሉ ። ጠላት ያለ የሌለ ኃይሉን አከማቸበት ቦታ ድረስ ሄዶ ጠላትን ሲያርበደብደው የከ ረመው የወገን ጦር ዛሬም ሽንጡን ገትሮ በመፋለም ላይ ነው ። ተጨማሪ ጦር እንደ ደረሰለትም በሰማ ጊዜ ኃይ ሉን ይበልጥ አጠናክሮ “ ሆ ” እያለ ወደፊት ገፋ ።

ታንክና እግረኛ ከፊት ፣ መድፈኞች ከኋላ ሆነው ሲገ ሰግሱ ያ ተኩስ የበዛበት ቦታ ከፊት ወለል ብሎ ቀረበ ። ሲፋለም የከረመው የወገን ጦር ከፊሉን የጠላት ይዞታ አስለቅቆ ለተቀረው ክፍል የሞት የሽረት ትግል ያደር ጋል አዲስ የደረሰው የወገን ጦር በረድፍ ፍልሚያው ውስጥ ገባ ። ከደንቀው ፊት ፊት የሚሮጠው ታንክ አከታትሎ በረጅሙ ሲተኩስ ከፊት ለፊት ካለው ጉራ ላይ ያለው ቁጥቋጦ ጋየ ። ከኋላ የተሰለፈው መድፍ አከ ታትሎ እንደ አንበሳ አገሳና ያ የጋየው ቁጥቋጦ ምንቅ ርቅሩ ወጣ ። እግረኛው ጥይት እያዘነመ ያንን ተራራ ተያያዘው ። ታንክ አሻግሮ ሲመታ ፣ እግረኛው የፊቱን ሲጠርግ ድብልቅልቅ ይላል ። ወዲያው አራት አይሮፕ

ላኖች መጥተው ጫፍ ላይ የያዙትን እራግፈው ይመለ ሳሉ ። የጠላት ታንክ መጨስ ይጀመርና ታንኩ ውስጥ የነበረው ሁሉ ታንኩን እየተወ ይፈተለካል ። ግማሹ ወደየት እንደሚሄድ ሳያውቅ እየተደናበረ ሲሮጥ እነደ ቀው ጦር ውስጥ ይገባል ። “ በሰው ---በሣንጃ--- በሣንጃ ” ይላል ደነቀው ። የሸሸው ብዙም ሳይቀር እዛው ቀረ ። ከተራራው ግርጌ ወደ ላይ መንገዝ የጀመ ረው የወገን ጦር እየገፋ ሲሄድ ታንክና መድፍ እሻ ግረው ሲመቱ ፣ አይሮፕላን ቁልቁል ሲያተራምሰው ፣ ከጫፍ ላይ ያለው ጠላት መግቢያ ቀዳዳ ይጠፋብታል ። መጨስ የጀመረው የጠላት ታንክ ይበልጥ ይያያዝና አካባቢው ሁሉ ይጋያል ። እነደነቀው ሣንጃቸውን ወድ ረው ከታንክ ጐን ወደፊት ሲሉ ታንኩ ሲጋይ የደነበ ረው ቁጥር ስፍር የሌለው ጠላት ዘሎ ይመጣባቸዋል ። “ ተቀላቀል ፣ ተቀላቀል ” ይላሉ እዛዡ ። ሁሉም ሳንጃ ውን እያሾለ ከጠላት ጋር ይደባለቃል ። የጥይቱ ድምጽ ጋብ ይልና ተራው የሳንጃ ይሆናል ። የደነቀው ፊት ፍም መስሎ ሳንጃውን ከአንዱ ላይ ነቅሎ አንዱ ላይ እስከ ሚሰካው ድረስ እየቸኮለ ያን የደነበረ ጠላት የባሰ ያደናብረዋል ። በግራና በቀኝ በኩል ያለው ጦር አሁንም የተፋፋመ ተኩስ ያደርጋል ። “ ተቀላቀል ተቀ ላቀል ” ያሉት እዛዥ “ወደፊት” የሚል ድምፅ እሰሙና ሁሉም ወደ ተራራው ጫፍ መሳብ ጀመረ ። ጠላት ማለ

ፊያ ማግደሚያውን ተኝቶበት ስለነበር በጠላት ሬሣ ላይ ነበር ጉዞው ። ደነቀው አንዱን አልፎ ሌላውን ሲራመድ ሲል ነሸጥ ያደርገውና ጠመንጃውን በሁለት እጁ ጭብጥ አድርጎ ከተጋደመው ላይ ሳንጃውን ይቃጣና መለስ ያደርገዋል ። በረድፍ የተሰለፈው ጦር ወደፊት ይገሰግሳል ። ደነቀው የወደቀውን ሁሉ እየዘለለ ሲገዝ ነጋድራስ " ጠላት ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር እዛው እምሽክ ብሎ ቀረ" እሚሉት ትዝ አለውና ግራና ቀኙን አይቶ ልቡ በጀግንነት ተሞላ ። ሄደው ሄደው ጫፍ ላይ ሊደርሱ ሲሉ ጠላት በተረፈው የሰው ኃይልና በቀረው ታንክ ግር ብሎ ይመጣና ተኩስ ይከፈትባቸዋል ። "በለው --- በለው" የሚል ድምጽ ተሰማ ። ሁሉም ባለ ኃይሉ በተረፈው ጠላት ላይ ይረባረባል ። ያ ግር ብሎ የመጣ ጠላት መጨረሻው መሆኑን ሲያውቅ ዓይኑን ጨፍኖ ይገባል ። ደነቀው እያ ከታተለ ቦምብ ይወረውራል ። ፊት ለፊት መግጠሙ አላዋጣው አለና ጠላት ጠመንጃውን በየደረሰበት እየጣለ መፈርጠጥ ጀመረ ። መኪና እንዳስደነበረው የበግ መንጋ ሁሉም በየአገኘበት ሲሸሽ አብዛኛው ሸሽቱ አላዋጣው ብሎት እዛው ቀረ ። ደነቀው እያከታተለ ቦምብ ሲወረውር ቆየና ከመሸገበት ወጣ ሲል ስፍር ቁጥር የሌለው የሚሸሽ ጠላት ከፊት መጣበት ። አሁንም እያከታተለ ቦምብ ወረወረ ። በብዛት ግር ብሎ የመጣው ጠላት የወገን ጦር ቁስለኛን ለማስንሳት የመጣችዋን ሄሊኮፍተር አይቶ በከፊል በርግጎ ወደመጣበት ተመለሰ ። ከፊሉ

መሸሻ ያሳጣውን የደነቀውን ቦምብ ጥሶ ለመሸሽ እየ
ጮኸ ወደ ደነቀው ሲገሰግስ ደነቀው ከምሽግ ወጥቶ ሁለት ቦምብ እንደ ወረወረ የወደቀው ወደቀና ከፊሉ ደነ
ቀውን ጥሶ ወደታች በረገገ ። ግራና ቀኝ ያለው ጦር ወደ
ፊት ሲገሰግስ ጠላት ይዞ የመጣውን ንብረት እያቃጠለ
ሸሸ ።

በጀግንነት ሲዋጋ የዋለው የወገን ጦር በረድፍ በረ
ድፍ ሆኖ " ሆ " እያለ በድል ካለመበት ከተራራው
ላይ ወጣ ። የጠላት ሬሣ በየሥፍራው ወድቋል ። ጩር
ስኝ እያለ ዓይኑን እሚያቁለጨልጭ ጠላት በየቦታው
ተዘርግቷል ። ቁጥር ስፍር የሌለው የጦር መሣሪያ በየቦ
ታው ወድቋል ። "ሆ" እያለ የገባው የወገን ጦር ያን
በጠላት ተይዞ የከረመ ምድር ዙሪያውን ከቦ የእናት ሀገ
ሩን ባንዲራ እያውለበለበ እንደገና " ሆ " አለ ። ደስታ
ሆነ ። ታንኮች ጠላት ወደሚሸሽበት አቅጣጫ ደጋግ
መው በመተኮስ የድልና የደስታ ድምጽ አሰሙ ።

ደነቀው " ሆ " ተብሎ ተራራው ጫፍ ላይ ሲወጣ
አብሮ አልወጣም ። የሚሸሸው ጠላት በእሱ በኩል ጥሶ
ለማለፍ በርግጎ ሲመጣ ቦምብ አከታትሎ ከወረወረ
ወዲህ አልታየም ።

ጦሩ በየክፍሉ ተሰማርቶ ሰፈረ ። የከባድ መሣሪያ
ጩኸት ከሩቅ ይሰማል ። ተኩሱ ጋብ ይልና መልሶ ድብ

ሊቅሊቅ ይላል ። ደንቀው አልተመታም ። ተራራው ሜዳ ድረስ በጀግንነት ተዋግቷል ። ግን የደረሰበት በላልታወቀ ጠላት እፍኝ ወስዶታል ተባለና ተወራ ።

ማለዳ ፀሐይ ባሻገር ከሚታየው ተራራ ጀርባ ሆኖ ብርሃኑን በድሉ ተራራ ላይ ስትፈነጥቅ ትናንት የሞት ሽረት ትግል ሲደረግበት የዋለውን ሜዳ አቋርጦ አንድ ሰው ሲገሰግስ ታየ ። በአካባቢው ሌላም ሰው የለ ። በጀርባውና በአንገቱ ዙሪያ የተሸከመው ነገር አለ ። ከሩቅ ማንነቱ በውል ባይታወቅም ተራራው ላይ የሰፈረው ጦር በተጠንቀቅ ጠበቀው ። ያ ሰው እየቀረበ መጣና አቀበቱን ተያያዘው ። ድካም ያለበት ይመስላል ። በእጅ ምንም ዓይነት ምልክት አያሳይም ። አሁን በተጠንቀቅ ይጠበቃል ። ከድሉ ተራራ ሜዳ ላይ ሲወጣ ማንነቱ ታወቀ ። ሁሉም " ደንቀው ፤ ደንቀው " እያሉ አንገቱ ላይ ተጠመጠመበት ። ደንቀው እሚፈረጥጠው የጠላት ጦር ግር ብሎ ጥሶት ሲያልፍ፡ ቦምብ እየወረወረ ተከትሎ በመሄድ ላይ ታወቀው ብዙ ይጓዝና ጥሶት ያለፈውን ብዙውን ጥሎ ስምንት አውቶማቲክ ጠመንጃ ይዞ መመለሱ ነው ። ሌሊቱን ሁሉ ሲጓዝ ስለአደረ የድካም ምልክት ይታይበታል ። ምርኮውን አውረደና አሻግሮ እየተመለከተ ፤

" ይኸ ታች ማን እሚባለው ከተማ ነው ? " አለና ጠየቀ ። " የጅጅጋ ከተማ ነው ፤ ይኸ ተራራ ደግሞ ካራማራ ይባላል ። " ብሎ መለሰ የሃምሳ አዛዡ ።

ደነቀው በሶስት ዓመት ደብረወርቅ ተመለሰ፣ደነቀ ውንና ጓደኞቹን "በድል ተመለስ" ብሎ የሸኛቸው ሕዝብ አሁንም ተሰልፎ ተቀበላቸው ። ወዲያውኑ ወደ ሠፈሩ አመራ ። ደነቀው "ቀኛማችን" ለማየት ቸኩሎ ቀኛ ማች በጠና ታምው ዛሬ ነገ ይሞታሉ እየተባለ ይጠበቃል ማለትን ሰምቷልና ።

ሠፈሩ እንደ ደረሰም ወደ እናቱ ቤትም ሳያመራ መን ገዱን አሳብሮ ወደ ቀኛማች ቤት ገሰገሰ ። በቀኛማች ቤት ብዙ ሰው ሲወጣና ሲገባ አየ ። እበሩ ላይ የቆሙት የደነ ቀው እናት ጓደኛ ወይዘሮ ጥሩየ ደነቀውን ሲያዩት ዘለ ው ተጠመጠሙበት ። ጥሩየ እምባ እየተናነቃቸው "አየ ልጄ እንዳው ዓይኑን ባየሁት ሲሉ እንኳን መጣህ፤ዓይ ንህን ዓይተውት ቢሞቱ ይሻላል" አሉት ። ቀኛማች የተ ኙባትን አልጋ ሰዎች ከበዋታል ። ደነቀው ዓይኑ እንባ ቋጥሮ፣ ቀኛማችን ትኩር ብሎ ተመለከታቸው ። የደነቀ ውን መምጣት ያዩ፣ የቀኛማችን አልጋ የከበቡ ሰዎች ሁሉ ዓይናቸውን ደነቀው ላይ አሳረፉ ።

"አባዬ ደነቀው መጥቷል" አላቸው የቀኛማች ልጅ ።

ቀኛማች ድንገት ከወገባቸው ብድግ እንደማለት እያሉ በዓይናቸው ዙሪያውን ማተሩና ደነቀውን ደረሱ በት ። ፈገግ አሉና ከእግር እስከራሱ እየመላለሱ ተመለ

ኩቱት ። ደንቀው የሚሊሺያ የደንብ ልብስ ለብሶአል ። መለዮውን ከብብቱ ሥር አግብቶ በከንዱ ጠበቅ አድርጐ ይዞታል ። ደረቱ ላይ የተለጠፈው የጀግና መዳሊያ ያብረቀርቃል ። እሱም ትኩር ብሎ እያቻቸውና በዓይኑ ጽጥሮት የነበረውን እንባ ለቀቀው ። ቀኛማች አፋቸውን በምላሳቸው አርሰው ለመናገር ሞከሩና አቃታቸው ። ዓይናቸው ቁልጭ ቁልጭ ማለት ጀመረ ። " ውሃ ነው እሚሉት በላቸው -- አቀብላቸው" አሉ ከአልጋው ግርጌ ቆመው ይመለከቱ የነበሩት የደንቀው እናት ጓደኛ ። የቀኛማች ልጅ ውሃ አምጥቶ በአባቱ አፍ ውስጥ ጠብ ጠብ ማድረግ ጀመረ ።

ቀኛማች የውሃውን ጠብታ በምላሳቸው እየተቀበሉ አፋቸውን አረጠቡና ዓይናቸውን መልሰው ደንቀው ላይ ተከሉ ። ጥቂት አዩትና ጣታቸውን ቀስረው አፋቸውን ከፈት ዘጋ እያደረጉ ቆዩ ። ሁሉም ፈዞ ይመለከታቸዋል ። የቀኛማች ልጅ እምባውን እሚጠርግበት ሸማ ርሶአል ። ደንቀው ፈዞ ሲመለከታቸው ቀኛማችም ትኩር ብለው እያዩትና --- ጣታቸውን ደረቱ ላይ ወደተንጠለጠለችው ሜዳሊያ እያመለከቱ " እየ --- ው --- ጀ -- ግና --- ቶሎ አይ - ሰበርም - አ - ባል -- ኩሀም" አሉና ከተኙበት ለመነሳት ታገሉ ። አልሆንላቸውም ። ወደቀኝም ወደ ግራም ተገላበጡ ፣ አልሆንላቸውም ። ዙሪያውን የከበባቸው ሁሉ የቋጠረውን እንባ ማዘል አልቻለም ። ደንቀው

ወደ ቀኛማች ጠጋ ብሎ እቅፍ አረገና ከስር ለቅቆ ከአንገታቸው ቀና አደረጋቸው ። እንደዬ ደኑቀውን አንድዬ ሜዳሲያዋን ደሞ የከበባቸውን ሰው በዚያ በደከመ ዓይናቸው ማተሩና "ሰላቶ ገዳይ ሰ-ላ-ቶ- ገ-ዳ-ይ ደ---ጁ--የጠ---ሩ ጌታ---አ-ን-ድ---ብቻወን---መቶ እሚ---እምቢ እምቢ---" ብለው ጉሮናና የሲቃ ድምጽ የወኔ የጅግንነት ሲቃ ድምፅ በማሰማት ፎከሩና ዓይናቸው የዕንባ ዘለላ እንደያዘ ቀና ያለውን አንገታቸውን መልሰው ደፉት ። "አይ-ጅግና አይ ቆራጥ--አይ ሰው" አሉ የቀኛማች የጥንት ጓደኛ ዘሩ አስፋው ምርር ብለው ከማሳቀሳቸው በፊት ።

የደኑቀው እናት ጓደኛ ወደ ደኑቀው ዞር አሉና ። "በል እንግዲህ እናትህን ጠይቃቸው ፣ ባይሆን ኋላ ትመለሳለህ ፣ ሂድ ሲሉ ሰሙኑት ። የተሰበሰበው ሁሉ አንገቱን እንደ ቀለሰ ደኑቀውን አጅቦ ወጣ ። "ተመለሱ" አለ ደኑቀው ። መንገዱን ብቻውን ተያያዘው ። ረባዳውን መሬት አልፎ አቀበቱን መውጣት ሲጀምር ግን ብዙ ሰው ከፍ ባለ ድምፅ ሲጮህ ፣ ሲያለቅስ ሰማ ።

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋው ብር 4.50